አትሂዱብኝ

ከነጂብ ሚሕፉዝ



ትርጉም - በአማረ ሀጎስ

t.me/OLDBOOKSPDF

አሰረኛው

ደራሲ—ነጄብ ማሕፉዝ

ግብፃዊው የኖቤል የሥነ ጽሑፍ ሽልማት አሸናፊ።

ትርጉም — በአማረ ማሞ

ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት
1984
Ethiopia Book Centre 1991

t.me/OLDBOOKSPDF

English Title:
The Search
by Naguib Mahfouz
The American University Press in Cairo, 1988
Amharic Translation
by Amare Mamo

ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት
የፖ.ሣ.ቁ. 1024 አዲስ አበባ

Ethiopia Book Centre
P. O. Box 1024 Addis Ababa

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

ቦሌ ማተሚያ ቤት ታተመ ።
Printed by Bole Printing Press

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አንድ

ዓይኖቹ እንባ አቅርረዋል ። ክፉኛ በሚጠላቸው ባላንጣዎቹ ፊት ማልቀስና በጎዘን መኰማተር የሞት ሞት መስሎ ቢታየውም ፡ ከውስጠ ንጉሥ ለመውጣት የሚታገለውን ስሜት መግታት አልቻለም ። አስከሬኑን ከቃሬዛው ላይ አንሥተው አፉን ከፍቶ ወደሚጠባበቀው መቃብር ሲወስዱት በእንባ በራሱ ዓይኖቹ ተከተለው ። ጥቂት ሰዎች በጎጭ መጎጎ ጩርቅ የተጠቀለለውን አስከሬን ይዘው ወደ መቃብሩ ሲፈጥኑ ምንም ነገር የተሸከሙ አይመስሉም ።

— ለካስ እንዲህ ከሰውነት ወጥተሽ ኖሮ አል ? ለእሪ ያድርገው ፡ እምዬ ! አለ በሐሳቡ ።

እይታው ዳምኖ አካባቢው ጭልምልም አለበት ፤ አቧራው አፍንጫውን ቁጢጢጠው ፤ የሰዎቹ አጉል ጠረን እውድ አደረገው ።

የለቀስተኞቹን ሴቶች ዋይታና የአቧራውን ስንፈጣ ሊቋቋመው አልቻለም ። ግና ፀፈር ባለበሰው መቃብር በኩል እልፍ እንደ ማለት ሲል ፡ ከኋላው ሳብ የሚያደርግ የሰው እጅ ተሰማው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚያም ፡ "ፈጣሪህን አትርሳ" የሚል ድምፅ ጆሮው ውስጥ ጥልቅ አለ ።

የትከሻው መነካት ክፉኛ ዘገነነው ፤ የነካው ንም ሰውዬ በሐሳቡ ረገመው ። ሰውዬው ከአብ ዛኛዎቹ ለቀስተኞች የተለየ አልነበረም ። በእሱ ግምት ሁሉም እዚህ ግቡ የማይባሉ ናቸው ። በሌላ በኩል ደግሞ ፡ የነዘነ ክብደት ስሜቱን ፈንቅሎ ልቡን በፀፀት ፍላፃ ወጋው — የሃያ አም ስት ዓመት ፍቅር ፡ ርኅራኄና እንክብካቤ እብስ ማለቱ ነው ፤ ፊጽሞ እንዳልነበረ ከዐፈር በታች ሊውል ነው ! አለ በሐሳቡ ።

የለቀስተኞቹ ዋይታና እሪታ ሲጠበቁ የነበ ሩት ዓይነ ሥውራን መምጣታቸውን አበሠረ ። ዓይነ ሥውራኑ በመቃብሩ ዙሪያ እግሮቻቸውን አቆላልፈው በመቀመጥ ቦታ ቦታቸውን ያዙ ። የለቀስተኞቹ ዓይኖች እርሱን ሰረቅ እያደረገ እንደሚያዩት ይሰማዋል ። እርሱም ቢሆን ፡ ለሁ ኔታው ቁብ የሌለው መሆኑን እንዲረዱለት ከሲታ ያረቱን ነፋ ከማድረግ አልቦዘነም ። ሰዎቹ በአቋ መም ሆነ በአለባበሱ ልዩ የሆነበትን ምክንያት በሐሳባቸው እያወጡ እያወረዱ መሆናቸው አል ቀረም ። እናቱስ ብትሆን ፡ ከቀዬው እንዲገለልና እንዳሻው እንዲኖር ያደረገችው ለምን ይሆን ?

— እነዚህ ሰዎች እዚህ የተሰበሰቡት ኀዘና ቸውን ለመግለጽ ሳይሆን እኔኑ ለማብጠልጠል ነው ፡ በማለት በሐሳቡ አውጠነጠነ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጉድንድ ቆፋሪውና ረዳቱ ካጐነበሱበት ቀና ብለው መቃብሩን በዐፈር መመላቱን በምር ተያያዙት ። ዓይነ ሥውራኑ ዜማቸውን እየተቀባ በሉ ያነበንባሉ ።

—ወይ ጉድ ፤ ብቻዋን መቅረትዋ ነው እኮ ! ይኸ ሁሉ የሰው ትርምስ አንድ የፈየደላት ነገር የለም ። ከበሬታው ፡ ከንፈር መምጠጡ ፡ ፊትን መሸፋፈኑ ምን ዋጋ አለው ! በማለት ከሐሳቡ ጋር መግት ገጠመ ። ወዳያው ደግሞ ወደ ቤቱ የመ ሄድና ብቻውን ተቀምጠ የደረሰበትን ጉዳት የማሰላሰል ፍላጎቱ አቅበጠበጠው ። እናቱ እንደሞ ነች በጨለመበት መቃብርዋ ውስጥ ብዙ ገበና ግላጭ ጥያቄዎች ይጠብቋታል ። በዚያን ጊዜ እዚህ ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል አይዞሽ የሚ ላትና የሚረዳት አንድም አይኖርም ። ሁሉም ዕጣ ፈንታውን ይጠብቃል !

የአካባቢው ጭርታ የሥነ ሥርዓቱን ፍፃሜ አበሠረ ። ጉድንድ ቆፋሪው እርሱ ወደ ቆመበት ጠጋ ማለት ሲጀምር በአቅራቢያው የነበረ አንድ ሰው ፡ ‘‘ግድ የለም አታስብ ፤ ጉድንድ ቆፋሪዎቹን ስለማውቃቸው እኔ አስተናግዳቸዋለሁ’’ አለው ። ነገር ዓለሙ ከፍፃሜ መድረሱን ሲገነዘብ ደግሞ የብቸኝነት ስሜት ቀስፎ ያዘው ። እንደገና ሰውነቱን ሰቀጠጠው ። ለመጨረሻ ጊዜ መቃብሩን አየት ሲያደርገው ፡ በሥርዓት መከወኑ ልቡ ውስጥ ሰላም ፈነጠቀበት ። ለወደፊትም ቢሆን ዘማች

t.me/OLDBOOKSPDF

ተከለች መቃብሩን እየታከከ ሲያለብሱት ማየቱ አይቀርም ። እናቱ — ነፍስዋን ይማረውና —ሀብትና ንብረት የምትወድ ሴት ነበረች ። ዛሬ ግን ቅርሴ የምትለው ነገር ቢኖር ይኸው መቃብርዋ ብቻ ነው ።

ለቀስተኞቹ የጎዘን ስሜታቸውን በመግለጽ እየተሰናበቱት መሄድ ጀመሩ ። ቀዳሚዎቹ ሴቶቹ ነበሩ ። ለቅሶአቸውን ፡ ዋይታቸውንና ከእግር እስከ ራሳቸው የሸፈናቸውን የጎዘን ልብሳቸውን ዘልቆ ለተመለከታቸው ፡ ቀላዋጭ ዓይናቸው ሴሰኝነታቸውን በግልጽ ይጠቁማል ። ቀጥሎ ወንዶቹ የጎዘን መግለጫ ቃላቶችን በመሰንዘር መሰናበት ያዙ ። ያካባቢው ሰባራ ስንጥር ቸርቻሪዎች ፡ ወሮበሎች ፡ ጩልፋዮችና አቃጣሪዎች ነበሩባቸው ። ነግ በኔ በሚል ስሜት እያንዳንዳቸውን ትኩር ብሎ እየተመለከተ አሰናበታቸው ።

ወደ ቤቱ ሲሄድ የፀደይ መዓዛ የተዋሐደው ነፋሻ አየር ሰውነቱን ቅዝቀዝ አደረገው ። ኤል ናቢ ዳኒያል ጐዳና የሚገኘው ቤቱ አያሌ የደስታና የፍስሐ ትዝታ መዘክር ነው ። ያ ሁሉ አልፎ አሁን የቀረው ትልቁ መኖሪያ ክፍልና ከእናቱ ሌጣ አልጋ ሥር የተጋደመው ጉማጅ የውኃ ቧንቧ ብቻ ነው ።

በቤቱ ሰገነት ላይ ተቀምጦ ሲጋራ እያጨሰ አል ናቢ ዳኒያልንና ሳአድ ዛግ ሉልን ጐዳናዎች የሚያገናኘውን አደባባይ ይመለከት ጀመር ። እርሱ ከተ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀመጠበት ሰገነት ትይዩ ካለው መንገድ ዳር አንድ አፓርትማ ይገኛል። በውስጡ የውጭ አገር ሰዎች ይኖራሉ። አፓርትማው ውስጥ ጉድ ጉድ የሚሉት ሰዎች ለግብግ የሚዘጋጁ ይመስላሉ። አንድ ወንድና አንዲት ሴት ገና ከማለዳው ዓይን ያወጣ ድሪያ ላይ መሆናቸው ይታያል።

ከዛሬዋ ዕለት ጀምሮ የሕይወቱን ትክክለኛ አቅጣጫ ከምር ለማወቅ የወሰነ ይመስላል። ለጊዜው ብቸኝነት፣ የወዳጅ ዘመድ እጦት፣ ሥራ ፈትነት፣ ቤተሰብ አልባነት ነው አዕምሮውን ሰቅዞ ይዞት ያለው። የወደፊት ተስፋውም ቢሆን ከቁም ሕልም የሚሻል አይደለም። ከዚች ቅጽበት አንሥቶ ግን ጥሮ ግሮ ራሱን ማስተዳደር እንዳለበት ተረድቷል። እስከ ዛሬ ድረስ በኑሮ ውጣ ውረድ በመንገላታት ሕይወትዋን የገፉችው እናቱ ነበረች። እርሱ እንደ ልቡ ፈንጭቷል፤ እንደ ልቡ የሕይወትን እፍታ ቀምሷል። ሞት የሚባለው ነገር የማይቀር ዕዳ መሆኑንም የተገነዘበው በትናንትናው ዕለት ነበር። ትናንት ልክ በዚህ ሰዓት ነው ባለ ጋሪው እናቱን ጭኖ እዚሁ ቤትዋ ያደረሳት። ለልጇ መኖሪያ ይሆናል በማለት ስትጠግነውና ስታድሰው ወደ ኖረችው ቤትዋ አቅፎ ደግፎ ያስገባት እሱው ራሱ ነበር። ድክምክም ብላለች፤ ፊቷ ተጨማዷል፤ በሃምሳ ዓመት ዕድሜዋ ላይ ሠላሳ የመከራና የሥቃይ ዓመታት ያከለችበት መስላለች። እናቱ—ባሲማ አምራን—አምስት ዓመት

t.me/OLDBOOKSPDF

የወሀኒ ሕይወትዋን ፈጽማ ስትወጣ የሚያስታውሳት በዚህ ሁኔታዋ ነበር ።

"ልጄ ፡ ሳብር ፤ እናትህ ከእንግዲህ አልቆላታል ።"

እንደ ቀላል ዕቃ ተሸክሚት እየተራመደ ፡ "እንዲህ አትበይ ፤ ገና በበሰለ ዕድሜ ላይ ነሽ ። ገና ምኑ ተይዞ ነው እንዲህ የምትዪው" አላት።

ልብሷን ሳታወልቅ አልጋው ላይ ጋደም አለች ። ቀና ብላ ፊት ለፊትዋ ያለውን መስታወት እየት እያደረገች ፡ "እናትህ ከእንግዲህ አልቆላታል ፡ ሳብር ። ይኸ የሚታየኝ የባሲማ አምራን ፊት መሆኑን ማን ያምናል . . ." አለች ።

ነገሩ ምንም ሐሰት የለበትም ። ያ ውብ የነበረው ክብ ፊትዋ ፡ ያ ታይቶ የማይጠገብ የነበረው የሰውነት ቅርጽዋና ወዘናዋ እንዳልነበረ ሆኖአል ። በመላዋ የኢስክንድርያ ከተማ ያስተጋባ የነበረው ሣቅና ጫወታዋ ረጭ ብሷል ።

"ሕመምን የመሰለ ክፉ ነገር የለም" አለ ሳብር ፡ በቁጭት ።

አየሩ ቀዝቀዝ ያለ ቢሆንም ፡ በፊትዋ ላይ የተከማቸውን ወዝ እያበሰች ፡ "ልጄ ለዚህ ያበቃኝ ሕመም አይደለም ። ለዚህ ሁሉ ያበቃኝ ወሀኒ ቤት ነው ። የታመምኩትም ወሀኒ ቤት ከገባሁ በኋላ ነው ። እኔ እናትህ ለወሀኒ ቤት አልተፈጠርኩም።

t.me/OLDBOOKSPDF

አንዴ ጉበትሽ ፡ አንዴ የደም ብዛትሽ ፡ አንዴ ልብሽ ነው ሲሉ ለዚህ አበቁኝ ። ሙመልሼ እንደ ድሮዬ እሆናለሁ ብለህ ነው?'' አለች ።

''ከድሮ የተሻለ ነው የምትሆኚው ። የሚያስ ፈልግሽ ፡ ጥሩ ሕክምናና በቂ ዕረፍት ብቻ ነው'' አላት ።

''ገንዘብ ከዬት ይመጣል ?''

የገንዘብ ነገር በመኑሚቱ ድንግጥ በማለት ምንም አልመለሰላትም ።

''ምን ያህል ቀሪ ገንዘብ አለ በእጅህ?'' ብላ ጠየቀችው ።

''እረ ብዙም አይደለም'' አላት ።

''ራስ ኤል ቲን ያለውን ቤት በአንተ ስም ማስመዝገቤ በጅቷል ። አሱንም ይወስዱብን ነበር '' አለች ።

''አሱንማ በገንዘብ እጦት ምክንያት ሸጬ ዋለሁ ። ቤቱ መሸጡን በወቅቱ ነግሬሽ ነበር እኮ'' አላት ።

ይህን ስትሰማ ክፉኛ አቃስታ ግንባርዋን በእጅዋ መዳፍ አስደግፋ አቀረቀረች ። ''ወየው ራሴን! ቤቱንስ ምነው ባልሸጥከው ። ያንን ሁሉ ገንዘብ የት አደረስከት ልትለኝ ይሆን? የእኔ ምኞት ሀብትና ንብረት ከተረፉቸው ሰዎች እኩል እንድትኖር ነበር ። ጥረቴ የተትረፈረፈ ሀብት ትቼ ልሀ ለማለፍ ነበር ። ዳሩ . . .''

t.me/OLDBOOKSPDF

"ገንዘብ ምን ሥር አለው ብለሽ ነው። ዛሬ አሰ ሲሉት ነገ እንደ ጤዛ ይረግፋል።"

"እውነትህን ነው። ብቻ የክፉ ሰው በቀል ክፉ ነገር ላይ ጣለኝ። ለሁሉም የሥራችውን ይስ ጣቸው። በሀብቱ ዓለሙን ሲያይ ኖሮ በመጨ ረሻው እንቅሮ ተፋኝ። ሲተወኝ ሲል ደግሞ ከዚህ ቀደም ተሰምቶት የማያውቀው ክብሩ ፥ የአገር ባህልና ዕድሩ ድንገት ትዝ ብሎት ትቶኝ እብስ አለ . . . የውሻ ልጅ . . . ፍርድ ቤት ውስጥ እኮ ፊቱ ላይ ነው የተፋሁበት።"

ሲጋራ እንዲሰጣት ጠየቀችው። አንድ ሲጋራ እያቀጣጠለላት ፥ "ባታጨሺ ጥሩ ነው። እሥር ቤት ውስጥም ታጨሺ ነበር?" አላት።

"እዚያማ ሲጋራው ሐሺሽ ፥ አፍዛዥ አደንዛዥ ዕፁ ፤ምኑ ቅጡ፤ እንደዚያም ሆኖ በየዕ ለቱ ስለ አንተ ነበር የማስበው።" ሲጋራውን ምጥ አድርጋ እየሳበች ፥ በላቦት የወዛ ፊትዋንና አንገትዋን በመሀረብ እየጠራረገች ፥ "ልጄ ፥ የወደ ፊት ዕድልህ ምን ይመስላል?" አለችው።

"እንዴት አድርጌ አውቀዋለሁ። ሥራ እንደ ሆን የለኝም። ያለኝ ዕድል ወሮበላ ፥ ማጅራት መቺ ወይም አቃጣሪ መሆን ነው።"

"ማን ፥ አንተ!?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እርግጥ እስክ ዛሬ ጥሩ ኑሮ እንድኖር አድርገሽኛል። ነገር ግን ከእንግዲህ ያለፈውን ማሰቡ ምንም አይፈይድልኝም።"

"አንተ እኮ አሁን ለምታስበው ሕይወት አልተፈጠርክም" አለችው።

"ታዲያ ምን ፍጠር ነው የምትዪኝ!" አላት፡ ድንገት በቁጣ ገንፍሎ፡ "አንቺ በመታሰርሽ ጠላቶቼ እንዴት እንደ ፈነጠዙ ልነግርሽ አልችልም!"።

"ልጄ ሳብር፤ አትቁጣ፤ አትናደድ። እኔን ወህኒ ቤት ያወረደኝ ቁጣና ንዴት ነው። ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳስበው ያንን ከሐዲ እየደለሉ መኖሩ ይሻለኝ ነበር።"

"በደረስኩበት ስፍራ ሁሉ የሚያጋጥሙኝን ሰዎች አነካክተህ ጣላቸው ጣላቸው ይለኛል።"

"ልጄ ሳብር፡ የፈለጋቸውን ቢሉ እጅህን እንዳትሰነዝርባቸው፤ እደራ።"

ጣቶቹን ሞበጥበጥ አድርጎ፡ ከንዱን አፈር ጥሞ፡ "ይኸ ከንዴ፡ ይኸ ጡጫዬ ባይኖር፡ በየደረስኩበት እዋረድ ነበር። እሥር ቤት እያለሽ በእኔ ፊት ስለ አንቺ አንድም ሰው አንዲት ክፉ ቃል መተንፈስ አይችልም ነበር።"

t.me/OLDBOOKSPDF

የሲጋራውን ጭስ አከታትላ ቡልቅ እያደረገች ፥ "እኔ እናትህ ከማንም ሳላንስ ተከብሬ የኖርኩ ሰው ነኝ ። የማንም ምናምንቴ ሲፎልል ብኝ አይችልም ። እነዚህ በየዶረሱበት ስሜን ሊያጠፉ የሚፍጨረጨሩትን ከንቱዎች እናቶቻቸው ምን ዓይነት ሴቶች እንደሆኑ አሳምሬ አውቃለሁ ። ብዙ ሀብትና ንብረት ያፈራሁት እናቶቻቸውን መጣሪያ እድርጌ በመጠቀም መሆኑን ማን በነገራቸው ። "

እናቱ ያነሳችው ጉዳይ እምብዛም አዝናኝ ባይሆንም ፥ ችምችም ያሉ ነጫጭ ጥርሶቿን በፈገግታ ገለጥ አደረጋቸው ። " እውነቱን ልንገርህ ሳብር ። ወንዶቻችንን ደህና አድርጌ አውቃቸዋለሁ ። በመልካቸው ፥ በቁመናቸው ፥ በልብሳቸው ፥ በውድ መኪናቸው ፥ በጥሩ ጠረናቸው ፥ በርቱዕ እንደበታቸውና በሚያጨሱት ውድ ሲጋራ ሳይቀር ያልሆኑትን ሆነው ለመገኘት የሚያደርጉት ጥረት ይሽ ነው አይባልም ። እኔ እናትህ ግን ከላይ እስከ ታች ደህና አድርጌ አውቃቸዋለሁ ። አልጋ ላይ እርቃን ሥጋቸውን አገላብጬ አይቻቸዋለሁ ። ስለ እያንዳንዳቸው የማውቀው ታሪክ ተነግሮ የሚያልቅ አይደለም ። አንዳንዶቹ እዚህ ግቡ የማይባሉ ወራዶች ናቸው ። ፍርድ ፊት ከመቅረቤ በፊት ፥ አንዳንዶቹ ማረፊያ ቤት ድረስ እየመጡ ፍርድ ፊት ስማቸውን እንዳልጠቅስ ይማ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጸኑኝ ነበር ። የተቻለንን ሁሉ አድርገን ነፃ እናወ ጣሻለን ያሉኝ ብዙዎች ናቸው ። እነዚህን የመ ሰሉ ሰዎች የእናትህን ስም በክፉ የማንሣት መብት የላቸውም ። እኔ እናትህ ከእነርሱ እና ቶች ፡ ከእነርሱ ሚስቶችና ከእነርሱ ሴት ልጆች አሥር እጅ የከበርኩ ነኝ ። ዮር ብዬ ሳስበው ደግሞ ፡ ሴቶች ቤተሰቦቻቸው ባይኖሩ ምኑን ክምን አድርጌ እኖር ነበር !”

ሳብር አሁንም ፊቱ በፈገግታ ገለጥ አለ ። “ለመሆኑ ያ ሁሉ ጣቅህ ፡ ያ ሁሉ ፈገግታህ ፡ ያ ሁሉ ደስታህ የት ደረሰ ?” አለች ከንፈርዋን እየመጠጠች ። “ሳብር ፤ መቼም ካንጀቴ እንደም ወድህ ፤ ካፈራሁት ሀብትና ንብረት አንዲት ቤሳ ቤስቲን ሳላስቀር እንድትጠቀምበት እንዳደረግሁ ታውቃለህ ። እኔ ከምኖርበት ወራዳ ዓለም ርቀህ በዚህ ውብ ቤት ውስጥ እንድትኖር ጥረት አድ ርጌአለሁ ። ያስቀየምኩህ ነገር ቢኖር ሳላውቅ በስሕተት ሊሆን ብቻ ነው የሚችለው. . .እስቲ አንድ ነገር ልምከርህ ፤ መልክህና ደም ግባትህ ማንንም ሊማርክ የሚችል ለግላጋ ጉበል በመሆ ንህ ፡ ከንዴትና ከቁጣ ተጠበቅ ። እናቴ እንዲህ ሆነች እያልክም አትበሳጭ ።”

ሳዘንዋና ትካዜዋ ተጋባበት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥቂት ሲያስብ ቆይቶ ፡ "በእኔ ይሁንብሽ ፤ ማንኛውም ነገር እንደ ወትሮው ነው የሚሆነው" አላት ።

"እንደ ወትሮው ይሆናል አልከኝ . . . አይ ሳብር ፤ እኔ እኮ አልቆልኛል ። እኔ እኮ ድሮ የምታ ውቃት ባሲማ አይደለሁም። ልሆንም አልችልም ። ለመሆን ብፈልግም እንኳን ጤናዬም ፖሊሶቹም አይፈቅዱልኝም" አለችው ።

እንቦንብሶ የቤቱን ወለል በትክዜ ሲመለከት ከቆየ በኋላ ፡ "ከቤቱ ሽያጭ የተረፈው ገንዘብ ብዙም የሚያወላዳ አይደለም" አላት ።

"ምን ይደረግ ። የመጣው ይምጣ እንጂ እስ ክሁን ከለመድከው ኑሮ ዝቅ ብለህ መታየት የለ ብህም !"

"እስከ ዛሬ ተስፋ ስትቈርጪ አይቼሽ አላ ውቅም ።"

"ተስፋ መቊረጥማ ያለ ነገር ነው ።"

"ያንቺ ነገር እዚህ ከደረሰ ፡ ወይ ሽንጤን ገትሬ መሥራት ፡ ወይም ደግሞ መወንበድ አለ ብኝ ማለት ነው ።"

ሲጋራዋን ተርከሳ ካጠፋች በኋላ ፡ ዓይኖቿዋን ከዳድና ሁኔታውን ማስተንተን ያዘች ።

"እንድ ዘዴ መኖር አለበት" አለ ሳብር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"አምን ፤ አንድ ዘዴ መኖር አለበት ። ወሂ ቤትም ሆኜ ይሽንኑ ጉዳይ ሳወጣ ሳወርድ ነው የነበርኩት" አለችው ።

በእናቱ ላይ የነበረው እምነትና አለኝታ ከሥር ከመሠረቱ ሲናጋ ተሰማው ።

"አምን ፤ ጉዳዩን በጥሞና አስቤበታለሁ ። ከእኔ እንዳትለየኝ የማደርገው ጥረት ፋይዳ የሌለው መሆኑን ተገንዝቤአለሁ ። ለአንተም የሚጠቅም አለ መሆኑን ከተረዳሁ ሰንብቻለሁ ።"

ፊቱን ቅጭም አደርጎ ፡ አትኩሮ ተመለከታት።

እርሷም መሸነፍ ጉልዩ በሚታይበት ስሜት ፡ "ምናልባት ሁኔታው ለአንተ ግልጽ ሆኖ ላይታይህ ይችል ይሆናል ። ከእንግዲህ ወዲያ አንተንም የኔ ነህ የማለት መብት የለኝም ። ይህም ግልጽ የሆ ነልኝ ፍርዴን ተቀብዬ ወሂ ስወርድ ነው ።"

ለጥቂት ደቂቃዎች በመኻላቸው ዝምታ ሰፈነ ። በፊትዋ ላይ ፍጹም የሆነ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ይነበባል ።

"ሳብር ፤ ከእንግዲህ ወዲያ የእኔና ያንተ አብሮ መኖር ፋይዳ የለውም" አለችው ።

"ምን አድርግ ነው የምትዪኝ?" አላት ።

"መሄድ ነው የሚያዋጣህ!"

"ወዴት ነው የምሄደው?"

"ወደ አባትህ" አለችው፡በሳግ በታነቀ ድምፅ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዓይኑን ፍጥጥ አድርጎ እያያት ፡ "ወደ አባትህ!?" አላት ።

ራሰዋን በአምንታ ነቀነቀች ።

"አባቴማ ሞቶአል ። እኔ ከመወለዴ በፊት መሞቱን ነግረሽኝ የለም እንዴ?"

"አዎን ፡ ነግሬሃለሁ ። ነገር ግን የነገርኩህ ሁሉ እውነት አይደለም ። "

"አባቴ በሕይወት አለ ማለት ነው? . . . እኔ አላምንም ! አባት አለኝ ማለት ነዋ !"

የስሜቱን መለዋወጥ ስታይ በጥርጣሬ ዓይን ትመለከተው ጀመር ።

"አባት አለኝ ማለት ነዋ! . . . ታዲያ እስከ ዛሬ ለምን ደብቀሽ አኖርሽው?" አላት ሳብር ፡ ስሜቱን መግታት እያቃተው ።

"አዎን ፤ እውነትህን ነው ። ሐቁ ይፋ የሚወጣበት ቀን ዛሬ መሆኑ ነዋ!" አለችው ፡ እያቃሰተች።

"ቀልዴን እንዳይመስልሽ ። አባቴ በሕይወቱ ካለ ፡ ስለ እርሱ የማወቅ መብት አለኝ!"

"ምን የሚሉት አባት ነው እንደ እኔ ሊያቀ ማጥልህ የሚችል ?"

"አቀማጥለሽ አሳድገሽ እዚህ ያደረስሽኝ መሆኑን አልክድም!"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንግዲያው እኔን መውቀሱን ትተህ ዛሬ ነገ ሳትል አባትህን ፈልገው።"

"አባትህን ፈልገው አልሽኝ?"

"አዎን፤ አባትህን ፈልገው። ከአባትህ ጋር የዛሬ ሠላሳ ዓመት ነበር በጋብቻ የተሣሰርነው። ዛሬ ግን የት እንዳለ አላውቅም።"

ነገሩ ፈጽሞ ግራ ያጋባው ቢሆንም፥ ረጋ ባለ ሁኔታ፥ "እማዬ፤ ኧረ እንዲያው በፊጠረሽ ምን ማለትሽ ነው?" አሳት።

"ማለቴማ፤ ከገባህበት የችግር አጣብቂኝ የም ትወጣበትን ዘዴ ማመልከቴ ነው።"

"ይኸ አባትህ የምትዪኝ ሰውዬ ሞቶስ እን ደሆን!"

"በሕይወት ሊኖርም ይችላል።"

"መኖር አለመኖሩን የማላውቀውን ሰው በመፈለግ የትም ተንከራተት ነው የምትዪኝ?"

"መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ የምትችለው ስትፈልገው ብቻ ነው። ለማንኛውም አባትህን መፈለጉ በሥራ አጥነትና በተስፋ ቢስነት ተከ ራምቶ ከመቀመጥ የሚሻል ይመስለኛል።"

"በጣም ግራ የሚያጋባ ነገር ነው።"

"ከእንግዲህ ወዲያ የሚጠብቅህ ሌላው አማ ራጭ፤ አጭበርባሪ፥ አታላሪ፥ ማጅራት መቺና አወ

t.me/OLDBOOKSPDF

ናብዶ አዳሪ መሆን ብቻ ነው። ስለዚህ የሚያዋጣህን መምረጡ ያንተ ፈንታ ነው።"

"ለመሆኑ እንዴት አደርጌ ነው የማገኘው?"

ይህንኛውን የልጅዋን ጥያቄ ስትሰማ መንፈስን የሚያዝል፣ ሰውነትን የሚያሸማቅቅ ዝዘንና ትካዜ ተሰማት። በመጨረሻም፣ "የአባትህ ስም በልደት ማስረጃህ ላይ ይገኛል። አባትህ ሰይድ ራሕሚ ይባላል" አለችው። ከዚያም የእንባ ደመና የለበሱ ዓይኖችዋን እያባበሰች፣ "ከአባትህ ጋር በፍቅር እብድ ካልን ሠላሳ ዓመት አለፈ። የካይሮ ኑሮዬ ትዝ ይለኛል።"

"ካይሮ? የሚኖረው እስክንድርያ ከተማ አይደለም ማለት ነዋ!"

መኖሪያው እስክንድርያ አልነበረም። እሱን ፈልጎ ማግኘትም ቀላል ነገር አይመስለኝም።"

"ልጁ ከሆንክ ለምን እሱ አልፈለገኝም?"

"ልጅ እንዳለው አያውቅም።"

የበስጭትና የቁጣ ስሜት ፊቱን ወረረው።

"ነገሩን ሳልጨርስልህ በገነፈለ ስሜት አትመልከተኝ" አለችው። "አባትህ በማንኛውም ረገድ የተቻለው ሰው ነበር። እኔና እርሱ በተዋወቅን በት ጊዜ ትምህርቱን በመከታተል ላይ ቢሆንም፣ ከወጣትነቱ ጀምሮ ስመ ጥር ሰው ነበር..."

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለ አባቱ የምትነግረውን ነገር በጉጉትና በተመስጦ ያዳምጣት ጀመር ።

“ አባትህ በጣም ይወደኝ ነበር ። እኔም — ያሁኑን አያድርገውና — በውበቱ ማራኪ ፥ በማ ሕበራዊ አቅዋሜ መናጢ ድሃ ነበርኩ ። እርሱም ዓለሜን በማይባት እልፍኙ የድብቅ አስቀመጠኝ።”

“ በመጨረሻስ ፤ ተጋባችሁ ? ”

“ አዎን ፤ የጋብቻችን የምስክር ወረቀት እስከ ዛሬ በእጄ ይገኛል ። ”

“ በኋላስ ፤ ተፋታችሁ ? ”

“ አዬ ፤ ምን እንፋታለን ፤ እኔ ትቼው ከመለ ልኩ ” አለች ቁና ቁና እየተነፈሰች ።

“ ትቼው ከመለልኩ ? ”

“አዎን ፤ ለጥቂት ዓመታት ያህል አብረን ከኖርን በኋላ ትቼው እብስ አልኩ ። በጊዜው አን ተኝ በንሼ ነበር ። የከመለልኩትም አንድ እዚህ ግባ የማይባል ሰው ወድጄ ነበር ። ”

ጭንቅላቱን እያነቃነቀ ፥ “ ፈጽሞ የማይታ መን ነገር ነው የምትነግሪኝ ” አላት ።

“ መቼም ሠረሀ ዘረሀ እኔኑ መውቀስህ አይ ቀርም ” አለችው ።

“ ኧረ እኔ አንቺን ምን አስወቀሰኝ ። ትተ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሽው ከኩበለልሽ በኋላ ምንም አልፈለገሽም ማለት ነው ?"

" እኔ እንጃ ፤ ጨርቄን ጠቅልዬ የጠፋሁት ወደ እስክንድርያ ከተማ ነው ። እስክንድርያ ከገባሁ በኋላ ስለ እርሱ ምንም ነገር አልሰማሁም ። ብዙ ጊዜ ግን ድርጅቴን እንደሚያዘወትሩት ወንዶቻችን እሱም አንድ ቀን ያጋጥመኝ ይሆናል የሚል ግምት ነበረኝ ። ግን ከተለያየንበት ቀን ጀምሮ ዓይኑን አይቼም አላውቅ ። "

የለበጣ ሳቅ እየሣቀ ፡ " ከሦስት ዓመት በፊት የተለየሽውን ሰው ፈልገው ነው የምት ዪኝ ?" አላት ።

"ችግርና ተስፋ መቁረጥ ብዙ ነገር ያሠራል ። ለማንኛውም የጋብቻችን የምስክር ወረቀትና ለማስታወሻ የተነሣነው ፎቶግራፍ በፍለጋህ ወቅት ስለሚረዳህ እሰጥሃለሁ ። ፎቶግራፉን ስትመለከት የአባትህ አምሳያ መሆንህን መገንዘብ ትችላለህ ። "

" የጋብቻችሁን የምስክር ወረቀትና ፎቶግራፍ እስካሁን ማስቀመጥሽ በጣም ይገርማል ።"

" ከሁሉም በላይ ፎቶግራፉ እንዳይጠፋብኝ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አደርግ ነበር ። እንደነገርኩህ ከሥር ከመሠረቱ ምስኪን ድሃ ነበርኩ ። ከአባትህ ከተለየሁ በኋላ በፍቅር የከንፍኩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለት ሰው·ዬም ውሎ ማደሪያ የሌለው ከርታ·ታ ሰው ነበር ። በተሰማራሁበት የሴተኛ አዳሪነት መ·ያዬ ፡ በሀብቱም በገናውም ስሜ የተጠራ ከሆነ በኋላ ነገር ዓለመ·ን ትቼው ነው ስኖር የነበ ረው . . .”

“ከአባቴ ጋር የነበረሽን ግንኙነት ከሚያስ ታው·ሱሽ ነገሮች መለየት አለመቻልሽ ነው ያስ ገረመኝ ።”

ፊትዋንና ማጅራትዋን ደጋግማ በመሀረብ እያበሰች ፡ “ብዙ ጊዜ እነዚህን ማስታወሻዎች አሽቀንጥሬ ለመጣል ይቃጣኝና አንድ ቀን ምን እንደሚሆን ይታወቃል የሚለው ስሜቴ እያሸነ ፈኝ እስከ ዛሬ ሳስቀምጣቸው ችያለሁ ።”

በክፍሉ ወለል ላይ ሁለት ምስት ጊዜ ከተ ንቀሳቀሰ በኋላ ፡ አረፍ ወዳለችበት አልጋ በመ ጠጋት ፡ “ፊልጌ ካገኘሁት በኋላ ‘አላውቅህም ፤ የምን ልጅ ነው ፤ እኔ ልጅ የሚሉት ነገር የለ ኝም’ ቢለኝስ ?” አላት ።

“ፎቶግራፉን አይቶ ልጄ አይደለህም ሊልህ አይችልም !”

“ካይሮ ቁላል ከተማ አይደለም ፤ ከዚህ ቀደም ረግጠው አላውቅም !”

“አባትህ የሚኖረው ካይሮ ነው ያለህ ማነው? እስክንድርያ ፡ አስዩት ወይም ደግሞ ደማንሁር

t.me/OLDBOOKSPDF

ሊኖር የማይችልበት ምክንያት የለም ። እኔ በበ ኩሌ እንዲህ ያለ ስፍራ ነው የሚኖረው ማለት አልችልም ። በአሁኑ ወቅት የት እንዳለ ፡ ምን እንደሚሠራ ፡ ባለ ትዳር ወይም ብቸኛ ይሁን ከእግዜር ሌላ የሚያውቅ የለም ።''

በቁጣ እጆቹን ግራ ቀኝ እያወራጨ ፡ ''ታዲያ እንዴት አድርገህ ነው ፈልገው የምት ዪኝ ?'' አሳት ።

''አባትህን መፈለጉ በቀላሉ ይሳካልሃል የሚል ግምት የለኝም ። በሌላ በኩል ደግሞ የማ ይቻል ነገር ነው ማለትም አልችልም ። አንዳንድ የፖሊስ መኩንኖችንና የሕግ ሰዎችን ስለምታ ውቅ ይረዱሃል የሚል ግምት አለኝ ። አባትህ የተቻለው ሰው እንደሆነ ነግሬሃለሁ . . .እንደ ርሱ ያለውን ሰው በካይሮም ሆነ በሌላ ስፍራ ሰው ያጣዋል ማለት አይቻልም ።''

''እርሱን ሳላገኝ የያዝኩት ገንዘብ ቢያልቅስ?''

''ፍለጋህን ሳትወል ሳታድር መጀመር አለ ብህ የምልህም ስለዚሁ ነው ።''

ነገሩን ለጥቂት ደቂቃዎች በሐሳቡ ካወጣ ካወረደ በኋላ ፡ ''እንዲያው ስታስቢው ይኸ ሁሉ ልፋት ፡ ይኸ ሁሉ መውጣት መውረድ የሚያስፈ ልገው ሰው ነው ነው የምትዪኝ ?''

''ያለ ምንም ጥርጥር ። ፈልገህ ማግኘቱ ከተሳካልህ ስትመኘው የኖርከው የተደላደለ ኑሮ

t.me/OLDBOOKSPDF

ባለቤት መሆን ትችላለህ ። አባትህን ካገኘኸው ለማይረባ ገቢ መጣርና መጋር ወይም ደግሞ ሰርቆና ቀምቶ እየባነኑ መኖር አይኖርብህም ።"

"መናጢ ድሃ ሆኖ ባገኘውስ ? አንቺስ ባንድ ወቅት የተረፈው ባለ ጸጋ አልነበርሽም ?"

"አባትህ የሚታወቀው ገንዘብ ያለው ሰው በመሆኑ ብቻ አይደለም ። እርግጥ ፡ እንዳልከው በአንድ ወቅት እኔም ገንዘብ አላቸው ከሚባሉት መካከል ነበርክ ። በገንዘቤ የረባ ኑሮ አላተረፍኩልህም ። እኔንም ሆነ ራስህን ታስከብር የነበረው በጉልበትህና በፈርጣማው ክንድህ ነበር ።"

የምትናገረው ሁሉ እውን ሳይሆን የቀን ሕልም መሰለው ። "አሁን ተነሥቼ ብፈልገው የማገኘው መሆኔን ከልብ ታምኚበታለሽ ?" አሳት ።

" አባትህ በሕይወት እንዳለና በርትተህ ከፈለግኸው ልታገኘው እንደምትችል ሰውነቱ ይነግረኛል ።"

ሁኔታው የማይጨበጥ መሆኑን ለመግለጽ ጭንቅላቱን በአሉታ ካወዛወዘ በኋላ ፡ "ጨክነሽ ፈልገው ነው የምትዪኝ ? ጠላቶቹ ይህንን ነገር ሲሰሙ ጨርቁን ጥሏል ብለው አይዛበቱብኝም ?" አላት ።

"በየአውራ ጐዳናው እየተንገላወድክ ስትሸቅልና ስታቃጥር ቢያዩህ ምን የሚሉህ ይመስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ልሃል ? እውነቱን ልንገርህ ፤ አባትህን ከመፈለግ የተሻለ አማራጭ የለህም !”

ዓይኖችዋን ከደን አድርጋ የደከማት መሆኑን በማጉመትመት ገለጸችለት ። እርሱም አረፍ እንድትልና ጭውውታቸውንም በማሥቱ ጠዋት እንደሚቀጥሉ ነግሯት ጫማዎችዋን አወላልቆ እንድትተኛ ከመቻቻት በኋላ የአልጋ ልብሱን ደረብ አደረገላት ። ሙቅቱ አፍኗት ስለ ነበር የደረበላትን ልብስ ጥላ ጥቅልል ብላ ተኛች ። ወዲያው እንቅልፍ ወስዷት ታኩርፍ ጀመር ።

ሴሊቱን መሉ አልጋው ላይ ሲወራጭና ሲገላበጥ ፤ በዓይኑ እንቅልፍ ሳይዞር አድሮ ንጋት ላይ እናቱን ለመቀስቀስ መኝታ ክፍልዋን ከፍቶ ቢገባ አልጋዋ ላይ ሞታ አገኛት ። ነፍስዋ ከሥጋዋ የተለየችው እንቅልፍ እንደ ወሰዳት ይሆን ? ወይስ ከመሞትዋ በፊት ጣርና ጩኸት አሰምታ ይሆን ? ከእንግዲህ ምን ይደረጋል? ትና ንት ከወሀኒ ቤት ለብሳው የወጣችውን ልብስ እንኳን ሳትለውጥ ክልትም ብላ ቀረችው. . .

ሳብር የእናቱን የጋብቻ ፎቶግራፍ አንሥቶ በጥንቃቄ ይመለከተው ጀመር ። ወላጅ አባት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሠላሳ ዓመት ያለ ፈው ብቸኛ ማስረጃ ! የአባቱ ትክክለኛ አምሳያ መሆኑ የሚታበል ነገር አይደለም ። መልከ መል

t.me/OLDBOOKSPDF

ከም ፡ ዘንካታ ፡ ወንዳ ወንድ ፡ ጠርቡሹ ወደ ቀኝ ጋደል ያለ ፡ ቁመናው የገሳላ ሸገና አባት ! . . .

ከጐረቤቶቻቸው በአንደኛው ቤት ወደ ተዘ ጋጀው ግብዣ የታደሙት እንግዶች መምጣት ጀምረዋል ። ሙዚቃው ይቀልጣል ። በባሲማ ቤት ውስጥ ደግሞ ፡ ለሙታን የሚፈጸመው የቁርአን የድግምት ዜማ ይሰማል ።

እንዲያው ለመሆኑ በዚህ ዓለም ላይ እውነ ትና ሕልሙን መለየት የሚቻለው በምን ዓይነት መንገድ ነው ? ከሰዓታት በፊት እንዲያ ትመክ ረውና ታዋራው የነበረችው እናቱ ከሞቱት አንዲ ሆናለች ። ለሦሳ ዓመታት የውኃ ሽታ ሆኖ የቀ ረው አባቱም በእግር በፈረስ የሚፈለግ ሰው ሆኗል ። ሳብርም ቢሆን የዋልጌነት ፡ የቅጥፈትና የወሸካታነት ሕይወቱን አድሶ ፡ የክብር ፡ የነፃነ ትና የተደላደለ ሕይወት ያስገኝልኛል የሚለ ውን ፍለጋ ሊያያዘው የቈረጠ ይመስላል . . .

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ሁለት

ሳብር ፡ አባቱን የመፈለጉን ነገር ለማንም ሳይናገር በምስጢር ሊያቆየው ወሰነ ። ምናልባትም ፍለጋው የማያዋጣው ሆኖ ካገኘውና ችግር ከገጠመው የዕርዳታ እጆቸውን ለመዘርጋት ወደ ኋላ የማይሉ ወዳጆች እንዳሉት ማወቁ የመንፈስ ጽናት ሰጠው ። ለማንኛውም ፡ ፍለጋውን ከዚያው ከሚኖርባት ከአስክንድርያ ከተማ መጀመሩ የሚሻል መሰለው ። በሌላ በኩል ደግሞ አባቱን የመሰለ ታዋቂ ሰው በአስክንድርያ ከተማ እየኖረ እናቱ እንዴት ላታውቅ ቻለች ? የሚለው ጥያቄ ግራ አጋባው ።

ሳብር አባቱን ፍለጋ ከመጀመሩ በፊት የሰዎች ስምና አድራሻ የተመዘገበባቸውን የተለያዩ የስሞች ማውጫዎች ማገላበጥ ያዘ ። ከሁሉ በፊት ትኩረት የሰጠው የቴሌፎን ደንበኞች በፊደል ተራ ለተመዘገበበት የስሞች ማውጫ ነበር ። ከ"ሰ" ፊደል ሥር የሰፈሩትን ስሞች ሲያነብ ፡ ሰይድ ኤል ራሕሚ የሚል ስም አገኘ ። እንዴት አድርጎ ይሆናል ? ይኸማ ልክ የአባቱ ስም ነው! ለካናው ይሆን እንዴ ? ሰይድ ኤል ራሕሚ ፡ የኤል ማንሽያ መጸሕፍት መደብር ባለቤት ። የማይሆን

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገር ነው ። የሳብር አባት የመጻሕፍት ቸርቻሪ መሆን አይችልም . . . ኤል ማንሽያ ደግሞ እናቱ ባሲማ ለሃያ አምስት ዓመታት በግልሙትና ከኖረችበት ሰፈር እምብዛም የራቀ አይደለም ። ቢሆንም ጉዱን እቦታው ድረስ ሄዶ ማጣራቱ አይከፋም ፤ ፍለጋው አንድ ስፍራ ላይ መጀመር አለበት ።

የመጻሕፍት መደብሩ ባለቤት ሳብር ከያዘው ፎቶግራፍ ጋር በምንም መንገድ የማይመሳሰል በሃምሳ ዓመት ዕድሜ ከልል ውስጥ የሚገኝ ሰው ነበር ። በፎቶግራፉ ላይ የማታየውን የእናቱን ምስል በእጁ ደበቅ አድርጎ የአባቱን ሥዕል ብቻ ለሰውዬው አሳየው ።

"አላውቅም" አለ የመጻሕፍት መደብሩ ባለቤት ፤ ፎቶግራፉን ከተመለከተ በኋላ ።

ሳብር ፎቶግራፉ የተነሣው ከሠላሳ ዓመት በፊት መሆኑን ስለሰውየው ገለጸለት ።

"ጥጼም አይቼውም አላውቅ" አለ ሰውዬው።

"ስማችሁ ተመሳሳይ በመሆኑ ምናልባት ዝምድና ይኖራችሁ ይሆናል" አለው ሳብር ።

"አይመስለኝም ። እኔም ሆንክ ዘመዶቼ የእስክንድርያ ነዋሪዎች ነን ። በእናቴ በኩል ጥቂት ዘመዶቼ የሚኖሩት ባላገር ነው ። ለመሆኑ ሰውዬውን የምትፈልግበት ምክንያት ምንድን ነው?"

t.me/OLDBOOKSPDF

የሰውዬው ድንገተኛ ጥያቄ ሳብርን ለአንድ አፍታም ቢሆን ግራ አጋባው ።

"የሚቹ አባቴ የብዙ ዘመን ወዳጄ ነው ። በኤል ራሕሚ ስም የሚጠሩ በሌላ ስፍራ የሚኖሩ የሚያውቋቸው ሰዎች ካሉ ቢጠቁመኝ ።"

ሰውዬው ሳብርን በጥርጣሬ ዓይን እየተመለከተው ፣ "ኤል ራሕሚ የቅድመ አያቴ ስም ነው። በአሁኑ ጊዜ በዚህ ስም የምንጠራው እኅቴና እኔ ብቻ ነን ።"

የሳብር የመጀመሪያ ተግባሩ በፍለጋው ወቅት የሚያጋጥመውን እክል ሁሉ በትዕግሥት መቀበል ነበር ። በእጁ ላይ ያለው ከአንድ ሺህ ብር የማይበልጥ ገንዘብ ብቻ ነው ። እሱም ቢሆን በየዕለቱ እየመነመነ መሄዱ አይቀርም ። የያዘው ገንዘብ እየተገባደደ መሄድ ደግሞ ፣ አባቱን አግኝቶ የተድላና የደስታ ኑሮ ባለቤት የመሆን ተስፋው የመጨጠጡ ምልክት ይሆናል ።

ሳብር በደረሰበት ስፍራ ሁሉ የሚያልፍ የሚያገድመውን ትኩር ብሎ በመመልከት ረዘም ያለ ጊዜ አሳለፈ ። ነገሩ የማያዋጣ መሆኑን በመገንዘቡ አንድ የሚያውቀውን ጠበቃ አማከረ ። ጠበቃው ፣ አንዳንድ ሰዎች እንደሚያደርጉት ፣ አባቱ ምናልባት በቴሌፎን ማውጫው ውስጥ ያልተመዘገበ የቴሌፎን ቁጥር ሊኖረው እንደሚችል ካስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ረዳው በኋላ ፣ "የሚሻለው የሰፈሩን የሃይማኖት መሪ ሼክ መጠየቅ ነው" አለው ።

"አባቴ እኮ የማንም አልባሌ ሰው አይደ ለም!" አለ ሳበር — በቁጣ ።

"ወንድሜ ፣ ሠላሳ ዓመት ብዙ ነገር ለለውጥ ይችላል ። እንደ እኔ ከሆነ ፣ በየወህኒ ቤቱ ተዘዋ ውረህ ብትጠይቅም አይከፋም ።"

"ወህኒ ቤት ?!"

"አዎን ፤ ምን አስበረገገህ ። ወህኒ ቤትና መስ ጊድ ለማንኛውም ሰው ክፍት ቦታዎች ናቸው ። አንዳንዴ ቁም ነገር ሠርተው ወህኒ ቤት የሚ ገቡ ሰዎች አሉ" አለ ጠበቃው ፣ ከት ብሎ የስ በጣ ሣቁን እያሰማ ።

"ለማንኛውም ፍለጋችንን ከሕዝብ ቁጠራ መመዝገቢያ ቢሮ እንጀምራለን ፤ ከዚያም የንብ ረት መመዝገቢያውን ቢሮ እንቃኛለን ። ሁለቱም ቢሮዎች ፍንጭ የማይሰጡ ከሆነ ፣ ያለው አማ ራጭ የየሰፈሩን ሼኮች መጠየቅ ነው ።"

በተጨማሪም ፣ በጋዜጦች ላይ ማስታወቂያ ለማውጣት የሚቻል መሆኑን ጠበቃው ቢጠቁ መውም ፣ በጠላቶቹ ዘንድ መጣፈጥና መሳለቂያ ላለመሆን ፣ ሳበር ሐሳቡን አልተቀበለውም ። በጋዜጦች ማስታወቂያ ማውጣት ቢያስፈልግም ፣ ከእስክንድርያ ከተማ እግሩን ከመንቀሉ በፊት

t.me/OLDBOOKSPDF

ሊሞክረው እንደማይችል ወስኖ ፡ በከተማዋ አራ ቱም ማዕዘናት የሚገኙትን መስጊዶች ሼኮች ማነጋገሩን ቀጠለ ።

"የምትፈልገው ሰውዬ ሥራው ምንድን ነው?"

"ምን እንደሚሠራ አላውቅም ። የታወቀና የተጻለው ሰው መሆኑ ብቻ ነው የተነገረኝ ። ይኸ ከሠላሳ ዓመታት በፊት የተነሣው ፎቶግራፍ ነው።"

"ለመሆኑ ለምንድን ነው የምትፈልገው?"

"የአባቴ የቅየ ጓደኛ ነው ። ፈልገው ተበዬ ነው እየፈለግሁት ያለሁት ።"

"በሕይወት ለመኖሩ ምን የምታውቀው ነገር አለህ?"

"እረ ፡ ምንም የማውቀው ነገር የለም ።"

"እስክንድርያ ከተማ ይኖራል ብሎ የነገረህ ማነው?"

"ማንም አልነገረኝ ፤ እንዲያው እዚህ ሳይኖር አይቀርም በሚል ግምት ነው ።"

ከዚህ በኋላ የሚሰነዘርለት ፡ "እዝናለሁ ፤ አላውቀውም!" የሚለው እጥር ምጥን ያለ መልስ ነበር ። ሳብርም መልሱ በጀሮው ውስጥ እያንቃጨለ ፍለጋውን ለመቀጠል ወደ ሌላ ስፍራ ያመራል። በያረሰበት ሁሉ ወደያቅጣጫው የሚተመውን አላፊ አግዳሚ ፊት በትኩረት መመልከቱንና

t.me/OLDBOOKSPDF

ከያዘው ፎቶግራፍ ከሚያውቀው ያባቱ መልክ ጋር ማገናዘቡን ይቀጥላል ። የአባቱ አምሳያ የሆነ ሰው ግን አያጋጥመውም ።

የዝናቡ መጣል መጀመር ይዘዋወርበት ከነ በረው የከተማይቱ የባሕር ዳርቻ ሚራማር ተብሎ ወደሚጠራው አካባቢ ጉራ እንዲል አደረገው ። ስማዮን ቀና ብሎ ቢመለከት ጨለማው በማምሻው ብርሃን ቦታ እየተኮካ መሄዱን ተገነዘበ ። ከተጠ ለለበት ቤት ውስጥ ፡ "እንኳን ደህና መጣህ ፤ ወደ ቤት ዝለቅ እንጂ!" የሚል ድምፅ ጋበዘው ።

የጋባገቦን እጅ በመጨበጥ ሰላምታ ከተለ ዋወጠ በኋላ ቤት ገብቶ አረፍ አለ ። "እናትህ ለቅሶ ላይ ባለመገኘቴ በጣም አዝናለሁ ። ወደ ሰፈራችን ብቅ ትላለህ ብዬ ጠብቄህ ነበር ። ወዳ ጅችህ ሁሉ 'የት ደረሰ?' እያሉ ሲጠይቁ ነው የሰነበቱት ።"

ዝናቡ ቆም ብሏል ። ሳብር ከሰው ጋር ቀጠሮ ያለው መሆኑን በመግለጽ ለመሄድ ተነሣ ። ሴትዮዋም እበር ድረስ ተከትላው ፡ "ምነው ፤ ገንዘብ ቸገረህ እንዴ ?" አለችው ።

—ለካስ ስለ እሪ ማውራት ጀምረዋል? አለ ሳብር በሐሳቡ ። ሴትዮዋ ከጀርባው ከተል እያ ለች ፡ "አንተን የመሰለ ሰው እንዴት ገንዘብ ይች ግረዋል?" አለችው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳብር ሴትዮዋን በገሙታ ተሰናበታት ። ‘እንኑን የመሰለ ሰው እንዴት ገንዘብ ይቸገረ ዋል?’ የሚሉት ቃላት ጆሮው ውስጥ እያንቃጨሉ በት መንገዱን ቀጠለ ። እነእሜቱም እጃቸውን እንዳይ ነው ፍላጎታቸው ፤ የጠላቶቼን አንጀት ለማራስ !—እዚህ ደረጃ ከመድረስ ሞት ይሻለኛል! አለ ሳብር በሐሳቡ ። የአባቱን ፍለጋ በተመለከተ እስክንድርያ ከተማ ውስጥ ምንም የቀረው ነገር አልነበረም ።

የቀረው ነገር ቢኖር የከተማይቱ መዳፍ አን ባቢ ብቻ ነው . . . እሱስ ቢሆን ምን አዲስ ነገር ሊያመጣ ይችላል? ሳብር ፡ መሞከሩ አይከፋም ወደ ሚለው ሐሳብ መጨረሻ ላይ ማዘንበሉ አልቀረም ።

ሳብር ፡ ከእርሱ የሚያመልጥ ነገር የለም እየ ተባለ የሚወራለትን ሼክ ፡ በእርጅና ውልቅልቁ በመውጣት ላይ በሚገኘው ምድር ቤቱ ወለል ላይ እግሮቹን አነባበሮ በመቀመጥ በጽሞና ላይ እንዳለ አገኘው ። ሳብር ከሼክ አንደበት በመ ጀመሪያ የሰማው ፡ “ፈልጉ ታገኛላችሁ” የሚ ለውን ቃል ነበር ። የባሕሩ ሞገድ ከምድሩ ጸርቻ ጋር በመላተም የሚያሰማው ድምፅ የጥሩ ነገር ምልክትነት እንዳለው ተሰማው ። “እንደ ክረምት ጨለማ የሚያሰለች ፍለጋ” አለ ሼክ ፡ ቀጠል አድርጎ ። ለሳብር እያንዳንዱ ዕለት እንደ አንድ ዓመት እየራቀበት በመሄድ ላይ ነው ።

“የምትፈልገውን ታገኛለህ!” አለ ሼክ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ድንጋጤ ያብረከረከው በሚመስል ድምፅ ፡ "ለመሆኑ ምን በመፈለግ ላይ ነው ያለሁት ?" አለ ሳብር ።

"አንተኑ በመጠበቅ ልቡ ተሰቅሏል ።"

"ስለ እሱ ያውቃል ማለት ነው?"

"ይጠብቅሃል እያልኩህ!"

ሳብር እናቱ ያልነገረችው ነገር እንዳለ ተሰማው ።

"በሕይወት አለ ማለት ነዋ?"

"ለፈጣሪ ምስጋና ይግባውና በሕይወት አለ ።"

"የት ነው ያለው? ያለበትን ነው ማወቅ የም ፈልገው !"

"ትዕግሥት ያሻል ፡ ወዳጄ ።"

"እስከ መቼ ነው የምታገሠው?"

"ገና ምኑ ተይዞ ፡ ወዳጄ ።"

"እስክንድርያ ከተማ ውስጥ ነው ያለው ?"

ሼክ ዓይኖቹን ከደን ከፈት እንደማድረግ እየ ቃጣው ፡ "ትዕግሥት ፤ ትዕግሥት ያሻል ነው የምልህ ፡ ወዳጄ!" አለ በሚያጉረመርም ድምፅ ።

"ትዕግሥት ፡ ትዕግሥት ከማለት በስተቀር እስካሁን አንድም የረባ ነገር አልነገርከኝም!" አለ ሳብር—በቁጣ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሊነገር የሚገባውን ሁሉ ነግሬሃለሁ ፡ ወዳጄ" አለ ሼኩ ፡ ቃላቱን ረገጥ እያደረገ ።

ሳብር በሆዱ እየተራገመ ከሼኩ ቤት ወጣ እንዳለ ከባድ ዝናብ ያጋተው ጥቁር ሰማይ ክራኝ እያስገመገመ ተቀበለው ። የእስክንድርያ ፍለጋው ውጤት ባለማስገኘቱ የቤት ዕቃዎቹን ሸጦ ወደ ካይሮ በመዝለቅ ፍለጋውን ለመቀጠል ወሰነ። ጠቀም ያለ ዋጋ ያወጣሉ የሚባሉትን ዕቃዎቹን ቀደም ባሉት ጊዜያት ጉብኝቱ እንደ ልቡ ተንደላቅቋል ። አሁን የቀረው የቤት ውስጥ ሰባራ ስንጥር ብቻ ነበር ።

በቤቱ ውስጥ የተረፉትን ፎቶዎች ፡ ወን በሮችና ጠረጴዛዎች በደለሎች አማካይነት የመ ሸጡ ነገር ደግሞ ፡ ያለበትን ሁኔታ ለወዳጅም ሆነ ለጠላት ይፋ የሚያወጣ በመሆኑ ደስ አላለውም። ስለዚህ የእናቱ የቅርብ ጓደኛ የሆነችውን እመት ናባዊያን ማማከር አለበ ። ከእናቱ የሙያ መሰሎች መካከል እመት ናባዊያ ለሳብር ቅርበት ነበራት ።

"የቤት ዕቃዎችህን ሬሳ በደስታ እገዛቸዋ ለሁ ። እስቲ አንድ ነገር ብቻ ልጠይቅህ ። እስክ ንድርያን ትተህ የምትሄደው በምን ምክንያት ነው?" አለችው ከምታ ጨሰው ሐሺሽ የሚወጣ ውን ጨስ ሬቱ ላይ ቡልቅ እያደረገች ።

"ወደ ካይሮ ሄጄ አዲስ ሕይወት መጀመር አለብኝ !"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እግዚር ነፍስዋን ይማረውና እንዲያ ትወ ድህ ስለ ነበር ከተራው ሰው ኑሮ አግልሳ ነው እኮ እዚህ ያደረሰችህ !"

"አዎን ፡ ከእንግዲህ እንደ ማንኛውም ሰው መኖር ያዳግተኛል" አላት፡በሐሳብዋ በመስማማት።

"እንዲያው ለነገሩ ፡ ካይሮ ሄደህ ምን ትሠራለህ?"

"እኔ አለሁልህ ያለኝ እንድ ጓደኛ አለኝ ።"

"የእኛ ሥራ የሚስማማው በእስነቱ ለሚ ተማመን ሰው ብቻ ነው" አለችው ።

መጓዛው ደስ የሚል የእጣን ጭስ በሚያቱ ነው እንክርት ሳይ አክታውን እንትፍ አለበት። የእናቱ የቅርብ ጓደኛ እመት ናባቂያ ለተናገረ ችው ቃል ሳብር የሰጠው መልስ ይኸው ነበር . . .

ባቡሩ ወደ ደቡባዊ አቅጣጫ ራቱን አዙሮ መክነፍ ሲጀምር ፡ የአስክንድርያ ከተማ ከዓይኑ እየራቀችና እያነሰች መሄድ ያዘች ። የሃያ አምስት ዓመታት ትዝታውና ትውስታው የጓዳርን ወር በሚያበሥረው ቀዝቃዛ ነፋስ እየተነጸ የአካባ ቢውን ሰማይ ከተጫነው ጥቁር ደመና ጋር በመ ዋሐድ ላይ እንዳለ ተሰማው ። ለብዙ ዘመናት የኖረባትንና መውጫ መግቢያዋን አብጠርጥሮ የሚያውቀውን ከተማ በሐሳቡ ተሰናብቶ ወደ ራት ሊያጋጥመው የሚችለውን ነገር ያሰላስል

t.me/OLDBOOKSPDF

ጅመር ። አብሮት ያለው የጉዞ ጓደኛው ሐሳቡ ብቻ ነበር — አባቱን ፊልጳ የማግኘቱ ሐሳብ ። ለእናቱ ደጋግሞ ላቀረባቸው ጥያቄዎች ያጎኛቸው ባብዛኛው ያልተሟሉ መልሶች በአዕምሮው ውስጥ ይመላለሳሉ ። ሳብር ፡ የተበታተነን ሐሳቡን ሰብሰብ አድርጎ ስለ ራሱ ሕይወት ማሰብ በሚጀምርበት ጊዜ ፡ አባቱና እናቱ ጊዜያዊ የወሲብ ፍላጐታቸውን ለማርካት የፈጠሩት ማንኛት ያስገኘው ዲቃላነቱ ዝግንን ያደርገዋል ።

የካይሮ ከተማ ውካታ ሳብርን ከሐሳቡ አባነነው ። ድንገት ሳያስበው ያጋጠመው የከተማ ይቱ ድብልቅልቅ ሁኔታ በሚቀጥለው ባቡር ተሳፍሮ ወደ እስክንድርያ የመመለስ ፍላጐት አሳደረበት ። የተሰማውን የእንግድነት ጭንቀት እንደምንም አሸንፎ ከባቡር በመውረድ ፡ ሻንጣውን ባቡር ጣቢያ ውስጥ በሚገኘው የመንገደኞች ዕቃ ማስቀመጫ ውስጥ አኑሮ ወጣ ሲል ፡ በቀኑ ማምሻ ፀሐይ የፈካችው የካይሮ ከተማ ተቀበለችው ። በአንዳፍታ ስሜቱን የሳበው የታላቂቱ ከተማ ውካታና ግርግርታ ነበር ። የመኪናው ፡ የአውቶቡሱ ፡ የእግረኛው ፡ የሻጭ የለዋጩ ብዛት . . . በሰሬው ጐዳና ውካታ ፡ በጠባቡ መንገድ ውካታ . . . በደረሱበት ትርምስ ፡ ውካታ ፡ ግርግርታ ። በደረሱበት ሁሉ ድሃው ፡ ሀብታሙ ፡ ጃዊ ሳው ፡ ገራሙ የሚርመሰመስባት መዲና ። የአየሩ ጠባይ እንኳን በቅሬኔ የተሞላ ይመስላል ። ለመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥለቅ ወደ ምዕራብ በማሽቆልቆል ላይ ያለችው ፀሐይ ጨረር ፡ ከምሽቱ ቀዝቃዛ አየር ጋር ፍል ሚያ የገጠመ መሆኑን ፡ በሙቀት ውስጥ ቅዝ ቃዜ ፡ በቅዝቃዜ ውስጥ ሙቀት መኖሩን ይመሰክ ራል ።

በመጨረሻም ግራ ቀኙ በሸቀጣ ሸቀጥ መደ ብሮች ከተጨናነቀ መንገድ ዳር ፡ "ካይሮ ሆቴል" የሚል ጽሑፍ የሚነበብበት ሕንፃ ታየው ። የሚ ሸጡ ዕቃዎች በመንገዱ ግራና ቀኝ የመላለፊያውን ጠርዝ ሳይቀር አልብሰውታል ። ሆቴሉ ከገንዘብ አቅሙ ጋር ሲመጣጠን እንደሚችል ሳብር ገመተ ። ከሆቴሉ ጀግቢያ በር አካባቢ ተቀምጠ የልመና ዜማ የሚያሰማው ለማኝ ግምቱ ትክክል መሆ ኑን አረጋገጠለት ።

ሆቴሉ ፡ ባለ አራት ፎቅ ፡ አሸዋማ መልክ ያለው አሮጌ ሕንፃ ነው ። ዋናው መግቢያ በር በቅስት ቅርጽ የተዋቀረ ሲሆን ወደ ውስጥ ገባ ሲሉ እርገማኔ ያለው ኮሪዶር ይታያል ። ኮሪዶሩ መጨረሻ ላይ ወደ ፎቅ የሚያወጡ ደረጃዎች አሉ ። ኮሪዶሩ መጋመሻ ላይ ሽምገል ያለ ሰውዬ ከበስተጀላው የተቀመጠበት የእንግዶች መቀ በያ ጠረጴዛ ይገኛል ። ሽማግሌው ጐን አንዲት ሴት ቆማለች ።

ሳብር ሴትዮዋ ላይ ዓይኑን ጣል ሲያደርግ ጊዜ ጭጋግ ተጋርዶ የቆየ ስሜቱ ሲቀሰቀስ

t.me/OLDBOOKSPDF

በት፡ ተሰማው ። የእስክንድርያ ከተማ ጠረንና የባሕሩ ሽውታ ትውስታ አወደው ። አያሌ ወራት የጋረዱት የስሜት ስካሩ ታወሰው ። ከሆቴሉ ጋር አንድ ዓይነት ፅጣ ፤ አንድ ዓይነት ኩነት ያጋጠመው መሆኑ ተሰማው ። ከብዙ ዓመታት በፊት በወበትዋና በሴትነት ዐዚምዋ ያጠመደችው የእስክንድርያዋ ዓይናማ ቆንጆ ትዝ አለችው . . .

በሆቴሉ ውስጥ ድንገት ያያት ሴት ፡ ሳያስበውና ሳይፈልገው የእስክንድርያ ፍቅረኛውን ትዝታ ቀሰቀሰችበት ። ጊዜው ከአሥር ዓመት በላይ ቢሆነውም ፡ ግንኙነታቸው ትናንት እንደ ተፈጸመ ያህል በዓይን ሕሊናው ጉልቶ ታየው ።

የድሮ ፍቅረኛውን መልሶ ማግኘቱ የማይታሰብ ነገር ቢሆንም እንኳን ፡ በሁለመናዋ የምትመስላት ይህችዋ ቆንጆ ደግሞ ትዳፍኖ የኖረውን የፍቅር ረመጥ ገለጥለጥ ልታደርግለት እንደምትችል ስሜቱ አበሠረው ። ሳብር አየት ሲያደርጋት አለሰለሰ በሚያካክሉ ውብ ዓይኖችዋ ገረፍ አድርጋው ጀርባዋን ሰጠችው ። ሳብር ፡ አጉልቶ የሚያሳይ የንባብ መነጽር በሚንቀጠቀጡ እጆቹ ይዞ ሰፊ መዝገቡን እያሰሰ ወዳለው ሽማግሌ ጠጋ ብሎ ቆመ ። ሽማግሌው ሆቴሉ ውስጥ እንግዳ የገባ መሆኑን ልብ ባለ ማለቱ ፡ ሳብር የሴትዮዋን ትኩረት ለመሳብ ይጣጣር ጀመር ። ሴት የውም ሠር ብላ በዓይኖችዋ ገርመም ካደረገችው

t.me/OLDBOOKSPDF

በኋላ ፡ ሽማግሌውን ትክሻው ላይ ነካ አደረገችው ። ሳብር ሽማግሌውን እጅ በመንሣት ሰላምታ ሰጠው ።

ሽማግሌው ካቀረቀረበት ራሱን ቀና አድርጎ ፊቱን እንደ ቋጠረ ሳብርን በማድየለሽነት አየት አደረገው ።

" ክፍል ለመከራየት ፈልጌ ነበር " አለ ሳብር ።

" ለአንድ ቀን ሃያ ፒያስተር እናስከፍላለን ። "

"ሁለት ሣምንት ከቆየሁስ ?"

" ሃያ ፒያስተር በዛብኝ ለማለት ነው ? በዛሬ ጊዜ በሃያ ፒያስተር የሚገዛ ነገር ያለ ይመስልሃል ? "

" አንድ ወር ወይም ከአንድ ወር ለበለጠ ጊዜ መቆየት እችላለሁ ?" አለ ሳብር ።

ሽማግሌው ክርክሩ የሰለቸው መሆኑን ለመግለጽ መዝገቡን እያገላበጠ ፡ "እንደ ፈለግህ ! " በማለት ቁርጥ ያለ መልስ ሰጠው ።

ሳብር ክርክሩ የማያዋጣው መሆኑን በመገንዘቡ ስሙንና አድራሻውን ማስመዝገብ ያዘ ። ሽማግሌው ስለ ሥራው ላቀረበለት ጥያቄ ፡ " በራሴ ንብረት የምተዳደር ሰው ነኝ " የሚለውን መልስ ሰጠ ። የመታወቂያ ወረቀቱን ለሽማግሌው አስረክቦ የማንነቱን ዝርዝር ሽማግሌው መዝገቡ ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲያሰፍር ሳብር ሴትዮዋ ላይ ዓይኑን ጣል አደ
ረገ ። እርስዋም አጸፋዊ እይታዋን ሰገሰችው ።
በዚህ ጊዜ ሴትዮዋን ከዚህ ቀደም የሚያውቃት
የመሆኑ አንዳንድ ፍንጭ በሐሳቡ ይታየው ጀመር ።
ብዙ ጊዜ የቆየ ትዝታም ተቀሰቀሰበት ፤ የእስክን
ድርያ ከተማ የባሕር ዳር ሽታ ፤ የፍቅረኛው ጥሩ
ጠረን እውድ አደረገው ። በዚህ ሁሉ መካከል ፥
አባቱን የማግኘቱ ተስፋ በልቡ ውስጥ አንሰ
ራራ ። ሴትዮዋን በፍቅር ማጥመድ እንደሚቻሰ
ውም ተማመነ ። ሴትዮዋ በውጫዊ ሁኔታዋ ለሳብር
ግድ ያላት ባትመስልም ፥ የፈለገችውን ወንድ በእጅ
ማግባት የሚሳናት ሴት እንዳልሆነች መገመት
አላዳገተውም ።

ሽማግሌው ምዝገባውን አከናውኖ የሙታ
ቂያ ወረቀቱን ለሳብር እየመለሰ ፥ “ የእስክንድ
ርያ ሰው ነሃ ? ” አሰው ።

ሳብር በአምንታ ራሱን እየነቀነቀ ፥ “ እስክ
ንድርያን አውታታለሁ እንዳትለኝ ! ” አለ ፥ ዓይ
ኑን ከሴትዮዋ ላይ ሳይነቅል ። የሳብር አነጋገር
ሽማግሌውን ፈገግ ቢያሰኘውም ፥ ሴትዮዋ ግን
ሳብር የተናገረውን ቃል የሰማች ለመሆንዋ አን
ዳችም ምልክት አላሳየችም ። ሳብር ቀበል አድ
ርጎ ፥ “ ሰይድ ኤል ራሕሚ ከሚባል ሰው ጋር
ትተዋወቁ ይሆን ? ” አለ ።

“ ላውቀው የማልችልበት ምንም ምክን
ያት የለም ” አለ ሽማግሌው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ የ·ኮ·ግናኛች·ሁ·በት·ን ቦታ·ና ጊዜ ልት·ነ·ግረኝ ት·ች·ላ·ለ·ህ ?” አለ ሳ·ብር ፡ ስ·ሜ·ቱ·ን መ·ጭ·ጭ አ·ድ·ር·ጋ ይ·ዛ ከ·ነ·በ·ረ·ች·ው ጐ·ብ·ል እ·ይ·ታ·ው·ን እ·ያ·ነ·ሣ·ና አ·ባ·ቱ·ን የ·ማ·ግ·ኘ·ት ም·ሯ·ቱ በ·ሐ·ሳ·ቡ· ው·ስ·ጥ እ·የ·ገ·ነ·ባ·ት ።

“ ቦ·ታ·ው·ና ጊ·ዜ·ው· ት·ዝ·ም አ·ይ·ለ·ኝ ። ”

“ ኤ·ል ራ·ሔ·ሚ እ·ኩ የ·ታ·ወ·ቀ ሰ·ው· ነ·ው ! ”

“ በ·ዕ·ድ·ሜ·ዬ ·ብ·ዙ· እ·ን·ቱ· የ·ሚ·ባ·ሉ· ሰ·ዎ·ች· አ·ጋ·ጥ·መ·ው·ኛ·ል ። ዛ·ሬ ግ·ን አ·ን·ዳ·ች·ው·ም ት·ዝ አ·ይ ሉ·ኝ·ም ። ”

ሳ·ብ·ር ፡ አ·ባ·ቱ·ን የ·ማ·ግ·ኘ·ት· ተ·ስ·ፋ·ው· በ·ው·ስ·ጡ· ማ·ን·ሰ·ራ·ራ·ት· ጀ·መ·ረ ። አ·ጠ·ገ·በ· የ·ቆ·መ·ች·ው·ን ጐ·ብ·ል ዞ·ር ·ብ·ሎ· አ·የ·ት· ሲ·ያ·ደ·ር·ግ ፡ አ·ን·ድ· የ·ታ·ቻ·ለ·ው· ሰ·ው· ይ·ህ·ን በ·መ·ሰ·ለ· ዝ·ቅ·ተ·ኛ· ሆ·ቴ·ል እ·ን·ዴ·ት· አ·ድ·ር·ጎ ሊ·ያ·ር·ፍ· እ·ን·ደ· ፈ·ለ·ገ· ሰ·ማ·ወ·ቅ· የ·ቸ·ገ·ራ·ት· በ·ሚ·መ·ስ·ል ሁ·ኔ·ታ· ከ·እ·ግ·ር· እ·ስ·ከ· ራ·ሱ· እ·ን·ደ·ም·ት·መ·ረ·ም·ረ·ው· ገ·ባ·ው· ። ሁ·ኔ·ታ·ዋ· እ·ም·ብ·ዛ·ም· ቅ·ር· አ·ላ·ሰ·ኝ·ው·ም ። ወ·ደ· ካ·ይ·ሮ· የ·መ·ጣ·በ·ት· ጉ·ዳ·ይ· ሲ·ከ·ሰ·ት·ላ·ት· እ·ን·ዲ·ህ ·ያ·ለ·ው· አ·ል·ባ·ሌ· ሆ·ቴ·ል ው·ስ·ጥ· ለ·ማ·ረ·ፍ· የ·መ·ረ·ጠ·በ ት·ን ም·ክ·ን·ያ·ት· እ·ን·ደ·ም·ት·ረ·ዳ·ው· አ·ል·ተ·ጠ·ራ·ጠ·ረ·ም ።

ለ·መ·ሆ·ኑ ጐ·ብ·ል·ዋ· ታ·ስ·ታ·ው·ሰ·ው· ይ·ሆ·ን ? የ·ቆ·የ· የ·እ·ስ·ክ·ን·ድ·ር·ያ· ት·ዝ·ታ·ው· አ·ገ·ረ·ሸ·በ·ት ። የ·ሰ·ላ የ·ው·ብ· ል·ጅ· ረ·ጃ·ጅ·ም· ጥ·ፍ·ሮ·ች· ገ·ላ·ው·ን ጥ·ር·ቅ·ም አ·ደ·ር·ገ·ው· ወ·ግ·ተ·ው· ሲ·ያ·ስ·ጨ·ን·ቁ·ት· ፡ ከ·ባ·ሕ·ሩ የ·ሚ ·ነ·ጥ·ሰ·ው· የ·ም·ሽ·ት· ቀ·ዝ·ቃ·ዛ· አ·የ·ር· ገ·ላ·ቸ·ው·ን አ·ብ·ሶ ሲ·ያ·ል·ፍ· ተ·ሰ·ማ·ው· ። በ·ዚ·ያ·ን· ወ·ቅ·ት· አ·ባ·ት·ዋ· እ·ስ·ክ

t.me/OLDBOOKSPDF

ንድርያ ነበሩ ማለት ነው ? ወደ ካይሮ መጥተው ይሆን ሆቴል ማስተዳደር የጀመሩት ከዚያን ጊዜ ወዲህ ይሆን ?

ጐበልዋ ፡ " መሐመድ አል ሳዊ ! " ብላ ስት ጣራ ሳብር በሐሳብ ከንጐደበት መለሰ አለ ።

በሩ አቅራቢያ ተቀምጠ የነበረ በዕድሜው የገፋ አንድ ጠቆር ያለ ሰው ከመቀመጫው አፈፍ ብሎ በመነሣት ወደ ጐበልዋ ቀረብ ብሎ ቆመ ። ሰውዬው ቁመቱ አጠር ያለ ፡ ሰውነቱ ከሲታ ፡ የተሸበጐረጐረ ጀለብያና ራሱ ላይ ነጭ ቆብ ያደ ረገ ነበር ።

በእጅዋ ወደ ሳብር እያመለከተች ፡ " ክፍል ቁጥር አሥራ ሦስት አድርሳቸው " አለችው ።

ሳብር የክፍሉን ቁጥር ሲሰማ ፈገግ አለ ። ሻንጣውን ከባቡር ጣቢያ ሚጮጣት ያለበት መሆ ኑን ተናግሮ ወደዚያው አመራ ። ዕቃውን ይዞ እንደ ተመለሰ ፡ በረኛው መሐመድ አል ሳዊ በአ ክብሮት ተቀብሎ ለሆቴሉ ተላላኪ ሻንጣውን ቁጥር አሥራ ሦስት እንዲያደርስ ስለ ነገረው ፡ ተላላኪው ሳብርን እየመራ ወደ ሕንፃው ሦስ ተኛ ፎቅ ይዞት ወጣ ። የሆቴሉ ተላላኪ በመካከ ለኛ ዕድሜ የሚገኝ ፡ አረማመዱ ፈጠን ፈጠን የሚል ፡ ዓይኖቹ ቁልጭልጭ ያሉ ፡ የጭንቅላቱ ማነስ ጭንጭኝ የሚያስመስለው ሰው ነበር ።

" ስምህ ማነው ? " አለ ሳብር ፡ ተላላኪውን ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"አሊ ሰርያኩስ እባላለሁ" አለ ተላላኪው።

ሰርያኩስ በሁኔታውና በንግግሩ በጥቅም በቀላሉ ሊያለል የሚችል ሰው መሆኑን ሳብር ጠረጠረ። ቀጠል አድርጎም፣ "እንግዴ ተቀባዩ ሽማግሌ የሞቱት ባለቤት ነው?" በማለት ሰርያኩስን ጠየቀው።

ሰርያኩስም ልዩ በሆነ ቅልጥፍና፣ "አዎን ነው፤ ከሊል አቡል ፍጋ ይባላል" አለ።

ሳብር፣ ሽማግሌው አጠገብ ቆማ ስለ ነበረች ው ገብል ሰርያኩስን ሲጠይቀው ፈልጎ፣ ግና ከመድረሱ ንገር ማብዛቱ እንደሚያስገምተው በማሰብ ጥያቄውን ከፋ መልሰው።

ሳብር፣ ከፍሉን ተረክቦ ብሯውን ከቀረ በኋላ፣ አካባቢውን መቃኘት ያዘ። የተከራየው ክፍል ጣራው ሰማይ የደረሰ፣ ግድግዳው ረጅም ዕድሜ ውን በማልጽ የሚናገር፣ አልጋው ግና በእጅ ነካ ሲያደርጉት የሚያቃስት ሆኖ አገኘው። በክፍሉ መስኮት በኩል የመንገዱን ሰሜናዊ ጫፍ ሲመ ለከት፣ ብዙ ሕፃናት በአደባባዩ መካከል ከሚገ ኘው የውኃ ፏፏቴ ውስጥ ገብተው ሲንቦጫረቁ አየ። ሳብር የክፍሉን መብራት አብርቶ አንድ አሮጌ ሶፋ ላይ በመቀመጥ ዓይኖቹን ከደን አደ ረገ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አባቱን ፈልጎ የማ ግኘት ሕልሙና የወሲብ ፍላጐቱ በአዕምሮው ውስጥ ተደበላልቀው ይጋጨበት ጀመር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ሆቴሉ ሲገባ ሽማግሌው አጠገብ ቆሟ ያያት ጉብል ጠጫ የሚያካክሉ ስልምልም ዓይ ኖች ሲጠቃቅሱት ታየው ። እርስዋም ብትሆን ወደምትኖርበት ሆቴል መጥቶ ፡ ክፍል ተከራይቶ የተቀመጠበትን ምክንያት በሐሳብዋ እንደምታሰላ ስል ተሰማው ። ከብዙ ዓመታት በፊት እስክንድ ርያ የሚያውቃት ቆንጆዬ ኮረዳ መሆንዋን መጠ ርጠር አልፈለገም ። በእስክንድርያ ወዶብ ውካታ ውና ትርምሱ መካከል ተገናኝተው ሊጠጋት ና ሊያነጋግራት ሲከጅል ፡ ትሸሸውና አትጠጋኝ ትለው የነበረው ሁኔታ በጉልህ ታየው ። እኔ ኑኝ ያለች ሴት ሳብርን ፊት ነሥታው እንደማታውቅ በሱራትና በወንድነት ስሜት እንደ ነገራትና ፡ እር ሷም ለማንም ወንድ ደንታ እንደ ሌላት እንደ ዘበት የገለጸችለት ታወሰው ። በመጨረሻም ረጅም ጸጉርዋን ከባሕሩ የሚነሣው ሽውታ እየነስነሰው እንዴት አልባሌ ሴት ተከትላ እብስ ያለችበት ትዝ አለው ። ዛሬ ደግሞ ሳያስበው እዚህ ሆቴል ውስጥ ድንገት ተገናኙተው ዓይን ለዓይን በተያ ዩበት ወቅት ፡ እይታዋ ቢማርከውም ፡ ከዚህ ቀደም የሚተዋወቁ ለመሆናቸውና በእስክንድርያ ከተማ ፡ በባሕሩ ዳርቻ የተሰለፉትን የዓሣ ማጥመጃ ጀልባ ዎች ተከልለው የተለዋወጧቸውን የድርያና የፍ ቅር ታላት የሚጠቁም ፍንጭ አላሰየችውም ። ከጥቂት ትግልና ልፊያ በኋላ ጉንጮችዋን ሳም እንዳደረጋትና እርስዋም በረጃጅም ጥፍሮችዋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈጭራ ሸሽታ ልታመልጠው ስትል ፡ " አንድ ቀን እነዚህን ጥፍሮችህን እሰባብርልሻለሁ " ያላት ታመሰው ።

ያን ዕለት ሳብር እስክንድርያ ወደብ ያገኛትን ገበል በዛቻ ብቻ አልተለያትም ። ከልጅቱ ጋር የቀረበ ዕውቂያ ለመመሥረት ያደረገው ጥረት የወንድነት ፍላጐቱን ማርካት አስችሎ ታል ። ይሁን እንጂ ፡ የሳብርና የልጅቱ ግንኙነት የመቀጠል ፡ የሚደግና የመገልበት ዕድል አላጋ ጠመውም ። ያንድ ቀኑ ድንገተኛ ትውውቅ ፡ በረጅም ዓመታት የመለያየት ጉም ተሸፍኖ የመቅረት ዕጣ ገጥሞታል ። እናቱ ፡ አልናቢ ዳኒያል ወደ ተባለው ምርጥ ሰፈር እስክ ተዛወረችበት ጊዜ ድረስ በሳብርና በእናቱ ላይ ብዙ ፈተና ፡ ብዙ መንገላታትና ብዙ ውጣ ውረድ ደርሰባቸዋል ። ምናልባትም ይኸ ዛሬ ያረፈበት ሆቴል ፡ ከብዙ ዓመታት በፊት ከተዋወቃት ከዚያች ወጣ ልጅ ጋር አንድ ዓይነት የመልካም ዕድል ቁርኝት ሊኖረው ይችል ይሆናል ። ይህች ገላል ድንገት ዓይኑን ክሳረፈባት ቅጽበት ጀምሮ ፡ የወንድነት ስሜቱ በደም ሥሮቹ ውስጥ እንዲንከላወስ አድርጋለች ። ሳብር ፡ አባቱን በመፈለግ የሚያጋጥመውን ወጣ ውረድና ብቸኝነቱን የሚያረሳሳ አንዲት ፍቅረኛ የምትለግሰው እርካታና አለሁ ባይነት እንደሚያሻው ገብቶታል ። አንድ ቀን ልፋቱ ሁሉ ፍሬ አፍርቶ ፡ ያሰበው ሲሳካለት ፡ " እኔ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳብር ፡ ሳብር ሰይድ ፡ ሰይድ ኤል ራሕሚ ነኝ ። የልደት መረጃዬና የወላጆቼ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ይኸው ። ይኸ ፎቶግራፍም የማያወላ ውል መረጃዬ ነው ! ” በማለት ፡ አፉን ሞልቶ የሚናገርበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ።

ያ ጊዜ ዕውን ሲሆን ፡ ከሥጋቱ ፡ ከጥርጣሬ ውና ከጭንቀቱ ሁሉ ይገላገላል ።

ከብዙ ዓመታት በፊት በአንድ ምሽት ውስጥ ያወቃትን ኮረዳ ፡ ዛሬ የተደላደለች እመ ቤት ሆና ነው ያገኛት ። ያ ሲግሊጋነትዋ ፡ ያ የባሕር ዳርቻ ወዘናዋ ፡ ያ ማራኪ ጠረንዋ ዛሬም እንዳለ ይሆን ? . . .

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ሦስት

ሳብር ሴሊቱን ከሦስት ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ ከተኛ በኋላ ፡ ማለዳ ላይ ድካሙም እንቅል ፋም ለቆት ተነሣ ። የክፍሉን መስኮት ከፈት ሲያደርግ ፡ የካይሮ ከተማ ከፊቱ ተንጣላ ተመለ ከተ ። ሰብዙ በመናት የኖረባትና ደህና አድርጎ የሚያውቃት የእስክንድርያ ከተማ የማለዳ ትእ ይንት ተለወጠ እንግዳና ባዕድ የሆነ አካባቢ ተተክ ቷል ። የሚተነፍሰው አየር እንኳን የተለየ ሆኖ በታል ። ያረፈበት ሆቴልም ሆነ አካባቢው የብ ዙኃነትና የእንግድነት ስሜት እንዲጫጫነው ቢያ ደርግም ፡ አባቱን ፊልጎ የማግኘቱ ተስፋ ደግሞ ጉንካሬ ሰጥቶታል ። አሲ ሰርያክስ ያመጣለትን ቁርስ ተመግቦ እንደ ጨረሰ ፡ ዕቃዎቹን ለማንሣት ተመልሶ ሲመጣ ፡ ‘‘ትናንት አቶ ከሊል አጠገብ ቆማ የነበረችው ሴትዮ ማናት?’’ በማለት ድን ገተኛ ጥያቄ ሰነዘረለት ።

‘‘ሚስቱ ናት !’’ አለ ፡ ሰርያክስ ።

ሳብር ያላሰበውን መልስ በማግኘቱ ግራ በተጋባ ስሜት ፡ ‘‘የእስክንድርያ ተወላጅ ናት?’’ የሚለውን ጥያቄ አከታተለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ትውልድ አገሯ የት እንደሆነ አላውቅም።"

"አቶ ከሊል ይህን ሆቴል የገዛው መቼ ነው ?"

"እረ እኔ እንጃ ፤ እኔ እዚህ ሥራ ከገባሁ አምስት ዓመት ብቻ ነው የሆንኝ ። "

"ከአምስት ዓመት በፊትም አብረው ነበሩ ማለት ነው?"

"እኔ እዚህ ከገባሁ ጀምሮ አብረው ነው ያሉት ። "

ሳብር ስለ ሴትዮዋ ያለፈ ታሪክዋ የገመተው ትክክልነቱንና ከብዙ ዓመታት በፊት ለአንድ ምሽት ዕድሚ ያወቃት ጉብል መሆንዋን በሐሳቡ አረጋገጠ ። ሽማግሌው ከሊል ከዚያች ከማትለያት አልባሌ ሴትዮ በገንዘብ ኃይል አባብሎ መስዶ ዘንካታ እመቤት እንዳደረጋትም ገመተ ። በሌላ በኩል ደግሞ ፥ ስለ ድሮ ፍቅረኛው ሲያሰላስል አባቱን የመረለገን ዓላማ ወደ ጐን ብሎ የያዘው ገንዘብ ሲያስበው አልቆበት ችግር ውስጥ እንዳይገባ ሥጋት አደረበት ። ከክፍሉ ወጥቶ ሆቴሉ እንግዳ መቀበያ ሲደርስ ሚስተር ከሊል ከሆቴሉ በር ጠባቂ ከመሐመድ አል ሳዊ ጋር ሲነጋገር አገኘው ። የሆቴሉ እንግዶች በማረፊያ ክፍሉ ውስጥ ተቀምጠው ጋዜጦች ያገላብጡ ፥ የጠዋት ቡናቸውን ይጠጡ ፥ ጥቂቶቹም ወሬያቸውን ይሰልቁ ነበር ። ሳብርም ለሆቴሉ ባለቤት ለከሊል ሰላምታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ካቀረበ በኋላ ፡ የከተማዋ ነዋሪዎች የቴሌፎን ማውጫ እንዲሰጠው ጠየቀ ።

ሰይድ . . . ሰይድ . . . ሰይድ . . . አዎ ። ሰይድ አል ራሕሚ ። አዎን ፡ ስሙ ተመዝግቦአል ማለት ነው ። የሳብር ልብ ከበሮ ይደልቅ ጀመር ። ከስሙ ቀጥሎ ፡ ሐኪምና የዩኒቨርሲቲ የሕክምና ትምህርት ፕሮፌሰር ይላል ። ከሆነ አይቀር እንዲህ ነው! ስለ አባቱ ዝና ከእናቱ የሰማው ሁሉ እውን እየሆነ ሲሄድ ታየው ። ከደስታው ብዛት ፡ "አምላኬ ሊረዳኝ ይሆን !" በማለት ጮክ ብሎ ተናገረ ። ከለሊ ቀና ብሎ ሳብርን በአይታው ገበኘው ።

"እዚህ ድረስ የመጣሁበት ጉዳይ ሊሳካልኝ ነው መሰለኝ !" አለ ሳብር ፡ ቀጠል አድርጎ ።

"ያሰቡት ሲሳካ ደስ ማሰኘቱ የተለመደ ነገር ነው" አለ ከሊል ፡ ፈገግ እያለ ።

—እንቱም ያችን መሳይ ቆንጆ የማለህ ስታደርግ ተሳክቶልሃል !— አለ ሳብር በልቡ ።

ከሊል ዓይኖቹን እላዩ ላይ ተክሎ በመቆየቱ ፡ "የሕይወቱ አለኝታ የሆነ አንድ ሰው በመፈለግ ላይ ነኝ" አለ—ሳብር ።

"እስከ ዛሬ ድረስ እዚህ ሆቴል አርፎ ፡ ረዘም ላለ ጊዜ የሰነበተ ሰው የለም ። ሁሉም የተለየ ጉዳዩን ለመፈጸም ይመጣና ፡ አንድ ቀን ፡ አንድ ሳምንት ፡ በዛ ቢባል አንድ ወር ቆይቶ እብስ ይላል" አለ ከለሊ ፡ በቅሬታ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ታዲያ ሰው የመጣበትን ጉዳይ ከፈጸመ በኋላ እዚህ ምን ሊያደርግ ይሰነብታል?" በማ ለት ሳብር መለሰ ።

"እኔን የሚያሳዝነኝ እዚህ ከሚያርፉት እንግዶች መካከል አብዛኛዎቹ ፡ አንድ ጣራ ሥር አብረው ሰንብተው ፡ በአንድ ማዕድ አብረው ተመ ግበው የረባ ዕውቂያ እንኳ ሳይኖራቸው መለያየ ታቸው ነው ።"

"እንደምገምተው ከሆነ በዚህ ሥራህ ሳት ደሰትበት አትቀርም" አለ ሳብር ፡ ጨዋታው እንዲ ቀጥል በመፈለግ ።

"ፈጽሞ አያስደስተኝም!" አለ ከሊል ።

—ምን ታደርግ ፤ ጊዜ አዘበናህ! የልጅ ልጅ ህን ያለ ሐሳብ ታቅፈህ ! — አለ ሳብር በሆዱ ።

ሳብር ከኋላው የሰው ዱካ ተሰማው ። ዞር ብሎ ቢመለከት ሴትዮዋ ጠቆር ያለ ጉርድ ቀሚ ስና ቀይ ሸሚዝ ለብሳ ፡ አንገቷ ላይ የሚያምር ኾንጉርጉር ሻሽ ሸብ አድርጋ ብቅ አለች ። አስተያየቷ ሰውነቱን ወረረው ፤ ልቡ ለአንድ አፍታ ምቱን ቀጥ አድርጎ ያቆመ መሰለው ። የእስክንድርያው ወደብ የባሕር ጠረን ዳግመኛ እውድ ሲያደርገው ተሰማው ። በር ጠባቂው ከተ ቀመጠበት ፈጠን ብሎ በመነሣት ፡ የያዘችውን ሻንጣ ተቀበላት ። ሽማግሌው ከሊል ካቀረቀረ በት መነገቡ ላይ ቀና ብሎ ፡—

t.me/OLDBOOKSPDF

“መሄድሽ ነው?” አላት።

“አዎን፡ መሄዴ ነው፤ ዶሎ እመለሳለሁ” አለችው። የሆቴሉን በር ጠባቂ፡ መሐመድ አል ሳዊን አስከትላ ከሆቴሉ ወጣች።

—አይ ከሲል! በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ እንዳ የሁህ ከሆነ፡ ማንኛውም ነገር ስሜትህን አይኬ ረኩረው፤ አስተያየትህን አያጠቁረው፤ ወይ አያፈ ካው! ምን ያለሽው ተአምረኛ ሰው ነህ?— አለ ሳብር በልቡ።

ሳብር ከሲልን ተሰናብቶ ከሆቴሉ ወጣቅ አለ። ወጣ እንዳለ ሴትዮዋና መሐመድ አል ሳዊ የሄዱበትን አቅጣጫ ሲቃኝ፡ ሁለቱም ተከ ታትለው ወደ አደባባዩ ሲያቀኑ አየ። ሬጥኖ በመ ራመድ በጥሂት ጊዜ ውስጥ ደረሰባቸው። መሐ መድ አል ሳዊ በጥርጣሬ ዓይን ስለ ተመለከ ተው፡ “እባክዎን አቶ መሐመድ፡ የአዝሃርን አደባባይ አቅጣጫ ያመልክቱኝ” አለው።

ሴትዮዋም በመገረም ሳብርን አየት አደረገ ችው። መሐመድ አል ሳዊ የተጠየቀውን ስፍራ በቃሉም በእጁም ያመለክት ጀመር። ሳብር በአ ንድ በኩል መሐመድ አል ሳዊ የሚናገረውን የሚሰማ እየመሰለ፡ በሌላ ወገን ደግሞ ሴትዮ ዋን ሰረቅ አድርጎ ይመለከታት ነበር። አስተያየ ትዋ ስሜቱን የሚቀሰቅስና ተስፋ የሚያጭር ሆነ በት። ከብዙ ዓመታት በፊት በተገናኙበት በዚያች

t.me/OLDBOOKSPDF

ምሽት ጸጉሯ ላይ ሽጣው ስለ ነበረው እምቢጥ አበባ ፥ የፍቅር ግለታቸውን ያበርደው ስለ ነበረው የባሕር ዳርቻ የምሽት ሽውታ ሊያነሣሳት ዳድቶት ነበር ። በመሐሉ መሐመድ አል ሳዊ ንግግሩን በማቋረጡ ፥ ሁለቱንም አመስግኖ ተለያቸው ። የቅርብ አጃቢዎን አስከትላ ወዴት መሄዷ ይሆን ? ሲል አሰበ ። አቀራረቡ ዓይን ያወጣ መሆኑም ተሰማው ። ሳብር አንድ ነገር ለማግኘት ከሰበ ወደ ኋላ የሚል ሰው አይደለም ። የዛሬው ሁኔታው ግን መረን ወደ መልቀቅ ያዘነበለ መሆኑን ሳይገነዘበው የቀረ አይመስልም ።

መሐመድ አል ሳዊ በንግረው መሠረት ፥ ሳብር የፈለገውን አድራሻ ያለ ምንም ችግር አገኘው ። ቢሮው ውስጥ ያገኘው ሠራተኛ ፥ ሐኪሙ ሥራ የሚጀምሩት ዕኩለ ቀን ላይ መሆኑን ስለ ነገረው ለመጠበቅ ወሰነ ። እንግዳ ማረፊያው ውስጥ ተቀምጠ ሳለ ፥ ቦታው አባቱ የሚሠራበት ቢሮ መሆን አለመሆኑ ፥ ከተገናኙ በኋላ አላውቅህም ቢለው ምን ማድረግ እንዳለበት በማውጣት በማውረድ በሐሳብ ይዋዥቅ ገባ ። ተስፋ ፥ ፍርሃት ፥ ተስፋ መቁረጥ ፥ ሥጋት ይፈራረቁበት ጀመር ። አልፎ አልፎም አቅሙ በቻለው መጠን መብቱን ከማስከበር ወደ ኋላ እንደማይል ለራሱ ቃል ይገባ ነበር ። በዚህ ሁሉ የሐሳብ ትርምስ ውስጥ እያለ ፥ የሐኪሙን የሕክምና ሙያ ዘርፍ ባለማወቁ ከተቀመጠበት የእንግዶች ማረፊያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተነሥቶ ወደ ረዳት ሠራተኛው ቢሮ በመግባት ፡ “ ለመሆኑ ዶክተሩ የታወቁበት የሕክምና ሙያ የትኛው ነው ? ” በማለት ጠየቀ ።

“የልብ ሐኪም ናቸው” አለ ፡ ረዳት ሠራተኛው።

“አመሰግናለሁ ፤ እንዲያው ለማረጋገጥ ብዬ ነው ። ለአገሩ እንግዳ ፡ ለሰው ባዳ ነኝ ። ከእስክን ድርያ ሰሞኑን ነው የመጣሁት ” አለ ሳብር ፡ ያቀረበው ጥያቄ ያስገምተኛ ይሆናል ብሎ በመሥጋት ።

“ ዕድሚያቸው ምን ያህል ይሆናል ? ” አለ ሳብር ፡ ጥያቄውን በመቀጠል ።

“ እሪ እኔ ዕድሚያቸውን አላውቅም ” አለ ረዳት ሠራተኛው ፡ በጥያቄው በመገረም ።

“ እንዲያው በግምት ማለቴ ነው ።”

“ የዩኒቨርሲቲ የሕክምና ክፍል ፕሮፌሰር ናቸው ” አለ ረዳት ሠራተኛው ፡ የጥያቄውን አቅጣጫ በመቀየር ።

“ ትዳር አላቸው ? ”

“ አዎን አላቸው ፤ የሕክምና ትምህርቱን በማገባደድ ላይ ያለ ልጅም አላቸው” አለ ፡ ረዳት ሠራተኛው ።

— ነገር ተበላሸ !— አለ ሳብር ፡ በሆዱ ። ከዚህ ቀደም መኖሩ የማይታወቅ የማንም ጋለሞታ የወለደችው ዲታላ ልጅህ ነኝ ብሎ ሲመጣ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቤተሰቡ መታመሱ እንደማይቀር ተሰማው ።
—የመጣው ቢመጣ ከእንግዲህ ወደ ኋላ አልልም !
አለ ሳብር ፥ በሐሳቡ ።

ሕመምተኞች አንዳንድ እያሉ በመምጣት የእንግዳ ማረፊያውን ክፍል ሞሉት ። በየተራ ቸው እየተጠሩ ሲገቡ ከቆዩ በኋላ የሳብርም ተራ ደረሰና ተጠራ ። ሥጋትና ጥርጣሬ እንደ ተጫ ነው በሩን ከፍቶ ዶክተሩ ቢሮ ገባ ። ሳብር የያ ዘው ፎቶግራፍና ሐኪሙ በምንም አይመሳሰ ሉም ። ሳብር ከሐኪሙ ትይዩ ተቀምጦ ትኩር ብሎ ከተመለከተው በኋላ ፥ " ሳብር ፥ ሰይድ ኤል ራሕሚ እባላለሁ " አለ ።

" ልጄ ነህ ማለት ነዋ ! " አለ ዶክተሩ ፥ ከት ብሎ እየሣቀ ።

" እርስዎ ዘንድ የመጣሁት ስሕክምና አይ ደለም " አለ ሳብር ፥ በለሆሳስ ።

ዶክተሩ በመገረም አስተዋለው ።

" ሰይድ ፥ ኤል ራሕሚ የተባለ ሰው እየፈለ ግሁ ነው ። "

" ተፈላጊው እኔ ነኝ ማለት ነው ? "

" እኔ እንጃ ፤ ስማንኛውም ይሆን ፎቶግራፍ አንዴ ይመልከቱት ። "

ዶክተሩ ፎቶግራፉን በጥንቃቄ ከተመለከ ተው በኋላ ራሱን በአሉታ ነቀነቀ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እርስዎ እዚህ ፎቶግራፍ ላይ የሉም ?" በማለት ሳብር ጠየቀ ።

"ጨርሶ የለሁበትም !" አለ ዶክተሩ : እንደ መሣቅ እየቃጣው ። "ፎቶግራፉ ላይ የም ትታየው ቆንጆ ሴትዮ ማናት ?" በማለት ለሳ ብር ጥያቄ ሰነዘረለት ።

"ከዘመዶችዎ አንዷ ልትሆን ትችላለች ። ከሦስት ዓመት በፊት የተነሣ ፎቶግራፍ ነው ።"

"ፊጽሞ ልትሆን አትችልም !" አለ ዶክተሩ።

"እርስዎ የራሔሚ ቤተሰብ አይደሉም ?"

"ኔኛ እንጂ ። አባቴ ኤል ራሔሚ ይባላል ። የፖስታ ቤት ሠራተኛ ነበር ።"

"ከቤተሰባችሁ ውስጥ በዚህ ስም የሚ ጠሩ ሴሎች አባላት ይኖራሉ ?"

"የሉም ። የቤተሰባችን አባላት በጣም ጥቂ ቶች ናቸው" አለ ዶክተሩ ።

ሳብር ፊቱን ቅጭም አድርጎ ከተቀመጠበት ብድግ አለ ። "በከንቱ ስላደከምኩት በጣም አዴ ርጌ አዝናለሁ ። በዚህ ስም የሚጠራ ሌላ ሰው አጋጥሞት ያውቃል ?"

"ፊጽሞ አጋጥሞኝም አያውቅ ። የምትፈልገው ነገር ምን እንደሆነ አልገባኝም !" አለ ዶክተሩ ።

"ሰይድ ኤል ራሔሚ የተባለ ሰው ነው የምፈልገው ። ከሦላሳ ዓመት በፊት በተነሣው በዚህ ፎቶግራፍ ላይ ያለውን ሰውዬ !"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዲህ ያለ ሰው እዚህ ቦታ ነው ያለው ማለት ያዳግታል ። ለማንኛውም የጠፋ ሰው የመ ፈለግ ሙያ የለኝም" አለ ዶክተሩ ፡ ግንኙነታ ቸው ማብቃቱን በሚጠቁም እንቅስቃሴ ።

ሳብር ከዶክተሩ ቢሮ ከወጣ በኋላ መጀመ ሪያ ካገኘው የመንገድ ዳር ቡና ቤት ውስጥ ገቦራ በማለት አንድ መለኪያ ብራንዲ አዘዘ ። ብራንዲ ውን ከተገነጨ በኋላ ፡ ከቴሌፎን ማውጫው ያገ ኘው መረጃ ራይዳ እንደ ሌለው በመገንዘብ ፡ የጥለጋውን ዘዴ በአዲስ መልክ መቀየስ እንዳለ በት ተገነዘበ ። ጠዋት ከሆቴሉ ሲወጣ ታይቶት የነበረው ብሩህ ተስፋ ጥቁር ደመና ሲሸፍነው ታየው ። ከዚህ ቀደም በእስክንድሪያ ከተማ ውስጥ ወደ ሕዝብ ቁጠራ ቢሮ ፡ ወደየቀበሌው ሽኮች መጅሊስ እየተንከራተተ ውጤት በሌለው ፍለጋ ያባከነው ጊዜ ታወሰው ። ካይሮ ደግሞ ከእስክን ድርያ አሥር እጥፍ የበለጠች ከተማ ናት ። በካ ይሮ የሚያውቀውና የሚያማክረው አንድም እገሌ የሚለው ሰው የለውም ። በጋዜጣ ማስታወ ቂያ ቢያወጣ ይረዳው ይሆናል ። በመጨረሻም ሽምገል ያለውን የቡና ቤቱን አስተናጋጅ በመጥ ራት ፡ "ሰይድ ኤል ራሕሚ የተባለ ሰው ታውቃ ለህ ?" በማለት ጠየቀው ።

"አምን አውቃለሁ ። እዚሁ አቅራቢያችን የግል ክሊኒክ አለው" አለ አስተናጋጁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ይሽኛውን ኤል ራሕሚ ማለቱ አይደለም። እኔ የምፈልገው ኤል ራሕሚ በጣም የታወቀና የተቻለው ሰው ነው” አለ ሳብር።

በአነጋገሩ ግብፃዊ አለመሆኑ የሚታወቅበት አስተናጋጅ፣ “ከደንበኞችን መካከል በዚህ ስም የሚጠራ ሌላ ሰው አላውቅም” አለ፣ የተጠየቀውን ስም እንድ ሁለቴ እየደጋገመ።

“እስከ ዛሬ ስትኖር የት እንደ ደረሰ የማታውቀውን ሰው የመፈለግ ችግር አጋጥሞህ ያውቃል?” አለ ሳብር፣ ከብራንዲው ጐንጨት እያደረገ።

“ባለፈው ጦርነት ወቅት ወጥቶ እንደ ቀረ ልጅ ዓይነት?” አለ አስተናጋጁ፣ ፊቱን ቅጭም እያደረገ።

ሳብር ራሱን በአሉታ ነቀነቀ።

“እውነትህን ነው፤ ጦርነቱ ካለቀ ቆይቷል፤ የሞተውም የተረፈውም ቁጠው ታውቋል” አለ ሰውዬው።

“የሞተ ሳይሆን ወጥቶ የቀረ ማለቱ ነው” አለ ሳብር።

ሳብር፣ “ስፈንክስ” በሚል ስያሜ የታወቀውን ጋዜጣ አድራሻ እንዲያመለክተው አስተናጋጁን ጠየቀው። አስተናጋጁ፣ የጋዜጣው አድራሻ በታሕሪር አደባባይ አካባቢ መሆኑን ነግሮት ተለያዩ።

የጋዜጣው ቢሮ የሚገኘው በአንድ ነጭ ሕንፃ ውስጥ ነበር። በሕንፃው ፊት ለፊት ከተሠራው

t.me/OLDBOOKSPDF

አደባባይ መካከል ንጹሕ ውኃ ይንፎለፎላል ። የእስክንድርያ ነዋሪ የሆነና ለእናቱ ቅርበት የነበረው የአንድ ዲታ ግሪክ መኖሪያ ቤት ትዝ አለው ። የጋዜጣውን ቢሮ ሕንፃ ዋና መግቢያ በር ዘልቆ እንደ ገባ ፡ ከሩቅ አንዲት ሴት በእጅዋ ስትጠቅሰው በማየቱ ገረመው ። ወዲያው እንደ ተረዳው ፡ ሴትዮዋ የምትጣራው ከኋላው ቆሞ የነበረውን ተላላኪ ነበር ። ተላላኪው ሴትዮዋ ወደ ቆመችበት ፈጥኖ በመድረስ አንድ ጥቅል ነገር አስረክቧት ወደ ሌላ አቅጣጫ አመራ ። ከዚያም ሳብርና ሴትዮዋ ፊት ለፊት ግጥምጥም አሉ ። ሴትዮዋ ወዲ ፊትዋን ፀሐይ ያጠየመው ፡ ዓይኖችዋ ከብለል ከብለል የሚሉና የሚያማምሩ፡ ገጽታዋ ብሩሕና አቅዋምዋ የተደላደለ ነበር ። ሳብር ግና እንዳያት ስሜቱ ተማረከበት ። የአክብሮት ሰላምታ ካቀረበላት በኋላ ፡ የጋዜጣውን የማስታወቂያ ክፍል እንድታመለክተው ጠየቃት ። አክብሮትና ትሕትና በተመላበት ሁኔታ ፡ "እኔም የምሄደው ወደዚያው ስለሆነ አብረን እንሂድና አሳይሃለሁ" አለችው ።

አድናቆት ፡ አክብሮትና ፍላጐት የተቀላቀለበት ስሜት እየተፈራረቀበት ከኋላዋ ተከተላት ። ከጋዜጣው ማስታወቂያ ቢሮ እንደ ደረሰ ፡ ከሠራተኞቹ መካከል የሚያነጋግረውን ሰውዬ አሳየችው። ከሰውዬው ጠረጴዛ ፊት ለፊት ኢሳን ታንታዊ የሚል ስም የተጻፈበት ምልክት ይታያል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳብር ሠራተኛው ጠረጴዛ ፊት ለፊት ከሚገኘው ወንበር ላይ ካረፈ በኋላ ፡ ‘‘ሰይድ ኤል ራሕሚ የሚባል ሰው እንድታፈላልጉኝ ነው የመጣሁት’’ አለ ።

‘‘የልብ ሐኪሙን?’’ አለ ሠራተኛው ። ሳብር ራሱን በመነቅነቅ ፡ ሠራተኛው ሌሎች በዚህ ስም የሚጠሩ ሰዎችን እንዲጠራለት አፍ አፉን እያየ ይጠባበቅ ጀመር ።

‘‘ከልብ ሐኪሙ ኤል ራሕሚ ሌላ በዚህ ስም የሚጠራ ሰው አላወቅም ። አንተ የምትፈልገው ኤል ራሕሚ ምን እንደሚሠራና የት እንደሚኖር የምታውቀው ነገር አለ?’’

‘‘ምንም የማውቀው ነገር የለም ። የማውቀው ነገር ቢኖር የታወቀና የተታለው ሰው መሆኑን ብቻ ነው ። የቴሌፎን ማውጫውንም አገላብጬ ያገኘሁት አሁን የጠራሽውን የልብ ሐኪም ብቻ ነው ።’’

‘‘የታወቀና የተታለው ሰው ከሆነ ቅጥሩ ማውጫው ላይ ላይመዘገብ ይችላል ። ወይም ደግሞ ከክሊማ ወጣ ብሎ ሊኖርም ይችል ይሆናል ። ለማንኛውም በጋዜጣ ላይ ማስታወቂያ ማውጣቱ ይጠቅማል ።’’

‘‘እንግዲያው ለአንድ ሳምንት የሚቆይ አጠር ያለ ማስታወቂያ አዘጋጅልኝ ። በካይሮ ሆቴል

t.me/OLDBOOKSPDF

በኩል በስልክም በፖስታም ልገኝ መቻሌን ግለ ጹልኝ ። ”

“ማስታወቂያው ላይ ስምህን መጥቀስ አለ ብን ።”

ሳብር በነገሩ ለጥቂት ጊዜ ካሰበበት በኋላ ፡ “ሳብር ሰይድ ብለህ መጥቀስ ትችላለህ” አለው።

ሠራተኛው የማስታወቂያውን ቅጽ መመ ላቱን ሲጀምር ፡ ሳብር አካባቢውን መቃኘት ያዘ ። በዚህ ጊዜ አብራው የመጣችው ቆንጅዬ ጆሮዋን ጣል አድርጋ ታሪኩን ታዳምጥ እንደ ነበር ተሰማው ። ማስታወቂያ ቢሮ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የክፍሉ ሠራተኞች ከአንዴም ሁለቴ ኤል ሐም እያሉ ሲጠሯት ጆሮው መዝግቧል ።

“የማስታወቂያውን ዓላማ መግለጽ ትሻለህ!” አለው ታንታዊ ።

“አስፈላጊ አይደለም” አለው ሳብር ። ቀጠል አድርጎም ፡ “በዙ ሰው እንደሚያውቀው ነው የምገምተው ። ዳሩ ግን እስካሁን አውቀዋለሁ የሚል ሰው አላጋጠመኝም” በማለት ለራሱ አጉ ተመለመ ።

“እንዲህ ያለው ጉዳይ አጋጥሞን አያው ቅም” አለ ታንታዊ በመገረም ፤ “ቴሌፎን ከሚ ደውልልህና ደብዳቤ ከሚጽፍልህ ግለሰብ መነ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከል ትክክለኛውን ሰው እንዴት አድርገህ መለ
የት ትችላለህ?”

“መረጃ አለኝ ።”

የሳብር ታሪክ ኤልሓምን ከተቀመጠችበት አስነስቶ በነገሩ ጣልቃ እንድትገባ ስላዳረጋት ፡ “በጣም የሚደንቅ ሁኔታ ነው ። ልክ በሲኒማ ውስጥ እንደምናየው ዓይነት . . . ” አለች ።

ኤልሓም ለጉዳዩ ሰሰጠችው ትኩረት ሳብር በደስታ ፈገግ ብሎ እያያት ፡ “ፍጻሜውም በሲ ኒማ እንደሚታየው ታሪክ እንዲያምርልኝ ምኞቱ ነው” አላት ።

“የታወቀና የተጅለው ሰው ነው ስትል የሰ ማሁህ መሰለኝ ። እንዲህ ያለ ሰው መሆኑን እን ዴት ልታውቅ ቻልክ?”

ሳብር በሐሳብ ተውጠ በመቆየቱ ፡ ጥያቄዋን በዝምታ ያለፈው ስለ መሰላት ፡ “ይቅርታ ፤ መስ ቀለኛ ጥያቄ ማቅረቤ አልነበረም” አለችው ።

አነጋገርዋ ልቡን ሰለበው ። ብቻዋን አግኝቶ ናሆዱን ዘክዝኩ ሊያጫውታት የመፈለግ ጠንካራ ምኞት አደረበት ። ሆቴሉ ውስጥ ካገኛት ሴትዮ ጋር ሲያወዳድራት አሥር እጅ የጨመተትና በራ ስዋ ጠንካራ እምነት ያላት ሆና ነው ያገኛት ።

“ወይዘሪት ኤልሓም ፤ እኔ ለከተማችሁ እንግዳ ነኝ” አላት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንግዳ ነኝ?"

"አዎን ፡ እንግዳ ነኝ ። እዚህ የመጣሁት ገና በቅርቡ ነው ። የመጣሁበትም ዋና ዓላማ ይሽንኑ ሰውዬ ፍለጋ ነው ። ምናልባት አንቺም ተጨ ምረሽ ከረዳሽኝ ፍለጋዬ እንደሚሳካልኝ ተስፋ አለኝ ።"

ጠየም ያለ ውብ ፊትዋን ፈገግታ አልብሳ ተመለከተችው ። እስክንድርያ ከተማ በሚገኘው ፡ "ታቨርና" ሆቴል ውስጥ ተቀምጠ ምርጥ ወይን እየተጐነጨ ያዳምጠው የነበረው ለስላሳ የመ ዚቃ ጣዕመ ዜማ ምቱ ጆሮው ውስጥ አስተጋባ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አራት

ሳብር እስከ ምሳ ሰዓት ቆይቶ ከጋዜጣው ቢሮ ወጣ። ኤልሓምን ከሥራ ሰዓት ውጪ ለማ ነጋገር ካደረበት ጥሳጭት የተነሣ፡ የጋዜጣው ቢሮ አቅራቢያ ከሚገኘው የአውቶቡስ መሳፈሪያ ሄዶ ይጠባበቅ ጀመር። በጋዜጣው ላይ የሚወጣው ማስታወቂያ ለጥቂት ቀናትም ቢሆን እፎይታ እንደሚሰጠው እምነት አደረበት። ቀዝቀዝ ያለ የነፋስ ሽውታ ፊቱን እየዳሰሰው ሲያልፍ ተሰማው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በጋዜጣው ቢሮ ሕንፃ ደጃፍ ላይ ኤልሓም ከጥቂት ሰዎች ጋር የደራ ጨዋታ ይዛ አያት። ወዲያው ከሰዎቹ ተሰናብታ መንገዱን በማቋረጥ፡ "ፑትር ኩ" የሚል ስም በራፉ ላይ ከተጻፈበት ምግብ ቤት ገራ አለች። ያለ አንዳች ማመንታት ተከተላት። ምግብ ቤቱ ውስጥ ከገባ በኋላ፡ ዞር ዞር ብሎ ሲመለከት ብቻዋን መቀመጥዋን ተረዳ። ወደ ተቀመጠችበት ስፍራ ከደረሰ በኋላ፡ "እንዴት ያለው መልካም አጋጣሚ ነው፤ አብሬሽ እንድ ቀመጥ ትፈቅጅልኛለሽ?" አላት።

"ተቀመጥ" አለችው ጣጣ ሳታበዛ። አሳላ ፈው ሳንድዊችና የብርቱካን ጭማቂ ይዘላት መጣ። ሳብርም የእሷኑ ዓይነት ምግብና መጠጥ አዘዘ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ችግር እንዳልፈጠርኩብሽ ተስፋ አደር ጋለሁ ። መቼም እንግዳ የሆነ ሰው ያገኘውን ማስ ቸገሩ አይቀርም ።"

"ከእንግዶች ጋር መተዋወቅ ያስደስተኛል" አለችው ።

"አመሰግናለሁ ። ምን ለማለት ያሰብኩ መሰ ለሽ ፤ እንግዳ የሆነ ሰው ፥ ያገኘውን ሁሉ ለመ ወዳጅት በሚያደርገው ጥረት ሰዎችን ያስለቻል።"

"ምንም የሚያስለሽ ነገር አላየሁብህም ።"

የመጣለትን ሳንድዊች ገመጥ እያደረገ ፥ "ዛሬ ከሥራ መልስ ሲኒማ ለመግባት አስበሻል?" አላት ።

"አላሰብኩም ። ከሁለት ሰዓት በኋላ ወደ ሥራዬ መመለስ አለብኝ ። የምኖረው ከካይሮ ወጣ ብሎ በሚገኘው ጂዛ ነው ፤ ከካይሮ ጂዛ ትራንስፖርቱ አስቸጋሪ በመሆኑ ምሳዬን እዚሁ በልቼ ወደ ሥራዬ እመለሳለሁ" አለችው ።

"የምሳ ሰረፍትሽን እዚሁ ምግብ ቤት ውስጥ ነው የምታሳልፈው?"

"አልፎ አልፎ የሥራ ሰዓት እስኪደርስ አባይ ወንዝ ዳር በእግሬ እንሽራሸራለሁ ።"

ሁለቱም በዝምታ መወጣባቸውን ቀጠሉ ። ሳብር አልፎ አልፎ ኤልሓምን ሰረቅ እያደረገ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያያታል ። ፀሐይ ያጠየመው ውበ ገጽታዋ ፡ ውኃ ስማያዊ ቀለም ያላቸውን ከብላላ ዓይኖችዋን አጉ ልዶታል ።

"በጋዜጣችሁ ላይ እንዲወጣልኝ ስላደረግ ሁት ማስታወቂያ ምን አስተያየት አለሽ ? ያሰብ ኩትን ይፈጽምልኛል የሚል ግምት አለሽ?" አላት ።

"የጋዜጣ ማስታወቂያ ስለሚሰጠው ጠቀ ሜታ ጥርጣሬ አይግባህ ። "

ስለ ጉዳዩ ጠለቅ አድርጋ እንድትጠይቀው ፍላጐት ነበረው ። እርሷ ግን በየዕለቱ ከሚያጋጥ ሟት የሰዎች ችግሮች የተለየ አድርጋ ጉዳዩን እንዳልገመተችው በመረዳቱ ፡ "ወጪቱን በጐጉት ነው የምጠብቀው" አላት ።

"ስለምትፈልገው ሰውዬ ምንም ዝርዝር ነገር አላወቅም ያልከው በእውነት የምርህን ነው?"

"አንድ ፎቶግራፍና ስለ ሰውዬው በቃል የተነገሩኝ ተጨባጭ ያልሆኑ አንዳንድ መረጃ ዎች እሱኝ" አላት ። ለጥቂት ደቂቃዎች ሐሳቡን ካወጣና ካወረደ በኋላ ፡ "ሰውዬውን እንድፈልገው የላከኝ አባቱ ነው ። ከብዙ ዘመናት በፊት የቅ ርብ ወዳጆች ነበሩ" አላት ። በፊትዋ ላይ የጥር ጣሬ አመለካከት ተሥሎበት ተመለከተ ። "የአ ባቴ የቅርብ ጓደኛ ነበር ። አንዳንድ ነገሮችን አብ ረው ያከናወኑ ነበር" አላት ፡ ፈገግ እያለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"የንግድ ሥራ አብረው ይሠሩ ነበር ማለ ትህ ነው?"

"እሱንም አብረው ይሞክክሩ ነበር ።"

ኤልሐም አቋመ ጽኑ ሴት መሆንዋን ቢገነ ዙበም እንኳን ፡ በውበቷ ልቡ መሰለቡን እየተ ረዳው መሄዱ አልቀረም ።

"የዛሬውን የመሰለ ስሜት አሸንፎኝ አያ ውቅም!" አለ ሳብር ፡ የንግግር ርዕሳቸውን ለመ ለወጥ በመሻት ። ኤልሐም በመገረም ትኩር ብላ ተመለከተችው ።

"ማለቴ እኮ . . ." አለ ሳብር ፡ ግራ በተጋባ ሁኔታ ፤ "ማለቴ ፡ ለአገሩ እንግዳ ሊሰው ባዳ መሆን፡ በተሰፋ መኖር ፡ እንቺን ከመሰለች ውብ እመቤት ጋር በአንድ ማዕድ መመገብ በውስጤ የፈጠረ ውን ስሜት ማለቴ ነው" አላት ፡ ሐሳቡን እንድ ትረዳው በመጣጣር ።

"ስለ እኔ የሰነዘርከውን ቃል ብዙ ጊዜ ሰም ቼዋለሁ" አለችው ፡ በለዘብታ ።

"ከሥራ ጓደኞችሽ?"

"ሊሆን ይችላል ።"

"ለመሆኑ በሥራሽ ደስተኛ ነሽ?"

"ምን?" አለችው ፡ በጥያቄው በመገረም ።

"ሥራሽን ትተሽ ትዳር መያዝ አያምርሽም?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሥራዬ ጊዜ ማሳለፊያ ሳይሆን መተዳደሪያ ብዬ የያዝኩት ነው" አለችው ፡ ፍርጥም ብላ ።

ሳብር ስለ ሴቶች ሥር የሰደደ አቋም ያለው ሰው ነው ። ስሜቱን ከሚማርኩት መልከ ቀና ሴቶች ጋር ያለው ግንኙነት በፍቅር ስሜት ጠፍ፡ በወሲብ እርካታ እንዲጠናቀቅ ይሻል . . . የእናቱ የግልመጥና መሃም ሆነ ያደገበት አካባቢ ይሆንኑ አቋሙን የሚያጥባለት ሆኖ ኖሮአል ። ሳብር በአ ዕምሮው መስጥ ቢያወጣ ቢያወርድ ፡ ኤልሓም እንደሚያውቃቸው ብዙ ሴቶች ፡ ቀሚሷን ስታ ወልቅለት አልታየው አለው . . . ከሚያውቃቸው ሴቶች የተለየች ፡ በጠለቀ ምስጢር የታጠረችና በቀላሉ የማትበገር ሆነችበት ። ፍላጐቱ እውን ቢሆን እንኳን ስሜቱ ሚሽሾ ወንድነቱ እንደ ሚከዳው ተሰማው ።

"የጣዖትሽን ጥፍሮች እንዴት አድርገሽ እንደምትንከባከቢያቸው አታይም !" አላት ፡ አፉ እንዳመጣለት ።

ኤልሓም ብልጭ አለባት ። መቄጣትዋን በሚ ያስተጋባ ድምፅ ፡ " አንተም አሥሬ ስትከመክ መው የዋልከውን ጸጉርህን እስቲ ተመልከ ተው !" አለችው ።

ሳብር በድንጋጤ ፡ "ይቅርታ አድርጊልኝ ። አቃቂር ማውጣቴ ሳይሆን ለውበትሽ ያለኝን አድናቆት መግለጤ ነበር" አላት ። ከዚያም በመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለሳለስ ፡ "ከአንቺ ጋር ያሳለፍከ·ትን ይሆንን ሰዓት· ወደ አገሬ ወደ እስክንድርያ ከሄድኩ· በኋላም አልረሳው·!" አላት· ።

"ማስታወቂያህን በእስክንድርያ ጋዜጦች ላይ ለምን አላወጣህም ነበር?" አለችው· ።

"ማስታወቂያ በጋዜጣ ላይ ማውጣቱ ከፍ ሰጋዬ አንዱ ዘርፍ ነው" ብሏት ፡ አጠገባቸው· ሰቆመው· አሳሳፊ የሁለታቸውንም ሒሳብ ለመክ ፈል እጁን ሲዘረጋ ፡ በጥድፊያ አንዱን ያረሰኝ በማንጣት ፈጽሞ የማይደረግ ነገር መሆኑን ገለ ጠችለት· ።

"የእኔን ሒሳብ ብትከፍይልኝ እምቢ አል ልም ነበር" አላት ፡ እየጣቀ ።

ከጀርባው· በስተግራ በኩ·ል የተሰቀለውን መስታወት ትኩር ብሳ ስትመለከት· ሰረቅ አድ ርጎ አያት· ። መስታወቱ ውስጥ የሚንፀባረቀው· የእሱ·ው ምስል በመሆኑ· እይታ·ዋ ደስታን አጭና ጸፈ·ው ። ልቧን ማርኬው· ይሆናል የሚል የተሰፋ ጭላንጭል ታየው ። ሁለቱም ከተቀመጠ·በት· ተነ ሥተ·ው· ሰላምታ ተለዋወ·ጠው· ተለያዩ ። ተከት ላት· እንዲሄድ የሚታ·ገለውን ጥላ·ቱን ተጣጥሮ በማሸነፍ ወደ ሆቴሉ· አመራ ። እዚያም እንደ ደረሰ ፡ ለሆቴሉ· ባለቤት· ለከሊል አበ·ል ናታ ፡ ለሆ·ቴሉ· በር ጠባቂ ለመሐመድ አል ሳዊ ፡ ሰይድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኤል ራሕሚ ከሚባል ሰው የቴሌፎን ጥሪ እንደ ሚጠብቅ አስታወቃቸው ።

"አባትህን ነዋ የምትፈልገው ?" አለው ሽማግሌው ከለ.ል ። "ለመሆኑ እንዴት አድርጎ ጠፋብህ ?"

"የጠፋው እሱ ብቻ አይደለም ፤ እኔም ጠፍ ቼበታለሁ ። ስለዚህ ነው የምፈልገው" አለ ሳብር ።

"ምን ያለው የሚገርም ታሪክ ነው" አለ ከለ.ል ።

"ምንም የሚያስገርም ነገር የለበትም !" አለ ሳብር ፡ በከለ.ል ሁኔታ ብስጭት በማለት ። "ለማንኛ ውም ቴሌፎን ተደውሎ ከተፈለግሁ አስጠራኝ ።"

ሳብር ጋዜጣ ይዞ ከእንግዶች ማረፊያ ክፍል ውስጥ ባዶ መቀመጫ ፈልጎ አረፍ አለ ። በአካባ ቢው ያሉት እንግዶች ስለ እርሱ እየተንሾካሾኩ የሚያወሩ ስለ መሰለው የሠራ አካላቱን ቅፍፍ አለው ። "አባቱን በመፈለግ በየስፍራው የሚባ ዝን አሳዛኝ ጉልማሳ" እያሉ የሚጠቃቀሱበት መሰለው ።

ቴሌፎኑ መደወል ጀመረ ። መጀመሪያ ደውሎ ያነጋገረው ቡላቅ በሚባል አካባቢ የሚኖር ጸጉር አስተካካይ ሰይድ ራሕሚን ነበር ። ከዚያ በኋላ ምኑ ቅጡ . . .መምህሩ ራሕሚ ፡ የአውቶቡሱ ሹፈር ራሕሚ ፡ አትክልትና ፍራፍሬ ሻጩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ራሕሚ ፤ ሁሉም እየደወሉ ሳብርን አነጋገሩት ። ተፈላጊው ሰይድ ኤል ራሕሚ ግን ድምፅ አላ ስማም ። ይህም ሁኔታ ሳብርን ክፉኛ አሳሰበው ። ሞቶ እንደሆንስ ብሎ አሰበ ። ወራሾቹ እንዴት ዝም ይላሉ ፤ እንርሱማ ከኤል ራሕሚ የወረሱትን ሀብት እጃቸው ስላስገቡ ለእርሱ ምንም ደንታ እንደማይኖራቸው ገመተ ፤ በአካባቢው ከተቀመጡት የሆቴሉ እንግዶች መካከል ግማሹ ያጨሳል ፤ ግማሹ ቡናና ሻይውን ይጠጣል ፤ ግማሹ ያወጋል ፤ ግማሹ ያንቀላፋል ። እርሱን ከመጤፍ አለመቁጠራቸው ደስ አሰኘው ። ማስታወቂያውን ያነበበ የለም ማለት ነው . . .

አምን ፡ አባቱ ወሬውም የለ ። ተስፋውና ምኞቱ ገም እንደ መዝገን እየሆነበት ነው ። ሕይወቱን ከባድ ባዶነትና የከንቱነት መርማ ተጭኖታል ። የሕይወቱ አለኝታ እናቱ . . . ምን ይደረጋል . . . እሷም ወደ ዘላለም ቤቷ ሄዳለች። በሕይወት ሳለች እንደ ልቡ ገንዘብ ትሰጠው ፡ በገንዘቡም እንደ ልቡ ይሆን ነበር ። የእርሷንም ስምና ክብር ለመጠበቅ ከማንም ጋር አምባጓሮ እያነሣ ይናቈር ነበር ። ገንዘብ . . .ደስታ . . .ደስታ . . ገንዘብ . . .ደስታ . . .አምባጓሮ . . .ሁሉም እንደ ልብ ነበር ።

"ጥ . . . ዘንድሮ ወሬው ሁሉ ጥጥ ብቻ ሆኖአል" አለ ከእንግዶቹ አንዱ ፡ ያነበው የነበረ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውን ጋዜጣ በማጣጠፍ አጠገቡ ወደ ተቀመጠው ጓደኛው ፊቱን እያዞረ ።

"ከዛሬ ነገ ይቀሰቀሳል እየተባለ የሚወራለት ጦርነትስ? ለጥጣችን የሚበጀው ይመስልሃል?" በማለት ጓደኛው ጠየቀ ።

"እውነትህን ነው ። ጦርነት ለምንም ነገር አይበጅም ። ጦርነቱ ከተቀሰቀሰ ምንም የሚተርፍ ነገር የሚኖር አይመስለኝም !"

"ለመሆኑ እግዜሩን ምን ነካው ? የዚህ ሁሉ ጉድ ፈጣሪና ጠባቂው እርሱ አይደለም እንዴ?" አለ በምፀት ።

እውነቱን ነው ። እግዜሩን ምን ነካው ? የት ደረሰ? ሳበር እግዜርን የሚያውቀው በስም ብቻ ነው ። ኑሮውና ድርጊቱ ከሃይማኖት ክልል ውጪ ሆኖ ነው የቆየው ።

የቴሌፎኑ ጥሪ ቆም ብሎአል ። እስካሁን የደረሱት ጥሪዎች ምንም አልፈየዱለትም ። ለማንኛውም ሌሎች ጥሪዎችን ነቅቶ መጠበቅ አለበት ። የከሊል ሚስትና ኤልሐም በሐሳቡ ድንገት ድቅን አሉበት ። ቀዝቃዛ የነፋስ ሽውታ . . . የፀሐይ ግለት . . . ሁለቱም በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ተፈራራቂ ነገሮች ናቸው ። አባቱስ? አባቱን መዘንጋት እንደሌለበት ሕሊናው አስገነዘበው ። አባቱን ካላገኘ የፍርሃት ፣ የችግር ፣ የአጉል ስምና የወንጀል ኑሮ ነው የሚጠብቀው . . .

t.me/OLDBOOKSPDF

የቱሴርኑ ድምፅ ሳብርን ከሐሳቡ አነቃው። ለእርሱ አልነበረም የተደወለው። የከለ.ል ሚስት መናገሪያውን ወደ ጆሮዋ ስታቀና አያት። ጥዘዝ ፡ ድንግጥ ብሎ ቀረ። ከሄደችበት መመለስ ዋን አላወቀም ነበር። የቱሴርን ንግግሯን እንደ ጨረሰች የጐን አየት ስታደርገው ተዳፍኖ የሰነ በተው ስሜቱ ተቀሰቀሰበት። ኤል ራሕሚንና ኤል ሐምን ከሐሳቡ ሰረዛቸው። ከተቀመጠበት የእን ግዶች ማረፊያ ክፍል በመነሣት ፡ ሦስተኛ ፎቅ ላይ ወደሚገኘው ክፍሉ አመራ። ወደ ክፍሉ ደርሶ በሩን በመክፈት ላይ ሳለ ከኋላው ሰው በመምጣት ላይ መሆኑን ሰማ። ዞር ብሎ ቢመለ ከት የከሊል ሚስት መሆንዋን አየ።

"እንኳን ደህና መጣሽ" አላት።

ራስዋን ዝቅ በማድረግ መልኳም ምኞቱን መቀበልዋን በፈገግታ ገለጠችለት።

"ናፍቀንሽ ነበር" አላት።

ሣቅ እያለች መንገድዋን ወደ አራተኛው ፎቅ ቀጠለች።

"የእስክንድርያው ስ !" አላት ፡ ድፍረቱን ሰባስቦ።

ቆመም ብላ ፡ "የምን የእስክንድርያው ነው ?" አለች።

"ዘነጋሽው ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን ማለትህ እንደሆነ አልገባኝም !"
"እንቺ ብትረሺው እኔ አልረሳሁትም ።"
"አብደሃል ?" አለችው ።

ዕጢው ዱብ አለች ። "ምን ማለትሽ ነው ? አንተዋወ . . ."

የጀመረውን ቃል አላስጨረሰችውም ። "ይህን እላቂ የወንዶች ዘዴ በእኔ ላይ ለመጠቀም አትሞክር" ብላው መንገድዋን ቀጠለች ።

"ለማንኛውም ስለ ውበትሽ አድናቆቴን ልገልጽልሽ እወዳለሁ" አላት ።

ምንም ቃል ሳትመልስለት ከዓይኑ ተሠወረች ። ሳብር ትንሩሹ መለስ እንዲልለትና የተወጠረ ፍላጐቱ እንዲረግብ የፎቅ መወጫውን ደረጃ ግድግዳ ደገፍ ብሎ ቆመ ። ከእስክንድርያ ይቱ ቆንጆ ጋር ያሳለፈው ምሽት ሥዕል በአዕምሮው ውስጥ በጉልህ ተቀረጸበት ። ወዲያው አሊ ስርያኩስ ከላይኛው ፎቅ ወርዶ ሳብር እቆመበት ደረሰ ።

"ተጠርተህ ነበር" አለው ሳብር ፡ ነገር ለመቀስቀስ እየቃጣው ።

"ማነው የሚጠራኝ ?"

"እሜቴ ትሆናለች የጠራችህ" አለው ቀጠል አድርጎ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"የማን እሜቴ ?"

"የከሊል ሚስት ናታ !"

"አልመሰለኝም ። ክፍል አሥራ አምስት ውስጥ ያለ እንግዳ ሳይጠራኝ አልቀረም ። እሜቴንማ ከፍላቸው ሲገቡ አይቻቸዋለሁ ።"

"ይሆናል ። እሜቴ አራተኛ ፎቅ ላይ ይኖ ራሱ ማለት ነው ?"

"ታዲያ የት ይኑሩ ልትል ነው ? ከባለቤታ ቸው ጋር ሕንፃው ጫፍ ላይ ራሱን የቻለ መኖ ሪያ አላቸው ።"

"ሰሞኑን ጥፍት ያሉቸው ወዴት ሄዳ ነበር?"

"እናትዋ ጋ ሄዳ ነበረ ። በየወሩ እናትዋን ለመጠየቅ ትሄዳለች" አለ ሰርያኩስ ።

ከሊልን ከፎቅ ሲወርድ ሳብር አየው ። ሰው ነቱ በአንድ አፍታ ሲለዋወጥ ፥ በጥላቻና በቅ ናት ሲላወስ ተሰማው ። ውበት . . .ንዴት . . . አውሬነት . . .በሦቱሉ ውስጥ የመሰንበት ፍላ ጐቱ ተሟጠጠ ። ከነፋሻው አየር ጋር የተቀላቀ ለው የፀሐይዋ ሙቀት ብስጭቱን ፥ ንዴቱንና ቅናቱን አባባሰበት ። የካይሮን ከተማ እየተዘዋ ወረ ማየት አሰኘው ። የመጨረሻው ማስታወቂያ የሚወጣው በነገ ዕለት በመሆኑ ፥ ከዚያ በኋላ በካይሮ ከተማ ውስጥ እንደ ልቡ በመንሸራሸር ተንፈስ የሚልበት በቂ ጊዜ እንደሚያገኝ ተገነዘበ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን አዲስ ነገር አለ ?" አለችው ኤልሐም ፡ ጋዜጣው በረሮ ገባ እንዳለ ።

"ብዙ የቴሌፎን ጥሪዎች ደርሰውኛል ። ውጤት ያለው ምንም ነገር አላጋጠመኝም !" አለ ሳብር ፡ በስጭት በማለት ።

"ትዕግሥት ያሻል ።"

በጽሕፈት መኪናው የፈደል ሰሌዳ ላይ እነ ዚያ ውብ ጣቶችዋ እንደ ልባቸው ሲንሸራሸሩ ፍዝዝ ብሎ ተመለከተ ። ኤልሐምን ማየት በመ ቻሉ ቢረክም ፡ ውስጣዊ ስሜቱን ይሽ ነው የማይ ለው ኃዘን ተጫነው ።

ኢሳን ታንታዊ በጋዜጣው ላይ የሚወጣ አንድ የሞተ ሰው ማስታወቂያ ጽሑፍ አቀርቅሮ ያዘጋ ጃል ። ሳብር የእናቱ የሕይወትዋ መጨረሻ ዕለት ትገ አለው ። ከመሞትዋ በፊት ብዙ ተቅራር በው ፡ ብዙ ተወያይተው ነበር ። መለስ ብሎ ሲያ ስበው ፡ ስለ አባቱ ያጫወቱችው የተስፋ ቃላት የሕልም እንጀራ ሆነው መቅረታቸው ሰላም እየ ነሣው ነው ። ታንታዊ የሚጽፈውን ፡ "የሞት ማስ ታወቂያ" ጨርሶ ቀና ሲል ሳብርን አየው ።

" ታዲያስ ፡ ማስታወቂያው እንዴታደስልህ ተፈልጋለህ ?" አለው ።

"እስካሁን በጋዜጣችሁ ያወጣችሁልኝ ማስ ታወቂያ ከብዙ ሰዎች ጋር አገናኝቶኛል ። የምፈ

t.me/OLDBOOKSPDF

ልገውን ሰው ብቻ ነው ማግኘት ያልቻልከት" አለው ሳብር ፡ ተስፋ በቈረጠ ስሜት ።

"አይዞህ ፤ እንዲህ ያለው ማስታወቂያ ትዕ ግሥትና ጊዜ ይጠይቃል" አለ ታንታዊ ፡ ሳብ ርን በማበረታታት ።

"በከተማይቱ የታወቀ ሰው እኮ ነው !"

"እንደ ነገርከኝ ከሆነ የምታውቀው የሰው ዬውን ስም ብቻ ነው ። የተረፈው ነገር ሁሉ አሉ ባልታ ነው ። በዚች ከተማ ውስጥ ላለፉት ሠላሳ ዓመታት በተለያዩ ስፍራዎች ኖሬአለሁ ። አንተ የምትፈልገውን ሰውዬ ስም ግን አንድ ቀንም ሰምቼ አላወቅም ።"

"እንድፈልገው የላከኝን ሰው ከልብ አምነ ዋለሁ" አለ ሳብር ።

"እንዲህ ከሆነ የፍለጋህን ምስጢር የሚፈ ታው ጊዜ ብቻ ነው ።"

"ከሠላሳ ዓመት በፊት የተነሣው ፎቶግ ራፍ አለኝ ።"

"ከማስታወቂያው ጋር ፎቶግራፉን ማው ጣቱ ይጠቅማል" አለ ታንታዊ ።

ሳብር ፎቶግራፉን ከኪሱ አውጥቶ ለታን ታዊ ሰጠው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሳላል ሰው አልነበረም ማለት ነው" አለ ታንታዊ ፡ እያጉመተመተ ።

በሳብርና ፎቶግራፉ ላይ በሚታየው ሰውዬ መካከል ያለውን መመሳሰል ታንታዊ እምብዛም አላተኰረበትም ። የአዲሱን ማስታወቂያ ሐሳብ ካሰላ በኋላ ዋጋውን ለሳብር ነገረው ። ሳብር ደስ ሳይለው ሐሳቡን ከፈለ ። ግንዘቡ እንደሆን በረ ከት እየራቀው ፡ እርሱ ከሚገምተው በላይ አሲድ እየለቀቀበት ነው ። ከጋዜጣው ቢሮ ወጥቶ ወደ ምግብ ቤቱ በሚሄድበት ፡ ኤልሐም ከምትቀመጥ በት ስፍራ ላይ አረፍ ብሎ ይጠብቃት ጀመር ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ስትመጣ ቦታዋ ላይ ተቀምጠ ስታየው ድንግጥ አለች ። ምንም ሐተታ ሳታበዛ ሳብር አጠገብ ሄዳ ተቀመጠች ። ለሁለት ሰው ምሳ አዘዘ ።

"ፎቶግራፉን አየሁት" አለችው ።

"አየሽው ?" አላት ፡ በመደንቅ ።

"አዎን አየሁት ፤ በጣም ትመሳሰላላችሁ ።"

"ከሰውዬው ጋር ?"

ራስዋን በአዎንታ እየነቀነቀች ትኵር ብላ ተመለከተችው ።

"ወንድሜ ነው" በማለት ዋሸት ።

"ወንድምህ መሆኑን ለምን ቀደም ሲል አልተናገርከም ?" አለችው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በፈገግታ እያያት ዝም አለ ።

"ፎቶግራፉ ላይ ያለችው ቆንጆ ሴት ማናት ?" አለችው ።

"ሚኺ ሚስቱ ናት ።"

"ነው ? . . . ወንድሜ አልከኝ ? . . . እንዴት አደርኅ . . ."

"እኔ ከመወለዴ በፊት ነው ወጥቶ የቀረው ። ከቤተሰብ ጋር መጋጨት . . . ወጣ ብሎ መቅረት . . . ከሠላሳ ዓመት በኋላ አባታችንን ፡ ልጆችንን እንፈልገው ማለት . . . የተለመደ ነገር ነው ።"

"ሁኔታውን ሳስበው ታሪክህ በጣም ነው የሚገርመኝ ። ለመሆኑ የምትፈልገውን ሰውዬ የታወቀና የተቻለው ሰው ነው የምትለው ከምን በመነሣት ነው ?" አለችው ።

"አባቴ በነገረኝ መሠረት ነው ። ምናልባት ላይሆንም ይችላል ። እኔን የደነቀኝ የሥራ ባልደረባህ ታንታዊ በእኔና በሰውዬው መኻከል ያለውን መመሳሰል ልብ አለማድረጉ ነው ። ወይስ እኔ ከወጣሁ በኋላ የተናገረው ነገር አለ ?"

"ምንም አልተናገረም ። የታንታዊ ጭንቅ ላት የተሞላው በስሌትና በአኅዝ ብቻ ነው" አለችው ።

የምግብ ቤቱ አሳላፊ የሁለቱንም ምሳ ይዞ መጣ ። ጥቂት ጊዜ በዝምታ ሲመገቡ ከቆዩ በኋላ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

መመገቢያ ስፍራሽን በድፍረት ይገቡ በመቆየቱ ይቅርታ አድርጊልኝ ። እንደ እኔ ያለውን ውሉ የጠፋበት እንግዳ ካይሮን የመሰለች ትልቅ ከተማ መላ ቅጡን ታሳጣዋለች" አላት ።

በፈገግታ እያየችው ፥ "ለመሆኑ ጊዜው እን ዴት ነው የሚያልፍልህ ?"

"ዓይኔን አፍጥጬ የቴሌፎን ጥሪ በመጠ በቅ" አላት ።

"በጣም ያሰለቻል ። ፍለጋና መጠበቅ ሁለት የማይለያዩ ነገሮች ናቸው ።"

"እርግጥ ፥ ሁለቱ የተቈራኙ ነገሮች ናቸው ።"

"እሺ ፥ መጠበቁንስ ጠብቅ ፤ በመጠበቅ ላይ እያለህ የምትሠራው ነገር አለህ ?"

"የለኝም ።"

"እንዴት አድርጎ ይሆናል !" አለች ኤል ሐም ፥ በሁኔታው በማዘን ።

"ይሸውልሽ ፥ በዚች ከተማ ውስጥ አንድ ሁነኛ ወዳጅ የሚያስፈልገኝ ስለዚህ ነው" አላት ፥ ሆድዋ እንዳረራለት በማስተዛዘን ።

ቀና ብሎ ሲመለከታት የርኅራኄ ምልክት ፊትዋ ላይ አየባት ።

"አንቺን የመሰለ ወዳጅ ግን የማገኝ አይ መስለኝም" አላት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የፍራፍሬ ጭማቂ የተሞላበትን ብርጭቆ አንሥታ ቀመስ አደረገችለት ።

"ታዲያ ምን ይመስልሻል ?" አላት ።

"ኋላ ይቈጭሃል" አለችው ።

"በእኔ ይሁንብሽ ፤ ፈጽሞ አይቈጨኝም ።"

"እንግዲያው ማስታወቂያህን ለማደስ ቢሮ ብቅ ስትል እንነጋገራለን" አለችው ።

"ማስታወቂያህን እያደስክ ኑር ነው የምት ዪኝ ማለት ነው ?" አላት ፥ እየሣቀ ።

"ፍለጋህ ውጤት እንዲኖረው የምትሻ ከሆነ ሌላ አማራጭ የለህም ።"

"ፍለጋውስ የጀመርኩት ከምሬ ነው ። በጋዜጣ ማስታወቂያ አማካይነት የምፈልገውን ሰውዬ ማግኘት ካልቻልኩ በሌላ ዘዴም ቢሆን መሞከር አለብኝ ።"

ብርጭቆዋን አነሣች ፤ እርሱም የራሱን አን ሥቶ ፥ "ለጤናችን !" አላት ።

"በጥንቃቄ መያዝ ያለብህ ሰው ትመስለኛ ለህ" አለችው ፥ በፈገግታ እየተመለከተችው ።

እይታና ፈገግታ እየተለዋወጡ ጭማቂያቸ ውን መጠጣታቸውን ቀጠሉ ። ከብዙ ዓመታት በፊት እስክንድርያ ወደብ ዳርቻ ዘንፋላ ጸጉራ ላይ እምበጥ አበባ ሰክታ ያገኟት ቆንጆ ትዝ አለችው ። — ያን ምሽት ያገኟት ኤልሓም ብት

t.me/OLDBOOKSPDF

ሆን ኖሮ ፡ እንደዚያ ልቤ እስኪወልቅ አልከፉ ላትም ነበር—ሲል አሰበ ። ገና ዓይኑን እንደ ጣለባት ነበር በዚያች ቆንጆ ፍቅር የተማረከው . . .

—ወይ ኤልሓም ፤ ፎቶግራፉ ላይ ያለችው ቆንጆ ማናት አልሽኝ ? — አለ አሁንም በሐሳቡ ። —አንቺ የሕይወትዋን መጨረሻ እንደ እኔ አላየሽም ። ያን የመሰለ ትንቡሽ ገላዋ አልቆ ፤ የውበት አበባዋ ረግፎ ፤ እላይዋ ላይ በደረበችው የአልጋ ልብስ ተጠቅልላ መትት ብላ እንደ ቀረች አላየሻትም . . .ወይ እምዬ ! . . .እንዳይሆን ሆንሽ !. . .

በሐሳብ ከነጐደበት መለስ በማለት ፡ “በእውነቱ ስለ ደግነትሽ በጣም ነው የማመሰግንሽ” አላት ።

ሐሳቡ ገበቷታል ፤ ምስጋናውን በጸጋ ከመቀበል ወደ ኋላ አላለችም ። እንደገና በመካከላቸው ጸጥታ ሰፈነ ። የመልካም ጅምር ምልክት መሆኑ ነው ። የሳበር አባቱን የመፈለጉ ነገር በቀላሉ የሚገፋ አይደለም ። ቢሆንም ፍለጋው ሲያደክመውና ሲያታክተው ማረፊያና ማረሳሻ ያስፈልገዋል . . .

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አምስት

የካይሮን አውራ ጐዳናዎች አላይ እታች በማ ለት ሰውነቱ ደክሚል ፤ መንገዱን ያጨናነቀውን ወጪ ወራጅ ከእግር እስከ ራሱ አትኵሮ በማ የት ዓይኖቹ ቀልተዋል ። ከእስክንድርያ የሚነ ሣው የመጸው ደመና ካይሮ ከመድረሱ በፊት እንደ ባዘቶ ጥጥ ብትንትኑ ይወጣል ። የተወለደባ ትና ያደገባት የእስክንድርያ ትዝታ ደስ ሲለውም ሲከፋው አይለየውም ። የከሊል ሚስት እናትዋን ገበኝታ ከተመለሰች ወዲህ ፡ የሞቴሉ የእንግዶች ማረፊያ ክፍል የሥቃይ ቦታ ሆኖበታል ። በየዕ ለቱ ከሽማግሌ ባልዋ አጠገብ አትለይም ።ሰረቅ እያደረገ ባያት ቊጥር እሚንቦገቦጉት ዓይኖችዋ ላይ የጉጉትና የማግባባት ምልክት የተሣለበት ይመ ስለዋል ። ዘይ ፊልጳ ሲቀርባት ደግሞ ትሸሸዋለች ።

ሰሞኑን ኤልሐም እምብዛም ትዝ አት ለውም ። በፍላጐት እሳት የምታንደው ከሽማግ ሌው ከሊል ገን ልጥፍ ብሳ የምትውለው ሚስቱ ናት ። አልፎ አልፎ ፡ በሞቴሉ የእንግዶች ማረፊያ ክፍል ውስጥ የሚነሣው የቆጥ የባጡ ጭውውት ውካታ ፡ የሲጋራው ጪስ እወዳ ፡ የቡናውና የሻ ሂው ሲኒ ኳኳታ ፡ ሕሊናውን ሊያስተው ከሚያር ሰው የወሲብ ውጥረቱ ፋታ ይሰጠዋል ። እንዳ ንዴ ደግሞ አጠገቡ የተቀመጠችን እንግዶች

t.me/OLDBOOKSPDF

ልብ ብሎ ሲመለከታቸው ፡ እነርሱም በሕይወታቸው አንድ የሚፈልጉት ነገር ፡ አንድ ገና ያልጨበጡት ተስፋ በሐሳብ እንደሚያናውዛቸው ይሰማዋል ። ውሉ የጠፋውን የሐሳቡን ልቃቂት በማጠንጠን ላይ እንዳለ ፡ የሆቴሉ በር ጠባቂ መሐመድ አል ሳዊ ፡—

"ሳብር ፤ ቱሌፎን ይፈልግሃል" አለው ።

ሳብር አፈፍ ብሎ ተነሥቶ የቴሌፎኑን መናገሪያ ጨበጠ ።

"ሃሎ !"

"በጋዜጣ ማስታወቂያ ያወጣኸው ሰውዬ ነህ ?"

"አዎ ነኝ ፤ ማን ልበል ?" አለ ሳብር ፡ ትን ፋሹ ቍርጥ ቍርጥ እያለ ።

"ሰይድ ኤል ራሕሚ እባላለሁ ።"

"ፎቶግራፉ በእርግጥ ያንተ ነው ?" አለ ሳብር ፡ ነገሩን ለማጣራት ።

"አዎ ፡ የእኔ ነው ።"

"የት እንገናኝ ታዲያ" አለ ፡ ትንፋሹ እንቅ እንቅ እያደረገው ።

"ለመሆኑ ለምንድን ነው የምትፈልገኝ ?"

"መጀመሪያ እንገናኝ ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለምን እንደምትፈልገኝ አንድ ፍንጭ እንኳን ስጠኝ እንጂ ።"

"በቴሌፎን የሚሆን ነገር አይደለም ። የፍለጋዬ ምክንያት እስክንገናኝ ቢቆይ የሚጐዳ ነገር የለበትም ።"

"ማን እንደ ሆንክ እንኳን ልወቀው ።"

"ማንነቴማ በማስታወቂያው ላይ ተገልጿል ።"

"ሥራህ ምንድን ነው ?"

"በግል ንብረቱ የምተዳደር ሰው ነኝ ።"

"አሁንም ደግሜ ልጠይቅህ ፤ ለምንድን ነው የምትፈልገኝ ?"

"በሚመችህ በማንኛውም ጊዜ እንገናኝና ሁሉንም ነገር ዘርዝሬ አስረዳሃለሁ ።"

ቴሌፎኑ ለጥቂት ጊዜ በዝምታ ተዋጠ ። ሳብር አፍታው ዓመት ሆነበት ።

"ከፈለግህ አሁኑኑ ና ። አድራሻዬ ፡ ቪላ አሥራ አራት ፤ ቴልባና መንገድ ፡ ሹባራ ነው" አለ የደዋዩ ድምፅ ።

ሆቴሉ ውስጥ የጠየቃቸው ሰዎች በሙሉ ፡ በካይሮ ከተማ ቴልባና መንገድ የሚባል መኖሩን አለመስማታቸውን ገለጹለት ።

"እስቲ ሹባራ ሂድና እዚያው ሰዎችን አጠያይቅ" አለው ፡ መሐመድ አል ሳዊ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳብሮ ቱነሥዱ መደ ሹበራ ሄደ ። በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎች ቱልባና የሚባል መንገድ እንደሌለና ሮሮም እንደማያውቅ እንደ ቂል እያዩት ነገሩት ። ምናልባት ስሙን በትክክል አልሰማሁት ይሆናል ብሎ አሰበ ። ወይም ደግሞ አንዱ ፈዘኛ ሲቀልድበኝ ደውሎ ይሆናል የሚል ጥርጣሬም ገባው ። ወደ ሆቴሉ ሲመለስ የከሲል ሚስት ባልዋ ሥር ተሸገጣ አገኛት ። የባሰ ብስጭት ተሰማው ፤ ፍላጐቱ በውስጡ የባሰውን ነደደ ፤ አፉን ደም ደም አለው . . .

ሳብር ሹበራ በሄደበት ወቅት አንድ ሰው ደጋግሞ መደወሉ ትንገረው ።

"የሄድክበት ቀናህ?" በማለት ከሲል ጠየቀው ።

"ምንም አይልም" አለ ሳብር ፡ ችግሩን በማ ለባበስ ።

ሳብር ሴትየዋን በዓይኑ ገረፍ አድርጎ ወደ እንግዶች ማረፊያው ክፍል አመራ ። የክፍሉ መብራቶች ደንገዝጋዛ ብርሃን የባሰውን ስሜቱን ተመነው ። ወዲያው ቴሌፎኑ አንቃጭሎ ሳብር ተጠራ ።

"ሃሎ !"

"ሳብር ፤ ቀኑን ሙሉ ስታስጠብቀኝ ዋልክ እኮ" አለ ፡ ደዋዩ ድምፅ ወቀሳና ቅርታ በተ ቀላቀለበት ስሜት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"መንገዱን ማግኘት አልቻልኩም ።"

"መጥቼ መንገዱን አጣሁት እንዳትለኝ ?"

"ቁጉን ሙሉ እዚያው ነው የዋልኩት ፤ ቱልባና ቁጥር አሥራ አራት ።"

"ምን ዓይነቱ ጅል ነህ እባክህ !"

ደዋዩ ድምፅ ከት ከት ብሎ ሣቁን ከለቀቀው በኋላ ፥ ቴሌፎኑ ሳብር ጆሮ ላይ ተዘጋ ። — የፈራሁት አልቀረም ። አንዱ ፈዘኛ ተጫወቶብኛል ። ጥለጋዬን 'ሀ' ብዬ መጀመር ሊኖርብኝ ነው—አለ ሳብር በሐሳቡ ።

ከሆቴሉ ወጥቶ በአቅራቢያው ወደሚገኝ ወደ አንዱ ቡና ቤት በማምራት ፥ እንደ ደረሰ አንድ ብራንዲና የዓሣ ምግብ አዘዘ ። — ዕለቱ እንደሆነ ያላንዳች ፋይዳ ተፈጽሞአል ። ሆዴን እንኳን ልመላው ፥ ብሎ በመወሰን ፥ ካዘዘው ምግብ ጋር አያሌ መለኪያ ብራንዲ ተጎነጨ ። ስለ ዋጋው እምብዛም አልተጨነቀም ። ልክ ባደገባት ከተማ በእስክንድርያ እንዳለ ነው የቈጠረው ። አዎን ፥ የእስክንድርያ ሕይወቱ ደስታና ፈንጠዝያ ያልተለየው ነበር ። ወረቱ ፥ ወይኑ ፥ ወሲቡ እንደ ልብ ነበር ። ካይሮ ግን ፥ ከልፋት ፥ ከብስጭትና ከተስፋ ቢስነት ሌላ እስካሁን አንዳችም ደህና ነገር አላሳየችውም ። እያንዳንዱ ሰዓት ጨለማ ለብሶ ነው ከፊቱ የሚደቀነው ። በየዕለቱ ዓይን

t.me/OLDBOOKSPDF

አፍጥጦ ጥበቃና እጅ እግር የሌለው ፍለጋ መጨረሻው ምን ይሆን?

ሳብር ወደ እስክንድርያ ቢመለስ የሰው መሣቂያ ሆኖ እንደሚቀር ተሰማው። ባባቱ ፍለጋ ወጣ ወረድ የትነሣ ጉልበቱ እየተዳከመ በመሄዱ የቅድሞ ባሳጋሮቹ በቀላሉ የሚበገሩለት እንደሚይሆኑ ታየው። የወንጀል ድርጊት ውስጥ ከመ ዘፈቅና ከሕግ እየኰበለሉና ዘወትር እየባነኑ ከመኖር ሌላ የሚጠበቀው በጐ ነገር እንደሌለ ገባው። ሳይፈልገው ሁለቱ ሴቶች በሐሳቡ ውስጥ ድቅን አሉበት። በእይታዋ ብቻ ልቡን ወክክ የምታደርገው የከሊል ሚስት... ሜምትዋና ልበ ሙሉዋ ኤል ሐም...። ይኸ ሁሉ ሐሳብ፥ ይኸ ሁሉ ምኞት አባቱን ካሳገኘ እውን ሊሆን አለመቻሉ ልቡን አበገነው። ከምግብ ቤቱ ወጥቶ እግሩ ወደ ወሰደው መሄድ አሰኘው።

እየተገባደደ በመሄድ ላይ በሚገኘው በዛሬው ዕለት ሊንድም ረብ ያለው ነገር አላከናወነም። ግን የወሲብ ፍላጐቱ በውስጡ ነግሦ ቅን ዝንባ ሊያደርገው ይታገለዋል... ከብዙ ዓመታት በፊት በእስክንድርያ ባሕር ዳርቻ የሰው ሰው እየተከታተለ እንዳንከወከወው ዓይነት... ወዲያው ደግሞ፥ እናቱ ዕፀ ፋርስዋን እያጤሰች በጉልምትና መዓዋ ስመ ስተናገድ የሚመጡትን ወንዶች ስሜት ስትቈጣጠር በሐሳቡ ድቅን

t.me/OLDBOOKSPDF

አለችበት ። የገንዘቡስ ነገር ! የያዘው ገንዘብ እየመነመነ በመሄድ ላይ ነው ። ድህነት ደግሞ ከሁሉ የባሰ ጠላት ነው ። ያዩትን ሁሉ መውደድ አያዋጣም ። ‹‹ብዙ ወዳድ ፥ በአንድ አትጠመድ›› የሚለው አነጋገር ትውስ አለው ። ፍቅር . . . ገንዘብ . . . ደስታ . . . ሙዚቃ . . . ውካታ . . . የሴት እሽታ ። ለመሆኑ ሰይድ ኤል ራሕሚን ምን ዋጠው?

ኤል ራሕሚ ! . . . የኤል ራሕሚ ነገርማ ስሚ ያጣ የምድረ በዳ ጩኸት ሆኖአል ። ደጋ ግሞ የጠላው ብራንዲ የሳብርን ስሜት ያሚሙቀው ፥ እግረ ሕሊናውን ያፈዋነው ጅምሮአል ። ማምሻውን ደግሞ መለስ ቀለስ እያለች ትውስታውን የምትገመበኘው የክሊል ሚስት ሆናለች ። በመጠጥ ኃይል የተጋጋለው ፍላጐቱ ከእሷው ጋር መዋደቁን ተያይዞታል ።

ሳብር ሽርሽሩን አብቅቶ ወዴ ሆቴሉ ተመለሰ ። እኩለ ሌሊት አልፎአል ፤ የሆቴሉ እንግዶች ክፍሎቻቸው ውስጥ ከት ብ ስላሉ በአካባቢው ጭርታ ነግሦአል ። ሳብር አሮጌና ርካሽ ክፍሉ ውስጥ ገብቶ ሲጋራ አቀጣጥሎ ማጨስ ያዘ ። የክሊል ሚስት ዓይኑ ላይ ትዘዋወርበታለች ። አልጋው ላይ ጋደም እንዳለ እንቅልፍ ይዞት ሄደ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንድ ድምፅ ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው ። ከአልጋው ላይ ቀና ብሎ ዓይኑን ገልጦ ጀሮውን ጣል አድርጎ ሲያዳምጥ የክፍሉ በር በዝግታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይንኳኳል ። — በውድቅት በሩን ማነው የሚያን
ኳኳው? እርሷ ትሆን ?—ብሎ አሰበ ። ሁኔታውን
ማመን ግን አቃተው ። እንደገና በሩ በቀስታ ተን
ኳኳ ። ከአልጋው ላይ ወርዶ በሩን በጥንቃቄ ለመ
ክፈት ሲሞክር ፥ ከውጪ የነበረው ሰው በሩን በር
ግዶ ገብቶ መልሶ ጥርቅም አድርጎ ዘጋው ።

"ኧረ እኔ አላምንም !" አለ ሳብር ።

አካባቢዋን ማረጋገጥ የምትመክር ይመስል
ክፍሉን አየት አየት ካደረገች በኋላ ፥ "ወይኔ
በሞትኩት ፤ የት ነው የገባሁት . . . በጣም ይቅ
ርታ እጠይቃለሁ . . . ተሳስቼ . . ." በማለት ዘር
ፋፋ የሴሊት ልብስዋን በእጅዋ ቀልበስ አድርጋ
የተጋለጠ ጡቶችዋን ሸፈነቻቸው ። ፈትዋ ፈገግ
ብሏል ። ሳብር በውስጡ ሲተራመስ በሰነበተው
ስሜቱ በመገፋፋት ሳብ አድርጎ ከደረቱ ጋር አጣ
በቃት ። እጁ ውስጥ መግባትዋን ያመነ አይመስ
ልም ። ወደ አልጋው ጉተት እያደረጋት መቧራ
ቱን አጠፋ ።

"ስምሽን እንኳን አላወቅም እኮ" አላት ።

"ከሪማ" አለችው ።

"ጥሩ ስም ነው ፤ ሰጋስ ማለት ነው እኮ"
አላት ።

ከዚያ በኋላ ሁለቱም ድምፅ አላሰሙ ፤ በጉ
ጉት ፥ በጥላቻና በሰመመን ተጣምረው ቀሩ ።
ከዚህ ቀደም የሚያውቀው የእስክንድርያው ባሕር

t.me/OLDBOOKSPDF

ዳርቻ የጨለማ ውስጥ ፍቅር...የብዙ ቀናት ፍላ ጐቴ ባልጠበቀው ጊዜና ባላሰበው ሰዓት እውን መሆን...የባሕሩ ጨዋማ ውኃ ዳርቻውን አልፎ እላያቸው ላይ መቸለስ...የለሳሳው አየር ሽውታ ሰውነታቸውን ዳስሶ ማለፍ... ሳብርና ከሪማ... በዚህ ሁሉ ትዝታ ውስጥ ሰምጠዋል። የሚሰማ ነገር ቢኖር ቍርጥ ቍርጥ የሚለው ትንፋሻቸው ብቻ ነበር... ጥቂት ቆይቶ ኮሽታ የተሰየው ጸጥታ... እፎይታ።

"ሲጋራ ስጠኝ" አለችው።

"ታጨሻለሽ እንዴ?" አላት።

"አልፎ አልፎ።"

ሲጋራ አቀብሏት ክብሪቱን ለኩሶ ሲያስጠጋው ብርሃኑ እርቃኑን ያለውን ደረቷን አጋለጠው። ሲጋራውን አያይዛ የክብሪቱን እሳት በትንፋሽዋ አጠፋችው። የሲጋራውና የፍቅራቸው ጠረን ተዋሐደ።

"ብዙ ቀናት አስቸግረሽኝ ቆየሽ" አላት።

"እኔ አላስቸገርኩም። ማስቸገር የሚሉት ነገር አላውቅም" አለችው።

"ካየሁሽ ዕለት ጀምሮ ያሳደርሽብኝን ስሜት መደበቅ አልቻልኩም።"

"ከአሥር ቀን በፊት ሆቴላችን ስትገባ ነው አጅሬ መጣልኝ ያልኩት" አለችው፡ ፊትዋን በፈገግታ አብርታ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"የእስክንድርያይቱ ነሻ !" አላት ፡ በድል አድራጊነት ስሜት ።

"የምን እስክንድርያ ነው የምታወራው ! ስለ እስክንድርያ ምንም የማውቀው ነገር የለም ! እኔ ገና ሳይህ ነው ልቤ ወከክ ያለው" አለችው።

"በእውነት የእስክንድርያው ትዝ አይልሽም?"

"ምንድን ነው አሥራ የእስክንድርያው የምትለው ?"

"እውነቴን ነው የምልሽ !"

"እኔም እውነቴን ነው የምልህ ። ምን አስ ዋሸኝ !"

"እንዲህ ከሆነ ነገሩ በጣም ይደንቃል . . . ሁለት ተመሳሳዮች አላችሁ ማለት ነው . . ."

"እባክህ ጊዜ አታባክን" አለችው ።

"ለመሆኑ እዚህ ድረስ እንዴት ልትመጪ ቻልሽ ?"

"ባለቤቴ ሐሳቡና ብስጭቱ ተግበስብሶ አላዩ ላይ የሚከመርበት መሸት ሲል ነው ። ዛሬ መተኛት አለብኝ ብሎ የእንቅልፍ መድኃኒቱን ቅሟል ።"

"እንዲያው ጉድ ነው ያደረግሽኝ ። እዚህ የመጣሁ ዕለት ሳይሽ ፡ የእስክንድርያዋ ልጅ ነች ፤ እሷ ከሆነች ደግሞ ፍለጋዬ ይቀናኛል ብዬ ተስፋ ጥዬብሽ ነበር ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ያባትህን ፍለጋ ማለትህ ነው ?"

"እምን ።"

"እኔ እኮ ያንተ ነገር አልገባኝም ። እንዲ ያው ለመሆኑ እውነተኛው ዓላማህ ምንድን ነው ?"

"ዓላማዬማ አባቴን ፈልጎ ማግኘት ነው ። ለብዙ ዘመናት ሞቷል ብዬ ነበር የተቀመጥ ኩት ። በኋላ ግን በሕይወት እንዳለ ተነገረኝ ። የፍለጋዬ መነሻውም መድረሻውም ይኸው ነው ።"

"ገንዘብ የማግኘት ፍላጐት ያለህ ይመስለ ኛል ።"

"ገንዘብ የማግኘቱ ነገር እንኳን ከእንግዲህ ዋጋ የለውም ። እንቺ ብቻ አትለዪኝ ። በየዕለቱ መገናኘት አለብን ።"

"በየዕለቱም ባይሆን ሲመቸኝ እንገናኛ ለን ።"

እቅፍ አድርጎ ሳማት ። እንደገና የፍቅር ንዳድ ውስጥ ገብተው እንደ ሰም ቀለጡ ።

"ሲመቸኝ ብቻ ሳይሆን ሲያሰኘኝም እንገ ናኛለን" አለችው : ቁና ቁና እየተነፈሰች ።

" የእስክንድርያውን አትክጂኝ" አላት : ጠትዋን ተንተርሶ ።

" ሰውዬው : በእስክንድርያ ተለክፈሃል መሰለኝ ። አባቴን እፈልጋለሁ የምትለውም አሥራ

t.me/OLDBOOKSPDF

እስክንድርያ እስክንድርያ እንደምትለውም ቅዠት እንዳይሆን ።"

"ቅዠት ቢሆንማ በማን ዕድሉ ፤ አርፌ እቀመጥ ነበር እንጂ እንዲህ አሥራ ቦታ አልረ ጥም፡ ነበር" አላት ፡ እያስተዛዘነ ።

"ካሰብከት በላይ ጣጣ አለብህ ማለት ነው ?"

"አምን አለብኝ ። ከእንግዲህ ወዲያ የምኾ ለውን ያህል እዚሁ መቆየት ነው ።"

"እዚህ እንዳትቆይ የከለከለህ አለ ?"

ጥቂት አሰብ አድርጎ ፡ "አባቴን ከማግኘቴ በፊት የያዝከት ገንዘብ ካለቀብኝ ወደ እስክን ድርያ መመለስ ይኖርብኛል ።"

"መቼ ልትመለስ ?"

"እዚያው ተመልሼ ሥራ ፈልጌ መያዝ ይኖርብኛል" አላት ። እጇን በእጅዋ እየዳሰሰች ፡ "አይሆንም !" አለችው ፡ ፍርጥም ብላ ። ስሜት ዋን መረዳት አላዳገተውም ። ወዲያው ቀጠል አደርጋ ፡ "ሥራ መያዝ የምታስብ ከሆነ እዚሁ ፈልገህ ለምን አትይዝም ?" አለችው ።

"የማይቻለውን !" አላት ።

"ነገርህ ሁሉ ግራ የሚያጋባ ነው ። ለማን ኛውም ስለ ገንዘብ ብዙም አትጨነቅ" አለችው ።

ልቡ ቆም ማለት ከጀለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"የተረፈ ገንዘብ አለሽ ማለት ነው ?" አላት ።

"ሆቴሉ ፡ የሆቴሉ ገቢ ፡ ሁሉም የሚካሄደው በእኔ ስምና በእኔ እጅ ነው ።"

"ባለቤትሽስ ተቀጣሪ ነው እንዳትዪኝ !"

"አይ ፤ እንደሱም ማለቴ አይደለም ። በሕይወት እስካለ ድረስ ሥራውን እርሱ ራሱ ይቈጣጠራል ።"

"ይቅርታ ፤ በማያገባኝ ጉዳይ ውስጥ ነው ጥልቅ ያልኩት" አላት ፡ አፈር እንደ ማለት እየቃጣው ።

"ዋናው ነገር አባትህን ማግኘቱ ነው ። እሱ ላይ ጠንክር" አለችው ።

"እውነትሽን ነው ፤ አባቴን ማግኘት አለብኝ ። ከዛሬ ጀምሮ አንቺንም በየዕለቱ ዓይኔን አፍጥጬ እዚሁ እጠብቅሻለሁ" ብሎ ሊያቅፋት ሲቃጣ ፡ ከአልጋው ላይ ፈንጠር ብላ ተነሣች ።

"ነህ እየቀደደ ነው ። መሄድ አለብኝ" አለችው ።

ሳብር አልጋው ላይ ጥቅልል ብሎ ተኛ ። አንሶላው ተጥመልምሎ እግርጌው ወርዷል ። የሆነው ነገር ሁሉ መሆን መቻሉ እውነት አልመስል አለው ። በሌላ በኩል ደግሞ ፡ አልፎ አል

t.me/OLDBOOKSPDF

ፎም በሆን ያባቱ ማረሳሻ የምትሆነውን ፍቅረኛ ማጣትን መቻሉ ቀልበን የሚያረጋጋ ፡ ሰውነቱን የሚያዝናና ስለመሙን ላይ ጣሰው ።

እንደ ልማዱ ቴሌፎኑ ድምፁን አሰማ ።

"ሃሎ!"

"ባጋዜጣው ማስታወቂያ ላይ የተጠቀሰው ሱበር ሰዩድ ኤል ራሕሚ ነህ ?" አለ ፡ እንድ ኩራ ያለ ድምፅ ።

"እምን ነኝ ። "

"እኔም ሰዩድ ኤል ራሕሚ እባላለሁ ። ለመሆኑ ምንድን ነው የምትፈልገው?"

"እንገናኝና . . . ። "

"መገናኘት ከፈለግህ ፡ ጋዜጣው ቢሮ አቅራቢያ ከሚገኘው ቮትር ሆ ምግብ ቤት እንገናኝ ።"

"እሺ ፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እደርሳለሁ ።"

ምግብ ቤቱ ውስጥ ገብቶ ሲመለከት ፡ እንድ ሰውዬ ኤልሐም የምትቀመጥበትን ቦታ ይዞ አየው ። በቱቴቮን ያነጋገረው ሰውዬ መሆን አለበት በሚል ግምት ወደ ተቀመጠበት ስፍራ አመራ ። አልተሳሳተም ። ሰውዬው የሚፈለገው አባቱ ነው ! በሠላሳ ዓመታት ውስጥ በፎቶግራፉ ላይ የማታየው መልኩ ብዙም አልተለወጠም ። ጸጉሩ ላይ አልፎ አልፎ ሽበት ጣል ጣል አድርጎበ

t.me/OLDBOOKSPDF

ታል ፤ ፊቱም በመጠኑ መሸብሸብ ጀምሮአል ። በተረፈ ግን ፎቶግራፉ ላይ ከሚታየው ሥዕል እም ብዛም አልተለወጠም ።

ሳብር ወደ ሰውዬው ሲቀርብ ፡ ፍርሃት ጨም ድዶ ያዘው ።

ሰውዬውም ሳብር አጠገቡ እንደ ደረሰ ፡ ከተ ቀመጠበት ብድግ ብሎ ፡ "ሳብር ማለት አንተ ነህ ?" አለው ።

"አዎን ፡ ነኝ ። ፎቶግራፉ ላይ ያለኸው ሰውዬ ነህ ማለት ነው?" አለ ሳብር ፡ ድምፁን ሰበር አድርጎ ።

"አዎን ፡ ነኝ ። ለካስ ገና ለግላጋ ጐበዝ ነህ ። ከዚህ ቀደም አንድ ቦታ ያየሁህ ይመስለኛል ። የት እንዳየሁህ ግን ትዝ አልልህ አለኝ ። "

"ትውልዴም ነዋሪነቴም እስክንድሪያ ከተማ ነው ። ሰጊዜው ያረፍክት ካይሮ ሆቴል ነው ። ካይሮ ከደረስክ ጀምሮ በከተማይቱ አውራ ጐዳና ዎች ስወጣ ስወርድ ነው የሰነበትከት ። አልፎ አልፎ ወደዚህ ምግብ ቤትም ብቅ እላለሁ ። እዚቹ ወንበር ላይ ነው የምስተናገደው ። "

"ምናልባት እዚሁ ከተማ ውስጥ አይቼህ ይሆናል ። እኔም አንዳንዴ ወደ እስክንድርያም ብቅ እላለሁ ። ይህንን ምግብ ቤትም አልፎ አልፎ እጐበኛለሁ ። "

t.me/OLDBOOKSPDF

"ማስታወቂያውን መቼ ነው ያነበብከው?" አለ ሳብር ።

"መጀመሪያ በጋዜጣ የወጣ ዕለት ። "

"ይገርማል ። ታዲያ እስካሁን ለምን ዝም ብለህ ቆየህ ?"

"በጋዜጣ ያወጣሽው ማስታወቂያ በተለ ያዩ መንገዶች ልታገኚኝ ሞክረህ እንዳልተሳካልህ ያመለክታል ። ማንም የሚያውቀኝ ሰው በመሆኔ ፣ እኔን ማግኘት አስቸጋሪ ሊሆን አይችልም ነበር። ስልክ ልያው ልልህ የወሰንኩት ፣ ማስታወቂያውን ያለ ማቋረጥ እንዲወጣ በማድረግህ ነው ። "

"ማንም ያውቀኛል ያልከውን ለመቅበል ያዳግተኛል ። የጠየቅኋቸው ሰዎች ሁሉ ፣ ኤል ሪሕሚ የሚባል ሰው እንደማያውቁ ነው የነገሩኝ ።"

"ለማንኛውም ያሰፈው አልፏል ። ለመሆኑ ዓላማህ ምንድን ነው?"

"አሁማ አንተን ከማግኘት የተለየ ዓላማ የለኝም ። "

ዝምድናዬን በመልኬ ያውቅ ይሆናል በሚል ተስፋ ሳብር ፣ ሰውዬውን ትኩር ብሎ ዓይን ዓይ ኑን ይመለከተው ጀመር ። ይህን እንጂ በሰውዬው ፊት ላይ ምንም ለውጥ ሊያይበት አልቻለም ።

"እስቲ ደህና አድርገህ ተመልከተኝ !" አለ አለ ሳብር ፣ ጮክ ብሎ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምነው ፤ ደህና አይደለህም እንዴ?" አለ ሰውዬው ።

ሳብር ከወደኋላው ለሰስ ባለ ድምፅ ስሙ ሲጠራ ሰማ ። ዞር ብሎ ሲመለከት ኤልሐም ከኋላው ቆማለች ። ሳብር ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ሰውዬውን ሊያስተዋውቃት ሲጀምር ፥ ሰውዬው ቀድሞት ፥ "እንደምን ነሽ ፥ ኤልሐም?" አሳት ።

ኤልሐም ወደ ሰውዬው ቀረብ ብላ ግንባሩ ላይ ሳም አታደርገው በማየቱ ሳብር በመገረም አፉን ይዞ ቀረ ።

"ይህን ሰው ታውቂዋለሽ እንዴ?" በማለት ሰውዬው ኤልሐምን ፍርጥም ብሎ ጠየቃት ።

ኤልሐም በአምንታ ራስዋን ነቀነቀች ።

"ከልጂ ጋር የት ነው የተዋወቃችሁት?" አለ ሰውዬው ፥ ሳብር ላይ ዓይኑን ትክሎ ።

"ከልጂ ጋር?... ምን ዓይነት ጉድ ነው!" አለ ሳብር ፥ ቅስሙ በተሰበረ ድምፅ ።

ኤልሐም ነገሩ ስላላማራት ፥ ሳብርም ሆነ ሰውዬው ሳያዩዋት ከምግብ ቤቱ ሹልክ ብላ ወጣች ። ሰውዬው በእርጋታ ወንበሩ ላይ አረፍ ብሎ ፥ "እስቲ የምትፈልገው ነገር ምን እንደሆነ ንገረኝ!" አለው—ሳብርን ።

ሳብር ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ ወንበሩ ላይ ዘፍ አለ ። ፎቶግራፉን ፥ የልደት የምስክር ወረ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቍጥንና የእናቱን የጋብቻ ማስረጃ ለሰውዬው ሰጠው። ሰውዬውም ለነዶሽን አንድ ባንድ ከተመለከተ በኋላ ፥ ሦስቱንም ብጭቅጭቅ አድርጎ ጣላቸው።

ሳብር ከመቀመጫው ላይ ዘሎ በመነሣት ፥ የሰውዬውን የክት ኮሌታ አንቆ ይዞ ፥ "የሕልውናዬ መረጃ የሆኑትን ሰነዶች እንዴት ትቃጸድብ ስህ ! ?" በማለት ጮኸበት።

ሰውዬው ረጋ ብሎ ፥ "ተነሥተህ ከፊቴ የምትጠፋበት ጥፋ! ሁለተኛ አጠገቤ እንዳትደርስ ! እንተም እናትህም ዋጋ ቢስች ናችሁ ! ሁለተኛ ዓይንህን እንዳላየው !" ሰውዬው ይህንን ቱናግሮ ሳብርን ገፍትሮት አለፈ። ሳብርም እየተንገዳገደ ሄዶ ከአንድ የምግብ ጠረጴዛ ሥር የአሊት ወደቀ።

ሳብር ከአንቅልፉ ነቃ። ሞቴሉ ውስጥ ሰስ የአልጋ ልብሱን ላዩ ላይ ጣል አድርጎ ተኝቷል። ሰውነቱን ላብ አስጥሞታል ፤ ትንፋሹ ቍርጥ ቍርጥ ይላል። የዐሐይዋ ብርሃን አሮጌውን መስኮት ዘልቆ ክፍሉን ፍንትው አድርጎታል። የሳብር የአባቱ ፍለጋ የቁም ሕልም ሆኖ መቅረቱ ይሆን ? ወይስ ፥ ከሪማ እንዳለችው ፥ ቅዠት ነው? ሳብር ይህንን የመሰለ አባናኝ ሕልም ዛሬ ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ማየቱ የማይቀር ነገር ነው . . .

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ስድስት

ሳብር ከሴሊት ሕልሙ መላቀቅ አልሆነለ ትም ፤ እየተመላለሰ ያስጨንቀዋል ። ከሕልሙ ሲነቃ የሚያጋጥመው ፡ በአካባቢው ነግሥ የሚያ ገኘውን ጸጥታ ብቻ ነው—በሙታን መቃብር ሰፈር እንዳለ ፡ እንደ መርግ የሚከብድ ጸጥታ ። ጭንቀ ቱም ጸጥታውም ሚቋረጫ አልነበረውም ። አው ሳላውን ነፍስ ሲመታው ሞገድ ፈጥሮ እንደ ቆፍ ጣና ፈረሰኛ እርስ በርሱ በመሽቀዳደምና በመ ሳበቅ ከባሕሩ ቃሊም ጋር እንደሚላተም ማዕ በል ፤ አንዱ አሰፈ ሲለት ሌላው በእግሩ ይተካ ቦታል ። ሳብር ፡ በሕልሙ አባቱ ሁሌ ይታየዋል። አባቱን የመፈለጉ ነገር ደግሞ የሕይወቱ አንቀ ሳቃሽ ኃይል መሆኑ እየቀረ መጥቷል ። በፍቅሩ ፡ በፍላጐቱና በምኞቱ መሐል አልፎ አልፎ ጣልቃ የሚያስገባው ነገር ሆኗል ። ለጊዜው ሁለመ ናውን የሚገዛው የሚኖርበት ክፍልጨለማ... የሆቴሉን አራት ግድግዳ ተገን አድርጎ የሚፈ ጽመው መቃበጥ ፡ ድሪያና ወሲብ ብቻ ነው ።

ሳብር ወደ ጋዜጣው ቢሮ ብቅ እንዳለ ፡ ኤልሐም እንደ ተለመደው በአክብሮትና በፈገ ግታ ተቀበለችው ። ሁኔታዋ ሁሉ የደስ ደስ ያለው

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር ። ከሁሉም በላይ ደግሞ በተናወጠ ባሕር መሐል የተተከለ አለት የሚመስለው የመንፈስ እርጋታዋ ያስቀናል ።

"ምን ወሬ አለ?" አለችው ።

"ጥቅም የሌለው መሆኑን ብረዳም ፣ የሆነው ይሁን በማለት ማስታወቂያውን ለማደስ ነው የመጣሁት ።"

"ያሰብከው ሌላ የተሻለ ዘዴ አለ?" አለችው።

ፊቱን ፈገግታ አልብሶ ተመለከታት ። እርሷ ባታውቀው ነው እንጂ አባቱን የመፈለጉ ጉዳይ በሕይወቱ ውስጥ እንድ አነስተኛ ጥግ ከያዘ ውሎ አድሯል ።

"እሺ አንድ መረጃ ደርሶናል" አለው ታንታዊ ።

ሳብር ታንታዊ አጠገብ አረፍ ብሎ ወሬውን ለመስማት ጆሮውን ቀቀረ ።

"አንዲት ሴትዮ ደውላ ነበር ። "

"ምን የሚል ሴትዮ ?" አለ ሳብር ።

"ስለ ማስታወቂያው ነው አጥብቃ የጠየቀችው ። "

"ማንነትዋን ተናግራለች?"

"እሺ አልተናገረችም ። ስለ ማስታወቂያው ብቻ ነው የጠየቀችው ። "

"ምናልባት ራሕሚን ታውቀው ይሆናል" አለ ሳብር ፣ ተስፋው እያንሰራራ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምናልባት . . . ምናልባት . . . "

"ሁለተኛው 'ምናልባት' ምን ለማለት ነው?" በማለት ሳብር ጠየቀ ።

" ምናልባት ሴትዮዋ አንተን ታውቅህ ይሆናል " አለ ታንታዊ ።

"ምናልባትም ፡ አንዱ ቀልደኛ እንደ ለመደው ሊጫወትብኝም ይሆናል ። ከዚህ ቀደም አንዱ ቀልዶብኛል" አለ ሳብር ፡ በመመረር ።

አዕምሮው አሥሩን ያወጣ ያወርድ ጀመር። ምናልባት የራሕሚ ሚስቱስ ብትሆን? ከሪማም ልትሆን ትችላለች ። ከሪማ እንደሆነች ባሕርይዋ የፍትወት ፡ የመቋመጥ ፡ የሽረኝነትና የጥፋት ነው ። ማን ያውቃል? ከሁለቱ አንዷ ልትሆን ትች ላለች ።

ሳብርና ኤልሐም በጋዜጣው ቢሮ አቅራቢያ በሚገኘው ምግብ ቤት ውስጥ በተለመደው ስፍራ ተቀምጠዋል ። አስጨናቂ ሕልሙ ትዝ አለው ።

"የፍለጋህ ስሜት ምነው ቀዝቀዝ አለ?" አለችው ።

"ቀዝቀዝ ማለቱ ሳይበርድ አይቀርም ። በሆነ ባልሆነው ሳይ ተስፋ መጣሉ ምንም አልረባኝም" አሳት ።

በልቡ ውስጥ— የፍለጋዬ ስሜት የቀዘቀዘበትን ዋና ምክንያት ባወቅሽው!— በማለት አሰበ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ትክክል ነው። እንዲህ ያለውን ጉዳይ ጊዜ እንዲፈታው በትዕግስት መጠበቁ የሚበጅ ይመስ ለኛል" አለችው ኤልሐም፡ በሐሳቡ በመስማማት።

"አስቲ ዛሬ እንኳን ምሳ እንድጋብዝሽ ጥቅ ጅልኝ" አላት።

"እንዴት እድርጎ ይሆናል፤ እንግዳው አንተ ነህ እንጂ እኔ አይደለሁም እኮ!" አለችው።

ሁለቱም ምግባቸውን በዝምታ መብላት ያዙ። በሺህ የሚቆጠሩ ጥያቄዎች በአዕምሮዋ ውስጥ የሚርመሰመሱ መሆናቸውን ሳብር ከዓይን ውኃዋ መገንዘብ አላዳገተውም። ያለፈው ምሽት ሁሉ ታው ታወሰው። ሁለት ገጽ፡ ሁለት ባሕርይ ያለው ሰው መሆኑ በእሳትና በውኃ በሚመሰሉ በሁለት ሴዮች መከከል መዋለሉ ገረመው።

"አባትህን ለመፈለግ ስትነሣ ረዘም ያለ ፈቃድ ተቀብለህ መሆን አለበት" አለችው።

ውስጠ ምስጢሩን መመርመር መጀመርዋ መሆኑ ስለ ገባው ሞንቅ ይለው ጀመር።

"ተቀጥሬ የምሠራ ሰው እንኳን አይደለሁም። በራሴ ሀብትና ንብረት ነው የምተዳደረው" አላት።

"ብዙ የማይንቀሳቀስ ንብረት አለህ ማለት ነው?"

"አባቴ በቂ ንብረት ያለው ሰው ነው" አላት። ነገሩ እሆዲ ጠብ እንዳላለ ከሁኔታዋ ተሰማው።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ዋናው ሥራዬ ያባቴን ንብረት ማስተዳደር ነው። እንዲህ ያለውን ኃላፊነት መሸከም ደግሞ በደመወዝ ተቀጥሮ ከመሥራት ይልቅ በጣም የከበደ ነው።" ሁለተኛ ውሸት! ሳብር፥ ለኤልሓም ውሸት ሲናገር ውስጣዊ ስሜቱ ክፉኛ ይቈስላል።

"ዋናው ነገር የምትተዳደርበት ሥራ ያለህ መሆኑ ነው። የሰው ልጅ ዋና ጠላት ቦዘኔነት ነው" አለችው።

"እውነትሽን ነው። ያለፉት ሁለት ሳምንታት፥ የቦዘኔነት ሕይወት የጨለመ መሆኑን አሳ ይተውኛል። አንቺ ቦዘኔነት ምን እንደሆነ የም ታውቂ አይመስለኝም ነበር" አላት።

"ባላወቅውም እንዲሁ ሳስበውና ስለ ቦዘኔ ነት ካነበብኩት ስገምተው አስከፊነቱ ይታየኛል።"

"ቦዘኔነትን ያልቀመሰ በሐሳብና በንባብ ብቻ እንዴት ያለ ሕይወት አጸያፊች መሆኑን ሊረዳ አይችልም" አላት፥ ኰስተር በማለት።

"እውነትህን ነው።"

"ሌላው ቀርቶ በእኔ ላይ የደረሰብኝን ነገር መገንዘቡ የሚቻልሽ አይመስለኝም።"

"ምንም እንደማያውቅ ሕፃን የምትገምተኝ ከሆነ በጣም ተሳስተሃል!"

የደስ ደስ ያላት ልጅ . . . በፍቅርዋ አጥምዳ ዋለች። እንደ ምንም ተበራትቶ፥ "እስካሁን ስለ

t.me/OLDBOOKSPDF

እኔ ብዙ ነገር ሰምተሻል ። እስቲ ስለ ራስሽ እንዳንድ ነገሮችን ንገሪኝ" አላት ።

"ስለ አንቱ ምን የማውቀው ነገር አለ?"

"ስሜን ፣ ምን እንደምሠራ ፣ ወደ ካይሮ የመጣህበትን ምክንያት . . . ከሁሉም በላይ ደግሞ እንደማፈቅርሽ ታውቂያለሽ" አላት ፣ ፈራ ተባ እያለ ።

ፈገግ እያለች ፣ "የሚሆነውንም የማይሆነውንም አንድ ላይ አትደበላልቀው" አለችው ።

—እኔስ ምኞቴና ጸሎቴ ፣ ይሆንልኛል ብዬ ያሰብኩት ይሁንልኝ—አለ በሐሳቡ ። ወዲያው ከባድ ደመና ፀሐይዋን ስለ ጋረዳት በምግብ ቤቱ ላይ ያረፈው ጥላ ተጫጫነው ።

"እስካሁን ስምሽንና ሥራሽን ብቻ ነው የነገርሽኝ" አላት ሳብር ፣ ውይይታቸውን በመቀጠል ።

"ሌላ ምን ለማወቅ የምትፈልገው ነገር አለ?"

"መቼ ነው ወደ ሥራ ዓለም የተሰማራሽው?"

"ትምህርቴን ጨርሼ እንደ ተመረቅሁ ነው ሥራ የጀመርኩት ፤ ሦስት ዓመት መሆኑ ነው ። በነገራችን ላይ አሁንም ትምህርቴን በከፍተኛ ደረጃ በመከታተል ላይ ነኝ ። "

—አደራሽን የእኔን የትምህርት ደረጃ ብቻ እንዳትጠይቂኝ—በማለት ሳብር ውስጥ ውስጡን ከሐሳቡ ጋር ተሟገተ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ጊዛ ነው መሰለኝ እኖራለሁ ያልሽኝ?"

"አዎን ፤ ጊዛ ነው የምኖረው—ከእናቴ ጋር። ቤተሰቦቻችን ያሉት ቃልዬብ ነው ። አጎቴ ሼልዩ ፖሊስ ይኖራል ። ከእኛም ቤተሰብ ወጥቶ የደረ ሰበት ያልታወቀ ሰው አለ ። "

"ማን?" አለ ሳብር ፡ አፉ እንዳመጣለት ።

"አባቴ" አለች ኤልሐም ፡ ሣቅዋን አፍና በመያዝ ። ከኤልሐም እንደበት የሰማው ቃል ፊጽሞ ያላሰበው በመሆኑ አጋጣሚው ሳብርን አስገረ መው ። ደጋግሞ ያያቸው ሕልሞች ትዝ አሉት ። —አባት ያልጠፋው የለም ማለት ነው እንዴ?— ብሎ አሰበ ።

"ያንቺ አባት ደግሞ እንዴት አድርጎ ነው የጠፋው?" አሳት ።

"የእኔ አባትና ያንተ ወንድም አጠፋፍ አይ መሳሰልም ። ለማንኛውም ምስጢሬን ጐልጉዬ እንድነግርህ መፈለግህ ትንሽ አልበዛም?"

ሳብር ኤልሐምን ትኵር ብሎ በመገረም ተመ ለከታት ።

"የእኔ ወላጆች ገና ሕፃን ሳለሁ ነው የተለ ያዩት ።"

"አባትሽ ጥሎሽ ነው የሄደው ማለት ነው?"

ኤልሐም ከት ብላ ሣቀች ። ሳብር ታሪኳን አሳምሮ ለማወቅ ጐመጀ ። "በሌላ አትተርጉሚ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብኻ ፤ እንደ ወጣ ቀረ ማለቴ ነው” አላት ፡ ግራ እንደ መጋባት እያለ ።

“አባቴ በአስዩት የሚኖር የታወቀ ጠበቃ ነው። ምናልባት ታውቀው ይሆናል ። አምር ዛይድ ይባላል ።”

ሳብር መንፈሱ መረጋጋት ጀመረ ።

“እኔስ ፡ ሰይድ ኤል ራሕሚ ልትዩ ነው ብዬ ነበር” አላት ።

“አንቴ መሆን ከጅሎህ ነበር ማለት ነሞ!” አለችው ፡ እየሣቀች ።

“እንዲያውም...!” አላት ፡ ቃላቱን እየተጫነ።

ፊትዋ ፍም መሰለ ። “እናቴ ...” አለች ኤልሐም ታሪኳን በመቅጠል ፤ “ወላጆቼ ሲለያዩ ፡ እናቴ ልጇን አልሰጥም ብላ ድርቅ አለች ። አባቴም ሴላ ሴት የማግባት ፍላጎት ስለ ነበረው አልተግደረደረም ። ጠቅም ያለ የፍቺ ገንዘብ ሰጥ ታት ስለነበር ወደ ካይሮ መጥቶን ከአያቴ ጋር እንኖር ጀመር ። አያቴ ከሞቱ በኋላ ፡ እኔና እናቴ ቤታቸውን ጠቅልለን ይዘናል” አለችው ።

ታሪኳን በጥሞና ቢያዳምጣትም ፡ የምትነግረውን ሀሉ መቀበል አልቻለም ። በተፈጥሮው ሴቶችን—በተለይም ደግሞ እናቶችን—ማመን ያዳግተዋል ። ደግነቱ ሳብር ምን ዓይነቱን የሕይወት ገዳና አቋርጦ እዚህ እንደ ደረሰ ኤልሐም

t.me/OLDBOOKSPDF

አታውቅም ። በሕይወቱ ዘመን ፥ ውሎውና አዳሩ ከአቃጣሪዎችና ከማንዘራሾች ጋር ነበር ። ይህን ጉዱን ፍርጥርጡን አውጥቶ ሊነግራት እንዴት ይችላል? በዚህም ሳቢያ ፥ ኃዘንና ትካዜ ሁለመ ናውን ሲወረው ተሰማው ። ኤልሐም ትረካውን አላቆመችም ፤ "አንድ ቀን አንቱ ፥ 'ይህች ልጅ አባትዋን ማየት አለባት' ብሎ ለእናቴ ነገራት ። እናቴ እሳት ለብሳ እሳት ጐርሳ ፥ ፈጽሞ አይደረግም ፤ በልጇ ላይ ዓይኑ እንኳን አያርፍም ፤ እስከ ዛሬ መች ዞር ብሎ አያት ፤ ፈጽሞ አይደረግም !' በማለት አራስ ነብር ሆነች ። አንቱ ግን ፥ 'ልጅቱ እያደገች ስለሆነ የግድ አባት ያስፈልጋታል' በማለት ድርቅ አለ ።"

ሳብር ሳያስበው ፥ "ነፃነት ፥ ክብርና የተደላደለ የሰላም ኑሮ!" በማለት አጉረመረመ ።

ኤልሐም ትክሻዋን ወደ ላይ መታ አድርጋ፣ "እናቴ በሐሳብዋ በመጽናት አባቴን እንዳላየው ከለከለችኝ ። እኔም ከማላውቀው አባት የሚያስተዳድረኝ ሥራዬ እንደሚበልጥብኝ በመገመት ፥ በእናቴ ሐሳብ ተስማማሁ ። የኋላ ኋላ እንደ ደረስኩበት ከሆነ ፥ የእናቴ ፍራቻ ፥ ልጇን አባብሎ ይወስድብኛል የሚል ነበር" አለችው ።

ሳብር የኤልሐም ንግግር ብቻ ሳይሆን የአንደበትዋ ርቱዕነትም መስጠታል ። በሌላ በኩል ደግሞ ፥ ነፃነት ፥ ክብርና የተደላደለ የሰላም ኑሮን

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚተካ ምን ዓይነት ሙያ ወይም ምን ዓይነት ሥራ ሊኖር ይችላል? የሚለው ጥያቄ በአእምሮው ውስጥ ይመላለስበታል ።

"ትምህርቴን በመቀጠል ላይ እያለሁ በአሁኑ ሥራዬ ለመቀጠር አመለክትኩ ። እንደምታየኝ ዛሬ፡ በሥራዬ ላይ ሆኜ የከፍተኛ ትምህርት ጥናቴን በማታ ትምህርት ቤት ቀጥያለሁ ። "

"ስለ አባትሽ አታስቢም?" አላት ፡

"ፊጽሞ አላስብም ። መኖሩም ትዝ አይለኝም ። የእርሱም ምርጫ ይኸው ነው ። "

"አባትሽን የማታስቢው ከማንም ምንም የማትፈልገ, በመሆንሽ ነው" አላት ።

"አይ ፡ እንደሱ እንኳን አይደለም ። ለምሳሌ ፡ እናቴ ምንም የተለየ ነገር አታደርግልኝም ። ነገር ግን እወዳታለሁ ፤ ከእሷ ተለይቼ መኖር የምችል አይመስለኝም" አለችው ።

—ምነው ሰው ሁሉ እንዳንቺ ሐሳብ የለሽ በሆነ ! በተስፋ መቁረጥ አዘቅት ጫፍ መንጠል ጠል ምን ማለት እንደሆነ የምታውቂ አይመስለኝም ። ነፃነት ፡ ክብርና የተደሳደለ የሰላም ኑሮ የመኖር ጉጉት ዳርሽ ድርስ ብሎ አያውቅም ። ሕይወትሽ የወንጀልና የውርደት ማቅ የተከናነበ አይደለም ። ምነው ሰው ሁሉ እንዳንቺ በታደለ— ሳብር ከሐሳቡ ጋር ይሟገታል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ይሽውልህ ፤ እንዳንተ በግል ሀብትና ንብ
ረቴ የምተዳደር ባልሆንም ፡ ሥራዬ ደስታና እር
ካታ ይሰጠኛል" አለችው ። ኤልሐም አስባም ይሁን
ሳታስበው የሳብርን ቀልብ ነካችበት ። ክፉኛ ተሰ
ማው ፤ በማስመሰልና በመግደርደር ላይ የተመ
ሠረተ ሕይወቱ እርቃኑን እየቀረ መሄዱ አሳሰ
በው ። ገመናውን ፍርጥርጥ አድርጎ ማውጣትም
አሰኘው ። ድፍረቱ ግን ከዳው ። ኤልሐም ወደ
ሥራዋ ለመመለስ ጥላው በመሄድዋ ብቸኝነቱ
ብቻ አብሮት ቀረ ።

ኤልሐም የረጋች ፡ በራስዋ የምትተማመንና
ጠባየ ሸጋ ሴት በመሆንዋ በቅርበት ለሚያው
ቃት ቀርቶ አላፊ አግዳሚው ከበሬታ የማይነፍ
ጋት ሴት ናት ። ሳብር በሴትነትዋ ፡ በውበትዋና
በማራኪነትዋ ተገፋፍቶ ሊያሸንፋት ቢቃጣው ፡
የክብርዋ መደፈር ሊያስከትልባት የሚችለውን
ስሜት ሊያስበው ፍላጐቱ ይገታል ። የለመደው
ሴትን ተጣጥሮ የማሸነፍና ፍላጐቱን የማርካት
ዝንባሌው ይሟሽሻል ። የብልሹ ገበናው መሸፈኛ
የሴቶችን ክብር መጻረር ቢሆንም ፡ በወንጀልና
በፍትወት ጽልመት በተሸፈነ ሕይወቱ ውስጥ
የብርሃን ፋና ሆና ከምትታየው ከኤልሐም ጋር
ሲሆን ፡ እንኑ ይከሰሳል ። ሳብር ችግሩን ሁሉ
የሚረሳው ከሪማ እቅፍ ውስጥ ገብቶ በወሲብ
ግለት ሲቀልጥ ብቻ ነው ። በዚህ ሳቢያም ፡ በሁ
ለት ተጻራሪ ዋልታዎች መካከል በመዋለል ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁለት የተለያዩ ገጽታዎች ያሉት ኑሮ ውስጥ ገብቶ ይባዝናል ።

ሳብር ከምግብ ቤቱ ሲወጣ የጓዳር ምሽት ቀዝቃዛ አየር ተቀበለት ወደ ሆቴሉ አዘገመ ። ሆቴሉ ውስጥ ከወትሮው የተለየ ነገር አላጋጠመ ውም ። ከሊል ባሕር መዝገቡ ላይ እንዳፐ'ነበሰ ፡ መሐመድ አል ሰዊ ደግሞ ሆቴሉ መግቢያ በር አካባቢ ከለው መቀመጫ ላይ እንቅልፍ ወስ ዶአቸው አገኛቸው ።

ሳብር ሆቴሉ እንግዳ ማረፊያ ክፍል ውስጥ ገብቶ አረፍ አለ ። ለአንድ ሰዓት ያህል ጋዜጠ ኞን ሲያገላብጥና ሲጋራ ሲያጨስ ቆየ ።

በመጨረሻ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ስልክ ደወለ ።

" ኤልሐም ፤ ነገ እዚያው ምግብ ቤት እንድ ንገናኝ ፈልጌ ነበር ፤ ይመችሻል ? "

" በደስታ ፤ ምነው ደህና አይደለህ እንዴ ? "

" ኧረ በጣም ደህና ነኝ ። እንድንገናኝ ስለ ፈለግሁ ነው " አላት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ሰባት

ሳብር ሌሊት ሌሊት ከከሪማ ጋር ሲዋደቅ ያድራል ። በዚያን ወቅት ነገር ዓለሙን ይረሳል ፤ ፍርሃቱና ሥጋቱ ፡ ሐሳቡና ትካዜው ጥሎት እብስ ይላል ። ከሪማ ፡ በሩካቤ የልብ አድርስ በመሆንዋ ውጥረቱን ታረግብለታለች ። በአንጻሩ ደግሞ ከኡ ልሐም የሚተርፈው መጕምጀት ፡ መቋመጥና ስት ለየው የሚሰማው የመንፈስ ባዶነት ብቻ ነበር ።

ሳብር ጥምብዝ ብሎ ሰክሮ ኑሯዩ ሳለ ፡ ከሪማ በሩን ቆቅታ አንኳኩታ ካ·ቃችውና የረጅም ጊዜ የወሲብ አምሮቱን እንዲወጣ ካደረገችው ወዲህ ፡ ሰዉ ክትት ፡ አካባቢው ጭር ሲልላት ሹልክ ብላ መምጣቱን አላቋረጠችም ። ከመጀመሪያው ግንኙነታቸው አንሥቶ ያሳደረችበት ወሲባዊ ተጽእኖ ሊያላውሰው አልቻለም ። ለወትሮው እኔ ነኝ ያለች ሴት በዚህ ሁኔታ አፍንጫውን ሰንጋ ይዛው አታውቅም ። ከሪማ በስሜቱና በፍላጐቱ ላይ ሙሉ ሥልጣን መቀዳጀቷን አሌ የሚለው ነገር ባይሆንም ፡ ከአንደበትዋ የሚወጡትን ቃላት አሜን ብሎ የተቀበለበት ጊዜ ግን አልነበረም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ ምሽት ከንዴን ተንተርሳ ተኝታ ሳለች ፡ ወደ ጆሮው ጠጋ ብላ ፡ "ያለ አንተ መኖር እንደማይሆንልኝ ታውቃለህ ?" አለችው ። ከዚህ ቀደም አዘውትሮ የሰማቸው ቃላት ነበሩ ። እነዚህ ሁሉ ቃላት በእስክንድርያ ከተማ በየሴሊት ክበቡ ፡ በየሴቲኛ አዳሪው ሰፈር ደግሞ ደጋግሞ ሰምቷቸዋል ። የቃላቶቹን ባዶነት በመረዳቱ ፡ ከከሪማ ወጥመድ ለማምለጥ ከጅለት ነበር ፤ ግን አልሆነለትም ። ከሪማ ዞሮ መግቢያው ፤ ከሪማ የአባቱን ፍለጋ እንዳያቋርጥ የተስፋና የኃይል ምንጩ ሆናለች ።

አንዳንድ ቀን ከሪማ ስሜትዋ ሁሉ ቀዝቅዞ አጠገቡ ጥቅልል ብላ ትተኛለች ። በዚህ ጊዜ ሳብር እንደ ልቡ ይሆናል ። ስሜቱ ተንፈስ ብሎ ለት ኤልሐም በሐሳቡ ስትመጣበት ከከሪማ ወሲባዊ እቶን መንጥቃ እንድታወጣው ይጎንጸና ታል ። በሌላ ወገን ደግሞ ያለ ከሪማ ምንም እን ደማይሆንለት ልቡ ይነግረዋል ።

ሳብር የሐሳብ ጉዞውን ሲጀምር ፡ በእስክን ድርያ ባሕር ዳርቻ በተደረደሩት ጀልባዎች ሥር ያሳለፈው ምሽት ትዝ ሳይለው ይቀራል ማለት ዘበት ነው ። በዘመናት ጭጋግ የተሸፈነው ገጠ መኖ ውስጣዊ ስሜቱን መልሶ ቀልሶ ይገ-በኘ ዋል ። ሳብር ከከሪማ የሚያገኘው ፍቅርና እርካ ታን ብቻ አይደለም ። ውጤት የለሽ ፍለጋው የሚያስከትልበትን ብስጭት ታስታግሥለታለች ፤

t.me/OLDBOOKSPDF

በኤልሐም አልጨበጨነት ውስጡን የሚያቄስለ ውን ጭንቀት ታረሳለታለች ።

"ምነው ዛሬስ ተለወጥሽብኝ ?" አለ ሳብር ፡ አንድ ምሽት እንደ ልማዳቸው አብረው ሁኖተው ሳሉ ።

"አንዳንዴ እለወጥብሃለሁ ማለት ነው ?" አለችው ከሪማ ፡ እንደ ሕፃን በመቅለስለስ ለጥያ ቄው ጥያቄ እየሰነዘረችለት ። ሽረኛዋ ከሪማ ። በቅርብ ፡ "ያለ አንተ መኖር አይሆንልኝም" ማለትዋን ዘንግታው ይሆን ? ሳብር ፡ በአንድ ወቅት እናቱ የሠራችው ነገር ትዝ አለው ። አንድ ቀን አንድ ደንበኛዋ 'ሊገ-በኛት' ብቅ ይላል ። እናቱ ስውዬውን እንዳይሸጥ እንዳይለ ወጥ አድርጋ ሰድባ ከቤት ታስወጣዋለች ። ሰው ዬውን ከአካባቢው አባርራ ጥቂት እንደ ቆየች ፡ ስቅስቅ ብሳ በማልቀስ ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት ትጀ ምራለች — ሴቶች ሲባሉ እንዲህ ናቸው !

"ያመመሽ መስሎኝ ነበር" አሳት ፡ አፉ እንዳመጣለት ።

"ሽረ እኔስ ደህና ነኝ" አለችው ፍርጥም ብሳ ። የታመምከውስ አንተ ነህ የሚል ስሜት ፊቷ ላይ አነበበ ።

"እንኳን ደህና ሆንሽልኝ" አላት ።

"ያላንተ ምንም እንደ ሌለኝ አይገባህም መሰለኝ" አለችው ፡ ጉንጩን እየደባበሰች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔስ ያላንቺ ማን አለኝ ብለሽ ነው። ተለይቼሽ መሄዴም የሚያሳዝነኝ ስለዚሁ ነው" አላት ፡ ሸረኝነትዋ ትዝ እያለው።

"የምን መሄድ ነው የምታወራው ?"

"መሄዴ ባላወራውም የሚቀር ነገር አልሆ ነም ።"

"የመሄድህን ነገር በተቻለ ማራዘም አለ ብህ ። መቼም እናንተ ወንዶች እንቅልፍ የሚነ ሣችሁ የገንዘብ ነገር ነው ።"

"ችግሬን ከገንዘብ በስተቀር የሚፈታው ነገር የለም ።"

"በቸገረህ ጊዜ ባለቤቱ እንዲረዳህ አደርጋ ለሁ ።"

"ባለቤትሽስ የገንዘብ ነገር እንቅልፍ ይነ ሣው የለም ?"

"በጣም እንጂ ። እርሱን የሚያንገበግበው ገንዘብ ሲባክን ማየቱ ነው ።"

"ባንቺስ ይቀናል ?"

"መቅኖት ነው ! ከመጠን በላይ እንጂ ። በዚህ ጉዳይ አንድ ስምምነት ላይ ደርሰናል . . . አርፈሽ ልቀመጥ . . .ወይም ደግሞ ስቀብጥ ብገኝ ልቅ ልወጣ ። ያንተስ ነገር እንዴት ነው ? የቴሌ ፎን ጥሪ ከመጠበቅ የተሻለ ነገር የለህም ማለት ነው ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

“ የምጠብቀው የቴሌፎን ጥሪ ቢያርሰኝ ከችግሬ እገላገል ነበር ። ”

“ እኔ ስለ አባቱ ደንታ ኑሮኝ አያውቅም ” አለችው ።

“ ለእኔ የሕይወቴ ዋልታ አባቴ ነው ። ”

“ ለመሆኑ እንዴት ነው የተጠፋፋችሁት ?”

“ ታሪኩ ረጅም ነው ። አንድ ቀን በሰፊው አወጋሻለሁ ” አላት ።

“ እርሱን በመፈለግ እንዲህ ስትንከራተት ፣ እንዴት እዚህ ነው ያለሁት የሚል ፍንጭ አይ ሰጥህም ? ”

ችግሩ ይኸው ነው ። የችግሩ ፣ የመንከራተቱ መነሾ ምክንያት የአባቱ ድምፁን አጥፍቶ መቅ መጥ ነው ። ሳብር አባቱን ካላገኘ ምን ይውጠ ዋል ? በችግር መማቀቅ ፣ መክራ ማየት ፣ ተስፋ ቢስ ሕይወት . . .ሳብር አባቱን . . .ካልሆነም አንድ ሥራ ማግኘት አለበት !

“ ወደዚህ ከመምጣትህ በፊት በምን ትተዳ ደር ነበር ?” አለችው ከሪማ ፣ ሐሳቡን በማቋረጥ ።

“ ብዙ ገንዘብ ነበረኝ ፤ አሁን ያለሁት በእጄ ያለውን እያሟጠጥኩ ነው ። ”

“ ምን ነበር የምትሠራው ? ”

“ ምንም ። ”

“ ታዲያ ሥራ ለምን አትፈልግም ? ”

t.me/OLDBOOKSPDF

“አባቴን ሳላገኝ ሥራ አልይዝም ። የምይዘውም ሥራ በእርሱ በኩል የመጣ መሆን አለበት ።”

“ነገሩ አልገባኝም ።”

“የምነግርሽ ይኸው ነው ” አላት ፡ ቆፍጠን ብሎ ።

“የንግድ ሥራ ለምን አትጀምርም ?”

“በምን ገንዘብ ! የንግድ ሥራም እኩ ልም ይጠይቃል ።”

“ተቀጥረህ ብትሠራስ ?”

“በምን ችሎታዬ ? ለምንም ዓይነት ሥራ የም መጥን አይደለሁም ” አላት — በምሬት ።

“ፍቅር ብቻ ነው የምታውቀው ማለት ነዋ ?” አለችው ፡ ጸጉሩን እያሻሸች ።

ፈገግታ የተላበሰ ፊቱን አዙሮ አሳያት ።

“የእኔና ያንቺ መጨረሻ ምን የሚሆን ይመስልሻል ?”

“ነገሩ ቀላል አይደለም ። ባሌ የዋዛ ሰው እንዳይመስልህ !”

“አርጅቶ አብቅቶለት የለም እንዴ ?”

“እያየኸው ምን ትጠይቀኛለህ ? ሞት የዘነጋው ሰው ነው ።”

“በእጄ ውስጥ ካለው ገንዘብ የበረከተ ዕድሜ እንዳለው ይሰማኛል ” አላት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ ሰውነቱ ብዙ ነገር ይነግረዋል ። እንድ ቀን ማንኑነታችን ያቋርጣል ብዬ እሠጋለሁ ። ”

ሳብ አድርጎ አቀፋት ። “ የቀረው ይቅራል እንጂ ተያይዘን ነው እብስ ብለን የምንጠፋው ” በማለት በጆሮዋ ነገራት ።

“ መጥፋቱንስ እንጥፋ ፤ መኑዳደሪያችን ምን ይሆናል ? ”

“ እውነትሽን ነው ። አባቴ ካልተገኘ ፍቅራችን ብቻውን ዋጋ የለውም ። ”

“ ይኸ አጉል ቅጥፖትህ ቢያበቃ ምን አለበት ? ”

“ ዝም ብለን የሚሆነውን እንጠብቅ ማለትሽ ነው ? ”

“ ዝም ብለንማ እንዴት እንጠብቃለን ? መጠበቁ ምን ውጤት አለው ? ”

“ውጤቱማ ሞት ነው!” አላት ፡ በቁርጠኝነት።

“ አንዳንዴ እኔን ሳያስቀድመኝ አይቀርም የሚል ፍርሐት ይሰማኛል ። እርሱ እንደሆነ አንድ ቀንም ራሴን ብሎ አያውቅም ። እኔ ነኝ ጉበቱን ፡ ሹላሊቱን እያልኩ ያለሁት ” አለችው ።

“ እሱ እያለ አንቺ . . .የሚታመን ነገር አይ ደለም ” ብሏት ፡ የምሬት ሣቁን አሰማት ።

“ የዋህ ሰው እንዳይመስልህ ፤ ሸረኛ ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የጥርጣሬ ጥንጮ ካየሁበት ወደዚህ ዝር አል ልም ” አለችው ።

“ ጨርቄን ጥዬ ነው የማብደው !” አላት ፡ በጩኸት።

“ ማበዴስ በእኔ ሳይብስ አይቀርም ። ግን ምን ይደረጋል . . . ? ”

“ ዝም ብሎ መጠበቁ ዋጋ ከሌለው ፤ ተነ ሥቶ መጥፋቱ ካለዋጣ ፣ የቴሌፎን ጥሪውን ዓይን አፍጥጦ መጠበቁ ከንቱ ድካም ከሆነ ፤ ታዲያ የሚያዋጣው ምንድን ነው ? ”

“ እምን ፤ የሚያዋጣው ምንድን ነው ? ” አለችው ።

“ እንደ እኔ ከሆነ ተነሥቶ መጥፋቱ ነው የሚያዋጣው ! ”

“ ፈጽሞ አይታሰብም! ” አለች ከሪማ ፡ ካን ጅትዋ ።

“ እንግዲያውማ ዝም ብሎ መቆየት ነዋ ።”

“ ዝም ብሎ መቆየቱ ፋይዳ የለውም !” አለችው ፡ ደብቆት ያለውን መጥፎ ሐሜት ፍርጥ አደርጎ እንዲያወጣ እየገፋፋችው ።

“ ታዲያ ምን ይበጃል ? ”

“ አይ . . .እንግዲህ . ...” አለች ከሪማ ፡ተስፋ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ መቅረጥ እየቃጣት ፤ “ የሚበጀውን ነገር ማድረግ የሚሰነን ከሆነ ባንገናኝ ይሻላል ። ”

አፏን በመዳፉ ከደን እያደረገ ፥ “ ከሱስ ሞቱን እመርጣለሁ ! ” አላት ።

“ ሞት !” አለች ከሪማ ቁና ቁና እየተነፈሰች ። ከዚያም ለራስዋ የምትናገር ይመስል ፥ “አዎን ፥ ሞት ” አለች ።

ሳብር ልቡ ክፉኛ ይደልቃል ፤ የትንፋሹ ፍጥነትም አይሏል ። በሁለቱ መካከል የሰፈነው ጸጥታ የተጫጫነው ይመስላል ።

“ ምነው ዝም አልሽ ? ” አላት ።

“ ደክሞኛል ። ከእንግዲህ ምንም ነገር አያስፈልግም ” አለችው ።

“ ለጉዳዩ አንድ መፍትሔ ሳናበጅለት ? ”

“ እባክህ ተወኝ ፤ ተከድኖ ይብሰል ። ”

“ እንዴት አድርጎ ? አንድ መፍትሔ መኖር አለበት ! ” አለ ፥ እየተለማመጣት ።

“ ምን የሚለት መፍትሔ ? ”

“ አንቺን እኮ ነው የምጠይቅሽ ? ”

“ እሱም አንተን እየጠየከህ ነው ! ”

“ እሷ ከአንቺ አንድ መላ ለመስማት ነው የምጠብቀው ” አላት ።

“ እኔ ምንም መላ አይታየኝም ። ሁኔታው ሁሉ ዝም ብሎ ሕልም ነው . . . የቁም ሕልም . . .

t.me/OLDBOOKSPDF

ቅገሮት ። አንቲ በየዕለቱ ቁጭ ብለህ እንደምትጠ ብቀው የቴሌፎን ጥሪ ። ምን ያደርጋል ታዲያ . . . የባሌን የተካበቲ ገንዘብና ይህንን ሆቴል መው ረስ ብችል ሞት እስኪለየን ድረስ አብረን እን ኖር ነበር ። ”

ሳብር ቁና ቁና ተነፈሰ ።

“ ችግሩ . . .” አለች ከሪማ ንግግሯን በመቅ ጠል ፤ “ጣጣው ... ለሚያጋጥመን እክል መፍትሔ ሲጠፉን ተቀምጠን በማይጨበጥ የቁም ሕልም ውስጥ ገብተን መዳከር ይቀናናል ። የቁም ሕልማች ንን . . .ቅዠታችንን . . .የመጥኜ እንላለን ። ”

“ አንዳንዴ ሕልምም እውን ሊሆን ይችላል” አላት ።

“ እንዴት አድርጎ ? ”

“ ሕልም እውን ይሆናል ሲባል አልሰማ ሽም ? ”

“ እንዲህ ባለው ነገር ታምናለህ ? ”

“ አላምንም ! ”

“ በል እንግዲያው . . .ህ እየቀደደ ስለ ሆነ ተኑሥቼ ልሒድበት ። መባል የሚገባውን ሁሉ አወርተን ጨርሰነዋል ። ”

በጭለማ ውስጥ ልብስዋን ስታጠላልቅ ቅር ጽዋ ታየው ። ዞር ብላ እቅፍ አድርጋ ከንፈሩ ላይ ስማው ውልቅ አለች ። ሳብር እንደ ልማዱ ጨለማ ውስጥ ብቻውን ቀረ . . . እንደ መርግ

t.me/OLDBOOKSPDF

በሚከብደው ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ አብሮት የቀረው ሐሳቡ ብቻ ነበር ። በሐሳቡም የእናቱን መቃብር ገበኘ ። በአሁኑ ጊዜ የእናቱም መቃብር ብቻውን በብርድና በጨለማ ውስጥ መሆኑ ታየው ። እናቱ ለፍርድ ስትቀርብ ፡ " ለዚህ ሁሉ ያበቃኝ ጠላቴ ማን እንደሆነ አውቀዋለሁ ። እኔ ራሴ በገዛ እጄ እገድለዋለሁ " ያለችውንም አስታወሰ ። ምን ያደርጋል ! ያለችውን ለመፈጸም ዕድሉ ሳያጋጥማት ወህኒ ቤት ማቅቃ ሞተች ።

ሳብር የሆዱን አወጣዮ ለኤልሐም አስመን ገሩ ሲያስበው ይቋጨዋል ። እርስዋ ገመናዋን ገላልጣ ስታጫውተው ፡ እርሱ አሥሩን እየቀባጠረ ባይዋሻት ኖሮ ፡ ይኸኔ ምን ያህል ሆድ ለሆድ በተቃራረቡ ። በሌላ በኩል ደግሞ አባቱን ሲያስታውስ አሰምሮውን ጥቂት ነካ ያደርገዋል ። እንዲህ የወታ ዝታ ሆኖ የቀረበት ምክንያት ፈጽሞ አይገባውም . . .

ኤልሐም በሐሳቡ ድቅን አለችበት ። በእን ዴት ያለ ዘዴ አግኝቷት ፡ ተዳርዮ ፡ ተሳፍዮ ፡ አስ ጨሆና አስለቅሶ ፡ ጨርቋን ቀዳዶና እርቃንዋን አስቀርቶ እንደሚያሸንፋት ያስላስል ገባ ። ወዲ ያው መዊዚኑ አማኞቹን ለማለዳ ጸሎት የሚቀሰ ቅስበትን ጥሪ አሰማ ። የዛሬውም ሌሊት እንደ ወትሮው ይሆን ያለፈው ? የተለየ ነገር ቢኖር ፡ በዛሬው ሌሊት ፡ በእግረ ሕሊናው ተገኘ እናቱን ፡ አባቱንና ኤልሐምን አግኝቷቸዋል . . .

t.me/OLDBOOKSPDF

ከንጋቱ አንድ ሰዓት ላይ ከመኝታው ተነ ሥቶ የክፍሉን መስኮት ከፈት ሲያደርገው ፡ አደ ባባዩ ዳር ተቀምጠ የሚያንበንበው ለማኝ ለአ ላፊ አግዳሚው የሚያሰማው ወልጋዳ ግጥም ጆሮ ውን ጐበኘው ። ከሊል በሰው ተደግፎ ፎቁን ሲወ ርድ አየ ። አቅፎና ደግፎ እያወረዱው ያለው አለ. ሰርያኩስ መሆኑ ነው . . .

ሳብር እንደ ልማዱ የእግዶች ማረፊያው ክፍል ውስጥ ተቀምጠ ከሊልን አትኩሮ ይመለ ከተዋል ። ከሊል ባሕር መዝገቡ ላይ አቀርቅሮ በሚንቀጠቀጥ እጁ ገቢውን ይመዘግባል ። — ገቢ... ገንዘብ . . .ሀብት . . .ንብረት ። ምነው እተቀመጥ ከበት ድርቅ ብለህ በቀረኸው ! ከአንግዲህ ምን ቀረኝ ብለህ ነው ተጨልተህ ያለኸው ? የከሪማ ውበት ለተሟጠጠ ፍላጐትህ ማጐልበቻ የሚሆነው እስከ መቼ ነው ? ልብስዋን ስታወልቅ ዓይንህን ከማቁለጭለጭና ሰውነትህን አሻሽታ እንድታ ስተኛህ ከማድረግ ሌላ ምን ትፈይድላታለህ ? ወይ አንተ ድብን ማለት ፡ ወይም አባቴ መጣኝ አለበት !

ሳብር ፡ በአስክንድርያ ከተማ ፡ ከሚፈልጋት ሴት ጋር እንደ ልቡ ተዳርቶ ፡ እንደ ልቡ ተማ ትዶ ፡ እንደ ልቡ የማንንም አገጭ እወልቆ ፡የማ ንንም አጥንት አድቅቆ ያለ ሐሳብ ያሳለፈው ጊዜ ትዝ አለው ። እንድ ምሽት በአንድ ዳንስ ቤት ውስጥ ባነጣው ጸብ ሳቢያ ፡ ሕጣ እንዲያስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከብር ከተጠራው ፖሊስ ጋር ተጣልቶ ከሞት አፋፍ መመለሱ ታወሰው ።

" ሁለተኛ በማንም ላይ እጅህን እንዳታነሣ ። የሚያስቸግርህ ሰው ካለ ለእኔ ንገረኝ ።እኔ ወደ መቃብሩ ሰተት ብሎ እንዲወርድ አደርገዋለሁ ! " ያለችው እናቱ በሐሳቡ ድቅን አለች በት ። እናቱ ፡ በአንድ ወቅት ፡ አንዲት ባላንጣዋን ከገጸ — ምድር እንድትወገድ አድርጋታለች ። ዓላማዋን ለአንድ ወዳጅዋ ደህና አድርጋ ትነግረዋለች ። ሰውዬው ማንም ሳያየውና ሳይሰማው ሴትዮዋን ጭጭ አድርጎ ወደ ሊብያ እብስ ይላል ። ሰው ሁሉ ሴትዮዋን ያስገደለቻት ባሲማ አምራን ናት እያለ ቢያወራም ምንም መረጃ ባለመገኘቱ የሟቹ ደም ደመ ከልብ ሆኖ ቀርቷል ።አሁን ከሊል ድንገት ፍጥም ቢል ለምን ሞቱ ብሎ የሚያገናልት ሰው ይኖር ይሆን ?

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ስምንት

“ ከእንግዲህ ማስታወቂያውን ማውጣት መቀጠሉ ምንም ፋይዳ የለውም ” አለ ሳብር ፡ በማግሥቱ ወደ ታንታዊ ቢሮ በመገሰቅ ። ታንታዊም ሐሳቡን አልተቃወመም ። “ እስካሁን የወጠትን ማስታወቂያዎች ሳይመለከታቸው ይቀራል የሚል ግምት የለኝም ” አለ ሳብር ፡ ውሳኔውን በማጠናከር ።

“ እስካሁን እንዴት ሳያየው ይቀራል ! ” አለ ታንታዊ ፡ በሐሳቡ በመስማማት ።

ኤልሐም በንግግራቸው መካከል ጣልቃ በመግባት ፡ “ ማስታወቂያውን ካየው ፡ ተፈላጊው ሰው እኔ ነኝ ብሎ ይፋ መውጣት አልፈለገም ማለት ነው ! ” አለች ።

“ ምናልባት ከአገር ወጥቶ ሊሆን ይችላል ። ለማንኛውም ከእንግዲህ ወዲያ ማስታወቂያውን ማውጣቱ አስፈላጊ አይመስለኝም ” አለ ሳብር ።

ኤልሐም ጉዳዩ እንዲህ ባጭሩ ተቀጭቶ እንዲቀር የፈለገች አትመስልም ። “ ከእንግዲህ ወዲያ ተፈላጊው ሰውዬ ራሱ ብቅ ማለት አለ

t.me/OLDBOOKSPDF

በት ። ምናልባትም እንዲያመነታ ያደረገው ምክ ንያት ሊኖር ይችላል ። ስለዚህ ለእንደዚህ ያለ ጉዳይ ሳይሰለቹ ጊዜ መስጠቱ ነው የሚበጀው ። ባልታሰበበት ቀን ብቅ ሊል ይችላል ። እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች አዘውትረው ሲያጋጥሙ አይተ ፍል ” አለች ኤልሐም ።

ሳብር አባቱን ማግኘት የሚመኘውን ያህል ፡ የአባትዬው ልጅን ማግኘት የሚፈይድለት እንዳ ችም ነገር እንደሌለ ኤልሐም አሳጨነችም ።ሳብር አባቱን ለማግኘት ሌላ ተቀን የሚማስንበት ዋናው ምክንያት ፡ ለወደፊት ኑሮው አለኝታ እንዲሆነው ብቻ ሳይሆን ፡ ካለፈው ወራዳ ሕይወ ቱም እንዲገላግለው ጭምር ነው ። የያዘው ገን ዘብ ቢያልቅበት ወዴት መድረስ ይችላል ? ማንስ አሰሁልህ ይለዋል ? አባቱን የመፈለግ ጥረቱን እን ዲገፋበት አቅም የሚሰጠውም ወደ ቀድሞው የዋልጌነትና የወንጀለኝነት ኑሮው የመመለሱ ፍራቻው ነው ። አባቱን መፈለጉን እርግፍ አድ ርጎ መተው ደግሞ ወንጀል የመፈጸም ድርጊቱን መልሶ እንደሚያድሰው ያውቃል ።

ይሀን የመሰለውን አስፈሪ ሐሳብ አውጥቶ ከወረደ በኋላ ፡ “ እሱቲ እንዳላችሁት ይሁን ፤ መቼስ ምን አደርጋለሁ ። ማስታወቂያው እንደጎና ይታደለልኝ ” አለ ሳብር ።

ሳብር የሚያዘወትረው ምግብ ቤት ውስጥ ተቀምጠ ኤልሐምን ይጠብቅ ጀመር ። ዕለታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዊው ግንኙነታቸው በናፍቆት የሚጠባበቀውና በከበሬታ የሚያስተናግደው ሥነ ሥርዓት ከሆነ ሰንብቷል ። ሳብር ቀን ቀን ከኤልሐም ጋር በእርጋታ ቁም ነገር በመጨዋወት ጊዜው ያልፍለታል ። ሌሊት ሌሊት ደግሞ በክረማ የጭቅር እሳት ሲነድ ያድራል ። ሊነጋጋ ሲል ኤልሐም እንደገና በሐሳቡ ውስጥ ድቅን ትልበታለች ። የሳብር ልብ ይሀን በመሰለ ሁሰት ተጸራሪ ዋልታዎች መካከል ይዋልላል ፤ ይዋዥቃል ፤ እንዴ በሌላው ላይ ሊያይል ባለመቻሉ ሐሳቡ ግራ ቀኝ ይዋከባል ።

ሳብር ፡ ሁለቱን ሴቶች ሊቀርባቸውም ሊርቃቸውም ልቡ እየከጀለ የሐሳቡ ሚጠር ውሉ እየ ጠፋው ይሾገራል ። ሁለቱም እርሱን መጥረው የሚይዙበት የተለየ ኃይል እንዳላቸው እያወቀ ፡ ክብሩን ላለማስደፈር ይፍጨረጨራል ። በሌላ በኩል ደግሞ ፡ ሁለቱንም ጨርሶ ሊተዋቸው ያስ ብና አቅም ያንሰዋል ። ምርጫው በየዕለቱ ከፊቱ ይጋረጣል ። ኤልሐም ደመና ያልጋረደው የጠራ ሰማይ አምሳል ስትሆን ፡ ከሪማ ዶፋን እንደሚያ መርደው ፡ ነጭድጓዳማ ጥቁር ስማይ ናት — ልክ እንደ እስክንድርያው ሰማይ ። ያኔ በዘያች ተወ ልዶ ባደገባትና በሚወዳት ከተማ ፡ ደመና በጋረ ደው በእስክንድርያ ሰማይ ሥር ስሜቱን ከሚያ ግሉት ፡ መንፈሱን ከሚያረክት ቆንጆድት ጋር ዓለመኑን ሲቀጭ ያሳለፈው ጊዜ ከፊቱ ድቅን ይልበታል ። ከሪማ የአገሩ ልጅ መሆንዋን ለምን

t.me/OLDBOOKSPDF

ይሆን የምትከደውን ባያት ቍጥር እነዚያን የፍስ ሐና የፈንጠዚያ ምሽቶች ፣ እነዚያን በፍቅር ከንፍ ወደ ሰባተኛው ሰማይ የመጠቀባቸውን ጊዜያት ሳታስታውሰው አታልፍም ። ከሪማ እንደ እሱው ደመ—ፍል ናት ። በአንፃሩ ደግሞ ፥ ኤልሐም ቢን ጠራሩ የማትደረስ ጭምት እመቤት ናት ።

ለምን ዝም እንዳለ ስለ ጠየቀችው ፥ "ይኸ ፍለጋዬ ዶሎ ብሎ ቍርጡ ቢታወቅ ፥ እዚህ ከተማ አንድ ቀንም አላድርም" አላት ።

አቀርቅራ መሬት መሬቱን እያየች ፥ "መቼ እንደምትሄድ ወስነሃል ማለት ነው?" አለችው ።

"ሳስበው ደግሞ ካይሮን የመሰለች ከተማ ትኖ መሄዱ ይጨንቀኛል ።"

"ከሚጨንቅህ ለምን ዝም ብለህ እዚሁ አት ኖርም?" አለችው ፥ ትኩር ብላ እየተመለከተችው ።

"ቢሆንልኝማ በማን ዕድሌ!" አላት ።

"የምታስበው ቢሆንልህ ፥ ቤተሰብህንና ሥራህን ትተህ እዚሁ መኖር ትችላለህ?"

"አይ ፣ ለእሱ እንኳን መንገድ አላጣለትም" አላት ። ጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ካሳለፉ በኋላ ፥ "ነገሩን በጥሞና ሳስበው ፥ ወደዚህ የመጣሁት ሰይድ ኤል ራሕሚን ለመፈለግ ብቻ ሳይሆን ፥ እግዚር አንቺን አግኝ ብሎኝ ነው ። እንዳንዴ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለማግኘት የምንሯሯጥለት ነገር ቀርቶ ፡ ማግኘት የሚገባንን ነገር የማግኘት ዕድል ያጋጥመናል ።"

የኤልሐም ገጽ የርኅራኄና የፈገግታ ጸዳል ለበሰ ። ፈርጠም ብላ ፡ "እንዲህ ከሆነማ ፡ የሰይድ ኤል ራሕሚ ውለታ አለብኝ ማለት ነው!" አለችው።

የሳብር የይሉኝታ ግድብ ተናደ ። "ኤልሐም እወድሻለሁ! ከተግናኘንበት ቀን ጀምሮ ላንቺ የሚሰማኝ ፍቅር በልቤ ውስጥ ሥር እየሰደደ ነው የሄደው ። አንቺ የሕይወቴ አለኝታ ፡ የኑሮዬ መነሻና መድረሻ ነሽ ። እንዲህ ያለ ስሜት ከዚህ በፊት ሞክሮኝ አያውቅም ። እመኚኝ ኤልሐም! ከአንደበቴ የሚወጣው እያንዳንዱ ቃል ከውስጤ የፈለቀ ፡ ከንጁቴ የመነጨ ነው ።"

ከንፈሮችዋ ሲርገበገቡ ታየው ።

"አንቺም እንደ እኔ ይሰማሽ ይሆን?" አላት ፡ ከዝምታዋ ሊቀሰቅሳት በማሰብ ።

"ይሰማኛል ፤ የበለጠ ነው የሚሰማኝ" አለችው — በርጋታ ።

ሳብር እጇን እጁዋ ላይ ሜን አድርጎ ይዳስሳት ፡ ያሻሻት ጀመር ። ደስታው ከልቡ አልፎ ራሱ ላይ ወጣ ፤ ውስጣዊ ስሜቱ መፈንጠዝና መጨፈር ያዘ ። ብዙም ሳይቆይ ከከሪማ ጋር የሚያሳልፈው አዳር ታወሰው ። ሰውነቱ ልውጥውጥ አለበት ። ብዙ ሴቶችን መውደድ ለሳብር አዲስ ነገር አይደለም ። የአሁኑ ግን መላው የጠፋበት ነገር

t.me/OLDBOOKSPDF

ሆኖበታል ። ምክንያቱም ፡ ከከሪማ ጋር ሲያድር ኤልሓም በሕልሙም በውኑም ከፊቱ ድቅን ትልበታለች ፤ ከኤልሓም ጋር ሲውል ፡ ከሪማ የት ዝታ አዚሟን ታዞርበታለች። ሁለቱ አንድ አካል፡ አንድ አምሳል ፡ አንድ ነፍስ ቢኖራቸው እንዴት ደስ ባለው!

"ከዚህ ቀደም ፍቅር ይሆሽ ያውቃል?"

"ፈጽሞ! ሞክሮኝም አያውቅ ። በልጅነቱ እንዲሁ የጨዋታ ያህል 'መደድኩሽ መደድኩሀ' መባባላችን ትዝ ይለኛል ። ካደግኩም በኋላ ከአንድ የሬልም ጥዋፍይ ጋር መቀራረብ ሞክሮኝ ነበር ። ብዙም አብረን ሳንቆይ ሰውዬው ሞተ ። እውነቴን ነው ሳብር ፤ ከዚህ ቀደም ፍቅር የሚለት ነገር የምር ይሆኝ አያውቅም ። ቆየት ብሎ ደግሞ ፡ ከአንድ ሰውዬ ጋር ተጫጭተን ነበር ። ሥራሽን መተው አልብሽ እያለ ስለ ጨቅጨቀኝ እርግፍ አድርጌ ተውኩት ። በምሠራበት አካባቢም አንዳንድ ሰዎች እጃቸው ውስጥ ሊያ ስገቡኝ መሞከራቸው አልቀረም ። ታሪኩ ረጅም ስለ ሆነ ስለ እሱ ወደፊት በሰፊው አጫወትሃለሁ ፤ ብድግ ብለህ እብስ ካሳልክ ወይም ደግሞ በካይሮ ያሳለፍከውን ጊዜ ከሐሳብህ አውልቀህ ካልጣልክ. . ."

"የሄድኩበት ብሄድ ፡ የደረስኩብት ብደርስ ካይሮን አልረሳትም" አላት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዲህ በማለትህ በጣም ደስ ይለኛል። እስቲ ስለ ፍቅር የምታውቀውን አጫውተኝ።"

"ፍቅር እንዲህ ያደርጋል የሚል ግምት በውኔ ቀርቶ በሕልሜም አልነበረኝ" አላት።

"በመጠኑም ቢሆን ስለ ሕይወት አንዳንድ ነገሮችን አውቃለሁ። ሳስበው ጥሩ ሰው ትመስ ለኛለህ" አለችው።

የመገረም ስሜቱ እንዳይታወቅበት እየታገለ፡ "አልገባኝም፤ ምን ማለትሽ ነው?"

"እኔ እንጃ፤ በውስጤ የሚሰማኝን ነው የገለጽኩት፤ ምን ማለትሽ ነው ብለህ አታስቸግረኝ። እንዲያው ብቻ. . . እንተኑትህ. . .ዓይነ—ውኃህ. . . ምን ብዬ ላስረዳህ. . .ልበ መሉነትህ አዘንም አለው" አለችው።

—እረ ጉዴ ፈላ፤ እኒህ ወብት የተላበሱ ማራኪ ዓይኖችሽ አንድ ነገር ከልሎአቸዋል ማለት ነው? እኔ አሁን ጥሩ መባል የሚገባኝ ሰው ነኝ? ያ ሁሉ ጉዴ ወዴት ደረሰ? በሕይወቴ የፊጸም ኳቸው እኩይ ተግባራት ሁሉ አሻራቸው ጠፍ ቷል ማለት ነው? እረ እባክህ አባቴ፤ አለሁ በለኝና ከዚህ ጉድ አውጣኝ! — በማለት ሳብር ከሐሳቡ ጋር መሟገት ያዘ።

"ራሴን ማመስገን አይሁንብኝና ላንቺ ያለኝ ፍቅር፡ ስለ ራሴ ካለኝ ግምት የተለየ በሆነ መንገድ፡ ከወጪ ለሚያየኝ ጥሩ ሰው መሆኔን አረጋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ግወልኛል” አላት ፡ የተናገረውን ማመንም አለ ማመንም እያዳገተው ።

“ጥሩ ሰው ለመሆንህ ምንም የሌላ ሰው ማረጋገጫ አያሻም ። የጠፋውን ወንድምህን ለማ ግኘት ያለ መታከት የምታሳየው ጥረት ራሱ በቂ ምስክር ነው ። ለመሆኑ ወንድምህን ታውቀው ነበር?” አለችው ፡ ሰው አማኟ ኤልሐም ።

“በዝና እንጂ በአካል አላውቀውም ።”

“በአካል የማታውቀውን ወንድምህን ልክ እንደምታውቀው ያህል ሌት ተቀን ትፈልገዋ ለህ ። ለአንተ ጥሩ ሰውነት ማስረጃ ከተፈለገ ይኸው ብቻ አይበቃኝም?”

—እሬ ጉዴ ግና ነው ፤ ስንቱን ነው ስዋሽላት የሰነበትኩት! ኤልሐም ፡ የምትናገሪው ሁሉ ከእኔ ነቴ ጋር አይገጥምም! — እያለ በሐሳቡ ውስጥ አውጠነጠነ ።

“መፈለጉን እንኳን እንደ ማንኛውም ሥራ ፈልግ ተብዬ ስለ ታዘዝክ ነው በመፈለግ ላይ ያለህት” አላት ።

“እንዲህ ማለት አትችልም ። ወንድምህን ብታገኘውም ባታገኘውም ላንተ ጠብ የሚልልህ አንዳችም ነገር አለመኖሩ ብቻ ፡ እንዴት ያለ ኸው ትልቅ ሰው እንደ ሆንክ ያረጋግጣል ።”

ከሪማና ሳብር በሕይወት ጉድፍ ሲበከሉ ኖረዋል ። ከዚህም የተነሣ በሩቅም በቅርብም ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

በሐሳብም በተግባርም መግባት ይችላል ። የግብረ ሥጋ ክንዋኔአቸው በሚጠዘበት ጊዜ እንኳን ከሪማ ፡ "የጭቅራችን እንቅፋት መቼ ነው የሚወገደው?" ብላ ከመጠየቅ ወደ ኋላ አትልም ። ጭልምልም ባለው የሆቴል ክፍሉ ውስጥ ሆኖ ብርታትዋንና ድፍረትዋን ሲያስበው እንደ በግ ነድታ እወንጀል አዘቅት ትጨምረኛለች የሚል ፍርሐት ይሰማዋል ።

ሳብር ፡ ለሴት ብሎ የሰው ነፍስ ያጠፋል የሚል ግምት ከሪማ እምብዛም የላትም ። ከሪማ አልመሰል አሳት እንጂ ይህን የመሰለው የወንጀል ድርጊት ለሳብር አዲስ ነገር አይደለም ። ከዚህ ቀደምም ቢሆን በሴት ምክንያት የሰው ነፍስ በእጁ አልፏል ። ወንጀልን ዓይኑን ሳያሽ መፈጸም ከእናቱ የተላለፈለት ውርስ ነው ። ባሲማ አምራን ለዚያ ሁሉ ውድቀት የበቃችው ፡ ከሕግ በላይ ነኝ በሚል ድፍረትዋ ከባድ ወንጀል ውስጥ እየገባች በመዘፈቅዋ አልነበረም?

—ኤልሐም ፡ ያፈቀርሽው እኮ የወጣለትን ወንጀለኛ ነው ። ውሸት እያወራሁልሽስ መኖር የምችለው እስከ መቼ ድረስ ነው? ግደል ፡ ግደል አሰኘህ አይደለም ፡ ሳብር? መግደል እኮ ላንተ አዲስ ነገር አይደለም ። የሚበጅህ እውነቱን ፍርጥርጥ አድርጎ ማውጣቱ ነው ። መናጢ ደሃ መሆንህን ፡ ኤል ራሕሚም አባትህ እንጂ ወንድ ም ህ አለመሆኑን ተናዘዝ ። ቀን ተሌት አባትህን

t.me/OLDBOOKSPDF

የምትፈልገውም ከድህነት እንዲገላግልህ መሆኑን አትደብቅ ። ያለፈውን በውንጀል የተበከለ ሕይወትህን ይፋ አውጣው ። ጉድህን ስትሰማ ኤልሐም እሪ ብሳ መጮህዋ ፡ በሥቃይና በፍራቻ መሸማቀቋ አይቀርም ። እናትህ ደህና አድርጋ አሳድጋህ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ወፍራም እንጀራ የሚበላ አቃጣሪ እንኳን ይወጣህ ነበር ። ዳሩ ምን ይሆናል ፤ እናትህ ለዚህ ሙያ እንኳን አላበቃችህም ፤ በተለባበሰ ሕይወት ዓይንህ ታውሮ እስካሁን ቆይተሃል ። እናትህ መሞቻዋ መቃረቡን ስታውቅ የአባትህን መኖር ልብህ ውስጥ በመለኰስ አትምህን አውቀህ አርፈህ እንዳትቀመጥ አድርጋሃለች. . .

"እናቴ እንድ ዓይነት የንግድ ሥራ ካይሮ ውስጥ መጀመር እንደምትችል ደጋግማ ነግራኛለች ። በነገራችን ላይ ፡ እናቴ ስለ አንተ ብዙ ነገር ታውቃለች" አለችው ኤልሐም ፡ በሐሳቡ ከባዘነበት በመመለስ ።

—እናቴ!— ሳብር እናቶችን ከሩቁ ነው የሚፈራቸው ። እናቶች እውነቷን የማውጣጣት ችሎታ አላቸው ። በሣቅ በፈገግታ አይደለሉም ።

"ምን ዓይነት የንግድ ሥራ?" አላት ሳብር ።

"የሚያዋጣህን ነዋ!"

—እስከ ዛሬ ያዋጣኝ ፤ በየመሸታ ቤቱ ዘው እያልኩ መጠጣት ፤ ከማንም ጋለሞታ ጋር ዳንኪራ

t.me/OLDBOOKSPDF

መርገጥ ፤ በየደረስኩበት ጸበ እየፈጠርኩ መደባ ደብ ፤ ካገኘኋት ጋር መጋደም ነው — አለ ሳብር በሐሳቡ ።

"የሚያዋጣኝ ርስትና ንብረት ማስተዳደር ነው" አላት ።

"ስለ ትምህርት ደረጃህ አልነገርከኝም እኮ።"

በትምህርት ገበታ ላይ ለስሙ ያሳለፈው አጭር ጊዜ ትዝ አለው ። የአረብኛና የውጭ አገር ትምህርት ቄነጸጽሏል ።

አባቴ ትምህርቴን እንዳጠናቅቅ አላደረገኝም ። ከታመመም በኋላ ትምህርቴን አቋርጨ እረዳው ነበር ።"

"እስቲ የሚስማማህ አንድ የንግድ ሥራ ካለ አስብበትና ከሚረዱህ ወዳጅቼ ጋር አገናኝሃለሁ።"

"መልካም ነው ፤ በመጀመሪያ ግን ከአባቴ ጋር መመካከር አለብኝ ።"

ሁለቱም ለመሄድ ከተቀመጡበት ተነሡ ።

—ኤልሐም ፤ እንዲያው አንድ ጊዜ ብቻ ሳም ባደረግኩሽ ፤ ምን ይሆናል ፤ እዚህ ደግሞ አይመኝም—አለ ሳብር በሐሳቡ ።

በሌላ ወገን ደግሞ ሐሳቡ በውስጡ ይሸፍ ትበታል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

—ኤልሐምን እርግፍ አድርገህ ብትተዋት ይሻልሃል ። ፈጽሞ አታዋጣህም ። ኤልሐም ልክ እንደ አባትህ ናት ። ብዙ ተስፋ ፡ ጽኑ እለ ኝታ ታይባታለህ ። ኤልሐም ጉም ናት ። ልትይዛት ልትጨብጣት አትችልም ። ከሪማም የእናትህ አምሳያ ናት ። ከእርሷም የሚተርፍህ ነገር ቢኖር ወሲባዊ እርካታና ወንጀል ነው ። የሚሻልህ ወደ እስክንድርያ መመለሱ ነው ። በምታውቀው አካባቢ ፡ በምታውቃቸው ጠላቶችህ መካከል አፋሽ አጐንባሽ ሆነህ መኖሩ ይበጅሃል ። ካልሆ ነም የምትገድለውን ግደል. . . ከሪማን አፋጣት ፤ ገንዘቧን ዝረፍ ። ኤል ራሕሚን ከተደበቀበት ጨለማ ውስጥ መንጥቀህ አውጣው ። ኤልሐምን አግባ ። የካይሮን ክረምት አትችለውም ። ካይሮ የሰው መርመስመሻ ፡ የሰው መናኸሪያ ፡ የሰው ልጅች ገበያ ናት ። ይህን በመሰለ ስፍራ አባቴን ፈልጌ አገኛለሁ እያልክ ስምን በከንቱ ትደክማለህ! ተወልደህ ባደግህበት ክተማ ፡ በምታውቀው አካባቢ አጭበርብረህም ሆነ አወናብደህ የፈለክትን ሴት መርጠህ ያለ ሐሳብ በደስታ መኖር ትችላለህ ። ይህን ሁሉ እርግፍ አድርገህ ትተህ ኤል ራሕሚን ፍለጋ መረጥክ ። ኤል ራሕሚ ፡ ‘እኔን የሚመስል ሰው እግርሽ እስኪቀጥን ብት ሂጂ አታገኚም’ በማለት እናትህን ያታለለ አፈ ጮሌ እንዳልሆነ በምን ታውቃለህ? በካይሮ አውራ ጐዳናዎች እላይ እታች እያልክ ስትባዝን አባትህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሺህ ጊዜ እያየ አልፎህ ይሆናል ። ልጅነትህን አይፈልግ እንደሆንስ? ወይም ደግሞ ፈርቶህ አድጭ እንደሆንስ? ሞቶ እንደሆንስ? ማን ያውቃል ? ለማንኛውም የካይሮ ክረምት መግቢያው እየተቃረበ ስለሆነ ነገ ዛሬ እያልክ ስታመነታ ችግር ማጥ ውስጥ ገብተህ እንዳትዘፈቅ. . .

የሆቴሉ በር ጠባቂ ፡ መሐመድ አል ሳዊ ፡ እንድ የታወቀ ጠንቂይ መኖሩን ነግሮት ፡ እርሱን ሄዶ እንዲጠይቅ ምክር በለገሰው መሠረት ፡ ሳብር ጠንቋዩን ፍለጋ ሄደ ። አድራሻውን አግኝቶ የጠንቂዩን መኖር አለመኖር ቢጠይቅ ፡ በአጭበር ባሪነት ተከሶ ወህኒ መውረዱ ተነገረው ። ለመሆኑ አጭበርባሪነት የሚያስከስስ ወንጀል የሆነው ከመቼ ወዲህ ነው? ሳብር ፡ የሚያደርገው ቢጨን ቀው ሆቴሉ ውስጥ ክትት ብሎ መዋል ያዘ ። የሆቴሉ የእንግዶች ማረፊያ ክፍልም እንደ ተለመደው በሰዎች ጭውውትና በሲጋራ ጭስ ተሞልቷል ። የእንግዶቹ መልክ በየዕለቱ ቢለዋወጥም የጭውውት ርዕሳቸው እምብዛም አይቀየርም ።

ከእንግዶቹ አንዱ ፡ "ነገሩ እንዲህ ከሆነማ ፡ የዓለም ፍጻሜ ደረሰ ማለት ነዋ!" ሲል ሳብር ሰማው ።

"ለእኔ ብላ ፡ ዓለም ለምን ገደል አትገባም!" አለ ሌላው ሰውዬ ።

ሣቅ ፡ ወካታና የሲጋራ ጭስ ክፍሉን ሞላው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከእንግዶቹ ሌላው ፡ "ለመሆኑ አንተ የምትደግፈው ምሥራቁን ነው ወይስ ምዕራቡን ዓለም?" የሚል ጥያቄ ሰነዘረ ።

"እኔ ሁለቱንም አልደግፍም" የሚል ከንቱ በላይ የሆነ መልስ ተሰጠው ።

ጠያቂው የሕይወት ውጣ ውረድ የመረረው ይመስል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ዘጠኝ

በተለመደው ሰዓት ከሪማ ሳትመጣ ዘገየች። ሳብር አልጋው ላይ ተጋድሞ ካሁን አሁን መጣች በማለት ልቡ በጉጉት ተሰቅሏል ። ነገር ግን ከሪማ ብቅ ሳትል አከለ ሌሊት አለፈ ። ሁኔታው የተለመደ አልነበረም ። ምክንያቱም ሳብርና ከሪማ በቅርብ ከተዋወቁበት ዕለት ጀምሮ ከጐኑ ተለይታ ያደረችበት ጊዜ አልነበረም ። ሳብር ሌሊቱን አሥሬ እየባነነ ሲጠብቃት በያድርም ከሪማ የውኃ ሽታ ሆናለች ። ነህ ሊቀድ ሲል የመአዚኑ የስግደት ጥሪ ጨርሶ መቅረትሞን አበሠረለት ። ቁርጡን ካወቀ በኋላ ጥቂት ሰዓታት ተኝቶ ከቀኑ አራት ሰዓት ላይ ተነሣ ።

ሳብር በሆቴሉ እንግዳ ማረፊያ ክፍል ውስጥ ቁርሱን በመመገብ ላይ ሳለ ከሊልና የሆቴሉ በር ጠባቂ መሐመድ አል ሳዊ የሞቀ ጨዋታ ይዘው አየ ። ፊቱ ቅጭም አለ ። የእርሱ ፍላጐት ጠዋት ከመኝታው ሲነሣ ከሊልን ከቦታው ማጣት ነበር ። ከሊል ግን ለጉድ የገለተው ሆኖ አስቸግሮታል ። ከሪማ ማታ የቀረችበትን ምክንያት በምን ዘዴ መጠየቅ እንደሚችል ሲያሰላስል ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሆቴሉ እንግዶች ሁለቱ በአንድ ጉዳይ ላይ በከረረ ሁኔታ ሲከራከሩ ሰማችው ። ክርክሩ እየቆየ ወደ ዘለፋና ዛቻ ተሣወረ ። ሳብር ነገሩ አላምርህ ስላለው ከሆቴሉ ወጥቶ ሄደ ።

ምሳ ላይ ኤልሐምን ፊትዋ ቅጭም ብሎ አገኛት ። ሳብር ኤልሐምን ሲያገኝ ሰውነቱን ቀለል ይለዋል ። "ከሚያጋጥመኝ ነገሮች መካከል ፍሬ አለው የምለው ከአንቺ ጋር በየዕለቱ መገናኘቴን ብቻ ነው" አላት ፡ ፊቱ በደስታ እየፈካ ።

"እኔንም አላስቆም አላስቀምጥ ያለኝ የሁለታችን ጉዳይ ነው" አለችው ኤልሐም ፡ ለሰው አሳቢነት በግልጽ በተሣሉባቸው ዓይኖችዋ ትኩር ብላ እያየችው ። ያለ ምንም ተንኰል ፡ በገራምነትዋ ብቻ ልትማርከው ጥረት በማድረግዋ ልቡ ተነካ ። ለከረማ ፍላጐት እየተሸነፈ ኤልሐምን ተወት ማድረጉም ቈጨው ።

"ስለ ሁለታችን ጉዳይ ማሰብሽ ደስ አሰኝ ቶኛል ። እኔንም የሚያሳስበኝ ሌላ ነገር የለም" አላት ።

"እንግዲያው እስቲ ሐሳብህን ንገረኝ" አለችው ፡ እየተሸኰረመመች ።

"የሰሞኑ ሐሳቤ ሥራና ትዳር መያዝ ነው ።"

"ምክሬን ሰምተሽኛል ማለት ነዋ?"

"አዎን ሰምቻለሁ ። መጀመሪያ ግን እዚህ የመጣሁበትን ጉዳይ ቀርጠን ማወቅ አለብኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚያም ወደ እስክንድርያ ተመልሼ ከአባቴ ጋር መመካከር ይኖርብኛል ።”

ውሸት በመናገሩ ሕሊናውን ሐፍረት ይሞር ደው ጀመር ። — እውነቱን ዝርክርክ አድርገህ ንገራትና የመጣው ይምጣ — የሚል ድምፅ ደግሞ በልቡ ውስጥ ያንቃጭላል ። ሳብር ይህን በመስ ለው የሐሳብ ግጭት ውስጥ ገብቶ መሠቃየት ከጀመረ ሰንብቷል ።

“እስቲ ሲኒማ ቤት እንግባ” አላት ። መሳ ቅጡ ቢጠፋው ።

ሲኒማ ቤት ገብተው እጅ ለእጅ ተያይዘው ተቀመጡ ። ስፍራው ጨለምለም ያለ ቢሆንም ፣ ሳብርን እርጋታ ስለ ተሰማው እጅዋን በክንፈ ሮቹ ይደባብስ ጀመር ። ኤልሐም የተቀባችው ሽቶ መዓዛ ከአፍንጫው አልፎ የሠራ አካላቱን በፍ ላጐት ወጣጠረው ። ወዲያው ደግሞ ምሽት ላይ የሚጠብቀው እንግልት ትዝ አለው ። — ከሪማ የምታሳየው አበሳ ። ሐሳቡን ከአዕምሮው ለመፋቅ ቢታገል አልሆንልህ አለው ።

“ምን ዓይነት ጭካኔ ነው!” በማለት ኤል ሐም አንሾካሾኩት — ፊልሙ ላይ ያየችው ድርጊት ስላሳዘናት ። ሳብር ፊልሙን አልተከታተለም ። ለሰነዘረችው ቃል መልስ ለመስጠት በማለት ብቻ ፣ “ጭካኔውስ ፣ ለአንዲት ቅጽበትም ቢሆን ከአንቺ መለየቱ ነው” አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚህ በኋላ ሳብር ፊልሙን መክታተል ያዘ። ፊልሙ፡ አንድ ሰውዬ አንዲት ልጅ ሲያገሳቁል ያሳያል። በልጅቱና በሰውዬው መካከል የሚካሄደው የቃላት ምልልስ እጅ አግር የሌለውና ትር ጉም የለሽ ሆነበት። የሰዎች ሕይወት ክሩቅ ሲያዩት መላቢስነቱ ገልጾ እንደሚታይ፡ የሁሉቱ ቀዋንያንም ግንኙነት መላ ቅጡ የጠፋ ሆኖ አገ ኘው። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች መሣቅ ሲገባቸው እየዬ ይላሉ፤ ማልቀስ ሲገባቸው ደግሞ ሲንኮተኩቱ ይታያሉ። ውሉ የጠፋበት ሕይወት። ሳብር፡ በዚህ ሁሉ መሐል የራሱ ሁኔታ ታወሰው። መቼም አባቱን ፍለጋ እየደጋገመ በጋዜጣ የሚያወጣውን ማስታወቂያ ያነበበ ሰው በሁኔታው መገረሙ አይቀርም። ልጅ አባቱን ክምር ሲፈልግ፡ አባት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ማድፈጡ ለሰሚ ግራ የሚ ያጋባ ነገር ነው። የሳብር ሐሳብ ወደ ሌላ አቅ ጣጫ ነጐደ። — ዛሬ ምሽት ከሪማ ትመጣ ይሆን? እንደ ልማድዋ አሳፈን ስታስቄጥረኝ ታድር ይሆን? —ከሐሳቡ መለስ በማለት ዞር ብሎ ኤልሐምን ተመለከታት። ፊልሙን በጥሞና ትከታተላለች። እጇን ከእጅዋ ቀስ ብሎ ለማላቀቅ ሲሞክር ጥብቅ አድርጋ ያዘችው።

ተያይዘው ወደ አውቶቡስ መሳፈሪያው ስፍራ አመሩ። ኤልሐም አውቶቡሱ ላይ ተጋብታ ስት ሂድ ሳብር ተሽከርካሪው ከዓይኑ እስኪሠወር ድረስ ቆሞ ሸኛት። ከዚያም ሆቴሉ አቅራቢያ ከሚገኘው በና ቤት ገራ ብሎ የሚቀመስ ነገር

t.me/OLDBOOKSPDF

በማዘዝ ፡ በብራንዲ ያወራርደው ጀመር ። መንፈቅ ሌሊት ሳይ ወደ ክፍሉ ገብቶ የተለመደ ጥበቃ ውን ተያያዘው ። ሌሊቱ እየተገባደደ ሲሄድ ከዚህ ቀደም ተሰምቶት የማያውቅ ወርደት ሰው ነቱን ወረረው ። በፍላጎት የተወጠረ ፍራቻ ፤ ውጪት አልባ የሆነ ፍሰጋና ጥበቃ ፍራቻ ፤ ፍራቻን የመፍራት ፍራቻ ሰንን ያዘው ። ሌሊቱ እያ ዘገመ አለፈ ፤ ከሪማ ብቅም አላለች!

በማግሥቱ ከሰዓት በኋላ ፡ ልክ መጀመሪያ ቀን እንዳየት ከሪማን ባልዋ አጠገብ ተቀምጣ አገኛት ። የሆቴሉ እንግዶች ማረፊያ ክፍል ውስጥ ተቀምጠ ወደ እርስዋ የሚያቀናውን እይታ ትኩረት አልሰጠችውም ። — የፍላጐቱን ጽናት ከምኔው ዘነጋችው? እንዲያ ልቤን ስታጠፋው የሰነበተችው ለዚሁ ነው ? — አለ ሳብር በሐሳቡ ። ወዲያው ከሪማ ከተቀመጠችበት ተነሥታ ወደ ፎቅ አመ ራች ። ዓይን ለዓይን ግጥምጥም አሉ ። አስተያየቷ ሳብርን ግራ አጋባው ። ከሊል እንደሆን በጠባዩም በሁኔታው ምንም የተለየ ነገር አልታየበትም ። አንድ ነገር ቢኖር ይታወቅበት ነበር ። ሳብር ከሪ ማን መከተል ዳዳው ። እርስዋ እንደሚከተሳት የጠረጠረች ይመስል አረማመድዋን አፋጥና ከዓ ይነ ተሠወረች ።

ሳብር ግንዘቡ እየመነመነበት ነው ። የአባቱ ፍለጋም ትርጉም የለሽ ልፋት ከመሆን ፈቀቅ አላለም ። ቀን ቀን አባቱን ሲፈልግ ይውላል ፤

t.me/OLDBOOKSPDF

ሌሊት ሌሊት ክሪማን ሲጠብቅ ያድራል ። ሲነ ጋለት ፡ የተቻለውን ይመገባል ፤ ሞቅ እስኪለው ይጠጣል ። እኩለ ሌሊት ደርሶ ክሪማን መጠበቅ መጀመር ይናፍቀዋል ። የጨለማ ውስጥ ጥበቃ. . . ድቅድቅ ባለ ጨለማ ውስጥ ተቀምጠ መጣች አልመጣች እያሉ መጓጓት ።

"አንድ ሰው ስልክ ደውሎልህ ነበር" አለ የሆቴሉ በር ጠባቂ ፡ ሳብር ሞቅ ብሎት ካመሸ በት ወደ ሆቴሉ ሊገባ ሲል ። ያ መከረኛ ቴሌ ፎን ። ሳብር እንደሆን በቴሌፎኑ ጥሪ ላይ ያሳደ ረው ተስፋ ከተሟጠጠ ሰንብቷል ። ግን ምን ይታ ወቃል፤ ቴሌፎኑም ተአምር ሊሠራ ይችል ይሆናል።

"እንዴት ሴት ናት የደወለችው" አለ የሆ ቴሉ በር ጠባቂ ፡ ሳብር ለመልእክቱ ቁም ነገር ያልሰጠው መሆኑን በመገንዘብ ።

"ስለ ጋዜጣው ማስታወቂያ ጉዳይ ይሆናል የደወለችው" አለ ሳብር ፡ በማፌሽኘት ።

"ማስታወቂያውን እንኳን አላነሣችም ። መኖር አለመኖርህን ነው የጠየቀችው ።"

ኤልሐም ... ባለራት ጥቂት ቀናት አልተያዩም። ከእንግዲህ ምን ማድረግ ይችላል. . .ዝም ብሎ ክፍሉ ገብቶ አልጋው ላይ ተዘረረ — የለመ ደው ጨለማ ውስጥ ። ጥቂት ቆየት ብሎ በሩ በቀስታ ተንኳኳ ። ሳብር ከአልጋው ላይ ተስፈን ጥሮ በመነሣት በሩን በርግዶ ። እጅዋን አፈፍ በማድረግ ወደ ውስጥ ጎትቶ አስገባት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"አንቺ!" አለ ሳብር ፡ መጮህ እየቃጣው ። ስሜቱን ፡ ፍላጐቱን መቆጣጠር እያቃተው ከሪማን ስቦ አልጋው ላይ አሳረፋት ። "አንቺ አዚመኛ ፤ አንቺ ሰይጣን!" አላት ።

"እረ እባክህ ፤ ሰውነቴን በጫጨቅከው!" አለችው ።

"አንቺስ ሥሮቼንና ጅማቶቼን ስትበጣጥሻቸው አይደል እንዴ የሰነበትሽው?"

"የእኔን ባየኸው ። ለመሆኑ ምንም ነገር ሳይሰማኝ የሰነበትኩ ይመስልሃል?"

ልብስዋን ከላይዋ ቀዳዶ ለመጣል ሲሞክር ታግላ አስጣለች ።

"እባክህ አትታገለኝ ። ሁኔታው አደገኛ ደረጃ ላይ ደርሷል ። ይልቅስ የምነግርህን ስማኝና ልመለስበት" አለችው ።

"ከአሁን ወዲያ ከእጄ የሚያወጣሽ ምንም ኃይል የለም!" በማለት ሳብር እጉመተመተ ።

"አሥራን አትወትውት ። በስካር መንፈስ የማይሆን ነገር እሠራለሁ ብለህ ነገሩን ሁሉ ታበላሸዋለህ ።"

ከተንጋለለችበት ገትዶ አስቀመጣትና ፡ "እንዲያው ለመሆኑ ምን ነካሽ?" ብሎ ጠየቃት ።

"ያን ዕለት እዚህ አድሬ ማለዳ ወደ መኖሪያችን ስመለስ ከሊልን ከእንቅልፉ ነቅቶ አገ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኘሁት ። አሥሩን ቁባጥሬ ከመኝታ ቤታችን የወ
ጣሁበትን ምክንያት አስረዳሁት ። ስመለስ አለ
ሰርያኩስም ሳያየኝ አልቀረም ። እሱ ካየኝ ጉዴ
ነው የሚወጣው በማለት ስርበተበት ነው የሰን
በትኩት ። እኔ እንጂ ፤ በጣም ፈርቻለሁ ።"

"ገም ብለሽ ነው የምትቃዢው!" አላት ።

"ምናልባት ቃሼቼ ይሆናል ፤ ምናልባትም
ቃሼቼ ላይሆን ይችላል ። ለማንኛውም ዓይናችን
እያየ ገደል መግባት የለብንም ። ካልተጠነቀቅን
መልፎን ነው የምወጣው ። ስናልመው የቆየ
ነው የወደፊት ሕይወታችን ፥ ፍቅራችንና ተስፋ
ችን ሁሉ ትቢያ ይለብሳል ማለት ነው ። ከከሊል
አፍ አንድ ቃል ከወጣ ነገሩ አለቀ ማለት ነው ።
ከዚያ በኋላ የሚጠብቀኝ መመለሻ የሌለው ድህ
ነትና ሥቃይ ነው ። ይሆንን መዘንጋት የለብህም ።"
ቁና ቁና ከተነፈሰች በኋላ ከሪማ ንግግሯን
ቀጠለች ፤ "ሰሞኑን መምጣት ያቋረጥኩት በዚሁ
ምክንያት ነው ። ሁኔታውን ቀደም ብዬ ልገልጽ
ልህ አላመቸኝም ። ስታጣኝ የተሠቃየኸውን ሥቃይ፥
እሬም በመቅረቴ በተሰማኝ ሥቃይ ሳልረዳው
የቀረሁ እንዳይመስልህ ። ከለሊል ያለ የሌለ ንብ
ረቱን ሁሉ የሰጠኝ ከእሱ ሌላ ወንድ እንዳልክ
ጅል ቃል አስገብቶኝ ነው ። ቀኝ እጄ ፥ የዓይኖቼ
ብሌን ፥ እንዲት ልጄ ፥ ግማሽ አካሌና ሁለመናዬ
ነሽ ነው የሚለኝ ። በዚህ በቀረው የሕይወቱ
አጭር ጊዜ ውስጥ በእኔ ላይ ለጣለብኝ እምነት
ብቁ ሆኜ መገኘት እንዳለብኝ ይሰማኛል ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ነገሩ እንዲህ ከሆነ ምን ማድረግ አለብን ማለት ነው?"

"እዚህ መምጣቱን ማቆም አለብኝ ።"

"ይሽማ እብደት ነው!" አለ ሳብር ፡ በማጉራራት ።

"የሚያዋጣው ይሽው ብቻ ነው ።"

"በዚህ ሁኔታ እስከ መቼ መቆየት እችላለሁ?"

"እኔ እንጃ" አለች ከሪማ ፡ በረጅሙ እየተነፈሰች ።

"ግንዘቤም ማለቁ ስለሆነ ተነሥቼ ወደ አገሬ መመለስ አለብኝ ማለት ነው" አላት ።

"እዚህ እስክ ቆየህ ድረስ የምችለውን ያህል ልረዳህ እሞክራለሁ ።"

"ግንዘብ ብቻ ሥቃዬን ሊያስታግሥልኝ አይችልም!"

"ታዲያ ምን አድርጊ ነው የምትለኝ ። እኔም እኮ ካንተ ያነሰ ሥቃይ አይደለም የሚሰማኝ ።"

"ማን እንደኔ! እኔ እኮ አንቺን ማጣቱም መናጢ ድሃ መሆኑም ዓይኑን እያፈጠጠብኝ ነው።"

"እኔን ዕረፍት የነሣኝ ፡ የራሴ ብቻ ሳይሆን የሁለታችንም ሥቃይ ነው ።"

"የሽማግሌው መሞት መቼ ይሆን?" በማለት ሳብር ራሱን በራሱ ጠየቀ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እሄ ምኑን አወቁ ፤ ጠንቋይ አይደለሁ" አለች ከሪማ ፡ የሳብርን ማጕመትመት በመስማትዋ።

"ታዲያ ምንድን ነሽ?"

"መያዣው መጨበጫው የጠፋብት መላ ቢስ ሴት ነኝ ። ታዘኔም እንቲ ከምታስበው የጸና ነው።"

"እኔንም አንቺንም ከሥቃያችን የሚገላግለን ሞት ነው ። አንድ ቀን ፍጣም ማለቱ አይቀርም ።"

"ምናልባት ።"

"ሰውዬው በቅዱታል እኮ ። ከዚህ ወዲያ ሰዘላለም አይኖር!"

"ዛሬ ሴሊት ወይም ደግሞ የዛሬ ሃያ ዓመት ሊሞት ይችላል ። ታላቅ እኅቱ የዛሬ ሁለት ዓመት ነው የሞተችው" በማለት ከሪማ በረጅሙ ተንፈሰች ።

ዶሮ እየደጋገመ ጮኸ ፤ ቀጥሎ ጎህ ይቀዳል ፤ ከዚያም መዌዚኑ አማኞች ለጸሎት እንዲማልዱ ድምፁን ያሰማቸዋል ።

"ከእንግዲህ የምናደርገው ምንም ነገር ያለ አይመስለኝም ፤ በል ልሂድበት" አለችው ።

"ካልሞተ አንገናኝም ማለት ነው?"

"ምንም ማድረግ አንችልም አልከህ እኮ!"

"እንችላለን እንጂ!" አለ ሳብር ፡ በመኰሳተር።

t.me/OLDBOOKSPDF

በሁለቱ መካከል የተፈጠረው ዝምታ እንደ መርማ የከበደ ነበር ።

ሳብር ፊቱን አኩሳትሮ ፡ "እኔና አንቺ እስካሁን የምንነጋገረው ሁሉ ሸላ በደፍን ነው ። አሁን ግን ማንኛውንም ነገር ፍርጥርጡን ማውጣት አለብን ። እቅጩን ማወቅ ከፈለግሽ ባልሽን መግደል አለብኝ!" አሳት ።

ከሪማ ሰውነቷ ተርበተበተ ፤ ድምፅዋም እንደ መዘጋት አለ ። "እንዲያው ለመሆኑ አሁን የተና ገርከውን ቃል ከልብ ታምንበታለህ? ስታስበው ሕሊና የሌለኝ ጨካኝ አረመኔ እመስልሃለሁ? አላወቅህልኝም እንጂ የእኔ ወንጀል ነፍሴ ጥፍት እስክትል አንተን መውደዴ ነው ። የሚያዋጣን ነገር ቢኖር ጸጥ ብሎ መጠበቁ ብቻ ነው ።"

"ሞት የረሳውን ሰው ተቀምጠ መጠበቁ ያዋጣል ነው የምትዪው?" አሳት ፡ ነገሯን በማን ቋሸሽ ።

"እግዜር እስከ ወሰነው ጊዜ ድረስ መጠበቅ ይኖርብናል ።"

ሳብር የሚያደርገውን ነገር ከእግዜር ቀድሞ ወስኗል ። የክረምቱ ሌሊት ቀዝቃዛ ቢሆንም እንኳን ፡ የሠራ አካላቱን ሙቀት ለቆበታል ። "ወንጀሉ ከተፈጸመ በኋላ ምንድን ነው የምናደርገው?" በማለት ሳብር ከሪማን በእርጋታ ጠየቃት ። መልስ አልሰጠችውም ። ጨለማው

t.me/OLDBOOKSPDF

ክፉኛ ይጫጫናል ። "ምን ዝም ያሰኝሻል!" በማለት ሳብር አፋጠጣት ። "ወንጀሉ ከተፈጸመ በኋላ ምንድን ነው የምናደርገው?"

ከሪማ መልስ ልትሰጠው እየፈለገች ከንፈሮችዋ ብቻ እየተርገበገቡ ጥቂት ጊዜ ክቆየች በኋላ : "ነገሩ እስኪረሳሳ ሳንገናኝ መቆየት አለብን ። ከዚያም በምስጢር መገናኘት እንጀምራለን። ነገሩ ከተረሳ በኋላ እኔንም ሀብቴንም ጠቅልለህ መያዝ ትችላለህ" አለችው ።

የቀኝ እጁን ቡጢ ጭብጥ አድርጎ : "ምንም ምርጫ የለንም ። ያተሸለ መፍትሔ መታጣቱ ነው ለዚህ ያበቃን!" : አላት እየተከሳተረ ።

"ነገሩ ያሳዝናል ፤ ግን ሌላ ምን ማድረግ ይቻላል!" አለችው ።

"እንዲህ ከሆነ ነገሩን እንዴት አድርገን እናቃነባብረዋለን?" አላት ።

ለጥያቄው መልስ የሰጠችው ምንም ሳታወላውል ነበር ።

"የሆቴሉን ክፍታ ገጠም ሕንፃ ደህና አድርገህ አጥናው ።"

—ለካስ ሁሉንም ነገር በቅድሚያ አቅዳ አጠናቃዋለች! ምንም አይደለም ። ስለ ወደደችኝ ነው ይህንን ሁሉ የምታደርገው — አለ ሳብር በሐሳቡ ።

"ከሆቴላችን ገጭ ያለው ሕንፃ የአሮጌ ልብሶች መሸጫ ነው ። ሌሊት ሰው አያድርበትም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የሀሰቱ ሕንፃዎች ጣሪያ የተያያዘ በመሆኑ ከአንዱ ወደ ሌላው ሕንፃ በቀላሉ መሸጋገር ይቻላል" አለች ከሪማ በሹክሹክታ ። "አንተም በጊዜ ከዚያኛው ሕንፃ ወደዚህኛው ተሻግረህ መኝታ ቤታችን ገብተህ ተደብቀህ ትጠብቀዋለህ ።"

"ወደ መኖሪያ ቤታችሁ የሚመጣው ከምሽቱ በሁለት ወይም በሦስት ሰዓት ላይ አይደለም?" አላት ።

"ነው ። ነገሩ እናቴን ለመጠየቅ በምሄድበት ጊዜ መከናወን አለበት ። በየወሩ ወደ እናቴ እሄዳለሁ ።"

"እዚህ ከመጣሁ ወር ሞልቶኛል ማለት አይ ነው ። ጊዜው እንዴት ይሮጣል!"

"የሚደረገውን ካደረግህ በኋላ ፡ በመጣህበት መንገድ ወደዚያኛው ሕንፃ ተሻግረህ ማንም ሳያይህ ከሕንፃው መውጣት ትችላለህ ።"

ፍርሐት አንደበቱን ያዘ እያደረገው ፡ "እንዲህ ያለው ወንጀል ሄዶ ሄዶ ቋጠሮው መፈታቱ አይቀርም!"

"መጨረሻ ላይ ቋጠሮው ስለማይፈታው ወንጀል የሚነግረን አላገኘንም" አለችው ፡ ሳታመነታ።

ከሪማና የሳብር እናት ካንድ ባሕር የተቀዱ ናቸው — ያሰበችን ከመፈጸም ወደ ኋላ የማይሉ— ጨካኞች ።

"የረሳነው ነገር ይኖር ይሆን?" አላት ።

"አምን አለ" አሰችው ። "ለወንጀሉ ማደነ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጋገሪያ እንዲሆን አንድ ዋጋ ያለው ነገር መስረቅ አለብህ ።"

"ምን የሚሰረቅ ነገር አለ?"

"እሱን ለእኔ ተወው ። አንተ ብቻ ምንም ዓይነት ፍንጭ ላለመተው በርቱ ጥንቃቄ ማድረግ አለብህ ።"

"እውነትሽን ነው ፤ መጠንቀቅ አለብኝ ።"

"ከዛሬ ጀምሮ የእኔና ያንተ ሕይወት አንድ ላይ ተቁራኝቷል ። ይህንን መዘንጋት የለብህም ። አንተ ላይ የሚደርስ ነገር እኔም ላይ ይደርሳል ማለት ነው ። የሚያዋጣን ሰምና ወርቅ መሆን ብቻ ነው ።"

ሜራቸው የማይታመን ቅዠት ስለ መሰለው እንቅልፍ እንዳልለቀቀው ሰው ጭንቅላቱን አርገ ፊገፊ ።

"ቅዠት . . . እብደት . . . ለመሆኑ የተነጋገር ነው የሚፈጸም ይመስልሻል?"

"ለማንኛውም የሕንፃውን መግቢያና መውጪያ ደህና አድርገህ አጥና ። ከዚያ ሕንፃ ስትወጣ ሰው እንዳያይህ ያስፈልጋል ። ከጥቂት ቀናት በኋላ እናቴን ለመጠየቅ እሄዳለሁ ። የተስማማን በትን ነገር ለመፈጸም ድፍረቱም ችሎታውም አለህ ። እስቲ እቅዳችንን አንድ ባንድ እንድገ መው" አለችው ።

በእሱይ ሐሳቡ ተውጦ የምትናገረውን አላዳመጣትም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥር

ሳብር ቁርሱን እንቀላል ፡ ፎርማጆ ፡ ፍራ ፍሬና አንድ ብርጭቆ ወተት ከተመገበ በኋላ ፡ የሆቴሉን እንግዶች ከእግር እስከ ራሳቸው ልብ እያለ ተመለከታቸው ። ሁለቱኛ የሚይገኙኑና ትኧቸው ወደ ደይን የሚወርድ ይመስል በዓይነ ሕሊናው አገላበጠ አስተዋላቸው ።

የቀኑ ብርሃን ለምሽቱ ጨለማ ቦታውን ሲለቅ ፡ ሳብር ልቡ ውስጥ አቅፎት የሰነበተው ወንጀል ሕይወት መዝራት ይይዛል ። ከሊልም እንደ ወትሮው ሁሉ ማለዳ ቱንሥዩ ከሆቴሉ እንግዳ መቀበያ ጠረጴዛ በስተጀርባ በመቀመጥ በሚንቀጠቀጡ እጆቹ የባሕር መዝገቡን ማገላ በጠን ፡ ገቢውንና ወጪውን መደመሩንና መቀነሱን ያለ አንዳች ሥጋት ይያያዘዋል ። ማን ያውቃል ፤ ዛሬ ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ የዚህ ዓለም ሕይወቱ ያበቃ ይሆናል ። ከሊል ዛሬም ቢሆን የዕለት ተግባሩን በማከናወን ላይ ያለው ገና ብዙ እኖራለሁ ብሎ በማሰብ እንጂ ፡ ሕይወቱ ድንገት መቀሰፉን እንደ ተረዳ ሰው በማድየለሽነትና ተስፋ በመቁረጥ አይደለም ። ከሊልን ከሥራው

t.me/OLDBOOKSPDF

ጋር ግንኙነት ያላት ትንሿ ነገር ከምር ታሳስበ ዋለች ። ምስኪን ከሊል ፤ የተደገሰለትን ምኑንም አያውቅም ። ደጋሹ ሳብር ግን በሆዱ እዩይ ሚራ ቋጥሯል ።

ቴሌፎኑ ድንገት ደወለ ። ሳብርም ከት ብሎ ሣቀ ። በዚች በመጨረሻዋ ሰዓት ስልክ የሚደውልለው አባቱ ይሆን?

የሆቴሉ በረኛ መሐመድ አል ሳዊ ስልኩን አንሥዱ ፡ "አይደለም ፤ አይደለም ነው የምልምት፤ ተሳስተዋል!" አለ ።

በሳብር ሐሳብ ውስጥ ብዙ ነገሮች ተመላለሱ ።

—ልክ ነው ፤ ተሳስተዋል ። አሁን የደወለው ወላጅ አባቱ ሰይድ ኤል ራሕሚ ምሕረት የሌለው ስሕተት ተሳስቷል ። እስከ ዛሬ በፍለጋ ሲንከራተት የኖረ ልጁን ዮር ብሎ ያላየ አሁን መደወሉ ምን ፋይዳ ይኖረዋል ብሎ ነው? ሞኙን ይፈልግ፤ እርሱ ልጅነቴን እንደ ካደ ሁሉ እኔም አባትነቱን ክጀለሁ! ከእንግዲህ ነፃነትን ፡ ክብርንና የተደላ ደሰ ኑሮን የምሻው ከአባቴ ሳይሆን ከሌላ ስፍራ ነው . . . ወይ ከሊል! ምን ያንጠራራሃል ? ምን ያዛጋሃል? ለዘለዓለም የምታሸልብበት ጊዜ እየተቃረበልህ ነው ። የማይቀረውን ዕጣ ፈንታህን ኮመቀበል ምን ያታግልሃል? ከሊል እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅህ ። እኔ አጥፊህ ፡ አንተ የለፋህበትን

t.me/OLDBOOKSPDF

ሀብትና ንብረት በእጇ አግብቼ የምንደላቀቀው ፤ እናቱ እንዲያ ተሞርዳና ተገሳቁላ ለሞት የበቃችው ፤ አባቴ እማሬ እስኪቀጥን ስፈልገው ጅሮ ዳባ ልበስ ብሎ ዝም ያለው ፤ ኑሮዬና የወደፊት ተስፋዬ ከሰዎች ጉዳትና ከሣራ ጋር የተቈራኘው ለምን እንደሆነ ልታስረዳኝ ትችላለህ ? አሁንማ ሳምንቱ ማልፉ ነው ። በየደቂቃው ሐሳቤ የሚሽ ከረከረው ልቤ በሚጠረው ወንጀል ዙሪያ ብቻ ነው ። ባቡር ተሳፍሬ ከአስክንድርያ ስነሣ የነበረኝ ተስፋ ከዛሬው ተስፋዬ እንዴት የተለየ ነው! ከእነዚህ ከሞቱት አንጣዮች መካከል በወንጀል ድርጊት እጁ ያልተበከለ ይኖር ይሆን? ስለ ገንዘብ ፡ ስለ ጦርነት ፡ ስለ አርባ ቀን ዕድል አሥሩን ሲያወሩ የሚውሉትን የሚያበቁትስ መቼ ይሆን? የሰዎች ሕይወት ወደፊት ምን ዓይነት ዕጣ እንደሚያጋጥማት ሲተነብዩ ይውላሉ ። በሴላ በኩል ደግሞ ፡ በቅርብ ጊዜ ውስጥ በሚኖሩበት ሞቴል ውስጥ ሲፈጸም የታቀደው ነገር የሽተኞችውም አይመስልም . . .

አራት ሰዓት ላይ ሳበር ከሲልን እጅ ነሥቶ ከሞቴሉ ወጣ ። አራት ሰዓት ላይ ከሞቴሉ ወጥቼ እስከ ሌሊቱ ሰባት ሰዓት አልተመለስኩም የሚሉትን ቃላት በሐሳቡ አሥሬ ይደጋግም ጀመር ። ወጣ እንዳለ ፡ ከሞቴሉ ቀጥሎ ያለውን ሕንፃ መግቢያ መወጫ ሲመለከት ፡ ብዛት ያላቸው ሰዎች ይገባሉ ፤ ይወጣሉ ፤ እንደ ገበረ ጉንዳን ይርመሰመሳሉ ፤ የሕንፃው ጣሪያ ላይ የሚንከሳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወስ ነገር አይታይም ፤ ከአካባቢው አይታም ሠወር ያለ ነው ። ከሰዓት በኋላ አሥራ አንድ ሰዓት ላይ አካባቢው ጨለምለም ማለቱ አይቀርም።

ከሦቱሉ እልፍ እንዳለ ኤልሐምን የመጐብኘት ፍላጎት ቢቀሰቀስበትም ፡ ወዲያው በውስጡ ይመላለስ በነበረው ሐሳብ ተጋረደ ። በሌላ በኩል ደግሞ ሊፈጽመው ያሰበውን እዩይ ተግባር በልቡ ቋጥሮ ከፊትዋ መቆም የሚይሆንለት መሆኑ ተሰማው ። "የሰው ነፍስ አጥፍቼ ለዘለዓለሙ ልለይሽ ነው" ብሎ ሊነግራትስ እንዴት ይችላል?

የጋዜጣውን ቢሮ አልፎ ሲሄድ ከባድ ኃዘን ልቡን ተጫነው ። ከኤልሐም ጋር የተገናኙበት ጊዜ ፡ ላጋጠመው ችግር የምታሳየው መቈርቈር ፡ ለመልካም ሰውነትዋ ፡ ለፍቅርዋ አጸፋውን መመለስ አለመቻሉ አስጨነቀው ።

ሳብር በከተማይቱ አውራ ጐዳና ላይ መለስ ቀለስ በማለት ብዙ ጊዜ አሳለፈ ። በመጨረሻ ወደ አንድ ግሮሰሪ ገራ ብሎ ምግብ ከቀመሰ በኋላ አንድ ሁለት መለኪያ ብራንዲ ተጐነጨ ።

"የዛሬው አየር በጣም አስጠሊታ ነው" አለ የግሮሰሪው ባለቤት ።

ሳብርም ፡ "እባክህ ተወኝ ፤ የወንጀለኛ ልጅ ወንጀለኛ ነኝ!" በማለት ከግሮሰሪው ውልቅ ብሎ ወጣ ። የሳብር አንጋገር የግሮሰሪውን ባለቤት አሳቀው ። ብራንዲ ምን የማይሠራው ነገር አለ!

t.me/OLDBOOKSPDF

ኤልሐምን የመገመበኝት ፍላጐቱ ድንገት አገረሸበት ። ዘወትር ይገናኙበት ወደ ነበረው ምግብ ቤት ቢሄድ አጣት ። የምግብ ቤቱ አሳላፊ ለምላ ብቅ ብላ ብዙም ሳትቆይ መመለስዋን ሲነግረው ፡ እርሷን የማየት ፍላጐቱ ከስም አለ ። ከሰዓት በኋላ እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ወዲህና ወዲያ ሲል ቆይቶ ወደ ሆቴሉ አካባቢ ተመለሰ ። ጊዜው ለዓይን ያዝ ማድረግ ጀምሮአል ። ሳብር ከሕንፃው ትይዩ ቆም ብሎ መግቢያ መውጫውን ይቃኝ ጀመር ። ያካባቢው ሰማኝ የተዘከሩኝ ዜማውን ማንቈርቈሩን አላቋረጠም ። የሕንፃው ዘበኛ ከአንድ ሰው በደረቱ ጋር በዋጋ ክርክር መግጠሙን በመገንዘቡ ፡ መንገዱን በፍጥነት አቋርጦ ሕንፃው ውስጥ ጥልቅ አለ ። ገበያተኛው ሕንፃው ውስጥ ይርመሰመሳል ። ብዙ ሰዎች ሳብርን በዓይናቸው ጨረፍ እያደረጉት ያልፋሉ ። እርሱም ከሆቴሉ እንግዶች መካከል በዓይን የሚያውቃቸው ይኖሩ እንደሆን በማሰት በአጠገቡ የሚያልፉትን ሰዎች በጥንቃቄ ይቃኝ ነበር ።

ሳብር እንደ ምንም ብሎ ሕንፃው ጣሪያ ላይ ወጣ ። ጣሪያው ላይ ምንም ነገር አለመኖሩን ለዓይን ያዝ በማድረግ ላይ ባለው ብርሃን ማየት ይቻላል ። ተሂዙሮ ቢመለከት እንደ ገመተው ስፍራው ሠፋራ ነው ። ዓይኑን ወደ ሆቴሉ ሕንፃ ጣሪያ ሲያቀና ከሪማን ተሰጥተው የዋሉ ልብሶች ስትሰበሰብ አያት ። ድንግጥ አለ ። በሆነ ባልሆነው አመካኝታ ስትጠብቀው ነበር ማለት ነው ። ምና

t.me/OLDBOOKSPDF

ልባትም መንገዱን አቋርጦ ሕንፃው ውስጥ ሲገባ አይታው ይሆናል ።

እርሷ ወዳለችበት ስፍራ ቀረብ እንዲል በእጅዋ ጠቀሰችው ። ቀረባት ። እርሷን በአካባቢው በማግኘቱ ፣ ቄርጦ የተኛበትን ድርጊት ከግቡ ለማድረስ መንፈሱ ተበረታታ ።

"ስትገባ ያየህ ሰው አለ?" አለችው ከሪማ፡ በጀርባዋ እየከለለችው ።

"ማንም አላየኝም ።"

"አሊ ሰርያኩስ እታች ስለሆነ ፡ አንተ ወደ ዚህኛው ሕንፃ እስክትሻገር ድረስ እኔ ወረድ ብዬ እጠብቅዋለሁ ።"

ከሪማ የሰበሰበቻቸውን ልብሶች ይዛ ከዓይኑ ተሠወረች ። ሳብር ጥቂት ደቂቃዎች ከቆየና አካባቢውን በዓይኑ ከቃኘ በኋላ ወደ ሆቴሉ ሕንፃ ጣሪያ በዝላይ ተሻገረ ። አንዲት ኮሽታ ሳያሰማ ወደኑከለል መኖሪያ ቤት አካባቢ ደረሰ ።

"በሩ ክፍት ነው ፤ ግባ" በማለት ከሪማ ስትጎሸካሸክ ሰማት ።

አየሩን ሳብ አድርጎ እስኪበቃው ከተነፈሰ በኋላ በሩን ከፍቶ ዘው አለ ። አካባቢው ከመጨለሙ የተነሣ ዓይን ቢወጉ አይታይም ። ከሪማ ድምፅ እያሰማች ከቀረበችው በኋላ የአካባቢውን መብራት አብርታ በሩን ከውስጥ ዘጋችው ። የከሪማ ዓይኖች የወትሮ ብሩሕነታቸው ያልከዳቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

ቢሆንም ፡ ፊትዋ ክፉኛ ገርጥቷል ። ያ—ማራኪ አስ
ተያየትዋ ከስሚል ። ከሪማና ሳብር እቅፍቅፍ
ብለው ቆሙ ። ስሜታቸው የቀዘቀዘ ፡ አጠቃላይ
ሁኔታቸው መውጫ መግቢያው እንደ ጠፋቸው
ሕፃናት የተወናበደ ነበር ።

"ዓላማችን ከከሸፈ አበቃልን ማለት ነው!"
አላት ።

"ምንም የሚያርበደብድ ነገር የለም ። ያስ
ብነው ሁሉ በእቅዳችን መሠረት ይፈጸማል"
አሰኘው ።

የመኖሪያውን ክፍል ኮሪደር ይዘው ወደ
ውስጥ ገቡ ። ክፍሉ የተንጣለለ የመኝታ ቤት
አለው ። ከመኝታ ቤቱ ቀጥሎ አነስተኛ የሆነ
የምግብ ቤት ይገኛል ። ሳብር የመኝታ ክፍሉን
የተለያዩ ዕቃዎች ሲቃኝ ፡ ሰፊው አልጋ ፡ በአካባ
ቢው የተደረደሩ ሶፋዎች ፡ ኮሞዲኖዎች ፡ በግርማ
ዳው ላይ የተሰቀሉ ሥዕሎችና ጌጣጌጦች አፈጠ
ጠበት ። የመኝታ ቤታቸው የፈጠረበትን ስሜት
ሊገልጽላት ከጅሎ ፡ ምን አገባኝ የሚለው ውሳኔ
አሸነፈው ።

"የሚያስጠላ ክፍል ነው" አላት ሳያስበው።

ከሪማ ሁኔታው አሳድሮባት ከነበረው ሥጋ
ትና ፍራቻ ጋብ ያለላት ይመስላል ።

"እንግዲህ እዚሁ መኝታ ቤቱ ውስጥ
ተደብቀህ ትቀያለህ ። መግቢያው በር መከፈቱን
ስትሰማ አልጋው ሥር ገብተህ መደበቅ አለብህ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

“ወለሉ እንጨት ነው?”

“አዎን ፤ ግን ክፍሉ በሙሉ ምንጣፍ የለበሰ ነው ።”

“ከገባ በኋላ ዋናውን በር ይዘጋው የለም?”

“አዎን ይዘጋዋል ። ወደዚህ ሲመጣ የሚከተለው መሐመድ አል ሳዊ ነው ። በተለይም እኔ እናቴን ለመጠየቅ ስሄድ አል ሳዊ እስክ መኝታ ቤታችን ድረስ ተከትሎ ያስገባዋል ። ከውስጥ በሩን የሚዘጋው ከሊል ራሱ ነው ። መክፈቻውን አንዳንዴ በሩ ላይ ይተወዋል ፤ አንዳንዴ ደግሞ እዚህ ጠረጴዛ ላይ ያስቀምጠዋል ። በሩን ከፍተህ መውጣት ትችላለህ ።”

“ጣሪያው ላይ ሰው ቢያጋጥመኝስ?”

“ማንም አያጋጥምህም ። ሰርያኩስም ከሊል ወደ መኝታ ክፍሉ ከገባ በኋላ ሦስተኛ ፎቅ ላይ ወዳለው መኖሪያው ክትት ይላል ።”

“በሩን ማን. . .”

ከሪማ ንግግሩን አላስጨረሰችውም ። “ስለ እሱ አትሥጋ ። መስኩዩቹ ዝግ ነው የሚሆኑት ። ሰዎች ማሰብ የሚችሉት አል ሳዊ መኝታ ቤቱ አድርሶት ከተመለሰ በኋላ ወይ በሩን ረስቶ አል ዘጋውም ፤ ወይም ደግሞ በሩ ተንኳኩቶ ተነሥቶ ከፍቶት ይሆናል ብለው ነው ።”

“ማንኑዝን ሳያጣራ ድምፅ በመስማት ብቻ በሩን መክፈት ይችላል?”

t.me/OLDBOOKSPDF

"የሚያውቀውን ድምፅ የሰማ መስሎት በሩን ሊከፍተው ይችላል ።"

"እንዲህ ከሆነ ጥርጣሬው በሦቱሉ ውስጥ በሚኖሩና አካባቢውን በሚያውቁ ሰዎች ላይ ለያተኩር ይችላል ማለት ነዋ?"

ብስጭት ባለ ድምፅ : "በወንጀሉ የማይጠረጠረውን ሰው ክመሬት ተነሥተው ይጠረጥሩ ታል ብለህ ሥጋት አይደርብህ! ዋናው ነገር የሚሠራውን ሠርተህ ሹልክ ብለህ መውጣት ነው" አለችው ። የእጅ በርሳዋን እያሳየችው : "እዚህ ያለውን ገንዘብና ጥቂት ዋጋ ያላቸው ጌጣ ጌጦች እጄ አግብቻለሁ ። የቁም ሣጥኑንም በቢላዋ ከፍቼ ከውስጡ ልብሶች በማውጣት በየ ቦታቸው በታትኛቸዋለሁ ። ለመሆኑ የእጅ ጓንቱ አዘጋጅተሃል?"

"አዎን : አዘጋጅቻለሁ ።"

"መልካም ።" መኝታ ቤቱ መካከል ወዳ ለው ጠረጴዛ እያመለከተች : "የበረት ዘንጉም ያለው ጠረጴዛው ሥር ነው ። ጓንቱን ሳታጠልቅ እንዳትነካው ። አልጋው ሥር ምንም ነገር እንዳ ትጥል" አለችው ። ዓይኖችዋ ወዲህና ወዲያ በመ ጣተር ጥድፊያዋን የሚገልጹ ቢሆንም : ፊትዋ ግርጥት : ከስም እንዳለ ነው ።

"እንግዲህ መሄድ አለብኝ" አለችው ።

እቅመበት ተቃቀፉ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሰውነቱ ጋር አጣብቆ ጭምቅ አድርጎ እንደ ያዛት ፡ "ምናለ አብረሽኝ ለጥቂት ጊዜ ብትቆዪ" አላት ።

"አይሆንም ፤ መሄድ አለብኝ ።"

"የተረሳ ምንም ነገር የለም?" አላት ።

"ከአሁን በኋላ ድፍረት ... እርጋታ . . . ድር ጊት. . ."

"ምን አልሽኝ?"

እንግዳ በሆነ የመገረም እይታ እየተመለከ ተችው ፡ "ምንም" ካለችው በኋላ በሹክሹክታ ፡ "በል ቶሎ በልና አልጋው ሥር ግባ!" የሚሉትን ቃላት አሰማችው ።

ለምስተኛ ጊዜ ተቃቀፉ ። በጥድፊያ ከእቅፉ ተላቃ ድምፅዋን ከፍ አድርጋ አለ. ሰርያኩስን እየተጣራች ጥላው ሄደች ። ሳብር ጊዜ ሳያባክን ከአልጋው ሥር ገብቶ ለጥ አለ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከሪማ አለ. ሰርያኩስን እስክትላ ተመለሰች ። መኝታ ቤቱ ውስጥ እንደገቡ መስኩዶቹን እንዲዘጋጋ ነገረችው ። መስኩዶቹ መዘጋታቸውን ካረጋገጠች በኋላ ፡ መብራቶቹን አንድ ባንድ አጥፍታ ከመኝታ ቤቱ ወጥታ ሄደች ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፡ ሳብር ከተደበቀበት አልጋ ሥር ወጣ ። የመኝታ ቤቱ ጨለማ ዓይን ቢወጉ አያሳይም ። ንጉሊቶቹን ከኪሱ አውጥቶ

t.me/OLDBOOKSPDF

እጆቹ ላይ በማጥለቅ በዳበሳ ጠረጴዛው ካለበት ስፍራ ደረሰና የብረት ዘንጉን አገኘው። የብረት ዘንጉን ይዞ አልጋው ወዳለበት በመራመድ ጫፉ ላይ ቁጭ አለ። አካባቢው እንደ መቃብር ቤት ጭር ያለና እንደ መርግ የከበደ ሆነበት። በዚያች ቅጽበት ለሳብር የሚሰማው፡ ከአልጋው ጋር ያለው ንክኪ፡ ከሪማ አውዳው የሄደችው የሽቱ መዓዛና በአካባቢው የነገሠው ጸጥታ ብቻ ነበር። ከእንግዲህ ወደኋላ ማለት አይቻልም። ከእንግዲህ በእጁ ጨብጦ የያዘውንና ጭጭ ምጭጭ የማያሰኘውን የብረት ዘንግ መሰንዘር አለበት። ነገ ተነገ ወዲያ እያሉ ቅሩጠው ያልታወቀ ተሰፋ ይዞ ከመኖርና ሌት ተቀን በፍለጋ ከመባዘን የማያዳግመውን የብረት ዘንግ አንዴ ሰንዝሮ ማረፉ ይሻላል። የከሪማ ፍቅርም ቢሆን መጨበጫ የሌለውና ሊፈጽመው ካቀደው ድርጊት የባሰ አደገኛ ነው። ለማኑ አሁንም ያንገራገራል። መቼ ይሆን የልመና ዜማውን የሚያቆመው? ቀኑን ሙሉ የሚያከማው ማን ይሰማኛል ብሎ ይሆን? ልክ እንደ ሳብር የጋዜጣ ማስታወቂያ . . . የማንም መጫወቻ እንደሆነው እንደ ሳብር እናት ንብረት... ዕድሚአቸው እየረዘመ እንደ ሄደው የሳብር የእስክንድርያ ትዝታዎች . . . ወይ ከንቱ ድካም!

ያሰበው ድርጊት ተፈጽሞ ከከሪማ ጋር የሚገናኝበትና ያልወጣለት ስሜታቸውን ያለ ሥጋት የሚያረክብት ቀን መቼ ይሆን?

t.me/OLDBOOKSPDF

አሊ ሰርያኩስ ጣሪያው ላይ ሆኖ ሲያንሰራ ገር ይሰማል ። በተረፈ አካባቢው በጨለማና በጸጥታ እንደ ተዋጠ ነው ። ሳብር አልጋው ጫፍ ላይ ተቀምጦ ያሳለፈው ጊዜ ያመት ያህል ረዘመበት ። ወዲያው የመኝታ ቤቱ ዋና በር መክፈቻ ቁልፍ ገብቶበት ሲንቃጨል ተሰማው ። ፊጠን በማለት አልጋው ሥር ገብቶ ተሸገጠ ። የሰው እግር እርምጃዎች እየቀረቡት መጡ ። መኝታ ቤቱ በብርሃን ተጥለቀለቀ ። የሳብር ትንፋሽ ቍርጥ ቍርጥ ማለት ጀመረ ፤ የልቡ ድውታ ከሩቅ የሚጣራ መሰለው ። ከአልጋው ሥር እንደ ተኛ ስድስት እግሮችን ቈጠረ ። ከሊል ፡ “በል እንግዲህ አሊ ፡ አንተ መሄድ ትችላለህ ። የቧንቧ ሠራተኛውን ነገር አደራ” አለ ።

ሁለት እግሮች ተቀነሱ ። ከሊል አልጋው ጫፍ ላይ አረፍ አለ ። እግሮቹ የሳብርን አፍንጫ ለመንካት ምንም አልቀራቸውም ። “መገናኘቱን ነገ እንገናኛለን ። ዋናው ነገር መቀለጃ መሆን እንደማልፈልግ መታወቅ ይኖርበታል” አለ ከሊል ።

“እውነትዎን ነው” አለ ፡ የሆቴሉ በር ጠባቂ፡ መሐመድ አል ሳዊ ።

“ሞላጫ ሰይጣን ነው ። አራት ጊዜ ከሞት አፋፍ መመለሱ እንኳን ትምህርት አልሆነውም።”

“መቼም እርስዎን የመሰለ ደግ ሰው በእግር በፊረስ ቢፈለግ አይገኝም ።”

t.me/OLDBOOKSPDF

ከጥቂት ጊዜ ዝምታ በኋላ ፡ "እንግዲህ ልሂዳ?" በማለት አል ሳዊ በትሕትና ጠየቀ ።

"እስቲ ትንሽ ቆይ ። ዛሬ ደግሞ የወገቤ ሕመም ተነሥቶብኛል ። ራስ ምታቴም ይወግረኛል ።"

—አል ሳዊ ምን ያህል ጊዜ ሊቆይ ይሆን ? ከሽማግሌው ጋር እዚሁ እንዳያድርና ጉድ እንዳይፈላ ። ሳብርን ሐሳቡ ራሱ ዝግንን አደረገው ።

ከሊል ብዙም ሳይቆይ የምሽት ጸሎቱን ማድረስ ጀመረ ። ይሻላል ። ጸሎቱን እንዳበቃ ፡ "በል እስቲ አል ሳዊ ጫማዬን አውልቅልኝና ፒጃማዬን አቀብለኝ" አለ ። ቀን ለብሶት የዋለውን ልብስ አውልቆ የሌሊት ልብሶቹን አጠለቀ ። ከዚያም ፡ "የእንቅልፍ መድኃኒቴን ከመሳቢያው ውስጥ አምጣልኝ" ብሎ አል ሳዊን አዘዘው ።

—መሳቢያው ደግሞ የቱ ይሆን? የቁም ሣጥኑ እንዳይሆንና የተመሰቃቀለው ንብር ዓላማዬን አጋልጦት እንዳያርፍ!— አለ ሳብር በሐሳቡ ።

ሳብር ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ መጨረሻውን ይጠብቅ ጀመር ። ከሊል ውኃ ተጎንጭቶ የእንቅልፍ ክኒኑን መዋጡን ሲሰማ የሳብር ነፍስ መለስ አለችለት ። ከዚያም አልጋው ውስጥ ገብቶ ተመቻችቶ መተኛት መጀመሩ በልብሶቹ ኩሽታ ተሰማው ።

"አል ሳዊ ፤ ዛሬ መነሣት የምችል አይመስለኝም ። በሩን ከውጪ ዝጋውና ማለዳ በተለመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ደው ሰዓት መጥተህ ቀስቅሰኝ" አለ ከሊል ፡ የአልጋ ልብሱን ወደ አንገቱ እየሳበ ።

ክፍሉን ድቅድቅ ጨለማ ዋጠው ። ወዲያው ደብዛዛው የራስጌ መብራት በራ ። አል ሳዊ እንደ ታዘዘው በሩን ከውጪ ዘግቶ ቁልፉን ይዞ ሄደ ። ነገ ማልዶ ሲመጣ የከሊልን ሬሣ አልጋው ላይ ተዘርሮ ሲያገኘው ምን ይሰማው ይሆን ? ገዳዩ ፡ መኝታ ቤት በየት አድርጎ ገብቶ በየት ወጣ ብሎ ይገምት ይሆን? መስኮቱ አለ ለካ — ወደ ጣሪያው የሚያወርደው መስኮት ። ወንጀል መርማሪዎችስ የዚህን ድርጊት አፈጻጸም ምስጢር እንዴት አድርገው ፈልፍለው ያወጡት ይሆን? ጭንቅቱና ፍርሐቱ ሳብርን ወጥሮ ያዘው ። የሐሳብ ውጣ ውረድ ፡ ወንጀሉን የመፈጸሚያው እቅድ ውስብ ስብነት ማዕበል እንደሚሰብቃት መርከብ ከግራ ወደ ቀኝ ያላጋው ጀመር ። ውስጣዊ ስሜቱ ሁኔ ታው እዚህ ደረጃ ከደረሰ በኋላ ወደ ኋላ ማፈግ ፈግ እንደማይችልና ያቀደውን ሳያመነታ ፈጽሞ እንዲገላገል ይገፋፋዋል ። የልቡ ድውድውታ ፡ የሐሳቡ መተራመስ የሚይዘውን የሚጨብጠውን አሳጥቶታል ። ከሊልን ቶሎ እንቅልፍ ይወስደው ይሆን? እያለ ሲያስብ ወዲያው ማሹረፍ ጀመረ ። የከሊል ኮርፊያ ፡ የሳብር እናት የሞትዋ ዋዜማ ሌሊት ያሰማችውን ይመስላል ። ሞት. . . ከፈን... ለቅሶ . . . ዋይታ ፤ የእስክንድርያ ከተማ ጎዘን ታየው ። በዚህች ወሳኝ ቅጽበት ያለፈውን ማስ ታወሰ ምን ፋይዳ አለው? ሳብር ከአልጋው ሥር

t.me/OLDBOOKSPDF

እየተሳበ ወጣ ። ንጉሡ ባጠለቀ እጁ የብረቱን ዘንግ ጥርቅም አድርጎ ይዞ አልጋው አጠገብ እንደ ጅብራ ተገተረ ።

ከለልም ሽፍንፍን ብሎ ተኝቷል ። ከአካሉ ክፍል የሚታየው ትራስ ላይ ካረፈው ጭንቅላቱ ግማሹ ነበር ። ሳብር ፡ የከለልን ፊት ሙሉ ለሙሉ ማየት አለመቻሉ ደስ አሰኘው ። ምራቁን ዋጥ አድርጎ ጠጋ ብሎ ተመቻችቶ ቆመ ። የብረት ዘንጉን ለመሰንዘር ከጭንቅላቱ በላይ ከፍ አድርጎ ያዘው ። በዚህ ቅጽበት ከለል ተወራጨ። ሳብር የብረት ዘንጉን ከራሱ በላይ አንሳፎ እንደ ያዘ ክው ብሎ ቀረ ። ከሊል ፡ ጭንቅላቱ ላይ ያረፈውን ልብስ አስወግዶ ዓይኖቹን ጭንብስ. . . ጭንብስብስ. . .ገለጥ. . . ገለጥለጥ አደረገ ። ሁለቱም ዓይን ለዓይን ተጋጩ ። ከሊል አልጋው አጠገብ እንደ ጅብራ የተገተረው ማን እንደሆነ ያወቀ አይመስልም ። ሳብር ያላሰበው ነገር የገጠመው መሆኑን በመረዳቱ ፡ ከራሱ በላይ ይዞት የነበረውን የብረት ዘንግ ከሊል ጭንቅላት ላይ በኃይል አሳረፈው ። የብረት ዘንጉ አሰነዛዘር ውጤት የሆነው ምት የፈጠረው ድምፅ ሳብርን ራሱን አስደነገጠው። ሽማግሌው ከሊል ለቅጽበት ተወራጭቶ ፡ መላ ሰውነቱ ከእግር እስከ ራሱ ተንዘፍዝፎና እንቋሮ ጸጥ አለ ። ሳብር፡ከሊል መሞቱን ለማረጋገጥ እምብዛም አልተጨነቀም ። መስኮቱን ከፍቶ ፡ ግራ ቀኙን ቃኝቶ ሰው አለመኖሩን ካረጋገጠ በኋላ ፡ ተንጠ

t.me/OLDBOOKSPDF

ላጥሎ ጣሪያው ላይ ዱብ አለ ። የወጣበትን መሰኪት ከውጪ መለሰ አደረገው ።

የብረት ዘንጉ በደም ተነክሮ ይሆን? ጣሪያው ላይ ምንም አልነበረም ይሆን? ሰዓቱ ስንት ይሆን? ሳብር ጣሪያውን አቋርጦ ወደ ሁለተኛው ሕንፃ ተሻገረ ። የብረት ዘንጉን እዚያው ለምን አላጠበ ውም? ከቤቱ ጣሪያ ወደ አንድ አቅጣጫ ወርውሮ መጣሉ ይበጅ ይሆን? ይሽማ አይሆንም ፤ እጅን አሳልፎ መስጠት ነው ።

ከአንድ አቅጣጫ የሰው ድምፅ ሰማ ። የጣሪያውን መከለያ የብረት አጥር ደገፍ ብሎ አዳመጠ ። ሦስተኛው ፎቅ ጨለማ የለበሰ ሲሆን ከሁለተኛው ፎቅ ብርሃን ይታያል ። የያዘውን የብረት ዘንግ ግራ እጁ ውስጥ ባጠለቀው ጓንቲ ጠራርጎ ደረጃዎቹን በዝግታ መውረዱን ተያያዘው። ሁለተኛው ፎቅ ሲደርስ የአንድ መኖሪያ ክፍል በር ተከፍቶ መብራቱ አካባቢውን ወግ አድርጎታል ። ወዲያው ሦስት ሰዎች ከመኖሪያ ክፍሉ ወጥተው ከኋላው ተከተሉት ። ሳብር እያዘገመ በመሄድ ሦስቱ ሰዎች ቀድመው እንዲያልፉት መንገድ ሰጣቸው ። ምድር ቤቱ ሲደርስ ከሦስቱ ሰዎች ጋር ለጥቆ አብሯቸው ከሕንፃው ውስጥ ወጣ ። የሕንፃው ዘበኛ መግቢያው በር አጠገብ ካለችው ትንሽ የጥበቃ ክፍል ውስጥ መቀመጡን አስተውሏል ። ከሕንፃው እንደ ወጣ ለአፍታ ያህል ቆም ብሎ ቁና ቁና ተነፈሰ ። ከሕንፃው

t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ መውጣቱን ያየው ሰው ይኖር ይሆን? ልብሱን ደም ነክቶት ይሆን? ከመንገዱ ባሻገር አንድ የቆመ ታክሲ አየ ። ከሆቴሉ አካባቢ ሰው እንዳያየው በመፍራት መንገዱን መሻገር አልደፈረም ። ከሕንፃው አቅጣጫ ወደ ጎን አጠፍ ብሎ በመራመድ መንገዱን አቋረጠ ። ከዚያም ታክሲው ወደ ቆመበት አቅጣጫ መለስ በማለት ፈጠን እያለ መራመድ ያዘ ። ለማኙ የዕለት ተግባሩን ፈጽሞ በመጫት ሳብር ወደሚገኝበት አቅጣጫ ማዝገም ጀምሯል ።

ለማኙ በአጠገቡ አለፈ ። ሳብር ለማኙን በቅርበት ደህና አድርጎ አየው ። ፊቱ የገረጣ ፡ አፍንጫው የተጣመመና ዓይኖቹ ደም የጐረሱ ፡ ጢሙ ምላጭ ነክቶት የማያውቅና የቱንጨፈረረ ፡ ራሱ ላይ የደፋው ቆብ በእድፍና በላብ የጠቆረ ፡ መላ ቁመናው ከሲታና ቀፋፊ ነበር ። እንዲህም ሆኖ ቀኑን ሙሉ ሲያዜም ይውላል ። ያንን ሁሉ ዜማ ሲያወርደው የሚውለው ምን ይወድቅልኛል ብሎ ይሆን ? የኔ ቢጤው በአጠገቡ ሲያልፍ የሳብርን አፍንጫ ያወደው ጠረን ከለማኙ አጠቃላይ ሁኔታ የሚጠበቅ ነበር ። ሳብር ወደ ታክሲው ፈጥኖ በመሄድ ሹፌሩን የሚከራዩ ጀልባዎች ወደሚቆሙበት አባይ ወንዝ ዳር እንዲወስደው ጠየቀው ። ከሕንፃው ሲወጣ ማንም አላየው ይሆን? የእጅ ጓንቲዎቹንና የብረት ዘንጉን ያስተዋለ ሰው ይኖር ይሆን?

t.me/OLDBOOKSPDF

ታክሲው ሲሄድ ለምንድን ነው የሚያዘግመው? ሹፌሩ ደግሞ እሥሩን ይቀባጥራል። ምን ዓይነቱ አብሽቅ ነው?

"እውነቴን እኮ ነው!"

"እ?"

"እኔ የምለው. . .ይኸ ሁሉ ዕብደት ለምኑ ነው?. . . ለእኔ እንደሚታየኝ ከሆነ ትዕግሥትን የመሰለ ነገር የለም።"

—ሹፌሩ ለምን አፉን አይዘጋም? ምን ልሁን ብሎ ነው እንዲህ የቆጥ የባጡን የሚዘላብደው?

የአባይ ወንዝ ዳርቻ ጨለማ ለብሷል። ከአሁን በኋላ ጓንቲዎቹን፣ የብረት ዘንጉንና የደሙን ምልክት ማንም ሊያየው አይችልም። በአሁን ሰዓት ጀልባ እየቀዘፉ በአባይ ወንዝ ላይ መን ሸራሸሩ የቱለመደ ነገር ባይሆንም፣ ምን ይደረግ? የቸገረው ከዚህ የባሰስ ነገር ይፈጽም የለ!

ሳብር ጓንቲዎቹንና የብረት ዘንጉን ያለ ሥጋት ወዲያ አሽቀንጥሮ ጥሎ እጆቹን በድፍርሱ የአባይ ወንዝ ውኃ መለቃለቅ ከሚችልበት አካባቢ ደርሷል። ጀልባዋን እየቀዘፈ በመጓዝ ላይ ሳለ ከዚህ መጣ የማይባል የድካም ስሜት ሰውነቱን ተጫጫነው። ጀልባዋን የወንዙ እንቅስቃሴ ግፊት ወደ ፈለገበት እንዲወስዳት በማለት ጀልባዋን መቅዘፉን ተወው። በወንዙ ዳርቻ ዓይን የሚስብ ምንም ዓይነት ነገር አይታይም። ጀልባዋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወንዙ ላይ እየዋለለች የጅራቱ ግፊት ወደ መራት ስትዋብ ደስ ማሰኘቱ! በአንጻሩ ደግሞ ፡ እነዚያን ያፈጠጡ ዓይኖች . . . ያንን ያጨነቄረ እይታ. . . ያንን ዘግናኝ ማንቋረር . . . ያንን የዘላለም ዝምታ ማን ሊረሳው ይችላል! የለማኙ ዓይን የሚያለቅሱት ደም ነው ወይስ እንባ! ከእንግዲህ የፊለገው ቢሆን ሳብር ግድ ያለው አይመስልም ። አባቱም ቢገኝ ባይገኝ የራሱ ጉዳይ! ለመሆኑ ፡ ያሰ ቀዛፊ ደፋ ቀና እያለች የምታዘማመው ጀልባ ወዴት እንደምታደርሰው ሳብር ያውቅ ይሆን?

ድንገት ጆሮ የሚሰነጥቅ ድምፅ ሳብርን ከሰመመኑ አነቃው ። አንድ መጠነኛ የሆነ ዕቃ ጫኝ መርከብ ጀልባዋን በጥቂት ጋት ርቀት አለፋት ። ጀልባዋ ፡ የመርከቡ እንቅስቃሴ በፈጠረው ማዕበል ላይ ወጥታ ደንገላሳ ትመታ ጀመር ። ሳብር ፈጥኖ መቅዘፊያዎቹን በመጠቀም የጀልባዋን አቅጣጫ አቃንቶ ወደ መቆሚያ ዳርቻ ወሰዳት ። ምሽቱ ድቅድቅ ያለ ጨለማ የነገሠበት ነበር ። በሰማዩ ላይ ከዋክብት ለምልክት እንኳን አይታዩም ። ሳብር የዚያን ዕለት ምሽት ለመጀመሪያ ጊዜ የከረምቱ ብርድ ሰውነቱን ዘልቆ አንሰፈሰፈው ። መውጋት እንዲሰማው በማለት ፡ የመንገዱን ጠርዝ ይዞ ፊጠን ፊጠን እያለ መራመድ ጀመረ ።

ቃስር ኤል ኒል የሚባለውን ድልድይ ሲሻገር ሳብርን አንድ ነገር አጋጠመው ። አንድ ትልቅ የቤት መኪና የትራፊክ መብራት አቁሞታል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መኪናውን የሚነዳው ግርማ ሞገስ ያለው ሀብታም መሳይ ሰው ነው ። ሳብር ሰውዬውን በመልክ የሚያውቀው መሰለው ። —አባቴ መሆን አለበት — ብሎ አሰበ ። ወዲያው የትራፊክ መብራቱ ወደ አረንጓዴነት ተቀየረ ። መኪናው ተንቀሳቀሰ ።

"ሰይድ ኤል ራሕሚ!" የጥሪው ጩኸት ቀዝቃዛውን የሌሊት አየር አናወጠው ። ሳብር ጨርቁን እንደ ጣለ እብድ በመሮጥ መኪናውን ተከተለው ። መኪናው ፍጥነቱን ጨምሮ በመንገድ ከዓይኑ ተሠወረ ። ሳብር ሩጫውን አጧርጦ ቁና ቁና ይተነፍስ ጀመር ። እሱ መሆን አለበት. . . ሰይድ ኤል ራሕሚ. . . ከሠላሳ ዓመት በኋላ ሳብር የመኪናውን ታርጋ እንኳን አልያዘም ። እንዴ ካመለጠ ምን ዋጋ አለው! ሕዋሳት—አዕምሮው የብርዱን ስሜት መቀበል ካቃተው ፡ ዓይኑስ እንዴት ሊታመን ይችላል? ኤል ራሕሚ ፤ ከእንግዲህ ምንም አትፈይድልኝም! ከእንግዲህ አለኝታዬ ከሪማ ናት. . .

መቼም ከሪማ እስካሁን አትተኛም ። በሐሳብዋ የምታወጣውና የምታወርደው የሳብርን ተልእኮ መሳካት ነው ። ከሪማና ሳብርን አንድ የጋራ የሆነ ፍላጐት አቈራኝቷቸዋል ። ከእንግዲህ መነጣጠል የሌለባቸው ቢሆኑም ፡ ሳብር ኤልሓምን አግኝቶ የሠራውን ጉድ ለእርስዋ ዘክዝኮ መናዘዝ እንዳለበት ይሰማዋል ። ከፊት ለፊቱ ካለው ሰፊ

t.me/OLDBOOKSPDF

አደባባይ እምብርት ላይ የቆመው ሐውልት ጫፍ የሚታየው ሰዓት እኩለ ሌሊት መድረሱን ያመለክታል። ወደ ሆቴሉ ለመመለስ ሲያስብ ሰውነቱን ሰቀጠጠው። የማይቀር ነገር በመሆኑ ፊቱን ወደ ዚያው አቀና። ከሆቴሉ ቅጥሎ ያለውን ሕንፃ ሲያልፍ የሠራ አካላቱን ውርር አደረገው። ያለማኝ ታወሰው። ወዲያው ደግሞ ፡ አንድ መጠጊያ ፡ አንድ ከለላ የሚያሻው መሆኑ ሐሳቡ ውስጥ ድቅን አለበት።

ሳብር ከውጪ ሆኖ ሲመለከት የሆቴሉ በር ጠባቂ መሐመድ አል ሳዊ ከሊል ወንበር ላይ ተቀምጧል። እንቅልፍ በዓይኑ ላይ የዞረበት አይመስልም። ሳብር ወደ ሆቴሉ ለመግባት ፊልጎ አንድ ነገር እግሩን የያዘው መሰለው። ሳይገባ ተመልሶ መሄዱ ደግሞ ጥርጣሬ ላይ የሚጥለው መሆኑ ተሰማው።

"ምንው የደከመህ ትመስላለህ?" አለ አል ሳዊ ፡ ሳብር ወደ ሆቴሉ እንግዶች መቀበያ አካባቢ እንደ ደረሰ።

"የዛሬው ብርድ አይጣል ነው" አለ ሳብር ፡ ጠንቀቅ እያለ።

"ዛሬም ደውላ ነበር" አለ አል ሳዊ ፡ ፊቱን ፊገግታ እያለበሰ።

"ማን. . .?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"መች አጣሃትና ነው የምትጠይቀኝ?"

ኤልሐም ናት ማለት ነው የደወለችው። ኤልሐም እኮ ፈሪ ናት። ስልክ ደውላ ስምዋን እንኳን መተው አይሆንላትም። ልክ እንደ ሰይድ ኤል ራሕሚ ግድርድር ናት...

"ከከተማችሁ ከችግር በስተቀር የተረፈኝ ምንም ነገር የለም" አለ ሳብር፡ ምርር ብሎ።

"የሕይወት ትርፉ ችግር ነው... ምንም ነገር አልሰማህም?"

አል ሳዊ የጠየቀው የአባቱን ፍለጋ ጉዳይ መሆኑ ገባው።

"ነገ ደግሞ አንድ ብዬ እፈልገዋለሁ... ከመቃብር ቤት ጀምሬ..."

ሳብር የሆቴሉን በር ጠባቂ መሐመድ አል ሳዊን ተሰናብቶ ወደ ክፍሉ አመራ። ክፍል ቁጥር አሥራ ሦስት... ነጃሳ ቁጥር!

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥራ አንድ

ሳብር ፡ ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ በዓይኑ ሳይዞር አድሮ ከንጋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ተነሣ ። ሌሊቱን ሙሉ ሕልም አይሉት ቅዠት ፡ ቅዠት አይሉት ሕልም እየተፈራረቀ ኀቡዕ ሕሊናው ሲተራመስ ነበር ያደረው ። ከሊልን አስቀምጠ ከከሪማ ጋር አምባጓሮ ፈጥሮ ሲነታረክ በሕልሙ እንዳየ በጉልህ ትዝ ይለዋል ። ከሊል በበኩሉ ለጸባቸው ደንታ ያልሰጠው መሆኑ ይታወሰዋል ። ሳብር ይህን የመሰለ ሕልም ከታየው ፡ እንቅልፍ የሚሉት ነገር በዓይኑ አልዞረም ለማለት ይቻል ይሆን?

የማለዳው አየር ቅዝቃዜ አጥንት ሰርስሮ ይገባል ። ሳብርን የመሰለ የወጣለት ወንጀለኛ ቅዝቃዜ ቀርቶ የባሰም ነገር ይችላል ።

ሳብር የክፍሉን መብራት እንዳበራ ቀኝ እጁ ውስጥ አጥልቆት የነበረው ጓንቲ ያልወለቀ መሆኑን አየ ። በድንጋጤ ዓይኑን አፍጥጦ ጓንቲውን እንደ ጉድ ይመለከተው ጀመር ። የግራ እጁን ጓንቲ አውልቆ ኩበረት ዘንጉ ጋር አባይ ወንዝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ አሽቀንጥሮ ሲጥል የቀኝ እጁን ጓንቲ ዘንግቶታል ። ጀልባዋን እየቀዘፈ ወደ ወንዙ ዳር ሲመለስ ፡ የመንገዱን ዳር ይዞ ወዳረፈበት ሆቴል ሲፈጥን ፡ ለትንሽ ካመለጠው መኪና ዘንድ ለመ ድረስ ትንፋሽ እስኪያጥረው ድረስ በሩጫ ሲከንፍ፡ የሆቴሉን ዘበኛ ተሰናብቶ ወደ ክፍሉ ሲገባ ሁሉ የቀኝ እጁን ጓንቲ እንዳጠለቀ ነበር ማለት ነው . . .

እንደ በረዶ የሚቀዘቅዝ ድንጋጤ አከርካሪ ውን አቋርጦ ሲወርድ ተሰማው ። ያ ሁሉ እቅድ፡ ያ ሁሉ ጥንቃቄ ውጤቱ ይኸው ሆኖ መቅረቱ ነው፤ እጅ ይዞ አሳልፎ የሚሰጥ ምን ሌላ ፍንጭ ሊኖር ይችላል? ሳብር አንሶላውን ፡ ብርድ ልብሱን ፡ ወለሉን ፡ ጫማውን ፡ የጫማ ሽራቦቹን ፡ ኮቱን ፡ ሱሪውን ፡ ሸሚዙንና መሐረቡን በጥንቃቄ መረመረ ። ፍርሐቱና ሥጋቱ በእንድ አፍታ ያመት በሽተኛ አስመሰለው ። በዚህ ዓይነት ወንጀል መርማሪዎችም ቢሆኑ የቱሪጸመውን ድርጊት ምስጢር አፍረጥርጠው ለማውጣት አፍታም አይወስድባቸውም ። እንዲያም ሆኖ ፡ ሳብር ጊዜ ሳያባክን የጓንቲውን ደብዛ ለማጥፋት ወሰነ ። ጓንቲውን በፎጣው ጠቅልሎ ፡ ለጠም መከርከሚያ የሚገለገልባትን አነስተኛ መቀስ ጢጃማው ኪስ ውስጥ ከትቶ ፡ ሳሙናውን ይዞ እንግዶች በጋራ ወደሚጠቀሙበት መታጠቢያ ቤት አመራ ። ጓንቲውን በመቀስዋ እንደ ዳቦ ቆሎ ከታ ትፎ ዓይነ ምድር መውጫው ውስጥ በመጨመር

t.me/OLDBOOKSPDF

ውኃውን ለቅቀበትና ተጠራርጎ ሲወርድ ቆሞ ተመለከተው ። ሳብር ፊቱን ተጣጥቦ ወደ ክፍሉ ሲመለስ አሲ. ሰርያኩስን ወደ መታጠቢያ ክፍል ሲያመራ አገኘው ።

"እንደምን አደርክ ፡ አቶ ሳብር ። ምነው ዛሬ በጠዋቱ ተነሣህ?" አለው ፡ ሰርያኩስ ።

—እረ የሚያነሣ ነገር ያንሣህ! አንተስ ብትሆን ኖኅ ለማኝ ሳያራ በየኮሪደሩ ምን ያንጠለጠልልሃል?— በማለት ሳብር በሆዱ ውስጥ ተራገመ ።

አሲ. ሰርያኩስ ፡ በሆቴሉ ውስጥ ስለ ተፈጸመው ወንጀል የሚያውቀው ነገር እንዳለ ወንጀል መርማሪው መኰንን ለሚያቀርብለት ጥያቄ ፡ ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ዕለት ክፍል ቍጥር አሥራ ሦስትን ተከራይቶ ያለው እንግዳ ፡ ያለ ወትሮው ማለዳ ተንሥቶ ከመኝታ ቤት ሲመለስ አግኝቼዋለሁ ማለቱ አይቀርም ። አሲ. ሰርያኩስ ፡ ባይጠየቅም ዛሬ ያያትን ነገር መለፍለፉ ሳይታለም የተፈታ ነገር ነው ። ከዚህ ሚርቶኛ ጋር መገናኘቱ ራሱ አጉል ገድ ነው ። ለመሆኑ ግንቲውን ቄራርጠ ዓይነ ምድር መውጫው ውስጥ ጨምሮ ውኃ ከለቀቀበት በኋላ ፡ ወለሉ ላይ ጠብ ያለ ነገር አለመኖሩን ሳብር አረጋግጦ ይሆን? ወይ አለመታደል! ወደ መጸዳጃው ክፍል እንደገና መመለስ አለበት ። ዓይነ ምድር መውጫውን ደም የመሰለ ነገር የነካው መሆኑን እንዳየ ትዝ አለው ። ሳብር ፊቱን ወደ መጸዳጃው ክፍል አዙሮ በመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቆም በር በሩን አትከሮ ይመለከት ገባ ። ወዲያው አሊ ሰርያኩስ ከመጸዳጃው ክፍል በመውጣት ፥ "ምነው ፥ የምረዳህ ነገር አለ እንዴ?" በማለት ሳብርን ጠየቀው ።

ሳብር ፥ አሊ ሰርያኩስን ሥር ብሎ ሳይመለከት ወደ መጸዳጃው ክፍል ገብቶ ዕቃውን ደም ነክቶት እንደሆን በማለት አጐንብሶ በጥንቃቄ መረመረው። ሁኔታውን አጣርቶ ሲወጣ አሊ ሰርያኩስ እቆ መበት ሆኖ ይጠብቀው ስለነበር ፥ "ሳሙኤልን ረስቼው ነበር" ብሎት ሊያልፍ ሲል ፥ "እረ ሳሙ ናህን አልረሳኸውም! ቅድምም እኮ በግራ እጅህ ይዘኸው ነበር" አለው ።

ሳብር የድንጋጤ ፈገግታ እያሳየ ፥ "በማ ለዳ መኳሳት ጣጣው ይኸው ነው ። ሌሊቱን በሙሉ ከሆቴሉ ውጪ ከባድ ውካታ ይሰማ ስለ ነበር ዓይኔ ፈጠ ነው ያደረው" አለ ። የድንጋጤ ፈገ ግታው ፊቱ ላይ እንደ ተሣለ ወደ ክፍሉ ገባ ።

—ምን ዓይነቱ ነጃሳ ቀን ነው! — አለ ሳብር በሐሳቡ ። በሌላ በኩል ደግሞ ችግሩን ከመጠን በላይ አባብሶ መመልከት እንደማያሻው ተሰማው። ልብሶቹን አንድ ባንድ በጥንቃቄ እያገላበጠ መር ምሮ ለበሰ ። ቀና ብሎ የክፍሉን ጣሪያና ግድግዳ ቃኘ — ልክ ከሊል አልጋው ላይ የተኛ ይመስል ። ሐሳቡ ራሱ ሰውነቱን ስቅጥጥ አደረገው ። መለስ አድርጎ ፥ ምናባቱ ፤ ሰው መግደል እንደሆን

t.me/OLDBOOKSPDF

በእኔ ብቻ አልተጀመረ — በማለት ራሱን ሰማጽ ናናት ሞከረ ። ተነሥቶ ወደ እስክንድርያ ለመሄድ የወጠነው ሐሳቡም የማያዋጣው መሆኑን ተገነ ዘበ ። የተረሳ ነገር ይኖር ይሆን ? መቼም የወን ጀል መረጃ ካላሰበት ቦታ ነው ብቅ የሚለው ። ሳብር ለብሶት የነበረውን ኮት ወደ ላውንድሪ ለመውሰድ አስቦ ፡ ኮቱን ጠቅልሎ ይዞ መውጣቱ አጉል ጥርጣሬ ላይ እንደሚጥለው በመገመት ሐሳ ቡን ሰረዘው ። ዛሬ ከሰዓት በኋላ ወንጀል መር ማሪዎች ፊት ቀርቦ ለሚሰነዘሩለት ጥያቄዎች መልስ መስጠቱ የማይቀር ነገር መሆኑ በግልጽ ታየው ። ሳብር በቀላሉ ከማይወጣበት የወንጀል አዘቅት ውስጥ ገብቶ የተዘፈቀ መሆኑ በምር ተሰማው ። ከዚህም የተነሣ የወንጀሉ ድርጊት ከመታወቁ በፊት ከሆቴሉ ወጥቶ ለመሄድ ቍርጥ ሐሳብ አደረገ ። የኮቱ መጽዳት አለመጽዳት ይህን ያህልም የሚያሳስብ ነገር አይደለም ። ስለዚህ የሆቴል ክፍሉን መለስ ቀለስ እያለ በጥንቃቄ ቃኘው ። እጁን የሚያስይዘው ፍንጭ አንድ ሰርቻ ውስጥ ተሸጉጦ ይሆን? ሳብር ወደ ሆቴሉ የእንግዶች ማረፊያ ከፍል ሲያመራ ፡ መሐመድ አል ሳዊ የማለዳ ጸሎቱን ያደርስ ነበር ። ቁርሱን ለመመገብ ከማዕዶቹ አንዱን መርጦ ሲቀመጥ ፡ እልፍ እልፍ ብሎ ጥቂት እንግዶች ቁርሳቸውን በመመገብ ላይ ነበሩ ። አሊ ሰርያኩስ ሳብር ወደ ተቀመጠበት

t.me/OLDBOOKSPDF

ማዕድ በመቅረብ ፡— "አቶ ሳብር ይህን ዕቃ ረስተኸው ነው ከክፍልህ የወጣኸው" አሉው ።

የተረሳው ዕቃ ቦርሳው ነበር! ኩቴን ከመልበሱ በፊት እያገላበጠ ሲመረምር ይሆናል ቦርሳው ሾልኮ የወደቀው ። ሳብር ቦርሳውን ከፊት አድርጎ ውስጡን ከተመለከተ በኋላ ፡ "በጣም አመሰግን ሃለሁ ፤ አሊ" በማለት ጉርሻ ብጤ አውጥቶ ሰጠው ።

"እልጋህ ሥር ወድቆ ነው ያገኘሁት" በማለት አሊ ሰርያኩስ የተሰጠውን ጉርሻ ተቀበለ ።

—ግና ያልደረስኩባቸው ስንት ስሕተቶች ሠርቼ ይሆን?— በማለት ሳብር በሐሳቡ ማውጣት ማውረድ ያዘ ። ያላሰበው አንዱ ስሕተት እንኳን አሳልፎ እንደሚሰጠውና በሕግ ፊት እናቱ እንደ ወለደችው እርቃኑን እንደሚያስቀረው ተገነዘበ ። አዎን ፡ እናቱ . . . ያች ለዚህ ሁሉ ጣጣ ያበቃችው እናቱ አምጣ ስትወልደው ራቁቱን እንደ ነበረ ። እናቱ በመሞቻዋ ምሽት ተኝታ ታኩርፍና ታን ቋርር እንደ ነበረ ፡ ከሊልም የተገላገለው የሷኑ በመሰለ መንገድ ነበር ። ከሆቴሉ እንግዶች አንዱ እያየው ፈገግ ፈገግ ሲል ከሳብር ጋር ዓይን ለዓይን ተገጣጠሙ ። በልቡ ውስጥ የሚያስላስለውን ሐሳብ ከገጹ ላይ የተረዳ ስለ መሰለው ሳብር ድንግጥ አለ ። የሆቴሉ የእንግዶች መቀበያ ክፍል ውስጥ መቆየቱ ቀፈፈው ። ከሆቴሉ ወጣ እንዳለ የተለመደው የልመና ዜማ ተቀበለው ። ያ አስፈሪና

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀፋፊ ለማኝ በዚማ የታጀቡ ግጥሞቹን ላላፊ ላግዳሚው ያሰማል ። ከሚያገኘው ምጽዋት ይልቅ ነጋ ጠባ አንድ ቦታ ተንልቶ ማዜሙ ደስ ያሰኘው ይሆን? የሆቴሉ በር ጠባቂ መሐመድ አል ሳዊ ከሊልን ከእንቅልፉ ለመቀስቀስ ሕንፃው ጣሪያ ላይ ወደሚገኘው መኖሪያው ክፍል እያዘገመ ነው ።

"አቶ ከሊል ፤ ንግድል ይነሡ! አቶ ከሊል! ኧረ ይነሡ! ኧረ አቶ ከሊል! አይሰሙኝም እንዴ! ከንጋቱ ሁለት ሰዓት ሊሆን እኮ ነው! አቶ ከሊል! ኧረ አቶ ከሊል !..."

በሩን ክፍቶ እንዲገባ የተለመደውን ፈቃድ ከውስጥ ባያገኝም ፡ አል ሳዊ ከውጪ ቆልፎት የሄደውን በር በቀስታ ከፍቶ ከገባ በኋላ ፡ በቀስታ፡ "አቶ ከሊል" በማለት ተጣራ ። መልስ የለም ። ከዚያም አልጋው ላይ ባየው ሁኔታ ክው ብሎ በመደንገጥ ፡ "ኧረ አምላኬ ፤ ምን ጉድ ነው! አቶ ከሊል! ኧረ ጉድ ሆንን! ኧረ ጉድ ሆነናል! አሊ! ያገር ያለህ! የሰው ያለህ! አሊ! አቶ ከሲል ተገድለዋል! ፖሊስ! ኧረ የፖሊስ ያለህ!..." እያለ ጩኸቱን አቀለጠው ።

እናትና አባቱ ተለያይተው እንደ ቀሩ ሁሉ ፡ ሳብርም አባቱን ለማግኘት የለፋው ልፋት ፋይዳ ቢስ ሆኖ ቀርቷል ። የወጣ የማይመለስበት ፡ የተጠፋፋ የማይገናኝበት ጊዜ! ሳብር መጥፋት መጥፋት አለው ። አንዳችም ዱካ ሳይተው ተንሥቶ እብስ ብሎ መጥፋት አሰኘው ... ምናልባት

t.me/OLDBOOKSPDF

ጊዜ ከፈቀደ . . . አንድ ቀን . . . አንድ ቦታ . . . ከከሪማ ጋር ተገናኝቶ ሲመኘው የነበረው የደስታ ፣ የፍስሐና የተደላደለ ኑሮ ቀማሽ ይሆን ይሆናል ።

ሳብር ፣ አላፊ አግዳሚውን አስተውሎ ሳይ መለከት ፣ የማንንም ድምፅ ሆን ብሎ ሳያዳምጥ እግሩ ወደ ወሰደው አቅጣጫ ማዝገሙን ቀጠለ ። አልፎ አልፎ ድካም ሲሰማው ወደ አንዱ የመን ገድ ዳር ቡና ቤት ገራ በማለት ለአጭር ጊዜ አረፍ ይል ነበር ። ሳብር ከእንግዲህ ምን ዕረፍት ይኖረዋል? ከቡና ቤቱ ወጥቶ መንገድ እንደ ቀጠለ ፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሕንፃ ከፊት ለፊቱ ተንጣልሎ ተመለከተ ። ሰማዩ ጠቆርቆር ባለ ደመና መሸፈን ጀምሮአል ። የእስክንድርያ ሰማይ ፤ እስ ክንድርያ ሰማይ ሳይ የሚንጣለለው ከባድ ደመና ትዝ አለው . . .

ከኤልሐም ጋር መተያየት ክፉኛ አሰኘው ። ወደ ማምሻው ሳይ ሁል ጊዜ ወደሚገናኙበት ቡና ቤት አመራ ። ማንኛውም ነገር ከተለመደው የተለየ ሆኖ ታየው ። ውስጣዊ ስሜቱ—የሠራኸውን ሁሉ እንድም ሳታስቀር ተናዘዘ ይውጣልህ እያለ አሳር ያበሳዋል ፤ እውነቱን ተናግሮ የመሸበት ማደር ይሻልሃል እያለ ይወተውተዋል ።

ኤልሐም ሳብርን በሚያማምሩ ዓይኖችዋ በቅሬታ እያየችው ፣ "እርግፍ አድርጎ ለተወኝ ሰው ሰላምታ የምሰጥበት ምክንያት አይታየኝም" አለችው ። መቀመጫው ላይ አረፍ እያለች ፣ "ዛሬማ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብለህ ብለህ አንዲት ቃል የማይተነፍስ ድዳ ሆነ ሃል" አለችው ፡ ሁኔታው ግራ ያጋባት መሆኑን በሚመሰክር አስተያየት ገልመጥ እያደረገችው።

"በጣም አጥፍቻለሁ ፤ ኤልሐም ። ሥራ በዝ ቶብኝ ስለ ሰነበተ ድካም ነው ያፈዘዘኝ ። "

"ስልክ መደወል እንኳን እንዴት ያቅትሃል?"

"ስልክ መደወሉም አቅቶኝ ነው የሰነበተው ። ለማንኛውም ጭቅጭቁን እናቁምና ዓይንሽን ባይኔ ልቃኘው ። "

ሁለቱም ቃላት ሳይለዋወጡ ዓይን ለዓይን በመተያየት ብቻ ዝም ብለው ተቀመጡ ። ሳብር ኤልሐምን ማየት ያሰኘው ለምን እንደሆነ ካጎ ኛት በኋላ ማወቅ አልሆነለትም ። ምናልባት ዓይ ኑን አፍጥጦ ከሚጠበቀው አደጋ ከለላ እንድ ትሆነው አስቦ ይሆን? ምኑንም የማታውቀው ኤልሐም በደም የተበከለ እጁን በመጨበጥ ሰላ ምታ ሰጥታው ዓይን ዓይኑን በፈገግታ እያየች አገር ጤና መስኟት አጠገቡ ተቀምጣለች ። ሳብ ርን ነገር ዓለሙ ከበደው ። ዓይኖቹ እንባ አቀ ረሩ . . . የመሰነባበቻ እንባ ።

"ክራኝ የደከመህ ትመስላለህ" አለችው ።

"አየሁት እኮ!" አላት ሳብር ፡ በሹክሹክታ ።

"ወንድምህን?"

"ሰይድ ኤል ራሐሚን ። "

"ቀናሃ!" አለችው ፡ በደስታ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ታሪኩን በትካዜ አወራላት ።

"ያየኸው ሰውዬ ወንድምህ ሊሆን ይችላል" አለችው ፡ ተስፋ በሚያጭር ስሜት ።

"ላይሆንም ይችላል ። "

"ይኸ ፍለጋህ መቼ ነው የሚያበቃው?" አለችው ፡ ቁርጡን እንዲነግራት በመለማመጥ ።

"በእኔ በኩል አብቅቷል ። "

"ኧረ እባክህ በጣም ደክሞሃል!"

"ከብዙ ሰዎች ጋር ስወያይ ነው የሰነበትኩት ። "

"ስለ ወንድምህ ግዴይ?"

"አዎን ። "

የቀረበላቸውን ጭማቂ በጸጥታ ጠጡለት ። ኤልሓም ፊትዋን በፈገግታ ወግግ አድርጋ ፡ "እኔ ትዝ ብዬህም አላውቅ ማለት ነዋ?" ስትል ጠየቀችው ።

"ከሐሳቤ ተለይተሽም አታውቂ ። "

"አትዋሸኝ እባክህ!"

ኤልሓም ቁስሉን ነካችበት ። ሳብር ወንድ ወጥቶት እውነቱን አፍረጥርጦ መቼ ነው የሚነግራት ? ከማስመሰልና ከመዋሸት መገላገያው መቼ ይሆን?

"ምን ዘጋህ ታዲያ ?" አለችው ፡ እየተቅለ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለሰች ። "ባለፈው ጊዜ እዚሁ ካይሮ ውስጥ አንድ ዓይነት ሥራ እንድትጀምር ተነጋግረን ነበር እኮ ።"

—የመጣው ይምጣ ፤ ልንገራትና ልረፈው! ሆዴ የተሸከመውን ልናዘዘውና ይወጣልኝ ፤ አፍኜ ይገፍ እስከ መቼ እዘልቀዋለሁ — እያለ በልቡ ሲያስብ ኤልሐም ለተናገረችው መልስ አለ መስጠቱ ስለ ታወሰው ፡ "እምን ፡ ተነጋግረን ነበር። አልረሳሁትም" አላት—በጥድፊያ ።

"የወንድምህ ፍለጋ ምን ጊዜ ሰጥቶህ ታስታውሰዋለህ!"

"እረ ስለ ሥራውም ሳወጣ ሳወርድ ነው የሰነበትኩት ። "

ሳበር ስሜቱ ገነፈለበት ። እንደ መሰንበቻው አምቆ ሊይዘው አልቻለም ። ወጣለት!

"ኤልሐም! እወድሻለሁ ። ከልብ እወድሻለሁ ። ከተገናኘንበት ዕለት ጀምሮ ስነግርሽ የነበረው ሁሉ ውሸት ነው!"

"ምንድን ነው የምታወራው ?" አለችው ኤልሐም ግራ በመጋባት ።

"እንድዋሽ ያደረገኝ ላንቺ ያለኝ ፍቅር ነው ።"

"የምትለው ፈጽሞ አልገባኝም !" አለችው ፡ ውብ ፊትዋ ልውጥውጥ እያለ ።

"ካይሮ ውስጥ በመፈለግ ላይ ያለሁት ወንድሜን እንደሆነ ነግሬሻለሁ ። ውሸት ነው ፤ የጠፋብኝ ወንድሜ ሳይሆን አባቴ ነው !"

t.me/OLDBOOKSPDF

"አባቴ?!"

"አዎን ፡ አባቴ!"

"አባትህ እንዴት አድርጎ ሊጠፋ ቻለ?" አለችው ።

"ከልጅነቴ ጀምሮ ወላጅ አባቴ መሞቱን አምኜ ነበር የተቀመጥኩት ። ነገር ግን እናቴ ከመ ሞትዋ በፊት አባቴ በሕይወት መኖሩን ነግራኝ እንድፈልገው አደራ አለችኝ ። "

"የጠፋው ወንድምህም ሆነ አባትህ ያሰብ ነውን ከመፈጸም አያግደንም" አለችው ኤል ሐም ፡ ሳብርን ውኃ ሰማያዊ በመሰሉ ውብ ዓይ ኖችዋ አትኩራ እያየችው ።

"ሙልጭ ያልኩ ድሃ ነኝ!" አለ ሳብር ጮክ ብሎ ። "እንደ ዋሽሁልሽ ሳይሆን ቤሳ ቤስ ቲን የሌለኝ ድሃ ነኝ ። እርግጥ እናቴ ሀብታም ነበረች ። እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ እንደ ልቤ ተንደላቅቄ ኖሬአለሁ ። በመጨረሻ እናቴ ስት ሞት ያወረሰችኝ የጋብቻዋን የምስክር ወረቀትና ከሠላሳ ዓመት በፊት ከአባቴ ጋር የተነሣችውን ፎቶግራፍ ብቻ ነበር ። ከዚህ በተረፈ አንዳችም ነገር የለኝም!"

ኤልሐም ሁኔታው ሁሉ ይሆናል ብላ ያል ገመተችው በመሆኑ ድንጋጤውና መገረሙ ደበ ታት ። የእናቱን ታሪክ ብትሰማ ምን ይሰማት ይሆን?

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምነው ተከዝሽ?" አላት ፡ በማስተዛዘን ።

"አልተከዝኩም ። እንዲያው ሁኔታው አስደ ንቆኝ ነው ። "

"ኤልሐም ፤ እሄ ለአንቺ የምመጥን ሰው አይደለሁም ። ላይሆንልኝ በባዶ ሜዳ ስደልልሽ መቆየቴ ያሳዝነኛል ። "

"ሁኔታው በመሉ ይገባኛል ። ውሸት የተና ገርክበትንም ምክንያት አረዳዋለሁ ። "

"ከሁሉም በላይ የሚቆጨኝና አንጀቴን ሲያሳርረው የሚኖረው በአንደበቴ ደልዬሽና ዋሽ ቼሽ እንድትወጂኝ ማድረጌ ነው ። "

"ለእኔ ያለህ ፍቅርም ውሸት ነው ማለት ነው?"

"ሬጽሞ! እንዴት ተደርጎ! ከልቤ ነው የማ ፈቅርሽ ፡ ኤልሐም!"

በረጅሙ ተነፈሰች። "እውነቱን አውጥተህ እን ድትነግረኝ የገፋፋህ ለእኔ ያለህ ፍቅር መሰለኝ ። "

"አምን ፤ ነው እንጂ . . . "

"እንዲህ ከሆነ ፡ እውነቱን ሸሽገህ በመያዝህ ምንም አላጠፋህም ። "

"ከእንግዲህ መለያየታችን መሆኑ ነው?"

"ለምን?" ብላ በመጮህ የሚተናነቃትን ምሬቅ ዋጥ አደረገች ።

"እጄ ባዶ ነው ፤ የሚረዳኝ የለኝም ፤ እንደ እኔ ያለ መናጢ ድሃ ምን ፋይዳ አለው!"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ቁም ነገሩ ገንዘብ አይደለም ። ከሰው የሚ ገኘውም ዕርዳታ እስከዚህም አያወላዳም ። እን ተው ራስህ ልትሠራው የምትችለው ብዙ ነገር አለ ።"

"እንጂ ፣ አይመስለኝም ። ትምህርት የለኝ ፤ ያካበትኩት የሥራ ልምድ የለኝ ፤ በሕይወቴ ሥራ የሚባል ነገር ይገር አላውቅ . . . አባቴን ካላገኘ ሁት ምንም ተስፋ የለኝም ። "

"አባትህ ችግርህን ሁሉ እንደሚያስወግድ ልህ ታምናለህ ማለት ነው ?"

"እናቴ ሀብት የተረፈው ሰው መሆኑን ነግ ራኛለች ። "

ኤልሐም ለጥቂት ደቂቃዎች ጸጥ ብላ ከቆ የች በኋላ ፣ "ያ ሁሉ የጋዜጣ ማስታወቂያ . . .ያ ሁሉ የቴሌፎን ጥሪ . . . ወጪቱ . . . "

"እውነትሽን ነው ። ምንም አልፈየደም ፤ ምንም ውጤት የለውም ። አባቴ የኮቻለው ሰው መሆን ቀርቶ ከይሮ ከተማ መኖሩንም አጠራጠ ራለሁ ። ምናልባት ከካይሮ ወጪ በአንዱ ክፍለ— ሀገር ውስጥ ሊኖር ይችል ይሆናል ። "

"ምነው ትናንት አየሁት ብለኸኝ!"

"ያየሁት መስሎኝ ነበር ። ከእንግዲህ የማ ውንም የማምን አይመስለኝም ። "

"ታዲያ እስከ መቼ ነው በዚህ ሁኔታ የምት ቆየው ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ፍለጋወም ሆነ ዓይን አጥጦ መጠበቱ በቅዶኛል ። "

"በቅዶህስ?"

"ምን እንደማደርግ እንኳ ። መግቢያ መውጫው ዝግትግት ነው ያለብኝ ። ወዳገሬ ተመልሼ አንድ ሥራ ፈልጌ መያዝ አለብኝ . . . አሰ በለዚያ ያለኝ አማራጭ ሕይወቱን በገዛ እጁ ማጥፋት ነው . . . "

"እወድሻለሁ ስትለኝ የነበረው ሁሉ ከንቱ ነዋ!" አለችው ኤልሐም ፡ ከንፈሮችዋን ንክሰ፡ አድርጋ እንባ ያጋቱ ዓይኖችዋን እየጨመቀች።

"ከንቱስ አይደለም ፡ ኤልሐም። ከልቤ ካንጀቱ እወድሻለሁ ። "

"እሄዳለሁ ፤ ራሴን እገድላለሁ እያልክ ምኑን ወደድከኝ?"

"ኤልሐም ፤ የምይዘው የምጨብጠው ነው የጠፋኝ ። ሕይወቱ በቀስታ በሥቃይ በማለፍ ላይ እንዳለች ሰው ነው የሚሰማኝ ።"

"እወድሻለሁ ብለኸኛል ፤ እኔም እወድሃለሁ እኮ!"

ጭንቀትና ተስፋ መቁረጥ ፊቱ ላይ ረበበ በት ። "ኤልሐም ፡ እኔ ላንቺ የምመጥን ሰው አይደለሁም" አላት ።

"መታገሥ አለብህ ፡ ሳብር" አለችው ፤ "እኔም ከጐንህ ሆኜ የተቻለኝን ሁሉ አግዝሃለሁ ። "

t.me/OLDBOOKSPDF

"የእኔ ነገር አብቅቶለታል። እኔን ጉድ ያደረገኝ አባቴን አገኛለሁ የሚለው የቁም ሕልሜ— ይህንኑ ሕልሜን የሙጭኝ ማለቴ ነው።"

"ሥራ፡ ሥራ፤ የችግራችን መፍትሔው ሥራ ነው!"

"ልሠራው የምችለው ነገር አለመኖሩን ነግሬሻለሁ እኮ!"

"እስቲ ለማንኛውም በጉዳዩ እንዳስብበት ጊዜ ስጠኝ። ማንኛውም ነገር እንዳሰብነው እንደሚሆን ተስፋ አለኝ።"

—የከሊል መገደልስ? የሱ ጣጣ እያለ ነው ያሰብነው የሚሳካው? የማይሆን ነገር . . . ከንቱ ልፋት! ኤልሐም እኮ፡ በሆዴ ውስጥ ሸሽጌ የሰነበትኩትን ምስጢር ጉልጉዬ የነገርኳት ይመስላት ይሆናል። ዋናው ጉድ ገና መች ተወርቶ!— አለ ሳብር በሐሳቡ።

"ኤልሐም፤ ያሰብነው እንዳሰብነው ሊሳካ አይችልም" አለ፡ በርጋታ።

"ግድ የለህም፤ አንድ ሁለት ቀን ታገሠኝ" አለችው፡ አጠንክራ።

ሳብር የእናቱን ታሪክ ዘርዝሮ፡ ከአንድ ቀን በፊት የፈጸመውን ድርጊት አንጠርጥሮ ሊነግራት ቃጣው። በደም ማኅተም የጸና ግንኙነት ከአንዲት ሌላ ሴት ጋር መፈጸሙንም ሊናዘዝላት ዳዳው። በዘያች ቅጽበት፡ እፊትዋ ቆሞ መጮህ፡ ኡኡ ማለት፡ አካባቢውን በእሪታ ማደባለቅ ከጀለው. . .

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

ሳብር እንደ ፈራው ፖሊሶች ወንጀሉ ከተ ፈጸመበት ስፍራ ደርሰው ምርመራቸውን አጧ ጠፈው ታል ። የተሠራውን ወንጀል አገር አው ቆታል ፤ የቀረ ነገር በኖር የወንጀለኛው ማንነት ብቻ ነው ።

ሳብር ከእንግዴህ ወደ ኋላ ማለት አይቻለ ውም ። ከሲል ሲሞት ያሳየውን የሰውነቱን መኰ መታተር ፡ የፊቱን መጨመታተርና የድምፁን መን ቋረር ወዲያ ረሱት ፡ ማንኛውንም ነገር እንዳላየና እንዳልሰማ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል ። ወደ ሆቴሉ ሲመለስ የተሰማው ፍራቻና ሥጋት ሰው ነቱን አርበትብቶ እንደ ወጣ እንዲቀር ገፋፍቶት ነበር ። የፈሰሰ ውኃ ስለማይታፈስ ፡ እንደ ምንም ተበራት ወደ ሆቴሉ ለመመለስ ቈረጠ ። በእነ ባበ ው ተክማችተው ሁኔታውን በመከታተል ላይ ባሉት በርካታ ሰዎች መካከል ተሸሸክልኮ በማለፍ ወደ ሆቴሉ ሲቃረብ አንድ ፖሊስ አቆመው ።

"ምንድን ነው ግርግሩ? የሆቴሉ እንግዳ ነኝ"

t.me/OLDBOOKSPDF

አለ ሳብር ። ሦር ብሎ ሲመለከት የሦቴሉ በር ጠባቂ መሐመድ አል ሳዊን ፊቱ በእንባ ርሶ አየው ።

"ሳዊ ፡ ምንድን ነው የተፈጠረው?"

አል ሳዊ ስቅስቅ ብሎ በማልቀስ ፡ "አቶ ከሊልን ገደሏቸው !" አለው ።

"ገደሏቸው ? አይደረግም !"

"አልጋቸው ላይ እንደ ተኙ ነው ተገድለው የተገኙት ። ገዳዩን እግዜር ይፍረድበት ። "

የሦቴሉን የእንግዶች ማረፊያ ፖሊሶችና ወንጀል መርማሪዎች ሞልተውታል ። ከሊል ወንበር ላይ የወንጀል ምርመራውን የሚመራው መኰንን ተቀምጧል ፤ ከአጠገቡ ከማተለየው ከሪማ ወንበር ላይ ደግሞ አንድ ሌላ ሰው ቁጭ ብሏል ። የምር መራው መሪ መኰንን በርከት ያሉ ሰነዶችን እያገላበጠ ይመለከታል ። ከሦቴሉ እንግዶች አንዱ ከፊት ለፊቱ ካለው ወንበር ላይ ተቀምጧል ። ሳብር የምርመራውን መሪ መኰንን አተ ኩሮ ሲመለከተው መልኩ አባቱን ቀርጥ መስሎ ታየው ። በድንገት የተሰማው ድንጋጤ ሰውነቱን በመላ አብረከረከው ። ወዲያው ደግሞ ፡ መኰንኑ በዕድሜው ከአባቱ በጣም የሚያንስ መሆኑን ሲረዳ ድንጋጤው ለቀቅ አደረገው ። ሰሞኑን ያለፈው ያገደመው ሁሉ አባቱን እየመሰለው መቸገር ይሠል ። ተነሥቶ ወደ ክፍሉ በመሄድና አርፎ በመቀመጥ መከከል ሐሳቡ ይዋዥቅበት ጀመር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ማድረግ ያለበትን ነገር በሐሳቡ ውስጥ ለጥ ቂት ደቂቃዎች ካስተናገደ በኋላ ፡ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ፎቁን ለመውጣት መንገድ ሲጀምር ፡ ከሪማ ወንበር ላይ ተቀምጠ የነበረው ሰውዬ ፡ "እዚሁ ብትቆይ ይሻላል" አለው ።

የጀመረውን መንገድ አቋርጦ ወደ እንግዶች ማረፊያ ክፍል በመመለስ ስፍራ ፈልጎ ከሦቱ እንግዶች ጋር ተቀላቅሎ ተቀመጠ ።

"ነገሩ ምንድን ነው?" በማለት ፡ ሳብር አጠገቡ የተቀመጡትን ሰዎች ጠየቃቸው ።

"አቶ ከሊል ተገድለው ተገኝ ተብለናል ።"

"እንዴት ሊሆን ይችላል?"

"ማን አወቀ ። ፖሊሶች ምርመራው እስኪ ጠናቀቅ ከዚህ እንዳትንቀሳቀሱ ብለውን ተቀ ምጠናል ። ሞቴሉን በሙሉ ሲፈትሹ ነው የዋ ሉት ። "

ሳብር ከአቅራቢያው የመንሰቅሰቅ ድምፅ ሰማ ። ዞር ብሎ ቢመለከት ፡ ከሪማ እርሱ ከተቀ መጠበት ትይዩ ሑርምት ብላ ተቀምጣለች ። ከግራና ከቀኝዋ አንዲት አሮጊት ሴትየና አንድ በዕድሜ የገፉ ሰውዬ ቁጭ ብለዋል ። ሲገባ እን ዳልተመለከታት ገረመው ። ማድረግ የሚገባውን ነገር ለጥቂት ጊዜ ካሰላሰለ በኋላ ፡ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ወደ ከሪማ በመቅረብ ፡ "እመቤቴ ፡ ልባዊ የሆነ የዘንዎ ተካፋይነቴን እገልጽልዎታለሁ ። እግዚር ብርታቱን ይስጥዎ" አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሪማ ቀና ብላም ሳትመለከተው እየቸንሰቀ ሰቀች ማልቀስዋን ቀጠለች ። ሳብር የተፈጸመው ወንጀል ስሜቱን የነካው መሆኑን በሚገልጽ ሁኔታ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ ወደ መቀመጫው ተመ ለሰ ። ወዲያው ደግሞ ፡ —አሁን ምን አቅብጠኝ ነው ከሰው መካከል ተስፈንጥሬ ተነሥቼ የነዘን መግለጫ ያቀረብኩት ? አጠገብዋ የተቀመጠችው አሮጊት የዚያች የእስክንድርያዋ ወዳጄ እናት ትሆን ? በእሁኑ ጊዜ ፖሊሶቹ ምን እያሰቡ ይሆን? ክፍል ቁጥር አሥራ ምስትን ተከራይቶ ስለሚኖረው እን ግዳ ጥያቄዎችን አቅርበው ይሆን? ሦቴሉ ውስጥ ከገ ባሁበት ጊዜ ጀምሮ ትከረታቸውን አሳርፈው ብኝ ይሆን? እኔ የጋለሞቶችን ጠባይ አብጠርጥሬ እንደማውቅ ፡ ፖሊሶችም የወንጀለኞችን ባሕርይ አፍረጥርጠው መረዳት ይችሉ ይሆን ?— የሚሉ የሐሳብ ድሮች አዕምሮው ውስጥ እየተወሳሰበ አስቸገሩት ። ከዚህም የተነሣ ፡ በዚያ ሦቴል ውስጥ የተከማቹትን ፖሊሶችና ወንጀል መርማሪዎች ጥልት አደረጋቸው ። ከሰማይ አንድ መዓት ወርዶ እንዲ ጨርሳቸው በልቡ ተመኘ ።

"እስክ መቼ ነው እዚህ የምንቀመጠው ?" በማለት አጠገቡ የተቀመጡትን እንግዶች ጠየቀ— ሳብር ።

"አንተኮ ከመጣህ ገና ጥቂት ደቂቃዎች ማለፋ ነው ። እኛ ከጠዋት ጀምሮ እዚህ ነን ።"

"ከሦቴሉ እንግዶች መካከል ጥያቄ የቀረበላ ቸው አሉ ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"አዎን ፡ ተጠይቀው እንዲሄዱ የተፈቀደላቸውም አሉ ። እኛም ተራችንን እየጠበቅን ነው ። ባለቤቲቱ ፡ የባለቤቲቱ እናትና አጎትዋ ሳይቀሩ ተመርምረዋል ። "

"ወንጀሉ ሲፈጸም ባለቤቲቱ እዚህ የነበረች አልመሰለኝም ። "

ያልተጠየቀውን መወትወት መጀመሩ ሳብርን አሰበረገገው ።

እንግዳው ንግግሩን በመቋጨል : " የባለቤቲቱ እዚህ መኖር አለመኖር ወንጀሉን በሚመለከት ምንም ፋይዳ የለውም ። ይህ ሆቴል እንደ ሆነ ብዙ ጉድ የተሰገሰገበት መሆኑ እየተገለጠ መጥቶአል ። ክፍል ቁጥር ስድስት ውስጥ ፖሊሶች መዓት ሐሺሽ አግኝተው ክፍሉን የቱከራ የወን ሰውዬ ይዘውታል ። ክፍል ቁጥር ሦስት ውስጥ ደግሞ አንድ የታወቀ ሌባ ተይዟል ። "

"እንዲህ ከሆነማ . . . "

"አንተ እንደምታስበውም ሊሆን ይችላል . . . ዋናው ጥያቄ ግን ፡ ወንጀሉ ሲፈጸም የቻለው በምን ምክንያት ነው ? የሚለው ነው ። "

"ምክንያቱ ዘረፋ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም!" አለ ሳብር ።

ሳብር ፡ አሁንም የማያገባው ጉዳይ ውስጥ ጥልቅ ብሎ አስተያየት መስንዘሩና አፉ እንዳመጣለት መዘላበዱ ጥርጣሬ ላይ እንደሚጥለው ተሰ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማው ። ፖሊሶች እጇን የሚያሲዘውን መረጃ አግ ኝተው ሊሆን ይችላል የሚልም ጥርጣሬም ገባው ። በሴላ በኩል ደግሞ ፥ ከከሪማ ጋር ተግናኝቶ ለመ ነጋገር ፍላጐት አደረበት ። አሥሬ እርሷ ወደ ተቀ መጠችበት አቅጣጫ ሰረቅ እያደረገ ይመለከታል ። ከሪማ ጠቃሚ የሆነ መረጃ ልትሰጠው እንደምት ችልም ገምቷል ። ይኽ ለማኝ ደግሞ ዜማውን አሁ ንም አላቋረጠም ።

የወንጀል ምርመራው መሪ መኰንን አሁ ንም አባቱን አስታወሰው ። ለምን ይሆን ? ከሦ ቴሉ እንግዶች እንዱ ፥ "እኛ እንደሆን ንጹሐን ነን ። ቢሆንም ምን እንባል ይሆን ? እያልን ልባ ችን ተንጠልጥሏል ። እኛ እንዲህ በሐሳብ የተሠ ቃየን ወንጀሉን የፈጸመው ሰው እንዴት ይጨ ንቀው ?" በማለት ሳብርን ከሐሳቡ አነቃው ።

እንድ ሌላ የሦቴሉ እንግዳ ቀበል በማድረግ ፥ "እንዴት ያልሆነች ቃል ከአፋችን ማምለጥ ብዙ ጣጣ ልታስከትልብን እንደምትችል አውቀን ፥ ከአ ጉል መዘላበድ ጠንቀቅ ማለት ይኖርብናል" አለ ።

"አታስብ እባክህ ፤ ከወንጀል ድርጊት እጁ ንጹሕ የሆነ ሰው ምን ጊዜም ክፉ ነገር አጋጥ ሞት አያውቅም" አሉ ሦስተኛው የሦቴሉ ነዋሪ ።

"ነው!?" አለ ሌላው በምዕት ።

ወንጀለኛ ሰው የሠራው እኩይ ተግባር ከሚያስከትልበት ቅጣት ሲያመልጥ ብዙ ጊዜ ታይቷል ። የሳብር እናት የፈለጓትውን ሠርታ ለረ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጅም ጊዜ ማን ነካት ? የወንጀልዋ ተባባሪ የነበረው ሰውዬ የሰው ነፍስ አጥፍቶ ወደ ጐረቤት አገር ሲያመልጥ ማን ዞር ብሎ አየው ? ዋናው ነገር ሳብር ወደ ሆቴሉ መመለስ አልነበረበትም ። ሌላ መውጫ መንገድ ፡ ሌላ ማምለጫ ዘዴ መፈለግ ነበረበት ። ከገባበት የወንጀል ማጥ ለመውጣት ደግሞ ፡ የአባቱ መገኘት ከምን ጊዜውም የበለጠ የሚያስፈልገው አሁን ነው ።

የሆቴሉ እንግዶች አንድ በአንድ እየተጠሩ ስለ ወንጀሉ ይጠየቁ ጀመር ። የሳብርም ተራ ደርሶ ወንጀል መርማሪው መኰንን ፊት ቀረበ ። ሳብር መኰንኑን ከፋኝ ጥልት አደረገው ። በተቻለው ሁሉ እጁን ሳልማስያዝ በሐሳቡ ወሰነ ። መርማሪው መኰንን የሳብርን የመታወቂያ ወረቀት እያገላበጠ በጥንቃቄ ተመልክቶ ሲያበቃ፡—

"የሆቴሉ መዝገብ እንደሚያስረዳው ከሆነ እዚህ ሆቴል ውስጥ ከአንድ ወር በላይ ተቀም ጠሃል" አለው ።

መኰንኑ አባቱን እንደማይመስል አሁን ደህና አድርጎ አረጋገጠ ። "በተለመደው ሰዓት ተነሥቼ ፡ ልብሴን ለባብሼ ቁርሴን ለመመገብ ወደዚሁ መጣሁ" በማለት መለሰ ሳብር—ያልተጠየቀውን ።

"በተለመደው ሰዓትማ አልተነሣህም ። ማል ደህ ነው የተነሣኸው ። "

"በአንድ በተወሰነ ሰዓት አይደለም የም ነሣው ። "

t.me/OLDBOOKSPDF

"የሆቴሉ ሠራተኛ እንደ ነገረን ከሆነ ዛሬ ጠዋት የተነሣኸው ከወትሮው በጣም ማልደህ ነው ።"

"በሌላ ቀን የምነሣበትን ሰዓት አያውቅ ይሆናል ። "

"ሌሊት የሰማኸው የተለየ ነገር ነበር ?"

"ምንም አልነበረም ። ወደ ክፍሌ ገብቼ እንደ ተኛሁ ወዲያው ከባድ እንቅልፍ ይዞኝ ሄዶ ምንም ሳልሰማ ነው ያደርኩት ። "

"ጠዋት ስትነቃ ከወትሮው የተለየ ነገር አላጋጠመህም ?"

"አላጋጠመኝም ። "

"ከሆቴሉ ሠራተኛ ከአሊ ሰርያኩስ ጋር በስንት ሰዓት ተገናኛችሁ ?"

"ጠዋት ከመጸዳጃ ቤት ስመለስ ። "

"በእርሱ ላይ ያየኸው የተለየ ነገር ነበር ?"

"ከወትሮው የተለየ ምንም ነገር አላየሁበትም ። "

"ስለ ራስህስ? ያልነገርከኝ ምንም ነገር የለም ማለት ነው ?"

"ምንም የለም ። "

" ቦርሳህን ክፍልህ ውስጥ ረስተህ አልወጣህም ?"

"አዎን ፤ ቦርሳዬን ክፍሌ ውስጥ ጥዬ ወጥቼ ነበር ። አሊ ሰርያኩስ ነው ያመጣልኝ ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ቦርሳህን ይዞልህ ሲመጣ ምን ተሰማህ?"

"ደስ አለኝ ። "

"ሌላስ ?"

"ሌላ ምን ይኖራል ?"

"አሊ ሰርያኩስ ቦርሳህን ይዞልህ በመም ጣቱ ታማኝነቱ . . . ትንሽም አላስደነቀህም ?"

"እኔ እንጃ . . . ትዝም አይለኝ . . . በነገሩ እምብዛም አላሰብኩበትም ። "

"በነገሩ ማሰቡ የተለመደ አይመስልህም ?"

"በመጠኑም ቢሆን ሁኔታው ሳያስደንቀኝ አልቀረም ። "

"በመጠኑም ቢሆን?"

"አዎን ፤ ጉዳዩ ይህንንም ያህል ትኩረቴን አልሳበውም ። "

"ስታስበው ፡ አሊ ሰርያኩስ ምን ያህል ታማኝ ሰው ይመስልሃል?"

"በበኩሌ ታማኝ አይደለም የሚያሰኝ ነገር ሲፈጽም አላየሁም ። "

"ጠዋት ከሆቴሉ ወጥተህ እስከ ተመለስክ በት ጊዜ ድረስ የት ነበርክ ?"

"በየቦታው ስዘዋወር ነው የዋልኩት ። "

"ሥራ የለህም ፡ አይደለም ? ሥራ የሌለህ መሆኑ መታወቂያ ወረቀትህ ላይ በግልጽ ሰፍሯል ። ዘመድ አዝማድስ አለህ ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ካይሮ ውስጥ ምንም ዘመድ የለኝም ።"

"ትናንት ከሆቴሉ ወጥተህ የሄድከው በስንት ሰዓት ነው ?"

"ከጠዋቱ በአራት ሰዓት ላይ ። "

"በስንት ሰዓት ተመለስክ ?"

"ዕኩለ ሌሊት ላይ ። "

"ቀኑን ሙሉ ሳትመለስ ነው የዋልከው ማለት ነዋ?"

"አልተመለስኩም ። "

"እዚህ ሆቴል ውስጥ ካረፍክበት ቀን ጀምሮ ጠዋት ወጥተህ እትመለስም ማለት ነው?"

"ከዚህ ቀደም አንድ ሁለቴ መመለሴ ትዝ ይለኛል ። "

"አንዴ ከወጣህ መመለስህን የሚያስታውስ ሰው አላጋጠመንም ። "

"እኔ ራሴ ደህና አድርጌ አስታውሳለሁ" አለ ሳብር ፣ ቄጣ ብሎ ።

"አንድ ሁለቴ አልከኝ ?"

"ምናልባት ሁለቴ ። "

"ለመሆኑ ምን ስትሠራ ነው የምትውለው?"

"በየቦታው በመዘዋወር ። ለአገሩ እንግዳ ስለ ሆንኩ የሚያጋጥመኝ ነገር ሁሉ ለእኔ አዲስና ብርቅ ነው ። "

t.me/OLDBOOKSPDF

"ስትመለስ ያጋጠመህ ነገር ነበር ?"

"የሆቴሉን በር ጠባቂ መሐመድ አል ሳዊን እዘሁ ተቀምጠ ፤ ተላላኪው አሊ ሰርያኩሰን ደግሞ ካረፍኩበት ክፍል በር ፊት ለፊት ቆሞ አግኝቼዋለሁ ። "

"አሊ ሰርያኩስ ምን ይሠራ ነበር ?"

"እኔ እንጂ ፤ የምፈልገው ነገር እንዳለ የጠ የቀኝ መሆኑ ይታወሰኛል ።"

"ከሆቴሉ ነዋሪዎች መካከል ያዩህ አሉ ?"

"እንጂ ፡ እንደምገምተው ግንም አላየኝም ።"

"ትናንት ከጠዋቱ አራት ሰዓት እስከ ምሽቱ ስድስት ሰዓት ምን ስትሠራ ዉለህ አመሸህ ?"

"እስከ ምሳ ሰዓት ስዘዋወር ነበር ።"

"ምሳህን የት ተመገብክ ?"

"ከሎት ቤይ ጐዳና ዳር ከሚገኝ አንድ ግሮሰሪ ውስጥ ነው ምሳዬን ሳንድዊች የተመገብኩት ። "

"የጠቀስከው ግሮሰሪ ፡ እንዳንተ ያለ 'በገዛ ሀብትና ንብረቴ ነው የምተዳደረው ' የሚል ሰው የሚመገብበት ስፍራ እንኳን አይደለም ። "

ሳብር በመኰንኑ ላይ ያደረበት ጥላቻ ሥር እየሰደደ ሲሄድ ተሰማው ።

"አሁን የጠቀስከትን ግሮሰሪ ድንገት ያገኘህት ካይሮ የገባሁ ዕለት በመሆኑ በጣም ነው የተለማመድኩት ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ከምሳስ በኋላ ምን አደረግህ?"

"አባይ ወንዝ ዳር ስንሽራሸር ነበር ።"

"የትናንቱ አየር ለሽርሽር የሚመች አል ነበረም እኮ ?"

"የእስክንድርያ ተወላጅ መሆኔን ረሱት እንዴ?" አለ ሳብር ፡ ፍርሐቱንና ጥሳቻውን በማቅ ለመሸፈን እየሞከረ ።

"ከዚያስ ?"

ሳብር የሚያዘወትረውን ቡና ቤት ለመጥ ቀስ አስቦ ኤልሓምን ጣጣ ውስጥ መክተት ስላል ፈለገ ፡ እስክንድርያ ከተማ በሚገኘው ሜትሮ ሲኒማ ቤት ያየው ፊልም ትዝ ስላለው ፡ "ሜትሮ ሲኒማ ቤት ገባሁ" አለ ፡ ፈጠን ብሎ ።

"በስንት ሰዓት?"

"አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ።"

"በዕለቱ የታየው ፊልም ማን ይባላል?"

" 'በደመናዎች አናት ላይ'የሚባለው ነበር።"

"ከምሽቱ ሦስት ሰዓት በኋላ ምን አደረግህ?"

"እንደ ተለመደው ከተማ ውስጥ መዘዋወሬን ቀጠልኩ ። ከዚያም ወደ ሔልዮፖሊስ በሚሄደው አውቶቡስ ተሳፍሬ እስከ መጨረሻው የአውቶቡስ ፌርማታ ጊዜ ለመግደል ተንዝዤ ።"

—መግደል ? ምን ዓይነት አጉል የቃል ምርጫ ነው !—አለ ሳብር በልቡ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እራት የት ተመገብክ ?"

"ሲኒማ ቤቱ ውስጥ ሳንድዊች ከተፈላ ቸኮላት ጋር ተመገብኩ" አለ ሳብር ፡ መርማሪው መኰንን ወጥመድ ውስጥ ላለመግባት እየተጠነቀቀ ።

"በዕለቱ የተገናኘኸው ሰው አልነበረም ?"

"አልነበረም ።"

"እዚህ ከተማ ውስጥ የምታውቀው ሰው አለ?"

"ኧረ ማንንም አላውቅ!" ሳብር ለጥቂት ጊዜ ከመነታ በኋላ ፡ "ስፈንክስ የተባለውን ጋዜጣ የማስታወቂያ ክፍል ኃላፊ አነጋግሬ ነበር ። የግሌ የሆነ ጉዳይ ነበረኝ ።" ቃሉ ከአንደበቱ ሳያስበው ከወጣ በኋላ ፡ የኤልሐምን ስም የሚያስጠራ እንዳይሆን በማለት ሥጋት አደረበት ።

"ከእስክንድርያ ወደ ካይሮ የመጣህበት ምክንያት ምንድን ነው?"

"ዝም ብሎ ለጉብኝት . . . በቱሪስትነት ማለት ይቻላል . . ."

"ታዲያ እንዳንተ ያለ የግል ሀብትና ንብረት ያለው ቱሪስት ይሆን በመሰለ ሆቴል ውስጥ ያርፋል ?"

"በበኩሌ ገንዘብ የሚቆጥብ ሆቴል ሆኖ አግኝቼዋለሁ ።"

"እንደምትለው ፡ የግል ሀብትና ንብረት ያለህ ሰው ነህ ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"አለኝ እንጂ..."

"ወደ ካይሮ የመጣህበት ዋና ዓላማ በእርግጥ ለአገር ጉብኝት ነው?"

ሳብር የምርመራው ሽምቀቆ እየጠበቀ በመሄድ ላይ መሆኑ ተሰማው። አሥሩን መቀላመዱ የማያዋጣው መሆኑን መረዳት አላዳገተውም። ወንጀሉን ለመፈጸም ባቀደበት ወቅት ይኸ ሁሉ ጥያቄ ይቀርብልኛል ብሎ ፈጽሞ አላሰበም።

"ወደዚህ ስመጣ ከአገር ጉብኝት በተጨማሪ አንድ ሌላ ጉዳይ ነበረኝ።"

"እስቲ ንገረኝ!"

"ቤተሰቤን የሚመለከት ነው።"

"የግል ሀበትና ንብረት አለኝ ስለምትለው በመጠኑም ቢሆን አስረዳኝ።"

"ገንዘብ ነው ያለኝ።"

"መሬትና ቤት የለህማ?"

"ገንዘብ ብቻ ነው ያለኝ፤ ጥሬ ገንዘብ..."

"የእስክንድርያው አድራሻህ በመታወቂያ ወረቀትህ ላይ የተመለከተው ነው?"

"አዎን፤ መኖሪያዬ በትክክል ተገልጹአል።"

"የትኛውን ባንክ ነው በደንበኝነት የምትጠቀመው?"

"የምን ባንክ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ገንዘብህን የምታስቀምጥበት ባንክ ነዋ!"

"በባንክ ተጠቅሜም አላውቅ ።"

"ታዲያ ገንዘብህን የት ታስቀምጣለህ?"

"በ . . . በ . . . በኪሴ ።"

"በኪሴ ? ይጠፋብኛልም ብለህ አትፈራም ?"

"ምን አለኝና ይጠፋል ? . . ." አለ ሳበር ፣ በሹክሹክታ ።

"መታወቂያ ወረቀትህ ሀብታም እንደ ሆንክ ይገልጻል ።"

"ሀብታምማ ነበርኩ ።"

"ታዲያ ለወደፊቱ ምን ለማድረግ አቅደሃል ?"

"አባቴን ፍለጋ ላይ ነበርኩ ። አሁንም ያለኝ ተስፋ እርሱኑ ፈልጎ ማግኘት ነው ።"

" 'አባቴን በመፈለግ ላይ ነበርኩ' አልከኝ ?"

"አዎን ፤ ሕፃን ሳለሁ ነው ከቤት ወጥቶ የቀረው ። የቤተሰብ ችግር እንዳለብኝ ቀደም ብዬ ጠቀስ ያደረግሁ መሰለኝ ። ይህን ያህልም ሰው ጀሮ መድረስ ያለበት ነገር አልነበረም ። የነበረኝ ገንዘብ በማለቁ አባቴን ከመፈለግ ሌላ አማራጭ አልነበረኝም ።"

"አባትህ የት እንደሚኖር የምታውቀው ነገር አለ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምንም አላውቅም ። ተስፋ አድርጌ ያለ ሁት ጋዜጣ ላይ ያወጣሁትን ማስታወቂያ ነው።"

"ወደ ካይሮ የመጣህበት ዋናው ምክንያት አባትህን ፍለጋ ነዋ ?"

"ምናልባት ፡ ሊሆን ይችላል ።"

"አለኝ የምትለው ገንዘብ ምን ያህል ጊዜ ያቆይሃል?"

"ከአንድ ወር አያሳልፈኝም ።"

"እስቲ አሳየኝ ።"

በልቡ ውስጥ ቅጥል እያለ ሳብር ቦርሳውን አወጣው ለመርማሪው መኰንን ሰጠው ። መኰ ንኑ ቦርሳውን ገለጥ ገለጥ አድርጎ ከተመለከተ በኋላ መለሰለት ።

"ገንዘብህ ሲያልቅ ምን ለማድረግ አቅ ደሃል ?"

"ሥራ ፈልጌ ለመያዝ እያሰብኩ ነበር ።"

"ምን ዓይነት ሙያ አለህ?"

"ምንም ሙያ የለኝም ።"

"ታዲያ ምን ዓይነት ሥራ ነበር ለመያዝ ያሰብከው ?"

"በንግድ ዘርፍ ማንኛውንም ዓይነት ሥራ ።"

"ያሰብከውን ሥራ ማግኘት ቀላል ይመስ ልሃል ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እስክንድርያ የሚኖሩ ወዳጅቼ ይረዱኛል ።"

"ለሆቴሉ ያልከፈልከው ሂሳብ አለብህ ?"

"በዚህ ሳምንት ውስጥ ያለብኝን ሂሳብ በቅድሚያ ከፍያለሁ ።"

"ይህን ሆቴል እንዴት አገኘኸው ?"

"በዋጋ ረከስ ያለ ሆቴል ሳፈላልግ ፡ ድንገት ነው ያገኘሁት ።"

"ወደ ካይሮ ከመምጣትህ በፊት በዚህ ሆቴል ውስጥ የምታውቀው ሰው ነበር ?"

"አልነበረም ።"

"እዚህ ከመጣህ በኋላ ከብዙ ሰዎች ጋር ተዋውቀሃል ፤ አይደለም ?"

"ከመሐመድ አል ሳዊና ከአሲ ሰርያኩስ ጋር ።"

" ከሊልን ማለቴ ነበር . . . ሚቹ ከሊል አቡል ናጋን ?"

"አዎን ፡ ከእርሱም ጋር ተዋውቀናል ። "

"ስለ ሚቹ ምን አስተያየት አለህ ?"

"መልካም ሰው ነበር ። "

"አንዱ በጭካኔ ባይገድለው . . . "

"በጣም የሚያሳዝን ድርጊት ነው ። "

"ከሊል የሚኖርበትን ስፍራ ታውቅ ነበር?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"መኖሪያው ሆቴሉ ሕንፃ ጫፍ ላይ ነው ሲባል ሰምቻለሁ ።"

"ማን ነገረህ?"

"አሊ ሰርያኩስ ።"

"ጠይቀኸው ነው የነገረህ?"

"ምናልባት ጠይቄው ነግሮኝ ይሆናል ።"

"ምን አስጠየቀህ ?"

"ለምን እንደሆነ ትዝ አይለኝም ። ከአሊ ሰርያኩስ ጋር በተገናኘን ቁጥር ስለ ተለያዩ ጉዳዮች እያነሣን እናወራለን ።"

"ትዝ የሚለህ ሌሎች የጠየቅኸው ጥያቄዎች አሉ?"

ልቡ እንደ ከበሮ ይደለቅ ጀመር። "ለጊዜው ትዝ የሚሉኝ ሌሎች ጥያቄዎች ባይኖሩም ስንገናኝ አሥሩን እያነሣን እንጨዋወት እንደ ነበር ይታወሰኛል" አለ ሳብር ፡ የምርመራው ሽምቀቆ ጠበቅ እያለ ሲሄድ እየተሰማው ።

"ካይሮ ምን ያህል ጊዜ ለመቆየት አስበሃል?" በማለት መኰንኑ ጥያቄውን ቀጠለ ።

"አባቴን እስካገኝ ፤ ወይም እንድ ዓይነት ሥራ አግኝቼ እስክይዝ ፤ ወይም ደግሞ የያዝኩት ገንዘብ እስኪያልቅ. . ."

t.me/OLDBOOKSPDF

መርማሪው መኰንን ሲጋራ ለኵሶ ልምጥ አድርጎ ስቦ ሞሱን ካቦነነ በኋላ ፡ "በተጨማሪ የምትነግረኝ ነገር ይኖርሃል?" አለው ።

"ምንም የለኝም ።"

"ለተጨማሪ ጥያቄ እንደገና ልንፈልግህ ስለምንችል እኛ ሳናውቅ ከሆቴሉ እንዳትወጣ ።"

"መልካም ።"

ሳብር እቅዱ የተዝረከረከ መሆኑ ይበልጥ እየገባው ሄደ ። ተኑሥዩ እብስ ብሎ መጥፋቱ ደግሞ የሠራውን ወንጀል እወቁልኝ ማለት መሆኑ ተሰማው ። ፖሊሶቹ ደግሞ እንቅስቃሴውን በቅርብ እንደሚከታተሉት ገብቶታል ። የሚያዋጣው ፡ አርፎ መቀመጥና ከመርማሪው መኰንን የቀረቡለትን ጥያቄዎች አንድ በንድ እየከለሰና ከመልሶቹ ጋር እያገናዘበ ያበላሸው ነገር መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ ብቻ ነው. . .

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥራ ሦስት

የሳብር ሁኔታ የተወሳሰበና በአደጋ የተጠላ ለፊ እየሆነ መሄዱን ቀጥሏል ። እርሱ የማያውቃ ቸውና የማያያቸው የወንጀል ምርመራ ሠራተ ኞች እያንዳንዱን ድርጊቱንና እንቅስቃሴውን በትኩረት መከታተላቸውን ተያይዘውታል ። ጊዜ ውና ሁኔታው ሲያመቻቸው እጁን ይዘው ፍርድ ፊት የሚያቀርቡበትን ደቂቃ በትዕግሥት እየተጠ ባበቁ ነው ። ከዚህም የቱኒዛ ፡ ከተለመደው አቅ ጣሜ እልፍ ፡ ከወትሮው ድርጊቱ ዝንፍ ቢል ወጥ መዳቸው ውስጥ መግባቱ አይቀርለትም ።

ሆቴሉ ጭር እያለ መሄድ ይጀል ። እንግዶቹን የሞት ሽታ ያባረራቸው ይመስል ከሆቴሉ እየ ወጡ ወደያቅጣጫው አምርተዋል ። ሁኔታውን ያላወቁ አዳዲስ እንግዶች ደግሞ መምጣታቸው አይቀርም ። የሆቴሉ የእንግዶች ማረፊያ እንደ መቃብር የሚከብድ ስፍራ ሆኗል ። በዛሬው ዕለት በወጣው ጋዜጣ ላይ አንድም አዲስ ነገር አይታ ይበትም ። ዛሬም እንደ ወትሮው የሚያወራው ያንኑ የጥጥ ዋጋ ፡ የዓለም የገንዘብ ምንዛሪ መዋዠቅ ፡ የጦርነት ወሬ ብቻ ነው ። የንፉሱ ፋጨት ደግሞ ፪ለማኙን ዜማ የሚያጅብ ይመስላል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳብር አካባቢውን ሲመለከት መሐመድ አል ሳዊ ከሪማን እጅ ሲነሣ አየ ። አንጀቱ ተንሰፈሰፈ ። ከሪማ ከእናትዋ ጋር ተቀምጣለች ። ከእንግዲህ የሆቴሉን ሥራ የምትመራው እርስዋ መሆንዋ ነው ። ከሪማ በአካባቢው በመገኘትዋ ሳብር ጥቂት ተንፈስ አለ ። ሁለቱ ብቻቸውን ተገናኝተው መወያየት የሚችሉበት ጊዜ ናፈቀው ። የሰበሰችው የጎዘን ልብስ ከሪማን የበለጠ ውበና የምታስ ገመድ አድርጎታል ።

ሳብር ያለበትን ውስጣዊ ጭንቀት በቅርቡ የምታውቅለት ከሪማ በመሆንዋ እንድታጽናናውና አይዞህ እንድትለው ይሻል ። ከሪማ ፡ በሹክሹክታ ከመሐመድ አል ሳዊ ጋር ስለ አንድ ጉዳይ ማውራት ይዛለች ። በጭውውታቸው መካከል ፡ "ወደ መኖሪያ ክፍሎችሁ እንድንገባ መቼ እንደሚፈቅዱልን አላወቅም" የሚሉት የአል ሳዊ ቃላት ሳብር ጆሮ ውስጥ ጥልቅ አሉ ።

— በሆቴሉ በየትኛው ክፍል ውስጥ ትኖር ይሆን? — በማለት ሳብር አሰበ ። ያረፈችበትን ክፍል ቢያውቅም ተከትሏት መሄዱ እንደማያዋጣው ተገነዘበ ። ከለሊል ላይ እጁን ከማንሣቱ በፊት የከሪማን እናት አድራሻ አለመጠየቁ ከፊ ጸማቸው ስሕተቶች አንዱ መሆኑ ተሰማው ። ለማንኛውም ከከሪማ ጋር — ሌላው ቢቀር — በቴሌ ፎን መገናኘት ይኖርበታል ። ሳብር በዚህም በዚያም ብሎ ከከሪማ ገንዘብ ማግኘት አለበት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሳብር ፡ ቴሌፎን ይፈልግሃል" የሚል መል እክት ደረሰው ።

ዘወትር የቴሌፎን ጥሪ . . . ዋጋ ቢስ የቴሌ ፎን ጥሪዎች ። — ዛሬም እንዴ ቀልደኛ ሰይድ ኤል ራሕሚ ነኝ ብሎ ሊጫወትብኝ ይሆን?— በማለት አሰበ ። ከተቀመጠበት ተነሥቶ ወደ ቴሌፎኑ ሲያመራ ፡ ከሪማ ወደ ተቀመጠችበት ስፍራ በመ ቅረብ እጁን ለሰላምታ ዘርግቶ ፡ "እመቤቴ ፡ ጥልቅ የሆነ የኀዘንሽ ተካፋይነቴን በድጋሚ እገ ልጻለሁ" አላት ።

ከሪማ እንዳቀረቀረች እጁን ጨበጠች ።

ሳብር ቴሌፎኑን እንሥቶ ሲነጋገር ዓይኖቹ ከሪማ ላይ እንዳረፉ ነበር ።

"ኤልሐም ነኝ ፡ ሳብር ።"

— ሰይድ ኤል ራሕሚ ድራሹ ጠፍቷል ማለት ነው? ተሳስቶ እንኳን ቢደውልልኝ ምን ነበረበት? ካይሮ ድረስ የለፋሁት ለማን ሆነና ነው እንዲህ ዝም የሚለኝ? ወደዚህ ሆቴልስ ምን እግር ጥሎ አመጣኝ? — የሳብር የሐሳብ ውጣ ውረድ . . .

"እንደምን ሰነበትሽ ፡ ኤልሐም?"

"ምነው ደህናም አይደለህ?" አለች ኤልሐም፣ ሐሳብ በገባው ድምፅ ።

"እረ ደህና ነኝ ፤ ምንም አልል . . ."

t.me/OLDBOOKSPDF

"ትናንት ምነው ሳትመጣ ቀረህ?"

"ደክሞኝ ስለ ነበር መምጣት አልቻልኩም።"

"ደህና ከሆንክ ምንም አይደለም ። ዛሬስ ብቅ ትላለህ?"

"ዛሬም አይመሽኝም ። ጉንፋኔ ሲሻለው እመ ጣለሁ ።"

"ደስ እንዶለህ ። በል እንግዲያው ፡ ሲሻልህ ልታገኘኝ የምትችልበትን ቦታ ታውቀዋለህ" አለችው ኤልሐም ፡ ቅር እየሰኘች ።

"እምን ፡ አውቀዋለሁ ።"

"በል ደህና ሁን ።"

"ደህና ሁኚ ።"

ኤልሐም መልእክትዋን ጨርሳ ቴሌፎኑን ከዘጋችው በኋላ ፡ ሳብር ከሪማን እየተመለከተ መነጋገሪያውን ጀሮው ላይ እንደ ደቀነ ንግግሩን ቀጥሏል ።

"አንድ ዘዴ ፈጥረሽ እንድንገናኝ ማድረግ አለብሽ ፤ ሌላው ቢቀር በቴሌፎን አነጋግሪኝ ።"

ከሪማ ቀና ብላ ሳብርን አየችው ። መልእክቱ ለእርስዋ እንዲደርስ የታቀደ መሆኑ ገብቷታል ።

"ላውቀው የሚገባኝ ብዙ ነገር አለ" በማለት ሳብር ንግግሩን ቀጠለ ። "ያለህበትን ሁኔታ ተረድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተሸዋል ብዬ እገምታለሁ ። ተገናኝተን መነጋገር አለብን ። ገንዘቤም እያለቀ መሆኑን አትዘንጊ ። ”

ከሪማ ሳብርን በዓይኖችዋ ገርመም አደረገችው።

“ያንቺንም ችግር ሳልገነዘበው የቀረሁ እንዳይ መስልሽ” አለ ሳብር ፡ በለዘብታ ። “ቢሆንም አንድ ዘዴ መፍጠር የሚያዳግትሽ አይመስለኝም ።”

ሳብር የቴሌፎን ንግግሩን ጨርሶ ወደ መቀ መጫው ሲመለስ ፡ ከጭንቀቱ ጨርሶ ባይገላገ ልም ፡ ያሰበውን መልእክት ለከሪማ ማስተላለፍ በመቻሉ ጥቂት ቀለል ብሎት ነበር ። ከሪማ እና ትዋን አስክትላ ከሆቴሉ እንግዶች ማረፊያ ወጥታ ሄደች ። ከተቀመጠችበት ተነሥታ ከሆቴሉ ውልቅ ስትል ዳግመኛ አንተያይ ይሆናል የሚል ስሜት አንጀቱን አላወሰው ። የሬጸመው ወንጀል እርሷን የሚያሳጣው ከሆነ ፡ ልፋቱና ጭንቀቱ ከንቱ መሆኑ ተሰማው ።

ሳብር እንግዶች ማረፊያ ክፍሉ ውስጥ ተቀ ምጦ የከሪማን የስልክ ጥሪ በጉጉት ይጠባበቅ ጀመር ። ከሪማ ከሄደችበት ጊዜ ጀምሮ የሆቴሉ የእንግዶች ማረፊያ ከባድ ጸጥታ ነግሦበታል ። በክፍሉ ውስጥ የቀረው ሳብር ብቻ ነበር ። ዞር ብሎ አካባቢውን ሲቃኝ መሐመድ አል ሳዊ ከሩቅ ሆኖ ሲመለከተው አየ ። ሰላምታ እንደ መስጠት አንገቱን ሰበር አደረገለት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"በቻህን እዚህ ምን ትሠራለህ?" አለ አል ሳዊ ፡ ሳብር ወደ ተቀመጠበት በማቅናት ።

"ግንሩን ይዞኛል ። አስፕሪን ወስጄ እዚሁ አረፍ ብያለሁ ። ሲሻለኝ ወጣ እላለሁ ።"

አል ሳዊ ከሪማ ተቀምጣበት ወደ ነበረው መቀመጫ አምርቶ አረፍ አለ ።

"ቴሌፎኑም ተስፋ እያስቈረጠኝ ነው" አለ ሳብር ፡ ለጭውውቱ ያህል ።

"ኤል ራሕሚ ያልደወለው አንድ የራሱ የሆነ ምክንያት ቢኖረው ይሆናል ።"

ሳብር ፡ አል ሳዊን በነዘኔታ እየተመለከተ ፡ "መቼም ከባድ ነዘን እንደ ደረሰብህ ይሰማኛል" አለው ።

አል ሳዊ እርጅና የተጫጫነውን ፊቱን ሸምትር ፈታ በማድረግ ፡ "በእኔ ላይ የደረሰው ነዘን አይድረስብህ!" አለ ።

"ከሊል ፡ መቼም መኝታ ቤት ስትገባ ያየኸው አሰቃቂ ትርኢት መሆን አለበት ። በሕይወቴ የሞተ ሰው አይቼ አላውቅም ። እናቴ ስትሞት እንዳላይ ብዬ ዓይኔን ጨፍኜ ካጠገብዋ ነው የሸሸሁት ።"

"ሞት ቢለህ ሞት መሰለህ ። በጭካኔ የተገደለ ሰው ማየት ከሁሉ የባሰ ዘግናኝ ነገር ነው ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እውነትህን ነው ። የሰው ነፍስ ማጥፋት ከደም ፡ ከጭካኔና ከአረመኔነት ሌላ ምን ደህና ነገር አለበት!"

"ዕድሜዬን በሙሉ የማልረሳው አረመኔነት። ለእንደዚህ ያለው ጭካኔ ምንም ዓይነት ቅጣት አይመጥነውም ።"

"እንዲህ ያለውን አሳዛኝ ወሬ በሰማሁ ቁጥር ፡ አንድ ነፍሰ ገዳይ እንዲህ ጨክኖ የሰው ነፍስ የሚያጠፋው በምን ምክንያት ይሆን? የሚለው ጥያቄ በልቤ ውስጥ ይቀሰቀስብኛል ።"

"ይህን የማያስብ ማን አለ ብለህ ነው!"

"ይኸኛው ነፍሰ ገዳይ ምን ዓይነት ሰው ይሆን?"

"በአንድ ወቅት ፡ ደህና አድርጌ የማውቀው የሰው ሕይወት በእጁ የጠፋበት አንድ ተላላኪ ነበር ። እኔ ልጁን የማውቀው ቅን ፡ ታዛዥና ታማኝ ሰው አድርጌ ነበር ።"

"በጣም የሚገርም ነው ።"

"ምን ይደረግ ፤ አንዳንዴ ያላሰቡት ሆኖ ይገኛል ።"

"እውነትህን ነው ፤ መቼም ይኸኛውም ወን ጀለኛ ቢሆን በቶሎ ከመያዝ አያመልጥም" አለ ሳብር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አል ሳዊ ሳብርን በ'ነዘኔታ እየ'መለከተ ፡ "ወንጀለኛው'ማ ተይዟል!" አለው ።

"ምን?"

"የከሊል ገዳይ ተይዟል ።"

"ገዳዩ ተይዟል? እስካሁን መያዙን እንዴት አልሰማንም?"

አል ሳዊ ራሱን በአምንታ ነቀነቀ ።

"ታዲያ ገዳዩ ማን ሆኖ ተገኘ?" አለ ሳብር፡ በሹክሹክታ ።

"አሊ ሰርያክ'ስ ።"

"ያ. . .ያ ደደብ?"

"አምን ፤ ልክ እንደዚያ እንዳጫወትከ'ህ ተላላከ. ልጅ ታሪክ መሆኑ ነው ።"

"ከትናንት ማታ ጀምሮ ያላየሁት ስለዚህ ነዋ?"

"እግዚአብሔር ሁላችንንም ይማረን ብቻ!"

"የከሊል ባለቤት ወሬውን ሰምታለች?"

"እሷማ የግድ ትሰማለች ።"

"ሰውን እንዴት ማመን ይቻላል!"

"መዓት ገንዘብ ነው በእጁ የተገኘው ።"

"ለገንዘቡ ሲል ነው የገደለው ማለት ነው!"

"መስረቁን ወዲያው ነው ያመነው ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ግድያውንስ?"

"እሱን እንጃ. . ."

"ምነው አሁን ገዳዩ ተይዟል ብለኸኝ?"

"ከሪማ ናት ተይዟል ብላ የነገረችኝ ።"

"የግድያው ምክንያት ስርቆት ነዋ?"

"ሳይሆን አይቀርም . . ."

"ለገንዘብ ብሎ የሰው ነፍስ ማጥፋት እስቲ ምን አስፈለገው?"

"ለስርቆት ሲንደፋደፍ ከሊል ከእንቅልፉ ነቅቶ አይቶት ይሆናል ። በዚያች ቅጽበት ሰውዬውን ገድዩ ልረፈው ብሎ አስቦ ይሆናል. . ."

"አሊ ሰርያኩስ እንዲህ ይሠራል ብሎ ማን ይጠረጥራል!"

"አንተኽ ነገሩን ጨርሰኸዋል ። ሰውን እንዴት ማመን ይቻላል?"

"የአሊ ሰርያኩስ ሁኔታ ደግሞ ከማንም የተለየ መሆን አለበት" አለ ሳብር ፡ ለነገሩ ክብደት በመስጠት ።

"ሆቴላችን ፊት ለፊት ሲያዜም የሚውለው ለማኝ ፡ ዛሬ እንዲህ ከመሆኑ በፊት ሰው የሚፈራው የሰፈሩ ቀማኛ እንደነበር ታውቃለህ?"

"ያ ቀፋፊ ሽማግሌ?"

"አዎን ፤ ሀብት ንብረቱን ፡ ጤናውን ካጣና

t.me/OLDBOOKSPDF

በመጨረሻም ዓይኑን ከታወረ በኋላ እዚሁ ተቀምጠ እያዜመ ይለምናል ።"

"በእኔ ግምት አሊ ሰርያኩስ ታማኝ የሚለው ሰው ነበር ። ሰሞኑን እንኳን ቦርሳዬን አልጋዬ ሥር አግኝቶ ለቁርስ ከተቀመጥኩበት ማዕድ ድረስ አምጥቶ ሰጠኝ ።"

"እኛ ከምናስበው በላይ መልቲ ሰው ነበር ማለት ነው ።"

ሁኔታው እንዴት አድርጎ እዚህ ደረጃ ሊደርስ እንደ ቻለ ሳብር ባይገባውም ፥ የወንጀሉ ጣጣ ከእርሱ ራስ የወረደ መስሎ ስለ ታየው የሠራ አካላቱን ቀለል አለው ።

"የገረመኝ ለማምለጥ አለመሞከሩ ነው" አለ አል ሳዊ ።

"ለማምለጥ መሞከርማ ወንጀሉን ይፋ ማውጣት ይሆናል ።"

"የሰረቀውን ገንዘብ እዚሁ ማረፊያ ክፍሉ ውስጥ መደበቁስ ፤ ድንቁርና አይደለም?"

"ገንዘቡን ሰፈሩ ደብቆት አግኝተውት ይሆናል ።"

"ሰፈሩ ወስዶ ደብቆም ከሆነ ተሞኝቷል ።"

"ምን ማድረግ ይቻላል ቀን ሲገድል" አለ ሳብር ።

አል ሳዊ በረጅሙ ተንፍሶ ፥ "እኛ አሥራን ብናወራ እማዜር ሁን ያለው አይቀርም" አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ወንጀሉ ተፈጸመ የተባለበት ቀን ማለዳ ሳገኘው ፡ ከወትሮው የተለየ ምንም ነገር አላየ ሁበትም ።"

የሳበር ልብ እንደ አታሞ ይደለቅ ጀመር ።

"እባክህ ተወኝ ፤ የገደሏቸው ሰዎች የቁበር ሥነ ሥርዓት ላይ የሚገኙ ልበ ደንዳና ወንጀለ ኞች ሞልተዋል ።"

ፍርሐቱ አሳልፎ እጁን እንዳያሲዘው ጥን ቃቄ ማድረግ እንዳለበት ሳብር ተገነዘበ ። ከሪማ እንደ ምንም ብላ ስልክ ብትደውልለት አንዳንድ ሁኔታዎችን ከእርስዋ መረዳት ሳይችል አይቀርም ነበር ።

አል ሳዊ በደከመና ዝዘን በተጫጫነው ስሜት ንግግሩን በመቀጠል ፡ "ፖሊሶች ከሁሉ አስቀድመው የመረመሩት እኔን ነበር" አለ ።

"እንዴት አንተን ?"

"ነገሩስ ትክክል ነው ። ሚታ አስተኛቼው የተመለስኩትና ዛሬ ማለዳ ላይ መኝታ ክፍሉን ከፍቼ የገባሁት እኔ ነኝ ።"

"አንተን ደግሞ ማን . . ."

"የቀረበልኝ ጥያቄ ስፍር ቁጥር አልነበረ ውም ። መስኮቶቹ መዘጋታቸውን አይቼ በሩን ዘግቼ ነበር የወጣሁት ። ጠዋት ግን አንዱ መስ ኮት መለስ ተደርጎ ነው ያገኘሁት ።"

"ሳይዘጋ ተረስቶስ እንደሆን ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"መስኩየቹ በመሉ ተዘግተው ነበር ።"

"ከውጪ መስኩቱን ከፍቶ ገብቷል ማለት ነዋ!"

"ፊጽሞ ሊሆን አይችልም ። መስኩቱን ሰመ ክፈት ሲታገል ድምፅ ይሰማ ነበር ። ከለሊ ደግሞ ኮሽታ የሚያነቃው ሰው ነው ።"

"ምናልባት በሩን አንኳኩቶ ከለሊ ከፍቶ ለት እንደሆነስ?"

"በበር ከገባ መስኩቱን መክፈት ለምን አስፈለገው? ከምርመራው እንደ ተጣራው ከሆነ ከለሊ የሞተው እተኛበት ነው ።"

የሳብር ዓይኖች ተቅለጨለጩ ። ወዲያው ቀጠል አድርጎ ፡ "አልጋው ሥር ተደብቆ አምሽቶ ይሆናል" የሚሉት ቃላት ሳያስበው አመለጡት ።

"ሊሆን አይችልም ። አሊ ሰርያኩስ ከከሊል መኝታ ቤት ከእኔ ቀድሞ ነው የወጣው ። በሩን ዘግቼ የሄድኩት እኔ ነኝ ።"

"እንግዲያው. . ."

ሳብር ፡ ዐረፍተ ነገሩን መጨረስ አልሆነለ ትም ። ፍርሐት እፍን አደረገው ። አሊ ሰርያኩስ መስኩየቹን የዘጋ መስሎ በመኝታ ቤቱ ውስጥ ተደብቆ እንደሆን ፡ የሚለውን ጥያቄ ለመሰንዘር ነበር ያሰበው ። መስኩየቹን የዘጋው አሊ ሰርያ ኩስ መሆኑን እንዴት አወቅህ የሚለውን ነጥብ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቢይዝብኝስ? የሚለው ሐሳብ ሳብርን አብረከረከው። ለጥቂት ነው ያመለጠው ።

"እንግዲያው ምን ?" በማለት አል ሳዊ ሳብርን አፋጠጠው ።

"እንግዲያውማ ፡ በሌላ ቁልፍ መኝታ ቤቱን ከፍቶ ገብቷል ማለት ነው ።"

"ሊሆን ይችላል ። ጉዱ መስኮቱ ተከፍቶ መገኘቱ ላይ ነው ።"

"መቼም መስኮቱ ተከፍቶ ከተገኘ ማታ ሳይ ዘጋ ተረስቶ ቀርቷል ማለት ነው ።"

"እንግዲህ ምስጢሩን እግዜር ይወቀው ።"

"ስሜትህ ክፉኛ ነው የተነካው" አለ ሳብር፡ በማስተዛዘን ።

"መርማሪዎቹ እኔን ለምን በነፃ እንደ ለቀቁኝ አልገባኝም ። የሚሠሩትን የሚያውቁ ስለሆነ አንድ የተለየ ምክንያት ቢኖራቸው ነው የሚል ግምት አለኝ ።"

"ጋዜጠኞች ደግሞ ስለ ግድያው ማውራት ያቆሙ ይመስላል ።"

አል ሳዊ እንባ እየተናነቀው ፡ "ከሊል እግዜር ነፍስህን ይማረው ። አብረን ያሳለፍነው ስድስት ዓመት ጥቂት ጊዜ አይደለም ።"

"ዕድሜው ምን ያህል ነበር?"

"ከሰማንያ ዓመት ይበልጠዋል ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ከከሪማ ጋር መቼ ነው የተጋቡት?"

"ከአሥር ዓመት በፊት ።"

"ያላቻ ጋብቻ ፤ አይመስልህም?"

"እንዳጫወተኝ ከሆነ ትዳር የያዘው በጉር ምስና ወራቱ ነው ። አንድ ልጅም ወልዶ ነበር ። ነገር ግን ባልታሰበ አደጋ ቤተሰቡ በሙሉ ከሞቱ በት በኋላ ፣ እንደገና ትዳር ሳያሰኘው ለብዙ ዘመን ብቻውን ይኖር ነበር ። በመጨረሻም ከሪማን አግ ኝቶ ተጋቡ ። ልክ ወላጅ አባት ሴት ልጁን የሚ ወዳትን ያህል ከማንኛውም ነገር አስበልጦ ይወ ዳት ነበር ።"

"ሁኔታው ሲታይ ቢወዳትም የሚያስደንቅ አልነበረም ።"

"ከለሊል ርኅሩኅና ለጋስ ሰው ነበር ። ነፍሱን ይማረውና ፣ ልጅቼን እንዳሳድግና እንዳስተምር የሚረዳኝ እርሱ ነበር ።"

"ከሪማን እንዴት ነው ሊያገኛት የቻለው?"

"በሥራ ምክንያት በየጊዜው ወደ እስክንድ ርያ ይመላለስ ነበር ።"

"እስክንድርያ! የእስክንድርያ ተወላጅ ናት እንዳትለኝ!"

"አይደለችም ። ከለሊል ወደ እስክንድርያ ሲሄድ የሚያርፈው ታንታ ከሚኖር አንድ ወዳጁ ዘንድ ነበር ። በዚያን ጊዜ ከሪማ ትዳር ላይ ነበ ረች ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"አግብታ ነበራ?"

"አንድ የማይረባ ባል ነበራት ። ከሊልና ከሪማ የተገናኙት በአንግድነት ባረፈበት ወዳጁ ቤት ነው ።"

"ባል ከነበራት እንዴት ከከሊል ጋር ሊጋቡ ቻሉ?" በማለት ጠየቀ ሳብር ። ሳብር በጥያቄ ላይ ጥያቄ እየደራረበ መሰንዘሩ አልተሰማውም ።

"ከባልዋ ጋር ተፋትታ ከሊልን አገባችው።"

"ዕድሜው ከሰባ ዓመት በላይ የሆነውን ሰው ማግባትዋ አይገርምም?"

"ምንም አይገርምም! ከሊልን በማግባትዋ ክብርና የተደላደለ ኑሮ ተጐናጽፋለች ።"

"የአዕምሮ ሰላምም አልነፈጋትም" በማለት፡ ሳብር በአል ሳዊ ቃላት ላይ ተጨማሪ ሐረግ አከለበት ። እናቱ በሕይወት በነበረችበት በመጨረሻዩቱ ደቂቃ ላይ የተናገረቻቸው ቃላት ናቸው ።

"የማይረባ ያልከው ባልዋ ይህችን የመሰለች ቆንጆ ሚስቱን እንዴት ሊፈታት ቻለ?"

"ይዋል ይደር እንጂ ሁሉም የጁን አያጣም ።" አል ሳዊ ይህንን የመሰለ ቃል ከአንደበቱ መውጣቱ ጸጸተው ።

ሳብርም ቀበል አድርጎ ፡ "ያለፈው አለፈ ፤ ከአንግዲህ ምን ዋጋ አለው!" አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"መናገር የሌለብኝን ብዙ ነገር ዘባርቄአለሁ ። ከሲልን በደም ተነክሮ ካየሁት ወዲህ አዕምሮዬ ሳይቃወስ አልቀረም ። እግዜር ብቻ ይቅር ይበለኝ ።"

የጋለሞታ ውላጅ. . .የወጣለት አለሌ. . .ልበ—ድንጋይ ወንጀለኛ. . . ለፍትወቱ አዳሪ. . . መጥሬያውን አባራሪ . . . ወደዚህ ጉሮሮ ሆቴል ነድዶ አምጥቶ ለወንጀል ፡ ለግድያና ደም ለማፍሰስ የዳረገው አጉል ቅዠት. . . እንደ ለየለት ዕብድ ስሰው መኪና እንዲያሳድድ የገፋፋው ጭፍን የሚት . . . የሳብር ያባት የናቱ ረጅት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥራ አራት

የሌሊቱ እንቅልፍ እጦት ካስከተለበት ድቅቅ የሚያደርግ ድካም ፋታ ያገኘ እየመሰለው ሳብር ቡና እየደጋገመ ይጠጣል ። አሰ ወትሮው ሲጋራ እያከታተለ በመለኰስ ጭሱ በሚፈጥረው ደመና አሾልኮ አሥራ ቴሌፎን ይመለክታል ። ልቡ የተሰቀለው የከሪማ የስልክ ጥሪ ከአሁን አሁን ይደርሰኝ ይሆናል በሚል ጉጉት ነበር ። ለጥቂት ደቂቃዎች የጣለው ከባድ ዶፍ አካባቢውን ጮርፍ አልብሶታል ። ጭንቀቱን ያልተረዳችው ከሪማም ጭጭ ብላለች ። በየቀኑ መጠጣት. . . እንቅልፍ አጥቶ ማንጋት. . . ሕልም. . .ቅዠት. . .ሕልም ። ይኽ ሁሉ መንገላታት አስተዋይ ከሆነ ተመልካች የማያመልጥ ምልክት በሳብር ገጽ ላይ ዱካውን ጥሎ ማለፉ አልቀረም ። ከሪማ እንደ ሆነች ባወጣ ያወጣው ብላ የተወችው ይመስላል ።

ከሦቱሉ እንግዶች አንዱ ሳብር የተቀመጠ በትን ገበታ ለመጋራት ፈቃድ ጠይቆ አጠገቡ አረፍ አለ ። የሦቱሉ የእንግዶች መመገቢያ ክፍል ከወትሮው የተለየ በሰው ተሞልቷል ። ከሳብር ጋር የተቀመጠው እንግዳ ሦቱሉ ውስጥ የሰንበተ

t.me/OLDBOOKSPDF

ባለመሆኑ ወሬ የጠማው ይመስላል ። ብዙም ሳይ ቆይ ከሳብር ጋር ጭውውት ከፈተ ።

"ለካስ ገዳዩን ይዘው ታል ?" አለ ሰውዬው ።

"መያዙን ሰምቻለሁ" በማለት ፡ ሳብር ፍር ሐቱን በፊገግታ በመሸፈን መልስ ሰጠ ።

"የያዙት አሊ ሰርያኩስ የተባለውን የሞቱ ለን ተሳላኪ አይደለም?"

"አዎን ፡ እሱን ነው የያዙት ።"

"የግድያው ምክንያት ስርቆት ነው ይባላል" አለ ሰውዬው ፡ መቀመጫው ላይ እየተመቻቸ ።

"ግምቱ ተሳስቷል ማለት ነው ።"

"ምን ነበር የገመትከው?"

"የሞቱሉን ባለቤት ሞት እንደ ሰማሁ የግ ድያው ጠንሳሽ ሴት መሆን አለባት ብዬ ነበር ።"

ሳብር ሰውዬውን ትኩር ብሎ ተመለከተው ።

ሰውዬው ንግግሩን በማከታተል ፡ "ብዙ ሀብ ትና ንብረት የመውረስ ዓላማ ያላት መልከ ቀና የሆነች ልጅግር ሴት አስገድላው ይሆናል የሚል ግምት ነበረኝ" አለ ።

"የኔም ጥርጣሬ ወደዚያው ግድም ነበር" አለ ሳብር ፡ ጅማቶቹ በፍርሐት ሲንገዱ እየተሰማው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

—የወንጀል መርማሪው መኰንን ይህን የመሰለው ሐሳብ በአዕምሮው ውስጥ አድሮበት ይሆን? — በማለት ሳብር ሐሳብ ገባው ። ከሪማ እንደሆነች ሞትን የመሰለ ዝምታ ተጭኗታል ። ቴሌፎኑ ጨርሶ ድምፁን አጥፍቷል ። ዝናቡ ፡ ብርዱ ፡ ጕርፉና ጭቃው የለማኙን እንጕርጕሮ አልገታውም ።

መሐመድ አል ሳዊ ወደ ቴሌፎኑ በእጁ እያ ሳየ ሳብርን ጠራው ። ከመቀመጫው ተነሥቶ የማ ዱን ወደ ቴሌፎኑ አዘገመ ።

“ሃሎ ፡ ማን ልበል?”

“ሳብር ነህ?”

ይህን በመሰለ የመንፈስ መረበሽ ውስጥ ድምፅዋን እሰማለሁ ብሎ ከቶም አላሰበም ።

“እንደምን ነሽ ፡ ኤልሐም?”

“ረበሽከህ መሰለኝ?”

“ፈጽሞ አልረበሸኝም ። መታመሜን እንደ ሆን በድምፄ ሳትረጂው አልቀረሽም ።”

ሳብር ጥርሱን ነክሶ ከኤልሐም ጋር የጀመረ ውን ግንኙነት ለማቋረጥ አሰበ ። የችግር ማጥ ውስጥ አብራው እንድትዘፈቅ አልፈለገም ። ከቴ ሌፎኑ ንግግር በኋላ እተለመደው ስፍራ ተገናኙ። ኤልሐም ምንም አልተለወጠችም ። የሰማችው ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

ያየችውና የጠረጠረችው ምንም ነገር ያለ አይመ ስልም ። ፈገግ እያለች ሳብርን በቅሬታ ትመለከ ተዋለች ።

"እንዲያው ለመሆኑ ፣ ይህን ያህል ጊዜ ሳንገ ናኝ ስንቆይ ምንም ቅር አላለህም?" አለችው ።

ሳብር መልስ አልሰጣትም ። እጆችዋ ውስጥ ያጠለቀችውን ጓንቶች አወላልቃ አረፍ አለች ።

"እውነትም ጉንፋኑ አድቆሃል" አለችው ።

"ምንም አላስተረፈኝም ።"

"አጠገብህ ማንም ሰው የሌለበት ነው የተጫ ወተብህ !"

"ማን አለኝ ብለሽ ነው ።"

"ወደ ሐኪም ዘንድ ሄደሃል?"

"አልሄድኩም ። ይውጣለት ብዬ ለጥ አልኩ በት ።"

"ፈሳሽ በብዛት መጠጣት አለብህ ። ፈሳሽ መጠጣት ለጉንፋን ሕመም በጣም ይረዳል ።"

የቀረበላትውን ምግብ በጸጥታ በሉ ። ኤል ሐም ቀና እያለች ዓይኗን ሳብር ላይ ትተክላለች።

"ብዙ ጊዜ ሆቴሉ ድረስ መጥቼ ላይህ አስቤ ነበር" አለችው ።

"እንኳን አልመጣሽ" የሚሉትን ቃላት ከምላሱ ጫፍ መለሳቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ያጉመተመታቸውን ቃላት በትክክል ማጤን ባለ መቻልዋ ፡ ትከሻዋን መታ አድርጋ ዝም አለች ። ከዚያም እንደ ሕፃን ልጅ በመቅበጥበጥ ፡ "እኔ እንደ ሆንኩ ሥራ ፈትቼ የሰነበትኩ እንዳ ይመስልህ!" አለችው ።

—ወይ ኤልሐም! ለምን እንዲህ ታሠቃይ ኛለሽ? ምነው እርግፍ አድርገሽ ብትተይኝ ! ምን ያለሺው የተቀደሽ ፍጥረት ነሽ ? — አለ ሳብር በልቡ ።

"እታምነኝም ማለት ነው?" አለችው ኤል ሐም ፡ ዓይኖችዋን በደስታ እያቁለጨለጩ ። "በል እንግዲህ ቁርጡን ልንገርህ ። አዲስ ሕይ ወት ልትጀምር . . . ልንጀምር ነው ። ምን ይመስ ልሃታል ጌታው ሳብር?"

እንደ ምንም ታግሶ የተጫጫነውን በማፍ ታታት ፡ "በእውነቱ እንቺ እግዜር የባረከሽ ሰው ነሽ ፤ እኔ ደግሞ ቅስሙ የተሰበረ አውሬ ነኝ" አላት።

"ለመነሻ የሚሆንህንም ገንዘብ አግኝቻ ለሁ" አለችው ፡ በልበ ሙሉነት ።

"መነሻ ገንዘብ?"

"አዎን ። ለክፉ ቀን ይሆነኛል ብዬ ያስቀ መጥኩት ገንዘብና የማልጠቀምባቸው ጌጣ ጌጦቼ ተሽጠው በቂ የሆነ መነሻ ካፒታል ይኖርሃል ።"

ሳብር እንዲህ ያለው ነገር ይሆናል ብሎ

t.me/OLDBOOKSPDF

በውት ቀርዮ በሕልሙም አላሰበም ። በወንጅል ድርጊት ያልተበከለ እጅ ያፈራው ገንዘብ . . . ንጹሕ ፍቅር የቸረው ሀብት . . . ተአምር ነው! የሚቻል ቢሆን ከሲል ከሞት ቢነጣና ሳብርም ከገባበት አበሳ ቢወጣ እንዴት ደስ ባለው!

"ኤልሐም ፡ ውለታሽ እየከበደኝ ነው ። አንቺ እንደዚህ ለእኔ በምትጨነቂበት ሠጠን እኔ ደግሞ ላንቺ የማልመጥን ሰው መሆኔ በጉልህ እየታየኝ ነው የሄደው ።"

"እንግዲህ ቅኔ መቀኘትህን ወዲያ ተወው ። የምናባክነው ጊዜ የለንም ።"

የኤልሐም ልብ ክፉኛ ፈንጥሏል ። ለበጎ ዓላማ የተንጣጣ ስሜትዋን ማጸፈን ምሕረት የሌለው ሌላ ወንጀል መፈጸም መሆኑን ሳብርም ሳይረዳው አልቀረም ። ኤልሐም ግን ፡ በጎ ዓላማ ዋን ልትገነባ የምትጥረው ውስጣዊ ባሕርይውን ባልተረዳችው ድቡሽት ላይ ነው ። ሳብር ራሱም ቢሆን ችግሩ ይህን በመሰለ ቀላል ዘዴ መፍትሔ ያገኛል ብሎ አላሰበም ። ፍቅር ፡ ነፃነት ፡ ክብርና የተደላደለ የሰላም ኑሮ የሚባለው ይኸው አይ ደል? ከፋቱ ሳብር ይህን ለመሰለ ዕፀብ ውለታ ብቁ ሆኖ አለመገኘቱ ነው ።

"ምንድን ነው እንደዚህ ዝም ያሰኘህ ? እሺ እኮ ደስታው ጮቤ የሚያስረግጥህ መስሎኝ ነበር ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንቺን የማልመጥን ሰው መሆኔን ደጋግሜ ነግሬሽ ነበር ። ለምንድን ነው የምታሞኚኝ ?" አለ ሳብር ፡ እውነቱን የመስሚያዋ ጊዜ መድረሱ እየታየው ።

"እውነቴን ነው እኮ! የምሥራቹን ስነግርህ ደስታ የሚፈነቅልህ መስሎኝ ነበር!"

"ከእንግዲህ ዋጋ የለውም!" አለ ሳብር ፡ ማልቀስ እየታጣው ።

"ጉዴ ፈላ ! አልወድሽም እንዳትለኝ !"

"ኤልሐም ፤ ነገሩ ወዲህ ነው ። እንቺን አል ወድሽም የምልበት እንጂት የለኝም! ያንቺን ፍቅር ለመቀበል የምበቃ ፡ ለመሆኑ እኔ ማን ነኝ?"

"ስለ አባትህ ፡ ስለ ድህነትህ ፡ ወይም በግል ሀብትህና ንብረትህ የምትተዳደር ስለ መሆንህ መስማት አልፈልግም!"

ሳብር መውጫ ቀዳዳ አጣ ። እውነቱን ተናግሮ እንዲወጣለት ወሰነ ።

"ጉንፋኑ ጨርሶ የተወህ አልመሰለኝም ። ለስሙ አብረኸኝ ተቀምጠሃል እንጂ ከእኔ ጋር አይደለህም ። መጀመሪያ የተገናኘን ዕለት ያየሁት ሳብር ወዴት ደረሰ?"

"እባክሽ እንደሱ አትበዪኝ !"

"ተወው ታመሃል!"

t.me/OLDBOOKSPDF

"የለም አልታመምኩም ።"

"ታዲያ ምንድን ነው? ምን ነካህ? ምን መዓት ወረደብህ? ዋጋ የለውም ያልኸኝ ምኑን ነው!" እንባዋ ዓይኖችዋ ውስጥ ግጥም ብሏል ።

"ዋጋ የለውም አልኩሽ እንዴ?"

"ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ብለኸኛል!"

"ካልኩም ሳንቺ ፍቅር ብቁ አለመሆኔን ለመግለጽ ፈልጌ ነው ።"

"አባክህ አሥሩን አትዘላብድ ። እኔ እንደ ሆንኩ አውንም እወድሃለሁ!" አለችው ፡ ቁጣ ብላ።

"በደሌና ወንጀሌ እንድትወጂኝ መንገድ መክፈቴ ነው ። የሚያሳዝነውም ፍቅርን ብቻ ማሰባችን ነው ።"

"ፍቅር ደግሞ ወንጀል የሆነው ከመቼ ወዲህ ነው?"

"ወንጀሉ ስለ ራሴ እውነቱን ሳልነግርሽ እስካሁን መቆየቴ ነው ።"

"የነገርከኝን ሁሉ በጸጋ ተቀብዬዋለሁ ።"

"የነገርኩሽ ስለ አባቴ ብቻ ነው ። ስለ እናቴ አልነገርኩሽም" አለ ሳብር ፡ በምሬት ።

በእምቢታ እያፈጠጠችበት ፡ "እኔ የምወደው አንተን ነው. . . አንተን ራስህን! ላለፈ ታሪክህ ዋጋ አልሰጠውም !" አለችው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለማንኛውም የምነግርሽን ስሚኝ ።"

"ስለ እግዜር ብለህ ፡ በሰላም ያረፈችውን እናትህን ተዋት ።"

"በእስክንድርያ ከተማ በሞሳ የሚታወቀውን ነው የምነግርሽ ።" ቀጥሎም ምሬትና ጎዘን በተቀላቀለበት ግትርነት ፡ "ሕይወትዋ ወደ ፍጻሜ የደረሰው ወህኒ ቤት ውስጥ ነው!" አላት ።

አጠገቧ የተቀመጠው ያ የምታውቀው ሳብር ወይም ናላው የቦረ እብድ መሆን አለመሆኑን መለየት ስላቃታት በድንጋጤ ክው ብላ ቀረች ።

"ምስጢሩን አሁን ተረዳሽው?" እንቅ የሚያደርገውን ምራቁን ዋጥ አድርጎ ፡ "መንግሥት በሠራችው ወንጀል የተነሣ ንብረትዋን ሁሉ በመውረሱ ነው እንዲህ ያጣሁ የነጣሁ ድሃ ለመሆን የበቃሁት ። የተወችልኝ ነገር ቢኖር በፍለጋ እያንከራተተኝ ያለውን ተስፋ ብቻ ነው ። ስለዚህ ነው አንቺን የመሰለች ሴት የመውደድ መብት የለኝም የምለው ። እስከ ዛሬ ድረስ የኖርኩት ከማንም ጋለሞታ ጋር እንደ ልቤ በመፈንጨት ነው ። ሌላ ምርጫ አልነበረኝም ። አንቺን የወደ ድኩት ደግሞ እንዲያው ጥሎብኝ ነው ።"

ኤልሐም ምንም ቃል አልተነፈሰችም ። ዝም በማለቷና ጥያቄ ባለመሰንዘሯ ሳብር አልተከፋም። የእናቱን ታሪክ በዝርዝር ማውራቱን እምብዛም አልወደደም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ከእንግዲህ ወዲያ ልክስኽ የምችለው ንጹሕ በሆነ የወንድምነት ፍቅሬ ብቻ ነው። እስካሁን ሕይወቴን ያሳለፍኩት እሱይ ተግባር በመፈጸም ብቻ ነው። በጎ ነገር መሥራትን ሞክሬውም አላ ውቅ። የሚቀናኝ ክፉ ሥራ መሥራት ነው።"

ሳብር ተነፈሰ ፤ ቀለል አለው። ቀኑ ቶሎ ባልመሸ የሚል ምኞት አደረበት። የወንጀል መር ማሪው መኰንን ይህን ሁሉ ምስጢሬን እስካሁን ልቅም አድርጎ ሳያወቅ አይቀርም ብሎ አሰበ። አንዴት ቃል ሳይተነፍስ ከተቀመጠበት አፈፍ ብሎ ተነሥቶ ኤልሐምን ሳይሰናበት ከምግብ ቤቱ ወጥቶ ሄደ።

በማግሥቱ ከሰዓት በኋላ የቴሌፎን ጥሪ ደረሰው።

"እንደምነሽ ፥ ኤልሐም?"

በሚንቀጠቀጥ ዝቅ ያለ ድምፅ ፥ "ሳብር ፥ ትናንት የነገርኪኝ ሁሉ ስለ አንተ ያለኝን ፍቅሬን እንዳለወጠው ላረጋግጥልህ እወዳለሁ" አለችው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥራ አምስት

ሳብር ፡ ከኤልሓም ጋር የመሠረተው ግንኙ ነት እንዳጀማመሩ የሚናፍቀውና በጉጉት የሚጠ ብቀው ሳይሆን የሚያሸሸውና የሚያስበረግገው እየሆነበት ሄዷል ። ከከሪማ ጋር ደም ያቈራኘው በመሆኑ ከሞት ሌላ የሚለያቸው ነገር አለመኖ ሩን ከተገነዘበው ሰንብቷል ። በሌላ በኩል ደግሞ ፡ ከሪማን አግኝቶ ቍርጠኝ የማወቅ ፍላጐቱ አላስ ቆም አላስቀምጥ ብሎታል ። እንደ ምንም ብሎ እንዴ እሷን ማግኘት አለበት . . . ሌላ አማራጭ የለውም!

ሆቴሉ ተሸሞ ከከሪማ ጋር ወዴ ሌላ ከተማ ሄደው መኖር የሚሻላቸው መሆኑን ሳብር በሐ ሳቡ ያወጣ ያወርድ ጀምሯል ። እንዲህ ካደረጉ ፡ ያለ ምንም ሥጋት ደስታና ተድላ የሞላበት የተ ደላደለ ኑሮ መኖር ይችላሉ ። ጠባዩን እንዲለውጥ፡ ኑሮውን በወጉ እንዲያስተካክል ከሚያስቸግረው ከኤልሓም የማያቋርጥ ምክርና ማባበል ይገላገ ላል ። ችግሩ ከሪማ ገዘም ማለትዋ ነው ። ገንዘቡ እንደሆን ማለቁ ነው. . . ታዲያ ምን ይበጀዋል! የሚሻለው ያገኘውን ማንኛውንም ሥራ እየሠራ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሪማን መጠበቅ ነው ። የአለ. ሰርያኩስን የተላላ ኪነት ሥራ በደግኝ እንኳን ዓይኑን አያሽም ነበር ። ምስኪን ሰርያኩስ! ጨክነው ይሰቅሉት ይሆን? ጉድ ነው ! ባንዱ ዳፋ ሴላው መሠቃየቱ... ግዳዩ ተቀምጠ ንጹሑ መያዙ. . . ምን ያለው ቅዠት ነው. . . እንዲህ ያለው የቱም ቅዠት የሚ ያበቃው መች ይሆን?

ሳብር ከሦቱስ ከመውጣቱ በፊት ከኤልሐም ዘንድ የቴሌፎን ጥሪ ደረሰው ።

"በጋዜጣ የምታወጣውን ማስታወቂያ ማደስ አስበሃል?" አለችው ፡ ደከም ባለ ድምፅ ።

"እረ አላሰብኩም" አላት ፡ ስልኮት እንዳለው እየታወቀበት ።

"ድንገት ቴሌፎን ማውጫ ላይ ያልተመዘገበ ቁጥር ይኖረው ይሆናል በሚል ግምት አንድ የማውቀውን ሰው እንዲያጣራልኝ ጠይቄው ነበር ።"

"መቼም መልስ ፡ 'አልተገኘም' ነው ።"

"አምን ፤ አልተገኘም ።"

"እባክሽ አትቸገሪ" አለ ሳብር ፡ በረጅሙ እየተነፈሰ ።

"በተለያዩ ከተሞች ውስጥ የሚገኙትን የጋዜጣችንን ወኪሎች በተቻላቸው እንዲፈልጉት አደራ ብያቸዋለሁ ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ከልብ ነው የማመሰግንሽ ፥ ኤልሐም ።"

"መቼ ነው መጥተህ የምትገበኘኝ?" አለች ፥ አፈር እንደ ማለት እየቃጣት ።

"መምጣት አልችልም!" አላት ፥ ኩስተር ባለ ድምፅ ። "ምክንያቱም ያንቺ ደኅንነት ያሳስበኛል" በማለት አከለበት ።

"ሁኔታህ እያሳሰበኝ ነው ።"

"ለእኔ አትጨነቂ ፤ ምንም አልሆንም ።"

"አንተ ምንም ባትሆን እኔ ሰላም አጥቻለሁ ።"

ቴሌፎኑ ድንገት ተቋረጠ ። ንግግራቸው እልባት አልያዘም ። ምን ይሰማት ይሆን? በደም በተበከለ ዓለም ውስጥ ወበት ምን ፋይዳ አለው? ኤልሐም ደግሞ ወበት እንጂ የዚህ ዓለም አሠቃቂ መልክ — ጥፉነት አይታያትም ።

ከሦቴሉ ሊወጣ ሲል መሐመድ አል ሳዊ ሳብርን በፊገግታ ተቀበለው ። ሳብርም ፍራቻ ወጣ በሚደብቅ ፊገግታ ፥ አጸፋውን መለሰለት ። አል ሳዊ አጠገቡ እንዲቀመጥ በእንቅስቃሴ ስለ ጋበዘው ፥ የስሚት ወጥረቱንና እልሁን በማለባበስ ከገኑ አረፍ አለ ።

"የምትቸኩልበት ጉዳይ እንዳይኖርህ" አለ ፥ አል ሳዊ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምንም የሚያስቸኩል ጉዳይ የለኝም ። ካል ከስ ምንም የምሠራው ነገር የለኝም ።"

"እንግዲያው አብረኸኝ ብትቆይ ደስ ይለ ኛል ። ከሊል ከሞተ ወዲህ በጣም ነው ብቸኝነት የሚሰማኝ ፡ የማነጋግረው ሰው እንኳን አጥቻለሁ።"

"ልጆች ሁህ?"

"ልጅቼ የሚኖሩት ካይሮ አይደለም ።"

በሆቴሉ የእንግዶች ማረፊያ ክፍል ውስጥ ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ ። የትራፊክ ግርግርታ የለማንን ዜማ ውጠታል ።

"አዲስ ነገር ምን አለ?" በማለት ሳብር ጠየቀ ።

"ከፖሊሶቹ መካከል የማውቀው አለ ። ጉራው አይቻልም እንጂ የማያውቀው ነገር የለም።"

"ምን ነገረህ?"

"ወንጀሉ በሙሉ ተጠቃለ የተዘረዘረው አሲ ሰርያኩስ ላይ ነው ። ሌላ ተጠርጣሪ አልተ ገኘም ።"

"ወንጀሉን አምኖ ይሆን እንዴ?"

"ማመን አለማመኑን አላወቅሁም ።"

"ለገንዘብ ብለ ይህን የመሰለ አሠቃቂ ወን ጀል መፈጸሙ ያሳዝናል ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ገንዘብ መስረቁንማ ክዷል ።"

"አምኗል ተባሎ የለም እንዴ?" አለ ሳብር ፥ በመኰሳተር ።

"መጀመሪያ አምኖ በኋላ ካደ ።"

"ቤቱ ውስጥ የተገኘውስ ገንዘብ?"

"ሴትዮዋ የሰጠችኝ ነው ብሏል ።"

"የማን ሴት? የከሊል ሚስት?"

"አዎን ።"

"እንዴት ገንዘብ ልትሰጠው ቻለች ?"

"ድግሞማ ሊሆን ይችላል ።"

"ሌሎች ሠራተኞችም ድግሞማ ያገኙ ነበር ማለት ነው?"

"ሌሎችን ስትደጉም አላየሁም ።"

"የሚገርም ነው!" አለ ሳብር ፥ ምራቁን ዋጥ እያደረገ ።

"የሚገርመው ገንዘቡን አልሰረቅሁም ብሎ ከካደ በኋላ እንደገና ደግሞ ሰርቄአለሁ ብሎ ማመኑ ነው ።"

"'ድግሞማ ሊሆን ይችላል' ብለኸኝ አልነበረም እንዴ?"

"አንዳንድ የምታዘውን ሥራ ሲያከናውን ጉርሻ እንደምትሰጠው አልካደም ። ገንዘብ የምታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስቀምጥበት ስፍራ ስለሚያውቅ ለስርቆት መጣ
ፋፋቱንም አምኗል ።''

''ለገንዘብ ብሎ የሰው ነፍስ አጠፋ ማለት
ነው?''

''መሆኑ ነዋ!''

''የመርማሪው መኰንን ሐሳብ ምን ይሆን ?''

''ማን ያውቃል ፤ እንደ ተረዳሁት ከሆነ ፥ ገዳዩ
አሊ ሰርያከስ መሆኑን ያመነበት ይመስላል ።''

''ምናልባት ግድያውንም አምኖ ይሆናል''
አለ ሳብር ፥ ተስፋ በሚያጭር ድምፅ ።

''ምናልባት ።''

''ምናልባት የሴትየዋ የገንዘብ ስጦታም
ለዚሁ ዓላማ የታቀደ ሊሆን ይችላል ።''

''ሊሆን ይችላል ።''

''እንዴ ማመን እንዴ መካድ ፤ ምን የሚ
ሉት ነገር ነው?''

''ማን ያውቃል!''

''ወንጀሉ ሌላ ገጽታ ሳይኖረው የሚቀር
አይመስለኝም ።''

''እግዜር ይወቀው'' አለ ፥ አል ሳዊ ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ሳብር የመሐመድ አል
ሳዊን ፊት ትኵር ብሎ ተመለከተ ። እርጅና ያነተ

t.me/OLDBOOKSPDF

በው ፊት ነበር ያየው ። ልብ ብሎ ሲመለከተው ከዚህ ቀደም ያላስተዋለው አዲስ ገጽታ ይከሰ ትለት ጀመር ።

"ወንጀሉ ሌላ ገጽታ ያለው አይመስል ህም?"

"እኔ እንዴት ላውቅ እችላለሁ?" አለ አል ሳዊ ፡ ጥያቄው የማያገባው መሆኑ እንዲታወቅለት ትከሻውን በመነቅነቅ ።

አምን ፡ ወደ ደይን አፉ በመቃረብ ላይ ያሉ ሰዎች እንደዚህ ነው የሚያቅበጠበጣቸው ።

"ከምትናገረው የበለጠ የምታውቀው ነገር እንዳለ ይሰማኛል" አለ ሳብር ፡ በማግባባት ።

"የሚበልጠውስ የማላውቀው ነው ።"

"ባለቤቲቱን እንደገና የጠየቋት ነገር አለ?"

"መርማሪው መኰንን ከአንዴም ሁለቴ እያስጠራ መርምሯታል ።"

"አሊ ሰርያኩስ ከሰጠው ቃል የተነሣ ይሆን?"

"እንደሱ ይባላል ።"

"ይህን ሁሉ መረጃ የሰጠህን ፖሊስ ወዳጅ ህን ታምነዋለህ?"

"ከእሷ ከራሷ እንደበት እኮ ነው የሰማሁት!"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ከማን? ከባለቤቲቱ?"

"አምን ፤ ትናንት ማታ ብቅ ብላ ነበር ።"

ሳብር አለመኖሩን አውቃ ነው የመጣችው። ምን ያስችው ሽረኛ ናት? የምርመራው ጋጋታ እንደሆን ፥ ያጋጠመውን ችግር ቅንጣት ታህል አልቀረፈለትም ። በሌላ በኩል ደግሞ ፥ ሳብር በመሐመድ አል ሳዊ ፊት አሥሩን ከመዘላበድ መጠንቀቅ አለበት ። ዳሩ ምን ይሆናል ፤ 'የበላ ውን ያብላላዋል' ይባል የለም?

"ሰሰርያኩስ ስለ ሰጠችው ገንዘብ የተናገረ ችው ነገር ይኖር ይሆን?"

"አምን ፤ በገንዘብ ረድቼዋለሁ ብላለች ።"

"እንዲህ እውነቱን ማውጣቱ ይሻታል ።"

"እንዴት ማለት?"

"ከአሲ ሰርያኩስ ጋር የምትዋደቅ. . ."

"ስለዚህ ነገር አንተ ምን ታውቃለህ?" ቡግለት አል ሳዊ አምሮ ጠየቀው ።

"ወንድ ሁሉ ወንድ. . .?"

"ወዳጄ ፥ እኔ በዕድሜ ብዙ እበልጥሃለሁ" በማለት አል ሳዊ ንግግሩን አቋረጠው ።

"መልካም ባሕርይ የላትም ማለትህ ነው?"

"አልወጣኝም!"

"በታማኝነትዋ አትጠራጠርም ማለት ነዋ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

አል ሳዊ ዓይኖቹን ደጋግሞ ከደን ከፈት ካደረገ በኋላ ፡ ‘‘መጠራጠር ሳይሆን ሥራዋን ደህና አድርጌ አውቃለሁ ።’’

የሳብር ምርመራ ከዋናው ምርመራ የበለጠ ውጤት እያሳየ ነው ። ያላሰባቸው ሁኔታዎች ቁልጭ ብለው መታየት ይዘዋል ።

‘‘ለባልዋ ታማኝ አልነበረችም ነው የምትለኝ?’’

‘‘ነገሩ ቢያሳዝንም ሐቁ ታማኝ አልነበረ ችም ነው ።’’

‘‘ምስጢሯን ከከሊል ሞት በፊት ታውቅ ነበር?’’

‘‘ደህና አድርጌ አውቅ ነበር ። ነገር ግን የምስጢሯ መጋለጥ ከሊልን ሰላም ይነሣዋል በሚል ፍራቻ ነው ዝም ያልኩት ።’’

‘‘መርማሪው መኰንን ሲጠይቅህ ይህን ሁሉ ገልጸህለታል?’’

‘‘የግድ ነዋ ።’’

‘‘በባለቤቲቱና በአሊ ሰርያኩስ መካከል ያለውን ግንኙነትስ?’’

‘‘አሊ ሰርያኩስ. . . የእርሱን ጉዳይ እንኳን አላነሣሁም ።’’

አል ሳዊ ወጥመድ ውስጥ ሊያስገባው እያ መቻቸው እንደሆነ ሳብር ጥርጣሬ ገባው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ስንጨዋወት የነበረው እኮ ስለ እርሱ ነበር?"

"ስለ እርሰዋም ተጨዋውተናል ።"

"እርሷንማ በእርሱ ምክንያት ነው ያነጣናት።"

"አይመስለኝም ። ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከ ተው ሌላ ሰው አለ ።"

—ነገር መጣ! የከሪማ ጣጣ ወደ ሌላ ሰው ሊዛመት ይሆን? — አለ ሳብር በሐሳቡ ።

"ሌላ ሰው አልከኝ?"

"አዎን ፤ የፈተኛው ባልዋ ።"

"ለከሊል የሸጣት ባልዋ?" አለ ሳብር ፡ ትንፋሹ ቀዝቀዝ ቀዝቀዝ አያለ ።

"መሸጥ ሳይሆን ለወረት ለወጣት ነው የሚ ባለው ።"

"ለመሆኑ ይህን ሁሉ ምስጢር እንዴት አድ ርገህ ልታወቅ ቻልክ?"

"ብዙ ጊዜ እናትዋ ቤት ሲመላለስ አይቼ ዋለሁ ።"

ጉድ ፈላ!

"ሁኔታውን ለማንም አልተናገርክም ማለት ነው?"

"ሁኔታውን ከሊል ቢያወቅማ በሕይወት አይቆይም ነበር ።"

"ቢቆይም እኮ መሞቱ አልቀረም ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"የሚያሳዝነው የፈራሁት መድረሱ ነው!"

"ለመሆኑ በየጊዜው እናትዋን እያሄደች እንድትጠይቅ እንዴት ሊፈቅድላት ቻለ?"

"እርጅናና ጥርጣሬ አይተዋወቁም ።"

"በምርመራው ወቅት ይህን ሁሉ ምስጢር አውጥተሃል ማለት ነው?"

"በሚገባ!"

"ሰውዬውን ይዘው አልመረመሩትም?"

"ግድያው በተፈጸመበት ምሽት ካይሮ አልነበረም ።"

"ካይሮ ባይኖርም ግድያውን አላቀደም ማለት አይቻልም ።"

"አቅዱ ይሆናል ። መርማሪዎቹ እንደሆን ለቀ ውታል ።"

"እንዴት ለቀቁት?"

"ምክንያት ሊኖራቸው ይችላል ።"

"ምስኪኑን አሊ ሰርያኩስን የያዙት ለማሳ ሳቻ ነው በለኛ!"

"ሌላም አልባሌ ሰው ቢይዙ ማን ይከለክ ላቸዋል!"

ሳብር ፣ ደጋግሞ ምራቁን በመዋጥ ጉሮሮውን ለማራስ ሞከረ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ስናወራው የቆየነው ነገር ሁሉ መሠረት የሌለው መላ ምት ነው ።"

"ሊሆን ይችላል" አለ አል ሳዊ ፡ በግድ የለ ሽነት ።

"በነገሩ እርግጠኛ ነኝ አላልከኝም እንዴ?"

"አንጋገሬ የተጐላደፈ ሊሆን ይችላል ።"

"እንግዲያው ዞረን ዞረን ጭውውታችንን ከጀመርንበት ስፍራ ተመለስን በለኛ?"

አል ሳዊ ጭንቅላቱን በአሉታ በመነቅነቅ፡ "ጥርጣሬዬ ትክክለኛ መሆኑን ቀልቤ አረጋግጠ ልኛል" አለ ።

"ከባልዋ ውጪ በመባለግዋና በወንጀሉ መካከል ግንኙነት ላይኖር የሚችል አይመስል ህም?"

"ላይኖር ይችላል ። ሊኖር ቢችልማ ሰው ዬውን አይለቁትም ነበር ።"

"አሊ ሰርያከስ ደህና ጠቅሟቸዋል ማለት ነው" አለ ሳብር ፡ በንቀት ።

"ከሊልን የገደለው እርሱ ከሆነ. . ."

"እርሱ ገዳይ መሆኑን ትጠራጠራለህ!"

"በዚህ ዓለም ከጥርጣሬ ውጪ የሆነ ነገር ብዙም አይደለም ።"

"ሳስበው ፡ የምታምነውንም የማታምነውንም ነገር መለየት ያቅተኛል ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለምን አላምንም? ስለ ተሳላኪው ልጅ የነገርከሀ ታሪክ ትዝ ይልሃል?"

"እንግዲያው እርሱው ነው ገዳዩ።"

አል ሳዊ በረጅሙ ተነፈሰ። "እኔ እንደሚ መስለኝ ገዳዩ በቅርቡ ሌላ ዱብ ዕዳ ነገር መፈጸሙ አይቀርም። ምን አለ በለኝ፤ ውሎ ይደር እንጂ በአንድ ነገር ላይ እጁን ይሰነዝራል።"

ሳብር ከሪማን አግኙዩ ማንኛውንም ነገር ሳይጠይቃት እንቅልፍ በዓይኑ ሳይዞር ቈረጠ። —ምን ዓይነት ሸረኛ ሰይጣን ናት? የመጣው ይመጣል እንጂ እንዲህ ተጫወታብኝ አትቀርም። መግደል የማይሰኝ መሆኔን እንደሆን አይታዋለች። ላማኛት ብቻ — በማለት ሳብር ከሐሳቡ ጋር ተሟገተ።

"የፊተኛው ባልዋ ግድያውን እንዳላቀደው እርግጠኛ ነኝ" አለ አል ሳዊ፡ ሳብርን ከሐሳቡ እያነቃው፤ "ግድያውን ያቀደ ለመሆኑ ፍንጭ ቢያገኙበት ኖሮ እንደዚያ በቶሎ አይለቁትም ነበር። ሌላው ወንጀል ግን..."

"ከፊተኛው ባልዋ ጋርማ ዝምድና አላቸው ይባላል። ያገኑትዋ ልጅ ነው መሰለኝ። ስለዚህ መጠያየቃቸው ነውር የለበትም" አለ ሳብር፡ አል ሳዊን በማቋረጥ።

"እኔ በበኩሌ ጥርጣሬ ካደረብኝ ቆይቷል። መጀመሪያ ላይ እናትዋ እዚው አቅራቢያ ትኖር

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር ። ከሊልም እናትዋን ለመጠየቅ በምትፈልግ በት ጊዜ እርሱው ራሱ ያደርሳት ነበር ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ፡ እናትዋ ፡ ዘይቱን ወደሚገኘው ወደ ሳሂል ገዳና ቅጥር ሃያ ተዛወረች ። ሆቴሉ ካለበት ብዙ ይርቃል ። ከሪማ ይህን ያደረገችው ከከሊል ተለይታ ጥቂት ቀናት ከእናትዋ ጋር ለመሰንበት እንድትችል በማለት ነው ። መጀመሪያ ላይ ሁኔታውን ከሊል አልወደደውም ነበር ። እያ ደር ግን ተለማመደው ።"

አል ሳዊ ያላሰበውን ፍንጭ ሰጠው ። ቅጥር ሃያ . . . ሳሂል ገዳና . . . ዘይቱን ።

የሳብር አዕምሮ ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ገብቶ ይናወጥ ጀመር ። አፉን ደም ደም አለው . . .

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥራ ስድስት

ሳብር ወደ ዘይቱን ተነሥቶ ለመሄድ ቢያ ስብም በዓይነ ቁራኛ የሚጠበቅ በመሆኑ ፡ ሐሳ ቡን በጥንቃቄ ከመፈጸም የተሻለ አማራጭ እንደ ሌለው ተገነዘበ ። መሐመድ አል ሳዊ ሰሞኑን ከሊል ወንበር ላይ መኰፈስ አዘውትሯል ። ሳብር ከሩቅ ሆኖ ሲመለከተው ልክ ከሊልን መስሎ ነው የታየው ። ወዲያው ደግሞ ነገሩ ይገባዋል. . . ሁኔታው ፍንትው ብሎ ይታየዋል. . . ከሊል ፈጽሞ በቦታው እንደ ሌለ. . . ከሊልን እሱ ራሱ እንዳ ልነበረ እንዳደረገው ሐቁ ይከሰትለታል ።

—ከሊል — ነፍሱን ይማረውና — ባሁኑ ጊዜ ከሊል ማሰብ ይችል ይሆን? ከቻለስ በአሁ ንዋ ቅጽበት ምን ይታየው ፡ ምን ያሰላስል ይሆን? ስለ እኔስ ምን ይል ይሆን? — እያለ ሳብር በሐ ሳቡ ያወጣ ያወርድ ገባ ።

ሳብር ጠጋ ብሎ አል ሳዊን ሰላም አለው ። አል ሳዊም ለቀረበለት ሰላምታ ከአንገት በላይ የሆነ አጸፋ መልሶ ሾቴሉ መዝገብ ላይ አቀረቀረ። የትናንቱን ወይይትና ጭውውት የረሳው ይመ ስላል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳብር ፡ ወደ ሆቴሉ መመገቢያ ክፍል አም ርቶ ሳያሰኘው የግዱን ቁርሱን ተመገበ ። ከሪማ ክፉኛ በነፍሱ በመጫወት ላይ እንዳለች ተሰማው።

—እንዲህ ቸልዳብኝ አትቀርም ። የፈለገውን ዘዴ ብትጠቀም አታመልጠኝም ። አደርግላታ ለሁ!—በማለት ሳብር በሐሳብ ይባክናል ። የሆቴሉ የእንግዳ ማረፊያ ክፍል ምንም የተለወጠ ነገር አይታ ይበትም ። የተለመደው ጫጫታ ፡ የተለመደው ወካታ ይሰማበታል ። ወሬው ሁሉ ስለ ጦርነት ፡ ስለ ወረት ብቻ ነው ። የለማኙ ዜማም አልተለ ወጠም ።

የኤልሐም የስልክ ጥሪ ።

“ዛሬ ለጥቂት ደቂቃዎች መገናኘት እንች ላለን?”

“አንችልም” አሳት ሳብር ።

“እስቲ መገናኘት የማንችልበትን አንድ በቂ ምክንያት ስጠኝ ።”

“አልችልም ።”

“የምንገናኘው አባትህን ለሚመለከት ጉዳይ ቢሆንም አትችልም ማለት ነው?”

“አባትህን?”

“አዎን ፡ አባትህን ።”

“ስለ አባቱ ምን ያገኘሽው ነገር አለ?”

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንግናኝና እነግርሃለሁ ።"

"አልችልም አልኩሽ!"

ከወረደበት መዓት የአባቱ መገኘት እንኳን ሊገላግለው እንደማይችል ተሰማው ።

"ስለ አባትህ ጉዳይ እኮ ነው የምፈልግህ ። እስከ ዛሬ በፍለጋ ስትንከራተት ስለ ቆየህበት ጉዳይ. . ."

"ታዲያ ምን ይሁን?"

"አንተ ካልቻልክ እኔ ልምጣ?"

"አትምጪብኝ!" አላት ሳብር ፥ ትዕግሥቱ የተሟጠጠ መሆኑን በሚገልጽ ድምፅ ።

—ኤልሐም ስለ አባቱ ምን ወሬ አግኝታ ይሆን?—በማለት አሰብ አደረገ ። ከእንግዲህ ወዲያ ያገኘችውን ብታገኝ ምን ፋይዳ አለው? በሳብር ጆሮ ውስጥ የሚያቃጭለው ዘይቱን የተሰኘው ስም ብቻ ነው ። ኤልሐም ፥ "ስለ አባትህ ጉዳይ እፈልግሃለሁ" እያለች የወተወተችው ባባቱ አመካኝታ እንደ ወትሮው ስለ ወደፊት ኑሮው ልታነጋግረው ሳይሆን ይቀራል! ሳብር ነገር ዓለሙን ተወት አድርጎ ካዘዘው ርካሽ ወይን በብዛት ተጎነጨ ። ከዚያም እላይ እታች እየተንጐራደደ በዓይነ ቁራኛ የሚጠብቁትን የምስጢር ሠራተኞች የሚሸውድበትን እቅድ በሐሳቡ ይነድፍ ጀመር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በመጨረሻም ድካም ስለ ተሰማው ወደ ክፍሉ አዘገመ ። ሴሊቱን በሙሉ እንቅልፍ ባይኑ አልሠረም ። ጠባቂዎቹ ይሽኔ ለጥ ብለዋል ብሎ በማሰብ ጎህ ከመቅደዱ በፊት ተነሥቶ በዝግታ ወደ ሆቴሉ ምድር ቤት ወረደ ። ከሆቴሉ ሠራ ተኞች አንዱ መግቢያው በር አጠገብ ተጋድ ሟል ። በሩን በቀስታ ለመክፈት ቢሞክር ተቆ ልፎ አገኘው ። በሩ አጠገብ የተኛውን ሠራተኛ ሊቀሰቅሰው አስቦ ከምስጢር ሠራተኞቹ አንዱ ይሆናል በሚል ፍራቻ ተወው ። ተመልሶ ፎቁን በቀስታ ሲወጣ አንድ ዘዴ ብልጭ አለበት ። ወደ ሕንፃው ጫፍ በፍጥነት ገሰገሰ ። ተዘግቶ የሰነበተውን የክሊልን መኖሪያ ቤት ሲያልፍ ሰውነቱን ስቅጥጥ አደረገው ። የሕንፃውን ድምድ ማት አቋርጦ ያለ አንዳች ማመንታት ወደሚቀ ጥለው ሕንፃ ጣሪያ በዝላይ ተሻገረ ። ቁና ቁና እየተነፈሰ የሕንፃውን ፎቆች አንድ ባንድ በመ ውረድ ከምድር ቤቱ ደረሰ ። የሕንፃው የጥበቃ ክፍል በሩ ተዘግቷል ። የሕንፃው ዋና መግቢያ በርም ተከርችሟል ። ከያቅጣጫው የሚያጋጥመው መሰናክል ብቻ ሆነበት ። በሩ ላይ የተሰካውን የቁልፉ መክፈቻ ቢሞክረው አልሆር አለው ። የበሩን እጀታ ሞከረ ። አልተዘጋም ። በቀስታና በጥንቃቄ በሩን ከፈተ ። ከተከፈተው በር ደፍ ላይ አንድ ሰው ድቅን አለበት ።

"ማን ልበል!" አለ አንድ ድምፅ ።

ሳብር ፡ ምንም ጊዜ ሳይሰጥ ሰውዬውን

t.me/OLDBOOKSPDF

በቡጢ መንጋጋው ላይ አቀመሰው ። የተመታው ሰው በድንጋጤ ግራ ቀኝ ሲንገዳገድ ፥ ሳብር ሆዱ ላይ በርግጫ ለትምት መሬት ላይ ዘረረው ። ሰውዬው ወድቆ መቅረቱን ሲረዳ ፥ ከሕንፃው በጥድፊያ ውልቅ ብሎ ወጣ ። በሩጫ መንገዱን አቋርጠ በአካባቢው ወዳለው አደባባይ ሲፈጥን ፥ ሳያስበው ከአንድ ነገር ጋር ተጋጨ ።

"ያገር ያለህ! የመንግሥት ያለህ! አትግደ ለኝ ዓይነ ሥውር ነኝ!"

"ይቅርታ ፥ ጭለማ በመሆኑ አላየሁህም" የሚለትን ቃላት ሰንዝሮ ፥ ሳብር መንገዱን ቀጠለ ።

ሁኔታው ሳብርን ስቅጥጥ አደረገው—የተረገመ ለማኝ ። መድረሻ ያሳጣህ! — አለ በሐሳቡ ።

የተሳፈረው ታክሲ ሳብርን ወደ ዘይቱን ይዞት በረረ ። — የምስጢር ሠራተኞቹ ሲፈልጉኝ ይክረሙ — በማለት እንደ መሣቅ ቃጣው ። ሳሂል ጐዳና እንደ ደረሰ ፥ ታክሲውን አስቁሞ ወረደ ። ጥቂት ርቀት በእግሩ ከሄደ በኋላ ለብቻው ወደሚገኘው አንድ ቪላ ቤት አመራ ። ሌሊቱ ወገግ ማለት ጀምሯል ።

ባመጣ ያምጣው በሚል ስሜት ፥ ሳብር የቪላውን ደወል አንቃጨለ ። በሩ ተከፈተ ። ከሪማ! መጀመሪያ የተዋደቁ ምሽት የለበሰችውን የሌሊት ልብስ አንገርግጋ ከፊቱ ግትር ብላለች ። ግሩ አድርጓት ወደ ውስጥ ጥልቅ ሲል ፥ ያገ አድርጋው ፥ "አብደሃል እንዴ?" አለችው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ከበሩ ገባ ብሎ በተንጣለለው ኃይለኛ መብራት ብርሃን ዓይን ለዓይን ተያዩ ።

"ጨርሶ ጨርቅህን ጥለሃል ማለት ነው?" አለችው ።

"ምንም አልቀረኝ!" ደም በለበሱ ዓይኖቹ ትኮር ብሎ ተመለከታት ።

"ይኸ ድርጊትህ ምን እንደሚያስከትልብህ ገብቶሃል?"

"ያለ ምንም የተስፋ ሚላንጭል ዓይን አፍጥጦ ከመጠበቅ የማይሻል ነገር የለም!" አላት : በምሬት ።

"አሁንም ታግሠህ መጠበቅ አለብህ ። እን ዲያው ስታስበው የእኔ ሁኔታ ካንተ አሥር እጅ የባሰ መሆኑ አይገባህም?"

"እስከ መቼ ነው የምታገሠው፣ እስከ መቼስ ነው የምጠብቀው? ነፍሴ እስክትወጣ? ስልክ ያልደወልሺልኝ ለምንድን ነው?"

"አል ሳዊ ድምፄን ይለያል ብዬ ፈርቼ ነው።"

"ብታስበበትማ በሌላ ሰው አስደውለሽ እንድቀርብ ልታደርጊ ትችዪ ነበር ።"

"መርማሪዎቹ በጥያቄ ስላዋከቡኝ በፍርሐት ስርበደበድ ነው የሰነበትኩት ።"

"እሱን ተዪው፤ በማበረ ሥጋ ማንኑነታችን

መካከል የግድያ እቅድ የምትነድፊው ሴትዮ ተርበደበድኩ ትይኛለሽ?"

"ኧረ እባክህን አትጩህ። እናቴ ተኝታለች።"

"እርሷማ ግብረ አበርሽ ናት።"

"ጨርሶ አብደሃል! ፊትህ ሁሉ ያስፈራል!"

"መኝታ ቤትሽን ማየት እፈልጋለሁ!"

"መኝታ ቤቴ ደግሞ ምን ያደርግልሃል?"

"አትቀልጂ፤ ከማን ጋር እንዳደርሽ ማየት እፈልጋለሁ።"

"በእውነትም ለይቶልሃል!"

"የቀድሞ ባልሽ አይደል ያለው?" አለ፣ ከፍሉ እስኪያስተጋባ በመጮህ።

"ማን ነው ከእኔ ጋር እዘሀ አለ ያለህ? ከእኔ ጋር ማንም የለም።"

"ማንም ይበል፤ እኔው ራሴ መኝታ ቤትሽ ገብቼ ማረጋገጥ አለብኝ።"

ወዲያ ገፍትሯት ወደ ውስጥ ተንደርድሮ በመግባት ዓይኑ ላይ ግጥም ያለውን በር ከፈተ። አሮጊት ሴት እንቅልፍ ድብን አድርጎ ወስዷታል። የሚቀጥለውን በር ከፈት ሲያደርግ ሰው የተኛ በት መሆኑ የሚያስታውቅ አልጋ ተመለከተ። የከሪማ መኝታ ቤት ይሆናል ብሎ አሰበ። በቪ ላው ውስጥ ያሉትን ክፍሎች በሙሉ እየከፈተ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቢፈትሽ ጥርጣሬውን የሚያረጋግጥለት ምልክት ማግኘት ሳይችል ቀረ ።

“ጭንቅላቴን ነው ያዞርሽው!” በማለት ከሪማ ወደ ቆመችበት ስፍራ ተመለሰ ።

“አንድ ነገር ላስጠንቅቅሽ ። ምርመራው እስኪያልቅ ድረስ ከቀድሞ ባልሽ ጋር መገናኘት የለብሽም” አላት ።

“ሳብር ፤ ይሆን ሁሉ እንድታደርግ የሚገፋፋህ በመካከላችን የገባ አንድ ሰይጣን የሆነ ሰው መኖር አለበት” አለችው ፣ ልታበርደው እየሞከረች።

“ያገኘትሽን ልጅ አልነበረም ያገባሽው?”

“አምን ፤ ነው ።”

“ለገንዘብ ብሎ አይደለም ለክሊል አሳልፎ የሰጠሽ? አንቺም ብትሆኚ ክሊልን በእጁ እንዲጠፋ ልታደርጊው የበቃሽው ለገንዘብ ብለሽ አይደለም?”

“በየደረስክበት እንዲህ የምትዘላብድ ከሆነ ይዘው ይጠፍሩናል ።”

“ጥያቄዬን መልሺ!”

“አንተ ምንም የማይገባህ ደደብ ነህ! ሕይወቴን አደጋ ላይ ለመጣል የበቃህት ሰው መስለሽኝ ስላፈቀርኩህ ነው!”

“የቀድሞ ባልሽ እዘህ ድረስ እየመጣ ይተኛሽ አልነበረም?”

t.me/OLDBOOKSPDF

“እባክህ እመነኝ! ወዳጅነታችንንም አትዘንጋ!”

“ሴት ስትባሉ አልጋ ላይ ስትወጡ የለየላችሁ ተዋናይ ትሆናላችሁ።”

“እመነኝ እባክህ! የምትናገረው ሁሉ ውሸት ነው!” እንደ መሣቅም እንደ ማልቀስም ቃጣት።

“ለመሆኑ ተይዥ በገመድ መንጠልጠሉን የምፈራ ሰው እመስልሻለሁ? ዓይኔ እያየ ሌላ ሰው እጅ ስትገቢ ዝም እንደማልልም እወቂ!”

“በመካከላችን ሌላ ሰው የለም። እመነኝ ነው የምልህ! እዚህ ቆመን የምንጨቃጨቅ ከሆነ ጀምበር ከመውጣትዋ በፊት ተይዘን ወህኒ መውረዳችንን እወቀው!”

“አንቺ ውሸታም ሸርመጣ! በውሸትሽ ሕይወቴን ገደል ከተሻታል!”

“እባክህ ተለመነኝ፤ እባክህ እመነኝ። እወ ድሃለሁ። ማንኛውንም ነገር ያደረግሁት ላንተ ስል ነው።”

“እሱ በእጄ ያስገኘሁትን የወንጀል ፍሬ ከወዳጅሽ ጋር ለመቋደስ ስትዪ ሕይወቴን ትበያ አልበሰሻታል!”

“ወዳጄ አንተው ብቻ ነህ። ነግሬሃለሁ፤ ኋላ እንዳይቆጭህ። መነታረኩ ይብቃን። እንዲያውም ብለህ ነው እንጂ ከቀድሞ ባሌ ጋር ከተያየን ዓመታት አልፈዋል።”

t.me/OLDBOOKSPDF

"አንድ የሚያንገበግበኝ ነገር ፥ አንቺ የኪሊ ልን ገንዘብ ታቅፈሽ ስትሄጂ ፥ ለእኔ የተረፈኝ የሰው ነፍስ ማጥፋት መሆኑ ነው ።"

"ምን ዋጋ አለው ። አሁንማ አልቆልናል፤ እንዲያው ለነገሩ ብቻ አሁንም አታምኚም?"

"አላምንሽም ።"

"ካላመንከኝ ፍላጐትህ ምንድን ነው?"

"አንቺን መግደል ።"

"ከገደልከኝማ ይሰቅሉሃል!" አለች በጩኸት ።

ወዲያው በርካታ የሰው ኮቴ ተሰማ ። በሩ በኃይል ተንኳኳ ።

ከሪማ እሪታዋን አቀለጠችው ። "ፖሊሶች! በቃ አለቀልን!" አለች ።

ሳብር ዘሎ አፈፍ አደረጋት ። እጆቹ አንገትዋን እንቅ ፥ ጉሮሮዋን ጭምቅ አድርገው ያዙ ። ትንቅንቅ . . . የበር ኳኳታ . . . ጩኸት . . . የበር ደምደምታ . . . ስልምልምታ . . . የበር ውልቅልቅታ . . . ወለልታ!

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ አሥራ ሰባት

ሳብር ወህኒ ቤት ወርዶ ብቻውን ኑርምት ብሎ ተቀምጧል ። ዞር ብሎ የሚያየው አንድም ዘመድ አዝማድ የለውም ። ኤልሓምም የረሸም ጊዜ ትዝታው ሆኖ ቀርታለች ። እርስዋም ብት ሆን ከሳብር ጋር የተገናኘችበትን ቀን ሳትረግም አትቀርም ።

ጋዜጦች በየዕለቱ ሁኔታውን ከተሰያየ አቅ ጣጫ በስፋት ያብጠለጥሉታል ። ሳብር ፡ ከሪማ ፡ መሐመድ ራጋብ — የከሪማ የመጀመሪያ ባል— በየቀኑ ከየጋዜጣው ዓምድ የማይለዩ ስሞች ሆነዋል ። የሳብር ፡ የኤልሓም ፡ የባሲማ አምራንና የጋብቻዋ ፎቶግራፎች የአንባቢዎችን እይታ ሲማ ርኩ ሰንብተዋል ።

ወህኒ ቤት እንደ እናቱ ማኅፀን ለሳብር ከሕ ይወት ውጣ ውረድና ጣጣ መጠለያ ሆኖታል ። ከወህኒ ቤት ውጪ ግን ስለ እርሱ ብዙ ይወ ራል ፡— ሳብር — ወዳጁን ሲገድል እጅ ከፍንጅ ተያዘ ። ሳብር — ብዙ ታሪክ ያለው ወንጀለኛ ። ባሲማ አምራን — የእስክንድርያ ሴተኛ አዳሪዎች ንግሥት! — ሳብር ከናቱ ያገኘው ውርስ . . .

t.me/OLDBOOKSPDF

ከብላይ አባት ... በፍለጋ መንከራተት ... የማይጨበጥ አለኝታ ... ተስፋ መቁረጥ ... ድህነት. . . ፍቅር. . . ግድያ ። —ሳብር የአንጉል ኑሮና የእሱይ ተግባር ተምሳሌት ። እነዚህ ሁሉ የሳብርን ሕይወትና ድርጊት እንዲያንጸባርቁ በጋ ዜጦች የሚወጡ አርዕስቶች ነበሩ ። ጋዜጦች ስለ ሳብር ሕይወት ሲያትቱ እንድ በጎ ጐን እንዳለው ሳያመለክቱ አላለፉም ። ከኤልሐም ጋር የመሠረ ተው ወዳጅነትና ፍቅር ፡ ከዚያ እሱይና አስከፊ ሕይወቱ ውስጥ ኤልሐም መገኘት መቻልዋ ያላ ስገረመው ፡ ያላስደነቀው አልነበረም ።

ባሲማ አምራን ፡ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን አንድ ልጅዋ ሳብርን በምኞትና በተድላ ተንደ ላቅቆ እንዲኖር አድርጋዋለች ። ሀብቷና ንብረቷ እንደ ማለዳ ጤዛ ሲረግፍ ፡ በፍለጋ አባቱ ካለበት ከመድረስ ፡ ወይም ደግሞ የሰው ነፍስ አጥፍቶ በሚያገኘው ጥቅም ራሱን ከማስተዳደር ሌላ አማራጭ እንደ ሌለው አስገንዝባዋለች ።

ወንጀል መርማሪው መኰንን ሳብር ላይ የጥርጣሬ ዓይኑን የጣለው ገና ከመነሾው ነበር ። ከዚህም የተነሣ የምስጢር ሠራተኞች እንቅስቃ ሴውን ሁሉ በቅርብ እንዲከታተሉ አድርጎ ነበር ። መሐመድ አል ሳዊም ፡ ስለ ከሪማ በባልዋ ላይ መወሰለት አሥሩን ያወራለት የነበረው ባዘጋጀ ለት ወጥመድ ውስጥ እንዲገባ አስቦ ነበር ። አል ሳዊ መሰሪ ሽማግሌ ነበር ። ሁሉም ነገር ካለፈ

t.me/OLDBOOKSPDF

በኋላ እንደ በግ ተነድቶ አራጁ ፊት መቅረቡ ሳብርን ክፉኛ ቆጭቶታል ።

የከሪማ የመጀመሪያ ባል ፡ መሐመድ ራጋብ ፡ መርማሪው መኩንን ፊት ቀርቦ ሲጠየቅ ፡ በክሊል ግድያ እጁን ያላስገባ መሆኑን አበክሮ ገልጿል ። ከዚህ የተነሣ የጥርጣሬ ዓይኖች በሙሉ ሳብር ላይ አትኩረዋል ። ጋዜጦችም ቢሆኑ መሐመድ ራጋብ ንጹሕ መሆን አለመሆኑን መለየት አዳግቷቸዋል ። ሳብርን ጭከና ከተሞላበት የወንጀል ሥራ ወደ መፈጸም ያደረሰው ምክንያት ምን እንደሆነ ሊደርሱበት የቻሉ አይመስልም። ሳብር ራሱም ቢሆን ፡ የሕይወቱ ድብቅ ምስጢር ከመሞቱ በፊት አይገለጥ ይሆናል በማለት እጁን አጣምሮ ለመቀመጥ ተገዷል ።

ሳብር ወህኒ ቤት ሆኖ የሞቴሉን በር ጠባቂ መሐመድ አል ሳዊን ሁል ጊዜ ያስታውሰዋል ። ሽረኛ ሰይጣን. . . ተናግሮ አናጋሪው መሐመድ አል ሳዊ ። እንደ ወራጅ ውኃ እያሟቀና እያለ ዘበ ወጥመዱ ውስጥ እንደ ጨመረው ሲያስበው ይገርመዋል ። የከሪማን አድራሻ እንኳን እንዴት አድርጎ በንግግሩ መካከል ጣልቃ አስገብቶ እንዳሳወቀው ሲያስታውሰው መሰሪነቱ ይደንቀዋል ። በውድቅት ተነሥቶ ከሪማ ወዳለችበት ስፍራ ለመሄድ ሲፈጥን አጋጥሞት በቡጢና በእርግጫ ዘርሮ የጣለው የሞቴሉ አገራባች ሕንፃ ዘበኛ በሐሳቡ ይመጣበታል ። በጨለማ ውስጥ ሲደናበር

t.me/OLDBOOKSPDF

ገጥሮ ያለፈው ያ ለማኝም ዜማው ጀሮው ውስጥ ያንቃጭልበታል ። የምስጢር ሠራተኛው ድም ፁን የሰማው ለማኙን ገፍትሮ ካለፈ በኋላ ይቅ ርታ ሲጠይቀው ሳይሆን አይቀርም ። ድራሹ የጠፋ ለማኝ!

ጋዜጠኛ የሳብርንና የእናቱን ያለፈና የጐደፈ የሕይወት ታሪክ እየጐለጐሉ ማውጣት ይዘዋል ። አንድ መጽሔት ፡ ስለ ሳብር ሕይወት ጠለቅ ያለ ጥናታዊ ጽሑፍ አትሞ አውጥቷል ። ጋዜጠኞም ሆኑ መጽሔቶቹ የደረሱባቸው መደምደሚያዎች የተለያዩ ነበሩ ።— የከሪማና የክሊል አላቻ ጋብቻ። —የገንዘብ እጦት ፡ የወንጀሉ ምክንያት ። —ከሪማ፡ የመደብ ፍልሚያው ሰማዕት. . . ሳብር — አስተዳደጉ በገመትና በወንጀል ሰፈር ።— ሳብርና ኤዲፕስ ሬክሳዊ የእናት ፍቅር ። — ሳብር ፡ ከሪማን የተመለከታት የእናቱ ምትክ ፡ የእናቱ አምሳል አድርጎ ሲሆን ፡ ከሊልን ደግሞ በሁለቱ ውሕደት መካከል እንደ ተጋረጠ እንቅፋት አድርጎ ያየው በመሆኑ መወገድ ነበረበት ።

ሳብር ስላለፈው ሕይወቱ ከያቅጣጫው የተሰነዘሩትን ጉራማይሌ አስተያየቶች ካነበበ በኋላ ፡ የሰጠው ምላሽ ትክሻውን መነቅነቅ ብቻ ነበር። ከሪማ የተናገረችው ውሸት ወይም እውነት መሆኑን ፤ ሰይድ ኤል ራሕሚ መኖር አለመኖሩን አውቃለሁ የሚል መኖሩ ዘበት ነው — የሚሰው ሐሳብም በልቡ ውስጥ ይጉላላ ጀመር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ የሕግ ጠበቃ ሳብር ወደ ታሰረበት ወህኒ ቤት መጥቶ ሊያነጋግረው ሐሳብ እንዳለው ገለጸለት ። ሳብር ጠበቃውን ከዚህ ቀደም አንድ ስፍራ ያየው ቢመስለውም የት'ና ምን ጊዜ እንደ ተገናኙ ማስታወስ አልቻለም ። በዕድሜው ጠና ያለውና ግርማ ሞገስ የተጐናጸፈው የሕግ ሰው ሊያነጋግረው በመምጣቱ ሰውነቱን ቀለል አለው ።

"በነገረ ፈጅነት እንድትቆምልኝ በፍርድ ቤት የተመደብክልኝ ጠበቃ ነህ?" በማለት ሳብር ጠየቀው ።

"አይደለሁም" አለ ሰውዬው ያለ ማመንታት። ከዚያም በለዘብታ ፡ "መሐመድ ኤል ታንታዊ እባላለሁ" በማለት ራሱን አስተዋወቀ ።

ሳብር የሰማውን ስም ማስታወስ አልቻለም ።

"ታዲያ ጉዳዬን ማን አቀረበልህ?"

"ለጊዜው እንደ ወዳጅህ ቁጠረኝ ።"

"ወዳጅነት ብቻውን አይበቃም ፤ በበኩሌ የምከፍልህ ምንም ገንዘብ የለኝም ።"

ሰውዬው ሳብርን በፈገግታ ከተመለከተው በኋላ ፡ "እኔ የኢሳን ታንታዊ ታላቅ ወንድም ነኝ ። 'ስፊንክስ' የተባለው ጋዜጣ የማስታወቂያ ክፍል ኃላፊ የሆነውን ታንታዊን እንደምታስታውሰው ተስፋ አደርጋለሁ" አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ደህና አድርጌ አስታውሰዋለሁ ። ግና ሳይህ የማውቅህ የመሰለኝ ለዚህ ነው ለካ!"

ሳብር ቀጠል በማድረግ ፡ "በነገረ ፈጅነት ትቆምልኛለህ ማለት ነው?" በማለት በማስተዛዘን ጠየቀው ።

"አዎን ፤ ፍቃድህ ከሆነ ።"

ሳብር ድንገት ትውስ ብሎት ፡ "ኤልሓም!" በማለት ጮክ ብሎ ተናገረ ።

ጠበቃውም ምንም ሳይናገር ሳብርን በፊገ ግታ ብቻ ተመለከተው ።

"ለአገልግሎትህ ምን ያህል ነው የሚከፈልህ?"

"ብዙም አይደል ። በምሰጥህ የሕግ አገል ግሎት ወቅት የሚያስፈልጉኝ ወጪዎች ከተሸፈኑ ይበቃኛል ።"

—ኤልሓም በሕይወቴ ልታደርግልኝ ያልቻ ልኸውን ውለታ ለመቃብሬ ዐፈር መመለሻ ልታ ውለው ይሆን? — ሲል አሰበ — ሳብር ።

"ጌታዬ ፤ እኔን ለመርዳት መሞከሩ ከንቱ ነገር ነው ።"

" 'ከንቱ' የሚለው ቃል በእኛ የሙያ መዝ ገበ ቃላት ውስጥ አልተመዘገበም" አለ ጠበቃው ።

"እኔ እኮ ሁለት ሰዎች በጭካኔ የገደልኩ ሰው ነኝ ። መግደሌንም አምኛለሁ ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"በሆንስ!"

"ኤልሐም እኔን ለመርዳት. . .?"

"እዚህ ከተማ ውስጥ የሥጋ ዘመድ ባይኖርህም የሚያስብልህ ወዳጅ የለህም ማለት አይደለም ።"

"የፈጸምኩትን ወንጀል በይፋ ካመንኩ በኋላም?"

"ችግርህን ተረድታዋለች ።"

ሳብር ዓይኖቹ ያጋቱትን እንባ አብሶ፡ "በሕይወቴ ለሁለተኛ ጊዜ ያፈሰስኩት እንባ" አለ ።

"እንባ ማፍሰስ ክፋት የለበትም ። ለማንኛውም በዋናው ጉዳይ ላይ ብናተኩር መልካም ይመስለኛል ።"

"የፈጸምኩትን ወንጀል አምኛለሁ እኮ ።"

"ወንጀሉን ብታምንም አንዳንድ ያካባቢ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ ።"

"የተከሰስኩበትን ጉዳይ ሊያግዙ የሚችሉ ምን ያካባቢ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ ብለህ ትገምታለህ?"

"አስተዳደግህ ፤ ፍቅርህ ፤ ቅናትህ ፤ ለኤልሐም ያለህ ስሜት ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እነዚህን ነጥቦች ማንሣቱ ለጋዜጦች የሚጠቅም መኖ ከማቅረብ ሌላ የሚፈይደው ነገር አይኖርም ።"

"ሥስፋ መቅረጥ የለብንም ።"

"ነገሩ ሁሉ እንደ ትንግርት ነው የሆነብኝ ። ከእስክንድርያ ተነሥቼ እዚህ ድረስ የመጣሁት አባቴን ፍለጋ ነበር ። በመካከሉ ያላሰብኳቸው እንግዳ ነገሮች ስላጋጠመኝ የመጣሁበትን ዓላማ እንድረሳ አድርገው ወሀኒ ለመውረድ አበቁኝ ።" ሳብር በረጅሙ ተንፍሶ ፣ "በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ማንኛውንም ነገር እርግጡ አድርጌ ትቼ ሐሳቤ ሁሉ ያተኰረው ወደዚህ ባመጣኝ ጉዳይ ላይ ነበር ። ሆኖም ከእንግዲህ ያለፈውን በማሰላሰል ጊዜ ማባከኑ ዋጋ የለውም ።"

"አሁን የጠቀስከው ለመከላከያ ክርክሬ የሚጠቅመኝ ነጥብ ነው ። ይህንኑ ነጥብ እንደ መጀመሪያው የወንጀል ምክንያት አድርጌ ላቅርበው አፈልጋለሁ — ከመወለድህ በፊት እንደ ተፈጸመ ወንጀል ።"

"አሁን አንድ ነገር አስታወስክ ። ከጥቂት ቀናት በፊት ኤልሐም ደውላልኝ ስለ አባቴ የሰማችው ነገር እንዳለ ነግራኝ ነበር ።"

"ምን አለችህ?"

"ቁጭ ብዬ በቀል ስጠነስስ መች ጊዜ አግኝቼ ተገናኘን!"

t.me/OLDBOOKSPDF

"አንድ ላረጋግጥልህ የምወደው ነገር ፡ ኤልሐም በደወለችልህ ጊዜ ስለ አባትህ ያገኘ ችው ምንም መረጃ እንዳልነበራት ነው ።"

ሳብር የነገሩ አካሄድ አልጨበጥ ስላለው ተስፋ በመቁረጥ ራሱን ነቅንቆ ፡ "ጋዜጦች የወ ንጀሉን ድርጊት በዓምዶቻቸው ላይ በስፋት ማውጣታቸው ፡ ሌላ ቢቀር በማስታወቂያነቱ አንድ ውጤት ሊኖረው ይችል ይሆናል" አለ ።

"በእኔ ግምት ከአሁን በኋላ ከአባትህ ልታ ነኝ የምትችለው ዕርዳታ ምንም ፋይዳ የለውም ።"

"መኖሩ ቢታወቅ አንድ ተአምር ሊፈጠር ይችል ይሆናል ።"

"እንዴት አድርጎ?"

"እንደሚባለው ትልቅ ሰው ከሆነ. . ."

"ሕግን መለወጥ የሚችል ትልቅ ሰው የለም!"

"ጌታዬ ፡ አንድ ነገር ልንገርህ! በአንድ ወቅት እናቴ የታወቀችና የተቻላት ሴት ነበረች ። አሁን አንተ ሕግ ሕግ የምትለውን ነገር እንዳ ሻት በመለዋወጥ የፈለገችውን ስትፈጽም ለምን እንዲህ ታደርገኛለሽ ብሎ የጠየቃት ሰው አል ነበረም ።"

"ሌላውን ነገር እንተወውና እስቲ አባትህ እንዴት አድርጎ ሊረዳህ እንደሚችል አስረዳኝ ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳብር ሲፈራ ሲቸር ፡ "ከወሀኒ ቤት እንዳመ ልጥ ሲረዳኝ ይችል ይሆናል" አሰ ።

"ከወሀኒ ቤት አመልጣለሁ ብሎ ማሰብ የሕልም እንጀራ ነው ። እንዲህ ያለውን ተስፋ ቢስ አማራጭ ማውጠንጠን ራሱ ጉዳት ከማስከ ተል በስተቀር የሚሰጠው ጥቅም የለም ።"

"ለማንኛውም በጣም ነው የማመሰግንህ ። ከአሁን ጀምሮ በምትፈልገው ነገር ሁሉ ልተባ በርህ ዝማጅ ነኝ ። እንድ ልጠቅስልህ የምፈል ገው ነገር ፡ "ተስፋ—ቢስ" የሚለው ሐረግ በእ ሬም መዝገበ ቃላት ውስጥ አለመስፈሩን ነው ።"

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ዳኛ የግራ ቀኙን ተክራካሪዎች ሐሳብ ሲመረምር ከሰነበተ በኋላ የፍርድ ውሳኔውን አስታወቀ ። ሳብር በስ ቅላት ሞት እንዲቀጣ ! ሳብር በፍርድ ቤቱ ውስጥ ሲካሄድ የሰነበተውን የሕግ ክርክር በቅርብ ሲከ ታተል ቢቆይም ፡ የመጨረሻው የፍርድ ብያኔ የሚተላለፍበት መሆኑን ቢረዳም ፡ ፍርዱን ከዳኛው አንደበት ሲሰማ ክፉኛ መደንገጡ አልቀረም ።

"ይግባኝ ማለት እንችላለን" አለ ጠበቃው ።

"ኤልሐም እንዴት ነች?" አለ ሳብር ፡ ተስፋው በተሟጠጠ ስሜት ።

"በጣምም ደህና አይደለችም ። በጋዜጦች ላይ የወጡ ዜናዎችና ትችቶች አባትዋን ከአ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስዩት እንዲመጣ አድርገውታል ። ከእርሱ ጋር ወደ አስዩት ሄዳ አየር እንድትለውጥና በየዕለቱ የሚሰራጨውን ወሬ ከመስማት ዞር እንድትል እየጨቀጨቃት ነው ።”

“የእርስዋ አባት ከተሸሸገበት ብቅ አለ ፤ የኔስ አባት. . .?” በማለት ሳብር አጕተመተመ ።

ጠበቃው ሳብርን ፈገግ ብሎ ተመለከተውና ፥ “ስለ አባትህ እንድ ነገር ብነግርህ ታምነኛለህ?” አለው ።

“ከእንግዲህ ማንንም አላምንም!”

“ግዴለህም” አለ ጠበቃው ። ንግግሩን በመቀጠል እንዲህ አለ ፤ “‘አንጋፋው ጋዜጠኛ’ የሚል የብዕር ስም ስለሚጠቀመው አንድ የታወቀ የዜናዎች ተንታኝ ሰምተህ ታውቃለህ? የዜና ቸን ታኙ ሐሳቡን በጋዜጣ ያቀርብ የነበረው ከሃያ ዓመት በፊት በመሆኑ ባታውቀው አይገርመኝም ። ከጋዜጠኛው ጋር በሄሊዮፖሊስ በጕርብትና አብረን እንኖር ነበር ። ከዚህም በተጨማሪ ፥ በዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት በምማርበት ጊዜ መምህሬ ነበር ። ሰሞኑን ስለ አንተ ጉዳይ እንሥትን ስንጨዋወት የአባትህን ስም ጠቀስኩለት ። ድንገት ንግግሬን አቋርጦ ፥ ሰይድ ኤል ራሕሚ እንዳ ይሆን? እርሱ ከሆነ በጣም አድርጌ አውቀዋለሁ ። ሽገናው ኤል ራሕሚን እኔ ሳውቀው ዕድሜው

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሃያ አምስት ዓመት አይበልጥም ነበር ። ከሠላሳ ዓመት በፊት መሆኑ ነው ።"

"ታዲያ ወዳጅህ በጋዜጦች ላይ የወጡትን ፎቶግራፎች እንዴት አላየም?"

"ጋዜጣ ማንበብ ካቆመ ሃያ ዓመት አልፎ ታል ። ሰውዬው ዓይነ—ሥውር ነው ።"

"ስሙንና ዕድሜውን በትክክል ነው የገለጸው" አለ ሳብር ።

"እምን ፡ የተሳሳተ ነገር ያለበት አይመስ ልም ።"

"አሁን የት ነው ያለው አለህ?"

"አሁንማ ያለበትን አያውቅም ።"

"ስለ አባቴ የመጀመሪያ ጋብቻ የነገረህ ነገር አለ?"

ጠበቃው ፈገግታ እያሳየ ፡ "የአባትህ ዋና ዓላማ ትዳር መያዝ ሳይሆን በፍቅር እፍ ብሎ ማበድ እንደነበር ነግሮኛል" አለው ።

"ከድታው የሄደችው እናቴ ስለሆነች መግ ፋቱን እንዴት ሊረሳው ይችላል?"

"ኤል ራሕሚን በመሰለ ሰው ሕይወት ሴቶች በየዕለቱ ይለዋወጣሉ ። ስለዚህ ከጂውና ተከጂው የትኛው እንደሆነ መለየት ያዳግታል ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እናቴ ይህን የመሰለ ባሕርይ ያለው ሰው መሆኑን አልነገረችኝም ።"

"ይህንን ባሕርይውን ላታውቅ ትችላለች ።"

"ጋብቻ እንዴት ሊደበቅ ይችላል?"

"አሊ ቦርሃን — አንጋፋው ጋዜጠኛ ማለቴ ነው — እንደ ነገረኝ ከሆነ ፡ አባትህ የተለያዩ ሴቶችን እንደ ሸሚዙ ይቀያይር ነበር ። አሮጊቶች ፡ ወጣቶች ፡ ሀብታሞች ፡ ድሆች ፡ ባልዋ የሞተባት፡ ከባልዋ የተፋታች ፡ ገረዶችና ጋለሞቶችን በጋብቻ ስም መቀያየር ቅር የሚለው ሰው አልነበረም ።"

"ይገርማል!"

"በጣም እንጂ ።"

"እንዲህ ሲያደርግ ምንም ችግር አያጋጥመውም ማለት ነው?"

"እንደ ሰማሁት ከሆነ ችግር የሚበግረው ሰው አልነበረም ።"

ሳብር ጆሮውን ማመን አልቻለም ።

"ለመሆኑ ሥራው ምን ነበር?"

"ገንዘቡን በሚሊዮን የሚቆጥር ሰው ፍቅርን ከማባረር ሌላ ምን ሥራ ይኖረዋል! አንዲት ሴት በፍቅሯ ይዛ ልታሰነብተው ጥረት ስታደርግ ጥሏት እብስ ይላል ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"የእናቴ የጋብቻ የምስክር ወረቀት በእጄ አለ እኮ!"

"አንተ እጅ ያለውን የጋብቻ የምስክር ወረቀት የመሰለ የያዙ ብዙ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ።"

"ተከሶ ፍርድ ፊት ቀርቦ አያውቅም ማለት ነው?"

"ማን ያውቃል። ፊት ነኝ ካሉ በቂ ምክንያት ነው።"

"ሕጉ አይመለከተውም?"

"በሕግ ተላላፊነት ተከሶ አያውቅም። ከአሊ ቦርሃን እንደ ሰማሁት ከሆነ፥ በአንድ ወቅት የአንድ ባለ ጸጋ ልጅ ሕግ ገስሶአል እየተባለ ስለ ተወራበት ነገሩ ከመባባሱ በፊት አገር ጥሎ ነው የሄደው።"

"ከስንት ጊዜ በኋላ ተመለሰ?"

"ጨርሶ አልተመለሰም። ዓለምን እየዞረ ያንኑ ፍላጐቱን በየደረሰበት ማርካቱን ነው የቀጠለው። ገንዘብ ካለ ምን ይቸግራል!"

"ወዳጅህ ይህን ሁሉ ምስጢር እንዴት ሊያውቅ ቻለ?"

"ኤል ራሕሚ አልፎ አልፎ ይጽፍለት ነበር።"

"አሁን ያለበትን ስፍራ ያውቅ ይሆን?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"አያቅም ። አባትህ በአንድ ስፍራ ለረጅም ጊዜ በመቆየት ቋሚ አድራሻ እንዲኖረው አይሻም ።"

"በውጪ አገርም የታወቀ ሰው መሆን አለበት ።"

"ገንዘቡን በሚሊዮን የሚቈጥረውን ሀብታም ማን ያጣዋል ብለህ ታስባለህ? ምናልባትም በደረሰበት ስፍራ ሁሉ ስሙን ሊለዋወጥ ይችላል ። አባትህን የመሰሉ ሀብታሞች ደግሞ ስማቸውን መለዋወጣቸው አዲስ ነገር አይደለም ።"

"የአባቴ የመጨረሻው ደብዳቤ ለወዳጅህ የደረሰው መቼ ነበር ?"

"አሊ ቦርሃን ፅድሚው ከዘጠና ዓመት በላይ ስለሆነ ብዙ ነገሮችን በትክክል አያስታውስም። የሚያስታውሰው ፣ ከተለያዩ የዓለም አካባቢዎች ወዳጆቹ ደብዳቤ ይጽፉለት እንደ ነበር ብቻ ነው።"

"ወዳጅህ ስለ አባቴ ቤተሰብ የሚያውቀው ነገር መኖር አለበት ።"

"ኤል ራሕሚ ግብፅ ውስጥ ዘመድ አዝማድ የለውም ። አባቱ ሕንዳዊ መጻጉኛ ነበር ። አሊ ቦርሃን በመጀመሪያ የተዋወቀው ከአባታቸው ጋር ሲሆን ፣ በእርሱ አማካይነት ደግሞ ከልጁ ከሰይድ ኤል ራሕሚ ጋር ለመተዋወቅ ቻለ ። አባትዬው ከአርባ ዓመት በፊት ሲሞት ሀብቱን

t.me/OLDBOOKSPDF

ብቸኛ ወራሹ የሆነው አንድ ልጁ ተረከበ ። የኤል ራሕሚ አባት ሀብቱን ያካበተው በመጠጥ ንግድ ነበር ። ሰይድ ኤል ራሕሚም ቢሆን በየቦታው ያፈራቸው ዲቃሎች ይኖሩት እንደሆን እንጂ እስከ ዛሬ ሕጋዊ ወራሽ የሆነ ልጅ ያለው መሆኑ አይታወቅም ።"

"ልክ እንደኔው. . .!"

"አዎን ፡ ልክ እንዳንተው ። እንደምትለው አባትህ ከሆነ. . ."

"ባሕርይውን ዘርዝረህ ከነገርከኝ እንደ ተገነ ዘበኩት ከሆነ ፡ አባቴ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም።"

ጠበቃው ፊቱን ፈገግታ ከማልበስ በቀር ምንም ቃል አልተነፈሰም ።

"አዎን ፡ ጠባዩ ጠባዬ ፡ ባሕርይው ባሕርዬ ነው ። እርሱ ዓለምን በመዞር ፍላጎቱን ሲያረካ ፡ እኔ ወህኒ ቤት ውስጥ ተኩራምቼ እንጉቴ ውስጥ ገመድ አጥላቂውን በመጠባበቅ ላይ እገኛለሁ ።"

"እርሱ እንዳንተ ሰው አልገደለም ።"

"ገድሎስ እንደሆን ማን ያውቃል? ያ ዓይነ— ሥውር ወዳጅህ ሁሉንም ነገር የሚያውቅ ይመስ ልሃል?"

"ቢሆንም ፡ ኤል ራሕሚ የሚሊዮን ብር ጌታ ነው!"

t.me/OLDBOOKSPDF

“ዋናው ነጥብ ፤ ሕግ ሕግ የምትለው ነገር እስከ ዛሬ ጫፉም አልደረሰ!”

“ለሕግ ተገዥ መሆን ያለባቸው የኔ ቢጤ ዎች መሆናቸውን ታውቃለህ ማለት ነዋ?”

“አባቴ ማን እንደሆነም አውቄአለሁ ።”

“ማወቁ ምን ይጠቅምሃል?”

“እርግጥ ፥ አባቴ ማን እንደሆነ ማወቁ ምንም ጥቅም ላይኖረው ይችላል ። እናቴ ከወዳጅህ የበለጠ አባቴን ደህና አድርጋ ታውቀው ነበር ። ከእርሱ ጋር በፈጠረችው ግንኙነት ሳብያ በቂ ሀብት ለማካበት በመቻልዋ የሕግ ተጽእኖ አልነበረባትም ። ወህኒ እስክ ወረደችበት ጊዜ ድረስ ለማንም ሳትበገርና ለማንም ሳትሸማቀቅ ልብዋ የተመኘውን እየሠራች መኖር ችላለች ።”

“ከታሪኩ እንደ ተረዳሁት ከሆነ ፥ ኤል ራሕሚ ችግር የሚሉት ነገር ደርሶበት አያውቅም ።”

“የአባቴን ማንነት ከተረዳሁበት ጊዜ ጀምሮ ወራዳና የተልከሰከሰ የእቃጣሪነት ሥራ ላይ መሰማራቱን መቀጠሉ የማይታሰብ ነገር ነው የሆነብኝ ።”

“የሚያሳዝነው ፥ ነገረ—ሥራህ የአባትህን ማንነት የሚያንጸባርቅ አለመሆኑ ነው ።”

“እኔ ምን አጠፋሁ ፤ እርሱን በመፈለግ የታቻለኝን ያህል ተንከራትቻለሁ ።”

t.me/OLDBOOKSPDF

"ቀደም ብለህ ራስህ እንዳልከው ፣ ካገርህ የወጣህበትን ዓላማ የረሳህበትም ጊዜ ነበር ።"

"ፍቅር ነው ጉድ ያደረገኝ ። አባቴም ቢሆን ችግሬን ሳይረዳው አይቀርም ።"

"ዳኛው እርሱ አይደለማ ።"

"እርሱ ነው ጥሎኝ የጠፋው!"

"በባሕርይም ሆነ በተግባር ከአንድ ባሕር የተቀዳችሁ በመሆናችሁ ያለ እርሱ ዕርዳታ ተሳክቶልህ ለመኖር እንደማይሳንህ ተሰምቶት ሊሆን ይችላል ።"

"ምነው እናቴ ጥላው በሄደች ኖሮ!"

"እናትህም እኮ ጥላው ሄዳለች ።"

"ምንም ይሁን ምን ጥፋቱ የእኔ አይደለም።"

"አሱስ እውነትህን ነው ።"

" በሠራህት ወንጀል መጠየቅ አልነበረብ ኝም?"

"እንዲህ የሚል ሕግ የለም ።"

"ከሪማን የመሰለች ዱብ ዕዳ አሳተችኝ ከማለት የተሻለ ምክንያት አይመስልህም?"

"ሕግ ሕግ ነው ። ያልሆነ ምክንያት ቢሰበ ሰብ ሊለውጠው አይችልም ።"

ሳብር በረጅሙ ተንፍሶ ፣ "ከመጀመሪያውም አባትነቱን አለመቀበሉ ይሻለኝ ነበር" አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"በዚህ ሐሳብህ እስማማበታለሁ ። እንዳየሁህ ግን ስለ አባትህ የማወቅ ጽኑ ፍላጎት አለህ ።"

"ታዲያ የሰማሁት ሁሉ ምን ጠቀመኝ ?"

ጠበቃው ራሱን በአምንታ ነቀነቀ ።

"አሁንማ ሁሉም ነገር ቀርቷል ፤ ነፃነት ፡ ክብር ፡ የተደላደለ ኑሮ. . . ኤልሐምና ከሪማም ቀርተዋል ። ካሁን በኋላ ያለው እርግጠኛ ነገር የሰቃዩ ገመድ ብቻ ነው!" አለ ሳብር ፡ ቁና ቁና እየተነፈሰ ።

"ይግባኝ የማለት መብት አለን" አለ ጠበቃው ። "ወዳጄ ቦርሃን የነገረኝ ሌላም ነገር አለ።"

"ምንድን ነው የነገረህ?"

"አንድ ቀን ፡ ራሕሚ ድንገት ቤቱ ድረስ መምጣቱን ነግሮኛል ።"

"መቼ?"

"ያለፈው ጥቅምት ወር ላይ ።"

"ጥቅምት?"

"አዎን ፡ ያለፈው ጥቅምት ወር ።"

"ያለፈው ጥቅምት ወር እስክንድርያ ውስጥ ስፈልገው ነበር ።"

"በዚያን ሰሞን ለስድስት ቀናት እርሱም እስክንድርያ ነበር ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን መላው የጠፋ ነገር ነው! እስክንድርያ ውስጥ እርሱን በመፈለግ ያልደረስኩበት ስፍራ አልነበረም። በጋዜጣ ማስታወቂያ ለማውጣት አስቤ የጠላቶቼ መሣቂያ እንዳልሆን ፈርቼ ተውኩት።"

"ከጠላቶችህ አለባልታ አባትህን ማግኘቱ አይበልጥብህም ነበር?"

"ነበር፤ ምን ያደርጋል፤ አሁንማ አለፈ!" አለ ሳብር፡ በነዘንና በትካዜ።

"ዝም ብለህ አትበሳጭ። ማስታወቂያው በእስክንድርያ ጋዜጦች ቢወጣም ላያነበው ይችል ነበር።"

"ማጽናናት ያልከው ነው?"

"ስለ አባትህ አሥሩን በመለፍለፌ አጥፍቼ ከሆነ ይቅርታ አድርግልኝ።" ጠበቃው ጭንቀት የተሣለበትን የሳብርን ገጽ ትኩር ብሎ ከተመለከተ በኋላ፡ ሊያጽናናው በማሰብ እንዲህ አለው፤ "አባትህ ወዳጄ ቤት ጐራ ያለው ወደ አንድ አገር ሊሄድ እግረ መንገዱን ነበር። ለአንድ ሙዱ ዓመት በጉርምስና የመኖርን ዘዴ የሚያስረዳ አንድ መጽሐፍና አንድ ሣጥን ምርጥ ውስኪ ለቦርሃን ስጦታ አበርክቶለት ነው የተለያዩት።"

"ያን ዕለት ምሽት መኪና ውስጥ ያየሁት እሱን ሳይሆን አይቀርም። ለወዳጅህ የሰጠው መጽሐፍ ላይ ፊርማውን አስፍሮበታል?"

t.me/OLDBOOKSPDF

“ሳይፈርምበት የቀረ አልመሰለኝም ።”

“ልታሳየኝ ትችላለህ?”

“በደስታ ፤ ይኸውልህ ።”

“እኔ ዘንድ ለጥቂት ጊዜ ላቆየው እችላለሁ?”

“መጽሐፉ አንተ ዘንድ ቢቆይ ወዳጄ የሚ ከፋው አይመስለኝም ።”

“እመሰግናለሁ ። ወዳጅህ የነገረህ ሌላ ምን ነገር አለ ?”

“ከቦርሃን እንደ ሰማሁት ከሆነ ፡ ኤል ራሕሚ በቁመናውም ሆነ በጥንካሬው ከሠላሳ ዓመታት በፊት ከነበረው ምንም አልተለወጠም ። ዓለምን ከዳር እዳር ሳያዳርስና በአራቱ ማዕዘናት የሚገ ኙትን ቆነጃጅት ፍቅር ሳይቀምስ ቢቀር ፡ በሕይ ወት መኖሩ ብቻ ትርጉም እንደማይሰጠው በገር ዝር ገልጾለታል ።”

“ስለ ወለዳቸው ልጆቹ የተናገረው ነገር ይኖራል ?”

“ይኖር ይሆናል ። አብዛኛው ንግግሩ ግን ፍቅር ላይ ያተኰረ ነበር ። የተገናኙ ዕለት ክፉኛ ሲጠጡ ነው ያደሩት ። ኤል ራሕሚ በደረሰበት ሁሉ የፈጸመውን የፍቅር ትንግርት ይተርክለት ነበር ። ቦርሃን እንደነገረኝ ከሆነ ፡ ኮንጎ በነበረ ጊዜ የሰማውን አንድ የፍቅር ዘፈን ሳይቀር አንቆ ርቁሮለታል ።”

t.me/OLDBOOKSPDF

"ጭውውት ፡ መጠጥ ፡ ዘፈን ፤ ስለ ልጅቱ አንዲት ቃል እንኳን አልተነፈሰም!"

"አባትነትም ሲበዛ ባሕርይውን መለወጡ ይቀራል ብለህ ነው ።"

" ቁጥራቸው ቢበዛም ልጆች ምን ጊዜም ልጆች ናቸው ።"

"አንዳንድ በባሕርያቸው ጽኑ የሆኑ አባቶች ልጅነትን የእኛኑ አርአያ ይከተላሉ የሚል እምነት ሲኖራቸው ነው ያልታሰበ ሁኔታ የሚፈጠረው ።"

ዋጋ የሌለው ሰበብ አስባብ ነው" አለ ሳብር ፡ በንቀት ።

"አባትህን የመሰለ በጠባዩ ልዩ የሆነ ሰው የሚፈጽመውን ድርጊት መቀበል ይኖርብናል ።"

"ወየው ራሴን! ዞረብኝ ። የሰማሁት ሁሉ የሚታመን አይደለም!"

"አዝናለሁ ፤ ይህን ሁሉ መናገር አልነበረ ብኝም ።"

"ምናልባት እዚሁ ግብፅ ውስጥ ይኖርስ እንደሆን?"

"እዚህስ አይደለም ። ከሄደበት አገር የፖስታ ካርድ ልኳል ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

"በስቅላት ከመሞቴ በፊት ይመለስ ይሆን?"

"በዚህ ዓለም ምን የማይሆን ነገር አለ ብለህ ነው!"

"እውነት ነው እኮ። እኔ ኤልሐምንና ወንድምህን ኢሳንን በተዋወቅህበት ጊዜ የአባቴ የኤል ራሕሚ ወዳጅ ከሆነው ከቦርሃን ጐረቤት፥ ከጠበቃው መሐመድ ኤል ታንታዊ ጋር እገናኛለሁ የሚል ሐሳብ አልነበረኝም።"

"አንዳንዴ ሕይወት እንደዚህ ናት።"

"መጨረሻዋ አላማረም እንጂ . . ."

"ተስፋ አለመቁረጥ ነው።"

"ከእንግዲህ ምን ተስፋ ይኖራል?"

"ቅጣትህ ከሞት ወደ ዕድሜ ልክ እሥራት ሊሻሻልልህ ይችላል።"

"ይኸንን ተስፋ አትበለው!"

"ዋናው ነገር መቆየት ነው። ከቆየህ ጉዳይህ ዳግመኛ እንዲታይልህ አቤት ማለት ትችላለህ።"

"ይግባኝ ከጸናብኝስ?"

ጠበቃው ለጥያቄው መልስ አልሰጠውም። ቀኝ እጁን በስሜት ጨበጥ ፈታ ጨበጥ ፈታ ያደርግ ጀመር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳብር ንግግሩን በመቀጠል ፡ "ድንገት ይግ ባኙ ከጸናብኝና ከስቅላቱ በፊት ጥቂት ጊዜ ከሰጡኝ እንደ ምንም ብለህ አባቴን ፈልግልኝ" አለ ።

"ወዳጄ ፤ ሕግ ሕግ ነው ያልኩህ መሰለኝ ። የእኔ ተግባር ጉዳይህን ከሕግ አንጻር መመልከ ትና ፍትሕ እንድታገኝ ማድረግ እንጂ ወደ ሰማይ እያንጋጠጡ ጉም ለመዝገን መሞከር አይደለም ።"

"ስለ አባቴ የሰማኸው ነገር የተለየ ሰው መሆኑን አያረጋግጥልህም?"

"እኔ ሙያዬ ጥብቅና ነው ። የማውቀው ነገር ቢኖር የአንተን ዕጣ የሚወስነው ሕግ ብቻ መሆ ኑን ነው ።"

"አንድ የመጨረሻ ዕድል ሊኖረኝ ይችል ይሆናል ። ደፈርክኝ አትበለኝና ይህች ያለችኝ አጭር ጊዜ ሳታልቅ እንደ ምንም ብለህ ፈቃዴን ፈጽምልኝ ።"

"በምን መንገድ ላግኘው እችላለሁ?"

"አንተ ብዙ ነገር የምታውቅ ሰው ነህ ፤ በተጨማሪ ጐረቤትህም ቢሆን. . ."

"ከአባትህ ጋር ግንኙነት መፍጠሩ ጨርሶ የማይቻል ነገር አይመስለኝም ። ችግሩ ጊዜ የሚ ፈጅ መሆኑ ነው ። ያንተ ጉዳይ ደግሞ ጊዜ የሚ ሰጥ አይደለም ። ሁኔታውን በዓለም አካባቢ ለሚ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገኑት ኤምባሲዎቻችን ማስታወቅ ይኖርብናል ። ክፋቱ ደግሞ ኤል ራሕሚ አንድ ስፍራ አይቀ መጥም. . .”

እየራቀና እየመጠቀ የሚሄድ ትዝታ ። ሲያስ ቡት የሚታክት ፣ ሲቀርቡት አርባ ክንድ የሚርቅ መላ ቅጡ የጠፋ ነገር ። የሰማዩን ደመና ነፋሱ ግራና ቀኝ እያዋከበ ብስክስኩን እያወጣው ነው ። በሳብር አዕምሮ ውስጥ ሥቃይና ጭንቀት ይፈራ ረቁበታል ። በሐሳቡ ውስጥ ለሚመላለሰው ዕውር ድንብር ጥያቄ የሚያገኘውም መልስ ዕውር ድን ብር ነው ።

“ሰውን ማመን ዋጋ የለውም ማለት ነው” አለ ሳብር ።

ጠበቃው ነገሩ የገባው መሆኑን በሚገልጽ ፈገግታ ሳብርን እየተመለከተ ፣ “ዋጋ ሊኖረው የሚችልማ የሚቻል ነገር ሲሆን ብቻ ነው” አለው ።

ሳብር ትከሻውን እየነቀነቀ ፣ “ከእንግዲህ ያበጠው ይፈንዳ!” አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ኑ ት በሆኑ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎቹ በአ
ረቡ ነው ሳይሆን ተጠበብ ውስኖች ኦዳሚ
አመሠ ዘጎረጎሟቸው በአየሉ አገሮች አንባ
ቢያን ቋንቋ ውስጥ ያተረፈው ግብ
ነዊ ማሕሩዝ ፡ በሦስት ጉዞዎች
ለደክ በልደ ለሆኑ ሥራዎቹ ፣1981
ዓመተ ምሕ ጀምሮ ከቅፍ የመዎያ ብቃት ምስ
ክር የሆኑውን የሦቢልያ ሃሥነ ጽሑፍ ሽልማት በ77
ዓመት ዕድሜው ያገኘ ብርቅ የብዕር ሰው ነው ።

የማሕፉዝ የፈጠራ ሥራዎች በተለያዩ የዓ
ለም አካባቢዎች በከፍተኛ ደረጃ ሥወዳድነት ያተ
ረፉ በሆንም ፡ በተለይ ሥራዎቹ አማካይነት ሃስ
ነሩ ማሕበራዊ ሕይወት ፕዩን ጥንትው ብለው እን
ዲወጣ በማድረጉ ለመግለጽ እስከ መፈረግ የበቃ
ደራሲ ነው ።

ማሪፉዝ ፡ በአብዛኛው ፡ ነጻነትን ከተነገ ጉራ
ማይሉ ሕይወት በተነ ሳዕሩ በመሠለ ተወዳዳሪ
የማይገኝለት የጥበብ ሰው ነው ። ኖቲሪኛው
በሚል ርዕስ የተተረጉመው መጽሐፉ ፡ ይህንን
የልዩ ተሰጥኦ ባለቤት የሆነውን ታሪቂ የብዕር
ሰው ከአሳገርኛ ኦንባቢያን ጋር ሳነስተዋወቋቸው እን
ደሚሆን አምነት አለኝ ፡

ዋጋው ብር